# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የ2005/2006 ኦዲት ዓመት
## የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት
## አጠቃላይ ዘገባ

**ጥራዝ 2**

**ሚያዝያ 2006**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

1. መግቢያ........................................................................................ 1
2. የ2005 በጀት ዓመት ፋይናንስ እንቅስቃሴ እና የ2005/2006 ኦዲት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም................................................................................... 5

## ክፍል ሁለት

3. የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች.............................. 36
   1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት...................................................... 36
   2. የተሰብሳቢ ሂሣብ................................................................................ 37
   3. የገቢ ሂሣብ........................................................................................ 41
   4. የወጪ ሂሣብ...................................................................................... 49
   5. የተከፋይ ሂሣብ.................................................................................. 57
   6. የበጀት አጠቃቀም................................................................................ 60
   7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ.................................................................. 61
4. ልዩ ልዩ.......................................................................................... 65
5. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች................................................................................................ 67
6. የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሣቦች........................................ 70
7. የልዩ ኦዲት ስራዎች............................................................................ 248
8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እርምጃ ያልተወሰዱ መ/ቤቶች........................ 249
9. መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች............................................ 249
10. ማጠቃለያ........................................................................................

## ክፍል ሦስት

1. መግቢያ.......................................................................................... 253
2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2005 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት............. 253
3. በ2005 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች .......................................................................... 257
4. የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች.................................................... 257
5. ስለልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ................ 267
6. በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ..................... 271
7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሂያቸው............................................................ 272
8. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች................................................. 273

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በ2005/2006 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም /ከጥር 1/2005 - ታህሣሥ 30/2006/

1. **መግቢያ**

የዋናው ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገርቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል።

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት፣ የአከባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶች ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሣብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንደርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው።

## 1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣን፤ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- ፌዴራል መንግሥት ከብር 1 ሚሊዮን /አንድ ሚሊዮን ብር/ በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የኘሮግራምና የአሠራር ቅልጥፍና ምርመራ ወይም ክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል። የፌዴራሉ መንግሥት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣

- ለግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፣

የሚሉት ናቸው::

## 1.2 የሪፖርቱ ዓላማ

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 13/1 እና 2 መሠረት በ2004/2005 የኦዲት ዓመት በአከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2004 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የስራ እንቅስቃሴ የ2005/2006 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው::

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሀሳቦች መሠረት ያደረጉት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ፣ የዓለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግሥት በገባው ውል መሠረት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት፣ የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤትና በመ/ቤታችን የተከናወኑ ልዩ ኦዲት ስራዎችን ነው::

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው:: ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፤ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት  እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2005/2006 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል:: የመጀመሪያው ክፍል የ2005/2006 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፤ በሁለተኛው ክፍል የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፤ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፤ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ እና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚመለከት ይሆናል::

በሁለተኛው ክፍል የቀረበውን የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት፤ እና የአካባቢና የክዋኔ ኦዲትን እንዲሁም መንግስት ከአለም ባንክ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሳብ ተከታታይ ኦዲት ያጠቃልላል::

## 2. የ2005 በጀት ዓመት ፋይናንስ እንቅስቃሴ እና የ2005/2006 ኦዲት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

### 2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

በ2005/2006 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አዲስ አሠራር መሠረት የመ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ዓመት ከጥር 1/2005 - ታህሣስ 30/2006 ቢሆንም፣ የ2005 በጀት ዓመት ስራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የ2005 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም**

| ተ.ቁ | የወጪ አርዕስት | የበጀት ኮድ | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ያልተሠራበት በጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች | 6100 | 13,871,346.00 | 13,749,559.00 | 121,787.00 |
| 2. | ለአላቂ እቃዎች | 6200 | 5,817,380.00 | 4,090,288.97 | 1,727,091.03 |
| 3. | ለቋሚ ንብረቶችና ግንባታ | 6300 | 56,850.00 | 12,320.00 | 44,530.00 |
| 4. | ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ | 6400 | 267,235.52 | 243,909.42 | 23,326.10 |
| | **ድምር** | | 20,012,811.52 | 18,096,076.69 | 1,919,734.80 |

በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የበጀት አፈፃፀሙ 90.42% ስራ ላይ ውሏል፡፡

### 2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 419 እና ለድጋፍ ሰጪ 264 በድምሩ 683 ሲሆን፣ በጥር ወር 2005 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 243 ኦዲተሮችና 142 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 385 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 85 ኦዲተሮችና 17 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 102 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን 7 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 1 በሞት የተለየ፣ 51 ኦዲተሮችና 24

ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 75 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 154 ወንዶችና 90 ሴቶች በድምሩ 244፣ የድጋፍ ሰጪ 69 ወንዶችና 91 ሴቶች በድምሩ 160 ሠራተኞች በአጠቃላይ 404 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን ፣281 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ይህም ቁጥር በመዋቅር ከተፈቀደው ጋር ሲነጻጸር የኦዲት ዘርፍ 244/419(58.23%) እና የድጋፍ ዘርፍ 160/264(60.60%) በአጠቃላይ 404/683(59.15%) ስለሆነ ፣ 40.85% በሰው ኃይል ያልተሞላ ክፍት መደቦች መሆኑን ያሳያል።

## 2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ በአራት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት በየሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፣ ከጥር 1/2005 እስከ ታህሣስ 30/2006፣ የ132 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የመደበኛ ኦዲት ለማድረግ በእቅድ በተያዘው መሠረት የ132ቱም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በዕቅድ ያልተያዙ በፍ/ቤቶች ትህዛዝና በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት 16 ልዩ ኦዲቶች ተከናውነው ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካለት ቀርቧል፡፡

የመሠረታዊ የአገልግሎቶች ማስከበር ኘሮጀክት ተከታተይ ኦዲትን በተመለከተም ለወረዳዎች ከተሰጠው የድጋፍ ሂሣብ ውስጥ የ2005/2006 ኦዲት ዓመት በ298 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ)፣ ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በኦዲት ዓመት የ281 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር

ተልኳል፡፡ ይህም ክንውን ከበጀት ዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻፀር 94.29% ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን የ132 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ281 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ በሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2004/2005 ኦዲት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ ቁ. | መግለጫ /የኦዲት አስተያየት/ | በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት | | የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት | | አጠቃላይ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በጀት ዓመት | 2004 | 2005 | 2004 | 2005 | 2004 | 2005 |
| 1 | አጥጋቢ ሆነው በመኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Clean opinion) | 49 | 59 | 13 | 1 | 62 | 60 |
| 2 | ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) | 48 | 49 | 270 | 280 | 318 | 329 |
| 3 | አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየትየተሰጠባቸው (Disclaimer of Opinion) | 6 | 7 | - | | 6 | 7 |
| 4 | የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው (Adverse Opinion) | 13 | 15 | - | | 13 | 15 |
| 5 | ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው | 1 | 2 | - | | 1 | 2 |
| | ድምር | 117 | 132 | 283 | 281 | 400 | 413 |

## 2.4 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በውጭ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን

በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ መ/ቤቱ ክትትል ከማድረጉም በላይ የግል ኦዲት ድርጅቶችም ሆኑ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ተፈላጊውን የሙያ ሥነ ምግባር ሳያጓድሉ ሥራውን እንዲያከናውኑ አቅም በፈቀደው መጠን ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በ2005 በጀት በዓመት በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የልማት ድርጅቶች 69፣ ፕሮጀክቶች እና የዕርዳታ ሂሳቦች በግል ኦዲት ድርጅቶች 145 ኦዲቶች በድምሩ 214 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) የተለያዩ በጀት ዓመት ሂሣቦች የተከናወኑ ሲሆን፣ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የልማት ድርጅቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 253 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

## 2.5 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ

በመንግሥት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት ያከናውናል፡፡ በዚህም መሠረት በ2005-2006 የኦዲት ሥራ ዘመን (Audit Calendar) በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች ከጥር 2005 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት ዓመት የዞሩ 10 ኦዲቶች/9 ኦዲቶችና 1ኦዲት የተቋረጠ እና ከጥር 2005 በኋላ ተጀምረው እስከ ታህሣስ 30/2006 የሚጠናቀቁ 10፤ እንዲሁም ከሰኔ 2005 በኋላ

ተጀምረው የዳሰሣ እና ቅኝት ሥራቸውን በማጠናቀቅ ወደ ሚቀጥለው የኦዲት ዓመት የሚዛሩ 8 ኦዲቶች በድምሩ 28 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲት ፕሮጀክቶች አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞሩትን 9 ኦዲቶች ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው የ20 ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን የ2 ኦዲቶች በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት በመሰረዛቸው 6 ኦዲቶች ሥራቸው ተጀምሮ በተለያየ የኦዲት ደረጃ ላይ ወደ ቀጣዩ ዓመት ተላልፏል፡፡ ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት 100% ሲሆን የኦዲት ስራቸው ተጀምረው የዞሩት 6 መ/ቤቶች በመሆኑ ከአጠቃላይ ዕቅዱ በስኬት መጠናቀቁን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 20 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች ሪፖርቶቹ በም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡/የተጠናቀቁት የክዋኔ ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች በዚሁ ጥራዝ ተራ ቁጥር 10 ስር በዝርዝር ቀርቧል/

## 2.6 አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2005 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀው የ2005 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የገቢ ሂሣብ

### 2.6.1 የ2005 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ገቢ እቅድና ክንውን በተመለከተ

**ግኝት**

በ2005 በጀት ዓመት ከድርጅቶች ለመሰብሰብ በታቀደው መሰረት ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በበጀት አመቱ የታቀደው እቅድና በትክክል የተሰበሰበው ገቢ ሲነጻጸር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የድርጅቱ ስም | የአመቱ እቅድ | የአመቱ ገቢ | ልዩነት በመብለጥ (በማነስ) |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | 10,000,000,000 | 7,802,600,000 | (2,197,400,000) |
| የብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር | 133,300,000 | 99,000,000 | (34,300,000) |
| የብሄራዊ ትንባሆ ድርጅት | 87,600,000 | 42,200,000 | (45,400,000) |
| የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት | 3,500,000 | 0.00 | (3,500,000) |
| **ጠቅላላ ድምር** | **10,224,400,000** | **7,943,800,000** | **(2,273,600,000)** |

**ስጋት**

የታቀደው ገቢ በአግባቡ ባለመሰብሰቡ ምክንያት የመንግስት የበጀት ጉድለት እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

በእቅዱ መሰረት ከእያንዳንዱ ድርጅት መሰብሰብ ያለበት ገቢ ክትትል በማድረግ እና ሊሰበሰብ ያልቻለበት ምክንያት በማጣራት የመፍትሔ አቅጣጫ ሊበጅለት ይገባል፡፡

**የስራ አመራሩ አስተያየት**

በ2005 በጀት ዓመት ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰበው ገቢ እንዲያስገቡ ለመ/ቤቶቹ እና ለድርጅቶቹ ደብዳቤ የተፃፈ ሲሆን እነዚህም መ/ቤቶች በአገኙት የትርፍ መጠን መሰረት አብዛኛዎቹ ፈሰስ ያደረጉ ሲሆን አንዳንዶቹ የገቢ መጠናቸው በማነሱ ፈሰስ ያደረጉት

ሂሳብ የለም፡፡ በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር በገቢያቸው መሰረት እና በአቀረቡት ትርፍ ገቢ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የገቢ ዕጥረት ስለገጠመው ገቢ ያደረገው ሂሳብ የለም፡፡ የብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት ገቢውን ሙሉ በሙሉ እንዲያስገባ በተደጋጋሚ ደብዳቤ ተፅፏል፣ ክትትልም ተደርጓል፡፡ ለወደፊት ክትትል ተደርጎ ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል ብለዋል፡፡

### 2.6.2 <u>በበጀት ታውጆ ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በ2005 በጀት ዓመት ከመልሶ ማበደር ይሰበሰባል ተብሎ በነጋሪት ጋዜጣ በታወጀው በጀት መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከሶስት ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው በብር 192,255,873.7 በማነስ እንደተሰበሰበ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የድርጅቶቹ ስም | በበጀት የተያዘ | በበጀትአመቱ የተሰበሰበ | ከበጀት በታች (ከበጀት በላይ) የተሰበሰበ |
|---|---|---|---|
| ወንጂ ስኳር ፋብሪካ | 41,150,277.24 | 6,217,051.07 | 34,933,226.17 |
| ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ | 54,938,622.36 | - | 54,938,622.36 |
| ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ | 102,384,025.19 | - | 102,384,025.19 |
| **ድምር** | **399,013,007.99** | **6,217,051.07** | **192,255,873.7** |

**<u>ስጋት</u>**

ከዕቅድ በታች በመሰብሰቡ ምክንያት የበጀት እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል::

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

በጀት በሚዘጋጅበት ወቅት በቂ ጥናት በማድረግ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተለያዩ በመልሶ ማበደር ገንዘብ ከወሰዱ ድርጅቶች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መከፈል የሚገባውን የዋና ገንዘብ እና ወለድ ክፍያ ባካተተ መልኩ

መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ከበጀት በታች የተሰበሰበውን በተመለከተ ደግሞ በቂ የሆነ ክትትል በማድረግ ተበዳሪው ዕዳውን በወቅቱ እንዲከፍል ማድረግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

3ቱም የስኳር ፋብሪካዎች ያለባቸውን ዕዳ እንዲመልሱ የመስክ ጉብኝት ቢደረግም እንዲሁም በከፍተኛ ኃላፊዎች ቢወሰንም ፋብሪካዎች ባለባቸው የአቅም ዕጥረት ምክንያት ሊሳካ አልቻለም፡፡ አሁንም ግን ተገቢውን ጥረት እየተደረገ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 2.6.3 <u>ተመላሽ የተደረገ የቀረጥ ሂሳብ በገቢ ተመላሽ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ መገኘቱ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት (በዋጋ ወይም በታሪፍ አመዳደብ ወዘተ) በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥ ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለ ለመሆኑ ሲታወቅና በኮሚቴ ሲረጋገጥ በስህተት የተከፈለው ቀረጥ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግለት ሲሆን በተሰበሰበበት በጀት ዓመት ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ መጠን ግን በገቢ ተመላሽ መያዝ ሲኖርበት በወጪ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴሩ እየቀረበ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህንኑ ሂሳብ በወጪ እያጠቃለለ ይገኛል፡፡

ለናሙና ያህል:-

- በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ቤት ብር 14,056,107.58 በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 976,135.67 በድምሩ ብር 15,032,243.25 በ2005 በጀት አመት በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ የነበረ የቀረጥ መጠን በ2005 በጀት ለባለመብቱ ተመላሽ ቢደረግም ከገቢ ሂሳቡ ላይ ተቀናሽ ሳይደረግ በወጪ ተመዝግቦ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሂሳብ ውስጥ ተጠቃሎ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

- በመሆኑም ባለፈው አመት አሰራሩ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ እንዲስተካከል ለሪፖርት አቅራቢውም ሆነ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሰራሩ አሁንም አለመስተካከሉ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ይህም በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያጠቃልለው ሂሳብ ላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ ትክክለኛውን ሚዛን እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በጋራ በመሆን በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በበጀት አመቱ ውስጥ በስህተት ተሰብስቦ ነገር ግን በዚያው በጀት አመት ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ሂሳብ በበጀት አመቱ የገቢ ሪፖርት ውስጥ እንዳያካትቱ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

ለሁኔታው የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የሚስተካከል መሆኑን በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

2.6.4 <u>የምዝገባ ማዘዣ ሳይሞላ ክፍያ የሚፈጸም መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 13 መሰረት ተገቢው ማዘዣ ሳይሞላ ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ስራዎች የሚሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትሬዠሪ አካውንት ክፍያ ለመፈጸሙም ሆነ ወደ ትሬዠሪ አካውንት ገንዘብ ለመግባቱ መረጃ ሲደርሰው ተገቢው ማዘዣ ሳይሞላ በባንክ አድቫይስ ላይ ብቻ ምዝገባው በማሳለፍ የሚመዘገብ መሆኑና በፋይናንስ ደንቡ መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ የምዝገባ ማዘዣ እየተዘጋጀ ለትክክለኛነቱም በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ምዝገባው መከናወን እንዳለበት በባለፉት ኦዲት ሪፖርት በተደጋጋሚ አስተያየት

የተሰጠ ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመትም እርምጃ ሳይወሰድ በአድቫይሱ ብቻ ምዝገባ መከናወኑ ታውቋል፡፡

**<u>ስጋት</u>**

ይህም የፋይናንስ ደንቡን የሚጥስ ከመሆኑም በላይ ለአንድ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ማለፍ ያለበት የሂሳብ ምዝገባ ለማለፉ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

**<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>**

በፋይናንስ ደንቡ መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ የምዝገባ ማዘዣ እየተዘጋጀ ለትክክለኛነቱም በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ስራው መሰራት ይኖርበታል፡፡

**<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>**

በ2004 በጀት ዓመት እንደ ግኝት መጠቀሱ እና ይህንን ችግር በ2005 በጀት ዓመት ላይ የተደገመበት ዋና ምክንያት የIFMIS (Integrated Financial Management and Information System) አሰራር ስርዓት በ2005 በጀት ዓመት ይተገበራል ተብሎ የታመነበት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ትግበራው ወደ 2006 በጀት ዓመት በመሸጋገሩ በዚህ ዓመትም ግኝቱ መከሰቱ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በ2006 በጀት ዓመት ከየካቲት ወር ጀምሮ ወደ ትግበራ ስለተገባ የነበሩትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ መፍትሔ የሚያገኙ መሆኑን በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

**2.6.5 <u>ሁሉም የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ አዘጋጅተው አሟልተው አለማቅረባቸው በተመለከተ፡፡</u>**

**<u>ግኝት</u>**

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 10 መሰረት የፌደራል መ/ቤቶች ስለ መ/ቤታቸው የፋይናንስ አቋም (Financial position)፣ የፋይናንስ አፈፃፀም (financial performance) እና የገንዘብ ፍሰት (Cash flow) መረጃዎች ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ አዘጋጅተው ማቅረባቸውና፣ የሂሳብ መግለጫው (Financial statement) የሂሳብ አያያዝ ስርዓቱን፣

ፖሊሲዎችን፣ የሂሳብ ማስታወሻዎች እንድይዝ ተደርጎ መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሁሉም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት የሂሳብ መግለጫ አዘጋጅተው ያላቀረቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

**ስጋት**

የሂሳብ መግለጫ አለመቅረቡ መንግስት ያወጣው መመሪያ ከመጣሱም በላይ ተጠቃሚዎች ወይም መ/ቤቱ ያለበት ሁኔታ የሚከታተሉ አካላት የሂሳብ መግለጫ ሳይቀርብ በቀላሉ ውሳኔ ለመስጠት (decision making) ይቸገራሉ፡፡

**የማሻሻያ እርምጃ**

ማንኛውም ባለበጀት መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቱ በሚያቀርብበት ጊዜ የሂሳብ መግለጫው አብሮ የማያቀርብ ከሆነ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ራሱን ያወጣው መመርያ ተግባራዊ መደረጉን መከታተል ይገበዋል፡፡

**የስራ አመራሩ አስተያየት**

በግኝት የተጠቀሱትን ሪፖርት ከማቅረባቸው በፊት በፋይናንሻል ስቴትመንት አዘጋጃጀት IBEX ተጠቅመው ለማዘጋጀት ስልጠና ለሁሉም ባለበጀት መ/ቤት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ከሁሉም ባለ በጀት መ/ቤቶች ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በኩል ስልጠና እንዲሰጣቸው ስለተደረገ በ2006 በጀት ዓመት ከላይ የተጠቀሱት ሪፖርቶች እንዲያቀርቡ አቅጣጫ የተሰጠ መሆኑን በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

### 2.6.6 ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተላቸው መ/ቤቶች በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፡፡

**ግኝት**

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ ሚኒስቴሩ

በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ቢያመለክትም መስሪያ ቤቶች እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ የሚያቀርቡት ሪፖርት የሌለ መሆኑን ታውቋል፡፡

## ስጋት

የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ ላይደረግ ይችላል፡፡

## የማሻሻያ እርምጃ

በመመሪያው መሰረት በስሙ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተለት የመንግስት መስሪያ ቤት የሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ አመቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተዘጉ ወይም ውላቸው የተሰረዘ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ዋጋ በወቅቱ ወደ ማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ እየተደረገ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

## የስራ አመራሩ አሰተያየት

የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች ከውጭ አገር ዕቃ ለመግዛት የሌተር ኦፍ ክሬዲት የሚያንቀሳቅሱበትን ባንክ አካውንት ለመክፈት ለባንክ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ መ/ቤቶች በስማቸው የተከፈተላቸው ሌተር ኦፍ ክረዲት እንቅስቃሴውን በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባሉ፤ እንዲሁም ከባንክ የተፈፀመውን ክፍያ ዝርዝር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት እንድያቀርብ በመንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ዓይነት ሪፖርት በወቅቱ አለመቅረቡን እየገለፅን ለወደፊት ተከታትለን የምናስፈፅም መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ Automation ስራ ላይ ስለሆነ ሪፖርቱን አላቀረበም። በአሁኑ ጊዜ ሪፖርቱን እንዲያቀርቡ ትሬዠሪ ደብዳቤ መፃፃፉን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል።

## 2.7 የሌሎች ስራ ክፍሎች አፈፃፀም

### 2.7.1 የዋና ኦዲተር ልዩ ጽ/ቤት

- ጽ/ቤቱ ከጥር1/ 2005 እስከ ታህሳስ 30/ 2006 ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ መ/ቤቱ የሚመጡ እንግዶችን ማስተናገድ፣ ቀጠሮ የተሰጣቸውን ማስታወሻ በመያዝ እንዲስተናገዱ ማድረግ፣
- በዋና ኦዲተር የሚመሩ ስብሰባዎችና ሌሎች ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያዙ ቀጠሮ ማስታወሻ በመያዝ ለዋና ኦዲተር ማስታወስና ለሚመለከታቸው ማሳወቅ፣
- የጽ/ቤቱን የጽህፈት ሥራዎች ማከናወን፣
- መልስ የሚሰጣቸውን ደብዳቤዎች ምላሽ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ በውክልና ለሚፈርሙት ምላሽ መስጠት፣
- የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና በመንግሥትና አጋር ድርጅቶች የሚተገበሩ ፕሮጄክቶች ኦዲት ሪፖርቶችን መከታተል /ብዛታቸው275 እስከ 300 የሚሆኑ/የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና በመንግሥት የሚተገበሩ ፕሮጄክቶች ኦዲት ሪፖርት ዋና ዋና ግኝቶችን ማጠናቀር፣
- በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት የተከናወኑ ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ማጠናቀር፣
- የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጄክቶች ኦዲት ሪፖርት በዓመታዊ ሪፖርት የሚካተተውን ማዘጋጀት/ማጠቃለል፣
- ከመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች፤ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ የኦዲትና ኦዲት ነክ ጉዳዮችን፤ ሪፖርቶችና ጥናቶችን በመገምገም ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ለወደፊት ዕቅድ የሚረዱትን በመለየት ለዋና ኦዲተር ማቅረብ፣
- ለፓርላማ የሚቀርበውን ዓመታዊ ሪፖርት/ማጠናቀር፣
- ከፓርላማ ጋር የሚደረጉትን ግንኙነት ማስተባበር፤
- የኦዲት ስራችንን በሚመለከቱ የተለያዩ ስብሰባዎች መሳተፍ፤
- የፌዴራልና የክልልዋና ኦዲተሮች ጉባዔ ማዘጋጀት፤

- ከተጠየቁት ልዩ ኦዲቶች በልዩ ጽ/ቤቱ የሚከናወኑትን ኦዲት ማድረግ /3 ልዩ ኦዲቶችን ማከናወን/፤
- ከተጠየቁት ልዩ ኦዲቶች በጽ/ቤት የሚሰሩትን ኦዲት ስራዎች ክትትል ማድረግ፤
- ከግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ጋር የመ/ቤቱን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማጽደቅና በግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ የሚቀርበውን የግዥ ውሳኔ መርምሮ መጽደቅ፤
- በመ/ቤቱ የተለያዩ የሥርዓተ ፆታ ሥራዎችን ማከናወንና መከታተል፤
- ሥነ-ምግባር ነክ ስራዎችን ማከናወንና መከታተል ለመስራት አቅዶ
  - ወደ ጽ/ቤቱ የመጡ እንግዶች በተሰጣቸው ቀጠሮ መሰረት እንዲስተናገዱ ተደርጓል፡፡
  - በዋና ኦዲተሩ የሚመሩ ስብሰባዎችና ሌሎች ጉዳዮች አስመልክቶ የዋና ኦዲተሩን በማስታወስ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡
  - ለፓርላማ የሚቀርቡ የ2005 ሪፖርቶች ተጠናቅሯል፣
  - ከህዝብ ተወካዮች መ/ቤት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል፤ ከፓርላማው የሚተላለፉ መልእክቶችም ለሚመለከታቸው በወቅቱ እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡
  - በፍርድ ቤት የታዘዙና በሌሎች አካላት የተጠየቁ 7 ልዩ ኦዲቶች (የጤናና የስነ ምግብ ኢንስቲትዩት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2004 በጀት ዓመት ኦዲት፣ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ከግለሰብ ጋር ስላለው የብድር ክርክር፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር የዳይስፖራ ፕሮጀክት ሂሳብ፣ የምእራብ አርሲ ገቢዎች ጽ/ቤት የአንድ ነጋዴ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሰቲ ለግንባታ የመጡ የአርማታ ብረትና ሲሚንቶ በውስጥ ኦዲተሮች የቀረበ ጉድለት

ማጣራት እና የጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌንየም ሜዲካል ኮሌጅ)ኦዲቶች ተከናውነው ወጪ ተደርገዋል፡፡

- ከሀምሌ 2004 - ሰኔ 30/2005 በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርጉ የደረሱን 214 የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ዝርዝርና የኦዲት አስተያየታቸው ተለይቶ ተዘጋጅቷል፣
- የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተሮች ከታህሳስ 1-3/2006 ለተደረገው ጉባኤ የማሰተባበር ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ጋር በመሆን የመ/ቤቱን ዓመታዊ የ2006 በጀት ዓመት ግዥ እቅድ ጸድቋል፡፡
- በግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ የሚቀርበውን የግዥ ዉሳኔ መርምሮ የማፅደቅ ስራ ተከናውነዋል፡፡
- በዋና ኦዲተሩ የሚሰሩ ልዩልዩ ስራዎች በውክልና ተከናውነዋል፡፡
- በዋና ኦዲተሩ የታዘዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች ተከናውኗል፣

2.7.2 <u>የህግ ክፍል</u>

ክፍሉ በ2006 በጀት ዓመት ውስጥ

- መ/ቤቱ የሚከስበትንና የሚከስባቸውን ጉዳዩች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መከታተልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣
- መ/ቤቱ ከውጭ አከላትና ግለሰቦች ጋራ ለሚያደርጋቸው ስምምነቶች ውል በማርቀቅ ማዘጋጀት፣
- መ/ቤቱ ሲወክል የሕግ አገልግሎቱ በተወከለበት መድረክ ሁሉ በመገኘት የተወከለበትን ጉዳይ መፈጸም፣
- ከመ/ቤቱ ከሁሉም የስራ ክፍሎች ለሚቀርቡ የቃልም ሆነ የጽሑፍ የሕግ አስተያየቶች ጥያቄዎች የሕግ አስተያየት መስጠት፣

- ከተለያዩ የመ/ቤት ሠራተኞች ከሥራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ላይ የሕግ ምክር ሲጠይቁ ምክር መስጠት፣
- የሕግ አገልግሎት በሚያዘጋጀው ኘሮግራም መሠረት የተለያዩ የመ/ቤቱን ወኪል መ/ቤችን በመጐብኘት ችግሮችን በመፈተሽ መወሰድ ስለሚገባ እርምጃ አወሳሰድ የሕግ አስተያየት ማቅረብ፣
- መ/ቤቱ ለተወካዮች ምክር ቤት የሚያቀርበው መሰረት ክስ እንዲመሰረትባቸው በተወሰኑት አካላት ላይ ለፍትህ ሚ/ር፣ ለፀረ ሙስና ኮሚሽን ግልባጭ ከተደረገ በኋላ እነዚህ የፍትህአካላት የወሰዱት እርምጃ ካለ መከታተልና የተወሰደውንም እርምጃ ለመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ማሳወቅ፣
- መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው ሥልጠና ላይ መሳተፍና ሲጠየቅም ሥልጠና መስጠት፣
- የመ/ቤቱን ሕልውና የሚነካና በሕግ የተሠጠውን ሥልጣኑን የሚያደናቅፍ ተግባር ሲፈጸም በሚገኘው ማናውንም ሕግ ወጥ ተግባር ጉዳዩ ለሚመለከተው የሕግ አካል ማስታወቅና መከታተል፣
- በፍ/ቤት ያሉትን እና በዲስፕሊን ኮሚቴክስ የቀረበባቸው ጉዳዮች ተከታትሎ ከግብ ማድረስ፣
- መ/ቤቱን የሚመለከቱ ህጎች ደንቦችና መመርያዎች (የስነ ምግባርን ጭምር) ከወቅቱ ጋር እንዲሄዱ በየጊዜው በመፈተሽ መስተካከል የሚገባቸውን በማጥናት ለመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ማቅረብ፣
- በመ/ቤቱ በማንኛውም የስራ ክፍል የተፈጸሙ የህግ ጥሰቶች ሲያጋጥሙ ከሚመለከተው ሃላፊ ጋር በመነጋገር እንዲስተካከል ወይንም የማሰተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ
- ከበላይ ሃላፊዎች የሚሠጡትን ሌሎች ሕጋዊ ተግባራቶችን መፈጸም፣ አቅዶ የሚከተሉትን ስራዎች አከናውኗዋል፡፡

- በተለያዩ የህግና የውል ጉዳዩች ላይ ጥያቄው ላቀረበው አካል የህግ አስተያየትና ምክር ተሰጥቷል፡፡
- የቋሚና የአላቂ ዕዎችና የህትመት አገልግሎት ግዥ ውል የመ/ቤቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ ተዘጋጅቷል፡፡
- የመ/ቤቱን የአስተዳደር ህግ እንዲረቀቅ ከክቡር ዋና ኦዲተር በተሰጠ የስራ ትዕዛዝ መሰረት የአሰተዳደር ህጉ ተጠናቆ ተሰርቷል፡፡
- የዓመት ፈቃድ አስመልክቶ በቀረበው አቤቱታ ላይ ግልጽ ባልሆኑ ህጎች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ለሚመለከተው ተቋም ቀርቧል፡፡
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ክስ እንዲመሰረት ተደርጓል፣ /1 በፍርድ ቤት እና 3 በዲስኘሊን ኮሚቴ/
- ክፍተት ባላቸው የህግ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማካሄድ ለበላይ አካል አስተያየት ቀርቧል፡፡

### 2.7.3 <u>የኦዲት ምርመርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት</u>

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ፡-

- በተቋም ደረጃ የጥራት ማረጋገጫ ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት አፈጻፀማቸውን መከታተል፣
- ወቅታዊ አካውንቲንግ እና ኦዲቲንግ ሁሉም ኦዲተሮች እንዲያውቁት ማድረግ፣
- በየደረጃው ላሉ ኦዲተሮች እና ኦዲስ ለተቀጠሩ ኦዲተሮች የስልጠና እና የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ለኦዲት የሚያስፈልጉ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችን መረጃዎችን አጠናቅሮ በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ተመዝግቦ እንዲያዝ ማድረግ፣
- የጥራት ማረጋገጥ ሥራ የሚመራበት የጥራት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- በኢንጌጅመንት ደረጃ በተመረጡ የኦዲት ሥጋታቸው ከፍተኛ የሆነ 16 የፋይናንሻል የኦዲት ሥራዎች ላይ

የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ክለሣ ሥራ ከሪፖርት በፊት መሥራት፣

- በኢንጌጅመንት ደረጃ በተመረጡ የኦዲት ስጋታቸው ከፍተኛ የሆኑ 8 የፋይናንሻል የኦዲት ሥራዎችና 2 የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች ላይ የኦዲት ማረጋገጥ ክለሣ ሥራ ከሪፖርት በኋላ መሥራት፣
- በእያንዳንዱ የፋይናንሻል የኦዲት ደረጃ የሚያጋጥሙ የጋራ ችግሮች ላይ ጥናት በማካሄድ ለውይይት ማቅረብ እንደ ዋና ዋና ሥራዎች ያቀደ ቢሆንም የክፍሉ ሰራተኞች በማኔጅመንት ትእዛዝ ልዩ ልዩ ስራዎች በመታዘዛቸው በ 'ረ' እና በ 'ሰ' የተመለከቱት ስራዎች አልተከናወኑም፡፡ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡
- ለኦዲት ሥራ አጋዥ የሆኑ 23 ሰርኩላሮች1 መመሪያ እና 33 አዋጆችና 371 ደንቦች ማሠራጨቱ፣
- 75 ለሚሆኑ አዲስ ለተቀጠሩ የማስተዋወቂያ (Induction Course)60 ለሚሆኑ ለነባር ኦዲተሮች የማጠናከሪያ ስልጠና መስጠቱ፣
- የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ ስራ(QAR) ፖሊሲ መዘጋጀቱ፣
- የሁሉም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የስጋት ደረጃ መከለስ የሚያስችል መረጃ መሰብሰቡ፣
- በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ የ154 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቋሚ ፋይሎች ዝርዝር በማዘጋጀት ለዉሳኔ ለመ/ቤቱ ኃላፊዎች መቅረቡ፤
- USAID ኦዲት ለማድረግ ፕሪኢንጌጅመንት የተዘጋጀ መሆኑን፣
- የመብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ልዩ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ መላኩ፣
- በገቢዎችና ጉምሩክ ላይ ልዩ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለስነ-ምግባርና ለፀረ- ሙስና ኮሚሽን መላኩ፣
- በ4 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ቁጥጥር በመስክ ላይ መከናወኑና

- በአገር አቀፍ ደረጃ በህገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር ላይ በሚካሄደው ግምገማ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

### 2.7.4 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለግል ኦዲተሮች እና ለሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስና የመሠረዝ ሥልጣን፤ እንዲሁም በማናቸውም የፌዴራል መ/ቤትና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊ የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከጥር 1/2005 እስከ ታህሣሥ 30/2006 ባለው ለ20 ኦዲተሮች ለ55 የተፈቀደላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

- የ466 የሂሣብ አዋቂዎችና የ83 ኦዲተሮች የዓመታዊ የሰርተፍኬት ዕድሣት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 10 የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡
- በመ/ቤቱ የስነ-ምግባር ኮሚቴ በኩል በቀረበባቸው ቅሬታ መሠረት ለ9 የግል ኦዲት ድርጅቶች የመጀመሪያና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲርሣቸው ተደርጓል፡፡

### 2.7.5 የመ/ቤቱ የግንዛቤ ማዳበሪያና የኮሙኒኬሽን ሥራዎች

የኦዲት አሠራርና ጠቀሜታ እንደዚሁም፣ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር የሚኖረውን ፋይዳ በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮች ቀደም ባሉት ጊዜያት እንደነበረ ሁሉ የተከናወነ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ፤

- የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተሮች የምክክር መድረክ ለ19ኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን፣ በዚህ ጉባዔ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ከፌዴራልና ከክልላዊ መንግታስት እንዲሳተፉ በማድረግ፣
- በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምጃ አወሳሰድና በኦዲት ሪፖርት የሚጠቀሱ የህግ ጥሰቶችን ለህግ ለማቅረብ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ዙሪያ በመወያየት በጋራ ሊሰሩ የሚገባቸውን ጉዳዮች፣
- በፌዴራልና በክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የሚሰጡ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ መሆን አስፈላጊነትናየቁጥጥር አግባብ፣
- የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊኖራቸው ስለሚገበው ግንኙነት
- በኦዲት ሽፋን፣ ጥራትና ወቅታዊነትን ለማሳደግ በሂደት ላይ ያሉትን የለውጥ ሥራዎችን ለማጠናከር፣ የመንግስት ሀብት አሰባሰብ አጠቃቀምና አስተዳደር የሚያስፈጽሙ በየደረጃው ያሉ አካላት በመልካም ስነ ምግባርና በአመለካከት በታነፁ አካላት እንዲመራና እንዲፈፀም የበኩላችንን ኃላፊነት በመወጣት መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የበኩላችንን ጥረት ለማድረግ በሚሉት ዙሪያ በጥልቀት ተወያይቶ የአቋም መግለጫ በመውጣት ተጠናቋል፡፡

### 2.7.6 <u>የትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት</u>

ዳይሬክቶሬቱ የተቋሙን ራዕይ እና ተልዕኮ ሊያሣካ የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት እንዲኖር ለማድረግ ሠራተኞች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስልጠና እንዲያገኙና ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን በእቅዱ ዘመን፣

- የትምህርትና ስልጠና ፍልጎት ጥናት ማድረግ እና ተለይተው በታወቁ የስልጠና ፍላጎቶች ላይ ስልጠና ማዘጋጀት፣
- የስልጠና አፈጻጸምን መገምገም፣

- አገር ውስጥና የውጪ የትምህርትና ስልጠና እድሎችን ማመቻቸት፣
- በመ/ቤቱ ድጋፍ ትምህርትና ስልጠና በመከታተል ላይ ላሉ ተገቢውን ድጋፍ በወቅቱ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መስፈጸም፣
- የዳይሬክቶሬቱን ስራዎች ማቀድ፤ ማስተባበርና መምራት አፈጻጸሙንም ለመገምገም አቅዶ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡
- 1 /አንድ/ የመ/ቤቱ ዳይሬክተር በQuality Assurance ኘሪቶሪያ በተካሄደው ወርክሾኘ ላይ ከOct. 7-11, 2013 ተሳትፈው ተመልሷል፡፡
- 2 የመ/ቤቱ ሠራተኞች ኘሪቶሪያ በተካሄደው የPerformance Audit 3 Module Course ከSep.30-Oct.4,2013 ሰልጥነው ተመልሰዋል፣
- 3 የመ/ቤቱ ሠራተኞች ኘሪቶሪያ በተካሄደው የSenior Managers Workshop ከSep.-Oct.4,2013 ተሣትፈው ተመልሰዋል፣
- 146 ለሚሆኑ የመ/ቤቱ ኦዲተሮች ለ4 ቀናት በ AFROSAI-E ኦዲት ማንዋል ላይ ስለተደረጉ ለውጦች ማስተዋወቂያ የTECHNICAL UPDATE ስልጠና በአገር ውስጥ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- በመ/ቤቱ ድጋፍ የACCA ትምህርት ለሚማሩ ሠራተኞች እአአ የ2014 ዓመታዊ ክፍያ እንድፈጸም ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ለመከታተል ከመ/ቤታችን ለተመረጡ ሠራተኞች ከዩኒቨርሲቲው ጋር በመነጋገር ትምህርት እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡
- ከሐምሌ ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ በመ/ቤታችን የተቀጠሩ 75 ሰራተኞች የማስተዋወቂያ እና መሠረታዊ የኦዲት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- አንድ የመ/ቤታችን ባልደረባ ታንዛኒያ አሩሻ ሂደው እ.ኤአ ከNovember 04-09, 2013 በሚካሄደዉ የPerformance ስልጠና ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡
- 4 የመ/ቤታችን አባላት (1 በአሰልጣኝነትና 3 በሰልጣኝነት) ወደ ደቡብ አፍርካ ሂደው እኤአ ከNovember 20-29, 2013 በሚደረገዉ 8ኛው የTechnical Update እና Refresher workshop ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤቱ ድጋፍ ሥልጠና የወሰዱ ሠራተኞች፤ የተሰጡ ሥልጠናዎች፤ የACCA ተማሪዎች፤ የ2ኛ ዲግሪ እና የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲሁም ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎች በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎች በተቀናጀ መልክ የሚያዝበትን ሥርዓት የማደራጀት ሥራ ተጀምሮ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- የIBEX እና TEAMMATE ሥልጠና የሚያስፈልጋቸዉ ሠራተኞች ዝርዝር የመለየት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከመ/ቤታችን የኢንፎርሜሽን ሲስተም ሠርቪስ ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን ከፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር እና ከዕቅድ ዝግጅት፤ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬቶች ለተውጣጡ ሠራተኞች የIBEX ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- ከሃምሌ 1 2005-ታህሳስ30 2006 ሥራቸውን በፍቃዳቸው የለቀቁ 5 ሠራተኞች በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣቸው መ/ቤቱ ለ"ACCA" እና ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የከፈለላቸውን ከነወለዱ ለመ/ቤቱ ተመላሽ እንዲያደርጉ ተደርጓል፣
- ከሐምሌ 1 ቀን 2005- ታህሳስ 30 ቀን 2006 ቤተመጻህፍቱ፣ የንባብና የውሰት እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት ለመጡ 24 መረጃ ፈላጊዎች አስፈላጊ መረጃ ሰጥቷል።

**በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር የተሰጡ ስልጠናዎች ማጠቃለያ**

| ተ/ቁ | የስልጠናው ዓይነት | የሀገር ውስጥ | የውጭ አገር |
|---|---|---|---|
| 1 | Quality Assurance | | 1 |
| 2 | Audit 3 Module Course | | 2 |
| 3 | Senior Managers workshop | | 3 |
| 4 | AFROSAI-E | 19 | |
| 5 | Performance Audit | | 1 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 19 | 7 |

### 2.7.7 <u>በኢንፎርሜሽን ሰርቪስ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች</u>

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የማደራጀት፣ የኮምፒውተር ስልጠናና ድጋፍ መሰጠት፣ ኮምፒውተርና የኮምፒውተር ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣ የቋሚ ፋይሎች የኦዲት ሪፖርቶችና የተለያዩ ሰርኩላሮች ዳታ ቤዝ ማዘጋጀት፣ በኦዲት ሶፍት ዌር ላይ ማጠናከሪያ ስልጠና መስጠት የመ/ቤቱን የኔትወርክ ኢንፈራስትራክቸር ማሻሻል፣ የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ፣

- በቤተመጻህፍት፣ በመዝገብ ቤት፣ በዕቃ ግ/ቤት እና በሰው ሀብት መረጃዎች ላይ የተዘረጉት አዲስ የመረጃ አያያዝ ሲስተሞች የማጠናከሪያ ሥራዎች በመስራት የመ/ቤቱ ሠራተኞች እንዲጠቀሙበት ድጋፍ መሰጠት፣
- የኮምፒውተርና የኮምፒውተር ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣
- የቋሚ ፋይሎች የኦዲት ሪፖርቶችና የተለያዩ ሰርኩላሮች ዳታ ቤዝ በማዘጋጀት የኢንትራኔት አገልግሎት መስጠት በኦዲት ሶፍትዌር አጠቃቀም ላይ ድጋፍ ማድረግ፣

- የመ/ቤቱ ሠራተኞች የኦፌስአፕሊኬሽን የሶፍትዌር ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ ስልጠና መስጠት፣ የሪሞትኮኔክሽን ፋስሊቲ፣
- የኢንትራኔት ፋሲሊቲእና የWLAN ፋሲሊቲ ሥራዎች በኔትወርክ ማስተር ፕላን በኩል የሚሠሩ ስርዎችን መከታተልና ሥራውም ሲጠናቀቅ ፋይሎችን ሊይዝ የሚችል ሰርቨር በማዘጋጀት Open Source ሲስተም እንዲጀመር ማድረግ፣
- የቢዝነስ ኮንቲኒዩቲ እና ዲዛዝስተር ሪከቨሪ ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣
- የመ/ቤቱን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሴኩሪቲ ፖሊሲ ተግባራዊነት መከታተልና
- የኢሜይል አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ በስድስት ወራት ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡
    - የቋሚ ፋይሎች የሚያዝበት ሲስተም ዲዛይን የተዘጋጀ ሲሆን መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ በኦዲት ጥናትና ምርምር ስርፀት ዳይሬክቶሬት በኩል እየተከናወነ ይገኛል፣
    - በTeammate Software ላይ እየሰሩ ላሉ ኦዲተሮች ድጋፍ ተደርጓል፣
    - ለመዝገብ ቤት በተዘረጋው አዲስ ሶፍትዌር ላይ ለክፍሉ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፣በርካታ መረጃዎች ወደ ሲስተሙ እየገቡ ይገኛሉ፡፡
    - ለቤተመጻሕፍት በተዘረጋው አዲስ ሶፍት ዌር ላይ ለክፍሉ ሠራተኛ ስልጠና ተሰጥቷል፣ሲስተሙን የማጥራት ስራም እየተሰራ ይገኛል፡፡
    - ለሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት በተዘረጋው ሶፍትዌር ላይ ለክፍሉ ሠራተኞች የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቶ የማሻሻያ ሥራ ተከናውኗል፣

- አዲስ ለተዘረጋው የኔትወርክ ሥራ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ተጠናቆ ለኢንተርኔት መስመር የሚያገለግል የፋይበር ኬብል ዝርጋታ በቴሌኮም በኩል ተከናውኗል፣
- ለመዝገብ ቤት እና ለቤተመጻሕፍት በተዘጋጁ ሲስተሞች ላይ መረጃ ሲያስገቡ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ችግር ሲያጋጥምም ከአቅራቢው ድርጅት ጋር በመሆን የማስተካከያ ሥራዎች እንዲሰሩ ተርጓል፣
- kaspersky አንቲቫይረስ በላፕቶፖች ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡
- የመ/ቤታችን የፋይናንስ ግዥ ዳይሬክቶሬት እና የእቅድ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የሚጠቀሙበትን IBEX ሶፍት ዌር በዳታ ማዕከል ውስጥ እንዲካተት በማድረግ ዳይሬክቶሬቶቹ እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡
- በExchange Server ላይ ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች ባሉበት የስራ ቦታ ላይ የአጠቃቀም ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- አአገልህሎት ላይ የነበረ የፋይል ሰርቨር በሌላ ስርቨር የተተካ ሲሆን የፋይል አወቃቀሩም በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤታችን ንብረት ክፍል ውስጥ በሚገኙ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች ላይ በተደረገ ፍተሻ አሥር ኮምፒውተሮች ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው በዋራንቲው መሠረት ወደ አስመጪው ድርጅት እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ የክልል ኦዲት ቢሮዎች 253 የላፕቶፕ ባትሪዎች እንዲስተካከሉ ወደ እዚሁ ድርጅት ተልኳል። ከተላኩት ውስጥ 100 ባትሪዎች ተስተካክለው ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገዋል፣
- ከተለያዩ ክፍሎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት የሶፍት ዌር ጥገናዎች ተሰርቷል፣

- ለኦዲት ሠርቪስ ኮርፖሬሽን መሠረታዊ የሆነ የኮምፒውተር አጠቃቀም ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፣

### 2.7.8 <u>የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ</u>

ዳይሬክሬቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ

- የመ/ቤቱን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ መሠረት በማድረግ በየሥራ ክፍሎች ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን ዓመታዊ እቅድ ማሰባሰብና ማጠናቀር፣
- ለመ/ቤቱ ለ2006 በጀት ዓመት የተፈቀደውን በጀት ለየዳይሬክቶሬቶች መደልደል፣
- የበጀት ዝውወር የሚያስፈልጋቸው ርዕሶች መለየትና ዝውውር መጠየቅ፣
- የወርሀዊ የሩብ፣ የስድስት ወር፣የዘጠኛ ወር እና ዓመታዊ የበጀትና የእቅድ አፈጻፀም ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣
- በዲሞክራሲ ተቋማት አቅም ግንባታ ኘሮጀክት (DIP) እና በDFID አማካኝነት የሚካሄዱ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የማስተባበር የማስፈፀም ሥራዎችን ለማከናወን አቅዶ
    - የመ/ቤቱ የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች የ2006 በጀት ዓመት የሥራ እቅድ የማጠናቀር ሥራ ተሠርቷል፡፡
    - በወርሀዊ የእቅድ አፈጻፀም ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡
    - የኦዲት ዳይሬክቶሬቶችና የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በየወሩ ያቀዱት እቅድና ያከናወኑትን ሥራዎች በማጠናቀር ያሉበት ደረጃ ግምገማ ተካሂዷል፣
    - የመ/ቤቱን የኦዲት ዘርፍ የ2005/06 የሁለት ሩብ ዓመታት እና የሦስት ሩብ ዓመታት የድጋፍ ሰጪው የ2005 በጀት ዓመት የአራት ሩብ ዓመታት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት በማጠናቀር ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል፡፡

- የመ/ቤቱን የ2005 በጀት ዓመት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፡፡
- የመ/ቤቱን የ2006 በጀት ዓመት የሥራ መርሀ-ግብር ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፡፡
- ለመ/ቤቱ ለ2006 በጀት ዓመት ፀድቆ የመጣውን እንደገና በየዳይሬክቶሬቱ የመደልደል ሥራ ተከናውኗል፡፡
- በየዕለቱ በዳሬክቶሬቶች የሚቀርቡ የውሎ አበል ጥያቄዎችን ከተደለደለላቸው በጀት ጋር በማገናዘብ በጀት ስለመኖሩ ማረጋገጫ ተሰጥቶበታል፡፡
- የመ/ቤቱን የ2003-2005 የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃጸምና የ2006-2007 እቅድ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤትና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፡፡
- በልዩ ልዩ ስልጠናዎች ተሣትፎ እና የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል፡፡
- በDIP እና በDFID አማካኝነት የሚሠሩ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶችን ማስቀጠል ስለሚቻልበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው ጋር የመረጃ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

### 2.7.9 የሰው ሀብት ሥራ አመራር

መ/ቤቱ በልዩ ልዩ ህጐች ደንቦች እና መመሪያዎች የተሰጡትን የሥራ ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለው ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማንኛውም ጊዜ እንዲኖረው ለማስቻል ክፍት መደቦችን በቅጥር፣ በደረጃ እደገትና በዝውውር ለመሙላት፣ እና የእያንዳንዱ ሠራተኛ የሥራ መዘርዝር በአግባቡ በማዘጋጀት የመ/ቤቱን ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን እገዛ ለማድረግና ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎች ለመሥራት አቅዶ

- የ53 ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል፣
- ከሐምሌ 2005 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2006 ባለው ጊዜ ውስጥ ለ41ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል፡፡

- ከሐምሌ 1/2005 - ታህሳስ 30/2006 ባለው ጊዜ ውስጥ 24 ኦዲተሮችና 28 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 52 ሠራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡
- የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥራ አፈጻፀም ሪፖርት በወቅቱ ተሞልቶ እንዲቀርብ ክትትል ተደርጓል፣
- የመ/ቤቱን የሰው ኃይል መረጃ በዕድሜ፣በሥራ መደብ፣ በትምህርት ደረጃ በደመወዝ፣ በአገልግሎት ዘመንና በፆታ በማጠናቀር ወቅታዊነቱን እንዲጠብቅ ተደርጓል፣
- ሁሉም የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥራ ሰዓት ማክበራቸውን ቁጥጥር ተደርጎ የሥራ ሰዓት ያላከበሩትና ከሥራ የቀሩ ሠራተኞች የሥራ ክፍላቸው አውቀው እርምጃ እንዲወሰዱ ተልኳል፡፡
- በሥራ አካባቢ ደህንነት በኩል የመ/ቤቱ ሠራተኞች የደንብ ልብስ እና የሥራ መሳሪያ ዝግጅትና አወጣጥ መመሪያ ተከልሶ የአፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት ከማነጅመንት አባላት ጋር ውይይት በማካሄድ የተገኙት ግብዓቶች በማጠቃለል ለበላይ ሃላፊ ቀርቧል፡፡
- በግላኮማ በሽታ እና ከኮምፒውተር አጠቃቀም ችግር የተነሳ በዓይን ላይ የሚደርስ ጉዳትን አስመልክቶ 200 በራሪ ወረቀት ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ተበትኗል፡
- በመ/ቤቱ ግቢ ውስጥ የጤና ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮች በማጣራት እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ለዉሳኔ ቀርቧል፡
- በኩላሊት በሽታ ዙሪያ150 በራሪ ወረቀት ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ተበትኗል፣
- በመ/ቤቱ የሠራተኞች መዝናኛ ክበብ ዙሪያ በደረሰው ጥቆማ መሰረት ጥናት ተካሂዶ እንዲስተካከሉ ለኮሚቴው ተልኳል፡፡

<u>የጋራ አገልግሎቶች</u>

የኦዲቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን የግቢና የንብረት ጥበቃ፣ የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመልዕክት፣ የግቢ ውበትና ጽዳት አገልግሎቶችን በመስጠት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በሌላም በኩል

ለ15 የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን የሰርቪስ እና ጥገና አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ፣ ጥገናቸው በኢንሹራንስ መሸፈን ያለበት አግባብ ባለው አካል በኩል በማስፈፀም፣ የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ለተጠቃሚዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲቀርብ በማድረግ፣ የተቋረጡ የተሰበሩ የአገልግሎት መስጫ አውታሮች በአፋጣኝ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

## 2.7.10 የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር

- የመ/ቤቱ አብይ ተግባር የሆነውን የኦዲቱን ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በወቅቱ ማቅረብ፣
- የደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ክፍያዎች መፈጸም፣ የሂሣብ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የበጀት ፋላጎት ማዘጋጀት፣ በየሦስት ወሩ ለመ/ቤቱ የሚያስፈልገው ሥራ ማስኬጃ ማዘጋጀትና ማምጣት፣ ለወኪል መ/ቤቶች ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎት ማስከበር (PBS) በጀት ወቅቱን ጠብቆ ማስተላለፍ፣ ገቢና ወጪ የሆኑ ሂሣቦች በተገቢው መንገድ መመዝገብ፣ ግዥዎች በደንቡ መሠረት መፈፀም የመ/ቤቱን ንብረቶች በአግባቡ መመዝገብና የመቆጣጠር ተግባራትን ለመሥራት አቅዶ የተጠቀሱትን ሥራዎች እስከ ታህሳስ 30/2006 አከናውኗል፡፡

## 2.7.11 የውስጥ ኦዲት

የመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት በበጀት ዓመቱ ውስጥ፡-

- የተገዙ እቃዎች በደንቡ መሠረት አግባብ ባለው የግዥ ዘዴ መፈፀሙን፣
- የመ/ቤቱ እና የአራት የወኪል መ/ቤቶች ንብረቶች መንግሥት ባወጣቸው ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መጠበቃቸውን፣ ተመዝግበው መያዛቸውን እንዲሁም ተገቢው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን፣

- የንብረት የጥሬ ገንዘብና የሠነዶች ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ የፊሰስ ሪፖርት ለገ/ኢ/ልማት ሚ/ር ማቅረብ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በተገቢው ሁኔታ መወገዳቸውን፣ የበጀት አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና ዝውውር በአግባቡ መሆኑን፣
- በሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የተከናወኑ ሥራዎች በደንብና መመሪያ መፈፀማቸውንና እና፣
- ለሥጋት የተጋለጡትን አካባቢዎች በመለየት ኦዲት አድርጎ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አቅዶ
    - በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የጥሬ ገንዘብ፣ የሰነዶችና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በማከናወንና ከወጭ ቀሪውን በማረጋገጥ ፊሰስ እንዲደረግ የኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፣
    - በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በንብረት ክፍል ውስጥ ከወጭ ቀሪ ሆነው የተገኙትን ንብረቶች ቆጠራ ሲካሄድ በአካል በመገኘት ቆጠራው ትክክል መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
    - የመ/ቤቱን የ2005 በጀት ዓመት የበጀትና የወጪ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖርት በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡
    - በመ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተፈጸሙ ግዥዎች የግዥ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋጥ ኦዲት ተደርጓል፡፡
    - ለዋናው መ/ቤት ለመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ (PBS) ተብሎ የተፈቀደው በጀት በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች ኦዲት ተደርገዋል፡
    - የመ/ቤቱን የ2006 በጀት ዓመት ከሐምሌ/2005- ጥቅምት/2006 የወጪ ሂሳብ ኦዲት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 2.8 ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ

በሥርዓተ ጾታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑት ተግባራት፣

- በስርዓተ ጾታ ተወካይና በመ/ቤቱ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባሪነት ለአምስተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የተለያዩ ትምህርታዊ መልዕክቶችን በማስተላለፍና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በማካተት ሠራተኛው የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች ልምዳቸውን የሚጋሩበት እና በሥራ ላይ ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የሚወያየዩበትና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያፈላልጉበት የሴቶች የጋራ የምክክር መድረክ ተቋቁሟል፣
- የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል "አንድም ሰው በኤች.አይ.ቪ. እንዳይያዝ ኃላፊነታችንን በመወጣት የሀገራችንን ህዳሴ እናሳከለን!!!" የሚል መልእክት በማስተላለፍና ሠራተኛው የቀይ ሪቫን በደረት ላይ በማድረግ የዓመቱ የዓለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል መልዕክት ላይ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣
- የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቀንን የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በመ/ቤቱ ተከብሮ ውሏል፡፡ በዕለቱም በሽታውን በመከላከል ረገድ ግንዛቤ ማስጨበጫ በራሪ ወረቀቶች ተበትኗል፡፡
- በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት (Risk Assessment) መጠይቅ በሠራተኞች ከተሞላ በኋላ ተተንትኖ መረጃው ለበላይ ሃላፊ ቀርቧል፡፡
- በመ/ቤቱ የስራ ዕቅድ በተለይ የክዋኔ ኦዲት በአካባቢ ኦዲት ላይም በማትኮር የሚሰሩት የአካባቢ ኦዲት ስራዎች ለአካባቢ ጥበቃ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡

# የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ዋና ዋና

# የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

በዚህ ክፍል የሚነሱ አብዛኞቹ ግኝቶች ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መ/ቤታችን በ2005/2006 የኦዲት ዓመት በ132 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መደበኛ የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ በክልል መንግሥታት ደግሞ በ281 የወረዳና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት

### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 1,272,093.33 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-3 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ3 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 997,412.79 በማነስ ታይቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-4 ተመልክቷል/ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና በማነስ/በመብለጥ የታየው ልዩነት ተጣርቶ እንዲተካ /እንዲስተካከል ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሒሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሒሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሒሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 5/ሀ - ረ ተመልክቷል፡፡/ እና ዝርዝር ችግሮቹ በልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ጥራዝ 1 ከገፅ 4 እስከ 5 እና በየዘርፉ የጥሬ ገንዘብ አያያዝ ስር ተመልክቷል/

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሒሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፣ እንዲሁም በሒሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሒሣብ ጋር ከቆጠራው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 1.3 የተሰብሳቢ ሒሣብ

### 1.3.1 በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሒሣብ

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ77 መ/ቤቶች ብር 877,045,264.30 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር173,607,265.52፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 149,427,709.65፣ የትምህርት ሚኒስቴር

ብር100,298,362.09፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 97,146,944.59 ፣ ግብርና ሚ/ር ብር 77,744,994.72፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,153,328.69፣ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 26,671,151.92 እና የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 22,945,234.57 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፣ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳብ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ስለብር 18,708,030.10 በሰጠው መልስ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በሂሳብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር 11,593,098.46 ከሽሽግር መንግስቱ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ክፍሎች በነበሩት አባላት የጠፋና ገንዘቡንም ለማስመለስ ክፍሎቹ በተለያያ ምክንያት የፈረሱ ወይም የታጠፉ ወይም ወደ ሌላ የጦር ክፍል የተቀላቀሉ በመሆናቸውና አባላቱን ይዞ ገንዘቡን ለማስመለስ አብዛኛው በህይወት የሌሉ፣ በተለያየ ምክንያት ከተቋሙ የለቀቁ ወይም የተሰናበቱና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ በዳይሬክቶሬቱ የሂሳብ ምዝገባ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የሚታይና ከመዝገብ ለማሰረዝ በወጣው መመሪያ መሰረት ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ ደጋፊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ አስፈላጊው ሰነዶች ሲሟሉ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡ መሆኑን፣

የሂሳብ መደብ 4210 በተመለከተ በማዕከል፣ በዕዞችና በዋና መምሪያዎች በተሰብሳቢ ከሚታየው ገንዘብ ውስጥ ብር 45,000,000.00 በመከላከያ የበላይ አካል ትዕዛዝ ከሰራዊት

የደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ ለዝቋላ ስቲል ሮሊን በ2004 በጀት ዓመት የተሰጠና በቀጣይ ድርጅቱ የሚመልሰው መሆኑን፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 87,179,420.79 በ2005 በጀት ዓመት ውስጥ ብቻ የተከሰተ የተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑን፤ መ/ቤቱ ካለው የስራ ባህሪ (ዋናው መ/ቤት እና ሚሲዮኖች መካከል ካለው ርቀት አንፃር) እና የ3ኛ ወገን (የሌሎች መ/ቤቶች) ሂሳቦች ጭምር የሚያንቀሳቅስ እንዲሁም ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የህክምና ወጪ ሽፍኖ እስከሚተካለት ድረስ ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ 2006 በጀት ዓመት የዞረ መሆኑን በ2006 በጀት ዓመት ክትትል ተደርጎ አብዛኛው የተወራረደ መሆኑን፤ ብር 102,430,856.14 ከአሁን በፊት ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የቆየና መ/ቤቱ በሂሳቦቹ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 45,063,222.52 በ2006 በጀት ዓመት መወራረዱን፤ ማስረጃ ከሌለው ብር 4,674,501.18 ማስረጃዎችን አሟልተው ከ3ኛ ወገን እንዲተካ በሂደት ላይ መሆኑን፣ ብር 14,000,691.61 ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ተብሎ በመ/ቤቱ በኩል ተለይቶ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ እና ማስረጃ ከሌለው ቀሪው ብር 35,583,206.29 ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸውን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑን ገልጿል፡፡

ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ሂሳቡን ለማወራረድ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ

መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

### 1.3.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የዓለም አቀፍ ግዥ ለማከናወን በንግድ ባንክ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተበት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ የነበረበት ብር 84,853,734.49 በሂሳብ መደብ 5516 (በተከፋይ ሂሳብ) ተመዝግቦ በመገኘቱ፣
- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 52,385.47 ተሰብሳቢ ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸዉ አለመቻሉ፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ መሳየት ከሚገበው የሂሳብ ሚዛን ውጭ ያልተለመደ ሚዛን የሚታይባቸው፣ ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይ ባቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 21,996,154.14 ፣
- ተሳብሳቢ ሂሳቡን በሌላ የሂሳብ መደብ የመመዝገብ ሁኔታ በበርካታ መ/ቤቶች የሚስተወሉ፣ በወጪ ተመዝግቦ እያለ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 26,896,921.16 መገኘቱ፣
- በአብዛኛዎቹ መ/ቤቶች ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ወይም ገንዘቡ የተከፈለው አካል ስም ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት የተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤

➢ በተሰብሳቢ መያዝ የሚገበውን ሂሳብ አለመመዝገብ ወይም በሌላ ሂሳብ ላይ የመያዝና በታብሳቢ መያዝ የሌለበትን ሂሳብ የመያዝ ችግሮች ናቸው፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2. የገቢ ሂሣብ

### 2.1 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 32,139,625.90 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 8 ተመልክቷል/

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 11,583,879.14 ፣በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,588,619.20፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,469,351.03 እና በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,223,745.32 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፤ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር

በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖሪት የመጫኛ ማራገፊና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፤ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 2.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 286,818,836.06 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 39,856,103.92 በድምሩ ብር 326,674,939.98 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-7 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 252,299,705.34፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 36,389,175.05፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,512,045.63፤ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 13,134,569.83 ሚሊዮን፤ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ብር

4,850,496.24 እና በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 3,342,102.41 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 2.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሶስት ቅ/ጽ/ቤቶችና በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 42,942,143.14 እና በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት /የ5 ዲክለራሲዮንና/ በሌሎች 5 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳብ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን ባለመኖሩ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኒ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-9/ሀ ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፤ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.4 <u>የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 69,356,951.11 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 10/ሀ ተመልክቷል፡፡/

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በገንዘብ ያልተገለፀ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በሪፖርት የማያካትቱ በ7 መ/ቤቶች/ዝርዝራቸው በአባሪ-10/ለ ተመልክቷል/ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 2.5 ከየመኖሪያ ቤት አበል ግብር የማይቀንሱ መ/ቤቶቸ

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12/1 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ደንቡ በሚያዘው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ብር 1,580,533.99 የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት በአይነት ከተሰጣቸው መምህራንና ሠራተኞች ላይ የገቢ ግብር የማይቀነስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-12 ቀርቧል/ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ የሚከፍል ቢሆን ሊቀነስ የሚገበው ግብር በገንዘብ አልተገለጸም።

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.6 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

በ2 መ/ቤቶች በተገቢው ሂሳብ መደብ ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር 8,412,089.37 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 255,389,061.56 የገቢን ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ የመዘገቡ መ/ቤቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-11/ሀ እናለ ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ተደርጎ ሊስተካከል ይገባል፡፡

## 2.7 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ

የገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት በትክክል መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 መ/ቤቶች ብር 2,164,212.26 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ሂሳብ መገኘቱና በሌሎች 3 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም ለተመለከተው ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ እንዲዘጋጅለትና ሌሎችም ገቢ የሚደረግ ሂሳብ ደረሰኘ ተዘገጅቶለት መመዝገብ እንደሚገባ ለመ/ቤቶቹ አሳስበናል ፡፡

## 2.8 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## 2.9 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ወይም ዋስትናው ያልታደሰ መሆኑ

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መውጣት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃው አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 2,840,773 እንዲሁም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 219,683,687.83 በድምሩ ብር 222,524,461 ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በናሙና ከታዩት ውስጥ :-

| | |
|---|---|
| በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት | ብር 976,135.67 |
| በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ቤት | ብር 14,056,107.58 |

በድምሩ ብር 15,032,243.25 ከሁለቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የተደረገው ሂሣብ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና

ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገ ሂሣብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001አንቀጽ17 (1) መሰረት አስመጪ ዉ ወይም ወኪሉ የጉምሩክ ዲክላራስዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ቀን ድረስ ቀጣዩን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር **883,692.79** ቀረጥና ታክስ የያዙ ዲክላራሲዮኖች ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርዓት ሳይፈጽሙ ወይም ሳይሰረዙ ከአንድ እስከ አራት አመት ቆይተዋል ፡፡

  በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

  በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

## 2.10 <u>የሌሎች መ/ቤቶች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች</u>

- ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 191,790,917.95 በጥሬ ገንዘብ፣ ብር 28,838,307.93 (ተሰብሳቢ) እና ብር 15,198,539.31 የባለድርሻ ተከፋይ በድምሩ ብር 235,827,765.19 ሪፖርት ያደረገ ቢሆንም ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የባህል ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሀን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተላከው የ2005 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት ደግሞ ብር 242,944,263.80 በመሆኑ በሁለቱ ሪፖርቶች መከካከል የብር 7,116,498.61 ልዩነት የሚታይ መሆኑ፣

- አክሱም ዩኒቨርስቲ ቤተመፃህፍትና ኢንፎርሜሽን ማእከል ማባዣ ወረቀት በብር 1,029,940.00 ለህትመት ክፍል ከመደበኛ በጀት ተገዝቶ የተሰጠው ቢሆንም የተለያዩ የህትመት አገልግሎት ሰጥቷል ተብሎ በድምሩ ብር 1,305,483.70 የተከፈለ መሆኑ፣

- የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ለመኪና መጠለያ እና ማቆሚያ እንዲሰራለት ለኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ብር 3,449,579.40 እና ተደራራቢ አልጋ እና ችፑድ እንዲሰራለት ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኮሌጅ ብር 12,186,065.56 በጠቅላላው ብር 15,635,644.96 ድርጅቶቹ የራሳቸው የሆነ ህጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው እና እንደ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ሳያሟሉ የአገልግሎቱ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ-የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ የተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ቋት ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፣ በውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ላይ የገቢ ምክንያት በትክክል የማይመዘገብና አመዘጋገቡም የተደበላለቀ መሆኑ፣ ከትርፍና ኪሳራ መግለጫ ውጭ/Income Statement/ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚገልጹና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ማመዛዘኛ እና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጅ መሆኑ እና በድምሩ ብር 97,237.00 ከመደበኛ ሥራ ውጪ ለሆነው የሳምንታዊ መጨረሻ መረሃ-ግብር የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም መምህራን ላስተማሩበት የውሎ አበል ክፍያ እና ለተከታታይ ርቀት ትምህርት ክፍል አገልግሎት የሚውሉ ቋሚ ዕቃ ግዥ ከመደበኛ በጀት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንድሁም በገቢ ደረሰኝ አያያዝ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 3. የወጪ ሂሣብ

### 3.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ23 መ/ቤቶች ብር 3,821,243,169.21 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩ በአባሪ -14 ተመልክቷል/

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር 3,242,150,462.37 የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 488,129,584.25፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 48,055,198.58፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 10,258,169.0 እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 6,421,520.70 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብ ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 3,242,150,462.37፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 477,475,634.45፤ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 17,778,644.44፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,258,169.01 እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 2.66 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎትና በሥሩ የሚገኙ ዋና መመሪያዎች ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎች መ/ቤቶችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰጡ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

## 3.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 202,587,739.10 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ -13 ተመልክቷል/

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል::

## 3.3 ከደንብና መመሪያ ወጪ አለአግባብ የተፈጸመሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ41 መ/ቤቶች ብር

75,992,434.84 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -16 ተመልክቷል/ ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣

ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,000,000.00፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 10,196,507.81፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,605,050.51፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,190,691.01 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,062,182.75 እና ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,956,941.47 ሲሆን፣ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት የቦርዱ ሰብሳቢ ስብሰባ ለመካፈል ላወጡት ወጪ በሚል ከውጭ አገር ከተመለሱ በኋላ ብር 7,744.00 በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ሲሆን ስብሰባው በ2004 የተካሄደና ክፍያው በዚያው በጀት ዓመት ከጉዞው በፊት በቅድሚያ መፈጸም ሲገባው ከበጀት ዓመቱ ውጪ በ2005 በጀት ዓመት በነሀሴ 12,2004 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ወጪውን ጋባዡ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን የ2 ቀን የአልጋና የቁርስ በዶላር 300 አላግባብ ተከፍሏል በወጪ ለተመዘገበውም ሂሳብ ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል።

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

## 3.4 ግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዦዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ43 መ/ቤቶች ብር 165,892,637.56 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-15 ተመልክቷል፡፡/

ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ በሀርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,061,100.00፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,117,878.73፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 18,344,467.23 ፣ ማዕድን ሚ/ር ብር 16,274,515.25 እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 14,168,410.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴን ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ጊዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትና መጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ የሚለውን ሳያሟሉ ግልጽ ጨረታ ያላወጣና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

## 3.5 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች በብር 22,557,742.81 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ- 18 እና አባሪ-19 ተመልክቷል/

ከዚህም ውስጥ ትምህርት ሚ/ር ብር 19,231,147.66፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,597,312.92 እና ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር

795,550.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፣

በተጨማሪም በ7 መ/ቤቶች ብር 1,557,178,357.45 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው ከዚህም ውስጥ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ብር 785,919,809.52 ፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 549,166,140.13፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 157,971,920.15፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,756,934.71 እና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 10.08 ሚሊዮን ይገኝበታል፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጠው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጣው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዘው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

## 3.6 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በበጀት በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 230,819,512.43 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የኢንዱስትሪ ሚኒሰቴር ብር 102,872,461.13፤ የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ብር 51,883,514.72 ፤ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 43,983,869.27 እና የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 13.00 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

## 3.7 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 1,943,820.40 እና በ7 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 2,527,401.22 በጠቅላላው ብር 4,471,221.62 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 23 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤በድግሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈል፣ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የቤት አበል የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማ ጥቅሞችን መክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 3.8 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ36 መ/ቤቶች ብር 20,390,081.45 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 22 ተመልክቷል/

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል በኢንዱስትሪ ሚ/ር ብር 5,094,395.50፣ በአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 3,629,095.64፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,110,536.44 እና በብሔራዊ ሜትዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 2,202,009.47 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 3.9 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,397,136.41 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2005 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -21 ተመልክቷል/

ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች ብቻ ብር 35,562,617.39 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት

ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/ ፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.11 <u>በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site)</u>

### <u>ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ፤</u>

በፌዴራል ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ11 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 168,570,095.60 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ እንዲተካ ከመደረጉም፣ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 18,281,997.57 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ/ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

ከዚሁ ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች በውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ግንባታውን በማያጠናቅቁት ተቋራጮች ላይ የጉዳት የካሳ ጥያቄ በውሉ መሰረት መቅረብ መ/ቤቶቹ ይህንን እንደማያደርጉ ተውቋል።

ለግንባታ የቀረቡ ግብዓቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ክፍያ መፈጸሙና ተቋራጮቸ ክፍያ ሲፈጸምላቸው ቀደም ሲል የተሰጠቸው ብድር ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ከውል በላይ ክፍያ እንዲፈጸም፣ የተሰጠ ብድርም እንዳይሰበሰብ ክፍተት ይፈጥራል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች እንዲሰበሰብ የወሰዱትን ግንባታ በወቅቱ በመያጠናቅቁ ተቋራጮች ተገቢው የጉዳት ካሳ በውሉ

መሰረት እንዲጠየቅና የግንባታ ስራዎት በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

### 3.12 በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

በወጪ ተመዘገበቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 1,204,219.62 እና በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 25,708,880.80 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘታቸው ተረጋግጧል።

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ይገኝበታል፡፡

አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገበ አሳስበናል።

## 4. የተከፋይ ሂሣብ

### 4.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ46 መ/ቤቶች ብር 471,620,351.75 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-28 ተመልክቷል/

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 221,664,033.96፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 148,635,332.93፤ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 21,255,177.05 ፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 16,930,809.30 ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,141,502.19 ፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,184,429.01 እናመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,995,439.11 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በሌሎች መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ይጨምራል፡፡

በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሰኔ 30/2005 የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ብር 198,888,924.20 ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ መገኘቱንና የሂሳቡን ትክክለኛነ ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በዋናው መ/ቤት እና በሚሲዮኖች መካካል ባለው የቦታ ርቀት ሂሳቡን ለማወራረድ ጫና መፈጠሩን እና በ2005 በጀት ዓመት የተከሰቱ ተከፋይ ሂሳቦችን በከፍተኛ ጥረት በ2006 በጀት ዓመት እየተወራረደ እንደሚገኝ፣ በ2006 በጀት ዓመት ብር 44,030,007.57 መወራረዱን ቀሪው ማስረጃ የሌለውን ብር 35,305,065.36 በተመለከተ ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸውን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑንና ሰነዶቹ ከተረጋገጡ በኋላ በግብረሃይሉ በቀረበው አስተያየት መሰረት እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጿል፡፡

የሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

## 4.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በርካታ የሂሳብ አያያዝ ችግሮች ያለባቸው ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣

- በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር (3,098,228.89) በነገቲቭ (ዴቢት) የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣

- የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጅ መሣሪያ ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ ብር 1,507,619.00 በተገቢው የገቢ ሂሳብ ኮድ መሰብሰብ ሲገባው በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ መደብ 5002 የመዘገበ በመሆኑ፣

- የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 3,429,889.46 ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን፣ ብር 203,666.66 ደግሞ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው ያለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣

- የጅማ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣ በሂሳብ መደብ 5001(የችሮታ ጊዜ ተከፋይ) ብር 19,354,879.04፣ በሂሳብ መደብ 5002(ልዩ ልዩ ተከፋይ) ብር 20,693.91 እና በሂሳብ መደብ 5004(የደመወዝ ተከፋይ) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ምዝገባ /Abnormal Balance/ ብር 187,311.07 ተይዞ መገኘቱ፤

- የትምህርት ሚ/ር በሂሳብ መደብ 5002 (ልዩ ልዩ ተከፋዮች) ብር 1,429,452.00፣ በሂሳብ መደብ 5005 (ሌሎች የደመወዝ ተቀናሾች) ብር 523,662.67 እና በሂሳብ መደብ 5054(ሌሎች የማያዣ ሂሳቦች) ብር 595,830.20 በድምሩ 2,548,944,.87 ከ1995-1998 እየዞረ የመጣና በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ መገኘቱ፣

- የጎንደር ዩኒቨርስቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 2,407,178.29 የሆስፒታል ማስያዣ ተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገው የተከፋዩን ስምና አድራሻ፣ የተያዘው የገንዘብ መጠንና የቆየበት ጊዜ የሚገልጽ ሰነድ ወይም ተቀጽላ ቋት ባለመኖሩ ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፣

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 9,733.84 ተከፋይ ሂሳቦች ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸው አልቻለም፡፡

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

## 5. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 5.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 379,901,964.67 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-29 ተመልክቷል፡፡/

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካከል ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 96,047,945.95 ፣ ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,117,768.20፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 21.80 ሚሊዮን፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,200,479.61፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 40,633,615.89 እና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,712,828.14 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም 9 መ/ቤቶች ብር 49,594,003.86 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 5.2 በስራ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ96 መ/ቤቶች ብር 2,259,197,962.73 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-29 ተመልክቷል/

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ብር 213,835,430.84፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 119,943,791.03 ፣ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 110,533,882.82፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 86,413,575.05 ፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 68,490,363.94 የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 62,189,884.33 ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 66,166,058.74 እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ብር 53,393,010.81 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

# 6. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

## 6.1 የቋሚ ዕቃዎችና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝተል፡፡

| | |
|---|---|
| ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ | 28 መ/ቤቶች |
| ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ | 13 መ/ቤቶች |
| የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ | 17 መ/ቤቶች |
| ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ | 32 መ/ቤቶች |
| አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው | 23 መ/ቤቶች |
| አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው | 47 መ/ቤቶች |
| ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው | 16 መ/ቤቶች |

እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል::/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም:: በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው:: አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከመችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይተል::

ሌሎች የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች 34 መ/ቤቶች ዝርዝራቸው በአባሪ- 30/ሸ የተመለከተ ሲሆን፣ ችግሮቹ በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ::

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት

መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 6.2 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

| | | |
|---|---|---|
| ሊብሬ ያልቀረበላቸው | በ16 መ/ቤቶች | 177 ተሽከርካሪዎች |
| በብልሽት ምክንያት የቆሙ | በ33 መ/ቤቶች | 298 ተሽከርካሪዎች |
| በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው | በ7 መ/ቤት | 25 ተሽከርካሪዎች |
| የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬው የማይገጥም፣ | በ2 መ/ቤቶች | 6 ተሽከርካሪዎች |
| የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣ | በ2 መ/ቤቶች | 5 ተሽከርካሪዎች |

መኖራቸው ታውቋል:: /ዝርዝሩም በአባሪ -31 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፤ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣለቸውና በሊብሬው ላይ የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየው ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል::

## 6.3 ነዳጅና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የታዩ ችግሮች

**የፋይናንስ ደኅንነት መረጃ ማዕከል:**

- የማዕከሉ ተሽከርካሪ መኪናዎች ላልሆኑ በተለያዩ ቀናት ለሥራ አገልግሎት የዋለ የናፍጣና ቤንዝን ግዥ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡ ተሸከርካሪ መኪናዎቹም እንዴት እንደመጡና አገልግሎት ሊሰጡ እንደቻሉ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ታውቋል፡
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-12464 በቀን 30/10/04 ብቻ 326 ሊትር ነዳጅ የቀዳ መሆኑ፣

* ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲው መኪናዎች ወጥነት ባለው አሰራር የተንዙበት ርቀት /ኪሎ ሜትር/ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ በአግባቡ ነዳጅ መስጠት እንዲያስችል አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንሚችል የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡
* የሠመራ ዩኒቨርስቲ በቅድሚያ ክፍያ እየተገዛ የሚመጣው የነዳጅ ኩፖን፤ ቅባትና ዘይት የገቢና ወጪ መከታተያ ካለመኖሩም በተጨማሪ በየወሩ ወይም በአንድ በተወሰነ ወቅት ሪፖርት የሚቀርብበት አሠራር የሌለ መሆኑ፡
* የጅማ ዩኒቨርስቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪው ሰልቫትዮ /ታንከር/ ከሚይዘው በላይ በቀን ከ600-700 ሊትር ነዳጅ በድምሩ 4411.16 ሊትር እና ለጀነሬተር 15 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 1000 ሊትር የቀዳ መሆኑ፤

የአዲግራት ዩኒቨርስቲ፣ የአክሱም ዩኒቨርስቲ፣ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ፣ የዋቻሞ ዩኒቨርስቲ፣ የወላይታ ዩኒቨርስቲ  የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ መኪናዎች አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንደሚችል የሚያሳይ በባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ የሌለ  መሆኑ፣

የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጅ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 7. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በ22 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-33 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

8. **ልዩ ልዩ**

8.1 **የ2005 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት መኖሩ**

**ግኝት**

በ2005 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት የተዘጋጀ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ በተለያዩ የገቢ ሂሳብ መደቦች በማነስ ብር 38,761,015.97 የታየ መሆኑ፤

- በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 3,001,218.85 ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 2,051.31 የታየ መሆኑ ፤
- በተለያየ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች ብር 1,149.70 በመብለጥ የታየ መሆኑ ፤
- በተለያየ የዝውውር የሂሳብ መደቦች በዴቢት ብር 11,958,683,009.62 በማነስ ብር 14,755,252,948.39 በመብለጥ እንዲሁም በክሬዲት ብር 35,671,892.76 በማነስ ብር 681,968.89 በመብለጥ የታየ መሆኑ ፤
- በ4101 እና 4103 ሂሳብ መደቦች የጥሬ ገንዘብ በመብለጥ በድምር ብር 149,668,608.49

የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

## ስጋት

ዋናው መ/ቤት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

## የማሻሻያ ሃሣብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡አሁንም ለተገኙት ግኝቶች ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

## 8.2 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

- የሂሳብ ምዝገባ ከመ/ቤቱ ውጭ ባለ ሰራተኛ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፤
- የሂሳብ ስራውን በሃላፊነት የሚሰራ ሰው ባለመኖሩ የተሰራውን የሂሳብ ስራ በአግባቡ ለኦዲት ስራ የሚያስረዳ ባለሙያ አለመኖሩ፤
- በአብዛኛው የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ(JV)ላይ ማዘዣው በሚጠይቀው መሰረት የሚመለከታቸው ሰዎች የማይፈርሙ መሆኑ::
- የሂሳብ ሠነዶች የፋይል አያያዝ ስርአቱን በጠበቀ ሁኔታ ባለመደራጀታቸው መረጃዎችን ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በርካታ አላቂ እቃዎች ከንብረት ክፍል ወጪ ተደረገው በሐምሌ ወር/2005 መጀመሪያ ላይ ተመልሰው ገቢ ተደርጎ መገኘቱ፤

ታውቋል፡፡

በመሆኑም በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ማስተካከያ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

## 8.3 በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ ሠራተኞችን በሚመለከት፤

- የጎንደር ዩኒቨርስቲ አፄ ቴዎድሮስ ግቢ በውጭ ሀገር ለትምህርትና ስልጠና ለተላኩ ብዛታቸው 32 የሚሆኑ መምህራን ለደሞዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሁም ለትምህርት ድጋፍ ብር 1,167,853.00 የተከፈለ ሲሆን መምህራኖቹ ትምህርታቸውን አጠናቀው በገቡት ውል መሰረት

የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመፈጸማቸው በዩኒቨርሰቲው ላይ ያደረሱት ጉዳትና ኪሳራ ተረጋግጦ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ባልደረባ ሁለተኛና ሶስተኛ ድግሪያቸውን ኢንስቲትዩቱ በሰጣቸው የትምህርት ዕድል ውጭ ሀገር ካጠናቀቁ በኋላ በውሉ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ባለማገልገላቸው የወጣባቸው 8,055.00 ብር የደመወዝ እና 21,827.00 ዶላር የትምህርት ወጪ ለኢንስቲትዩቱ ገቢ እንዲደረግ ለተወካያቸው ደብዳቤ የተጻፈ ቢሆንም ክፍያው ያልተፈጸመ /ያልተጀመረ/ መሆኑ፣
- በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው ወጪ ትምህርታቸውን የተከታተሉና ግዴጃቸውን ሳይወጡ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ 63 ሰራተኞች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ፣

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በውሉ መሰረት በተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

## 9. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች

### 9.1 መግቢያ

በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ

በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በ2005/6 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶችና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS-2) ፕሮጀክት የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ቀርቧል፡፡

## 9.2 በ2005/6 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም;-

**ጥሬ ገንዘብ**

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣

**ተሰብሳቢ ሂሳብ**

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው እና አለመፈጸማቸው፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ዋና እና ተቀጽላ ሌጀሮች አለመቋቋም እና የተቀጽላ ሌጀሮች ምዝገባ ወቅታዊ አለመደረግ፣

## ወጪዎች

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የውሎ አበል ፎርም በአግባቡ አለመሞላት፡

## የሂሳብ ሪፖርት

- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣

## ንብረት

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፤
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና በአብዘኛው መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎችን አለመመዝገብ፡

## የክትትል ኦዲት

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣እና
- ትኩረት አለመስጠት

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 9.3 በ2005/6 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ የተሰጡ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinion)

በ2005/6 የኦዲት ዘመን (ከጥር/2005 እስከ ታህሣሥ/2006) 281 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሶስተኛ ዙር (PBS-3) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ላይ የተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinion) እንደሚከተለው ተጠቃሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ - 36(Annex I) በሚል ተመልክቷል/

| ተ.ቁ | የተሰጠው የኦዲት አሰትተያየት | የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር) | በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|
| 1. | ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified) የኦዲት አስተያየት | 1 | 0.3 |
| 2. | ነቀፌታ ያለበት (Except for) የኦዲት አስተያየት | 280 | 99.7 |
| 3. | ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse) የኦዲት አስተያየት | - | - |
| 4. | አቋም የማይወስድ (Disclaimer) የኦዲት አስተያየት | | |
| **ድምር** | | **281** | **100** |

## 9.4 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመሠረታዊ አገልግሎቶች 'PBS II' ፕሮጀክት የ2005 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተልና በስምምነቱ በተቀመጠው (TOR) መሠረት ኦዲት ተደርጎል፡፡

የኦዲት ስራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ደረጃ በተዘጋጀው የተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የተከናወነ ዓመታዊ ኦዲት ሲሆን የተሰጠው የኦዲት አስተያየት "ነቀፌታ የሌለበት" (Unqualified) ነው፡፡

## 10. የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሣቦች

የክዋኔ ኦዲት መሠረታዊ ተልዕኮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የተመደበላቸውን የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸውን በብቃት በማከናወን የተሰጣቸውን የሥራ ኘሮግራም ከግብ በማድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት አካሂዶ የታዩ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ለሥራ አመራሩ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሣብ ማቅረብና ተፈፃሚነታቸውንም በመከታተል ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ መርዳት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ሥራዎች በተመደበላቸው በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን እንዲሁም የሥራ ኘሮግራሞቻቸው ስኬታማ መሆናቸውን የፌዴራል ዋናው ኦዲተር አጣርቶ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኦዲት አድርጎ፣ ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የታዩ ጉልህ ድክመቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 10.1 በኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት የእህል ግዥ፣ ሽያጭ እና ክምችትን በተመለከተ

1. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የእህል ግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት በዋናው መ/ቤት እና በሥሩ ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከድርጅቱ በተገኘው የእቅድ ክንውን መረጃ መሰረት ከ2002-2004 ባሉት የበጀት ዓመታት የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያከናውኑት የእህል ግዥ ከዕቅዱ አንጻር ዝቅተኛ መሆኑ፤

   በዚህም መሰረት ድርጅቱ ባሉት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት

   - በ 2002 በጀት ዓመት 1,495,000 ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶችን ለመግዛት አቅዶ 458,095 ኩንታል እህል (የእቅዱን 31%) ማከናወኑ፣
   - በ2003 በጀት ዓመት 1,634 000 ኩንታል የተለያዩ የእህል አይነቶች ለመግዛት አቅዶ 877,959 ኩንታል (የእቅዱ 54 %) ማከናወኑ፣
   - እንዲሁም በ2004 በጀት ዓመት 1,752,000 ኩንታል እህል ለመግዛት አቅዶ 781,227 ኩንታል (የእቅዱን 45 %) ማከናወኑ
   - በተጨማሪም በኦዲት ወቅት በናሙና ከተመረጡት

(ናዝሬት፣አሰላ፣ባህር ዳር እና ጅማ) የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የየበጀት ዓመቱን እቅድ ሲያዘጋጁ ከየወረዳው/ ክልል የግብርና ጽ/ቤቶች/ ቢሮዎች የምርት ግምገማ መረጃን ወጥነት ባለውና ታአማኒነት ባለው መልኩ የማይሰበስቡ መሆኑ፤

**በድርጅቱ የሚጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ**

2. ድርጅቱ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እና በመስኩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት እንዲረዳው የተለያዩ ጥናቶችን በማስጠናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ድርጅቱ ባጠናውና ተግባራዊ እያደረገ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የእህል ዋጋ የመወሰን ስልጣንን ከማእከል አሰራር ወደ ስራው ባለቤቶች የማውረድ ስራን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡  በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ መሠረታዊ አሰራር ሄደት ለውጥ ጥናት አካሂዶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ታውቋል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ የተካተተው በማዕከል ብቻ ተወስኖ የነበረውን የእህል ዋጋ የመወሰንን ሥልጣን ወደ ስራ ባለቤቶቹ እና ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ማውረድ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡
3. ይሁን እንጂ በእህል ግዥ ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊው በተወሰነ መልኩ ዋጋ የመወሰን ኃላፊነት እንዲሰጠውና እንዲወሰን የተጠናው ጥናት ላይ ቢቀመጥም ተግባራዊ አለመደረጉ፤ የእህል ግዥ ዋጋ አወሳሰን ሥርዓት በማዕከል ብቻ በዋናው መ/ቤት የተያዘ መሆኑ፤

**ድርጅቱ በውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ ማሳደጉን በተመለከተ**

4. ድርጅቱ በገበያ ውስጥ የሚሳተፍባቸው የእህል ግዢና ሽያጭ አይነቶች በማሳደግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የገበያ ድርሻ ሊያሻሽል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ የሆነውን የእህል ምርትን በዋነኛነት ለአለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ የሚለውን ለማሳካት ወደ ውጭ የሚልካቸውን የእህል ምርቶች መጠን ና ዓይነት ሊያሳድግ ይገባል፡፡
5. ድርጅቱ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱ ላይ የገበያ ማስፋፊያ እና አማራጭ የኤክስፖርት ገበያዎችን እንደሚያስፋፋ ቢገልጽም የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትም ሆነ በኋላ በ16 የምርት አይነቶች የእህል ግዥና ሽያጭ ስራ ውስጥ  እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናቱ

ላይ አስፈላጊው የገበያ ጥናትና ልማት ስራ በማከናወን ወደ አዳዲስ ገበያ በመግባትና ተጨማሪና አማራጭ የኤክስፖርት ገበያዎችን እንደሚፈጥር አስቀምጦ፤ በዚህም ድርጅቱ ያለውን የውጭ ገበያ ድርሻ ከ 3 ከመቶ ወደ 6 ከመቶ የማሳደግ በጥረት ተደራሽ ግብ ይዟል፡፡ ከድርጅቱ ከቀረቡ መረጃዎችም ሆነ ከብሄራዊ ባንክ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በወጪ ንግድ ሽያጭ የድርጅቱ አገር አቀፍ የገበያ ድርሻ በ2002 በጀት ዓመት 4.48 ከመቶ ፤በ2003 በጀት ዓመት 6.46 ከመቶ እንዲሁም በ2004 በጀት ዓመት 2.47 በመቶ መሆኑ፤

6. ድርጅቱ ባለፉት 3 ዓመታት ተግባራዊ እያደረገ ባለው አዲሱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ ድርጅቱ ያቀደውን ያህል እህል ላለመግዛቱና የግዥ መጠኑን ማሳደግ ካልቻለባቸው ምክንያቶች መካከል ፈቃድ የሌላቸው የእህል ነጋዴዎች በብዛት ገበያ ውስጥ መግባታቸውና የገበያ ሽሚያ መፍጠራቸው እንደሆነ በማስቀመጥ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከምርት ገበያ ድርጅት ጋር በበለጠ በመስራት ህጋዊነትን ማጠናከር የሚል የመፍትሄ ሀሳብ በማቅረብ ያስቀመጠ ቢሆንም ባለፉት 3 ዓመታት በዚህ ጉዳይ ድርጅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ስለጉዳዩ ጠለቅ ያለ አውደ ጥናት በማዘጋጀትም ሆነ በሌላ መልኩ ችግሩን ለመፍታት ያደረገው ጥረት አለመኖሩ፤

**የግዥ አፈጻጸም ክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ**

7. በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግዥ፤ ሲከናወን የአፈጻጸም ስርዓቱን ሊያጠናክር የሚችል የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የሚዘረጋው ሥርዓትም ዋናው መ/ቤት ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ ለግዥ ማዕከላት የሚያስተላልፉት ገንዘብ ለተባለለት አላማ በተባለበት ጊዜ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ዙሪያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካገኘነው መረጃ እንደተረዳነው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለግብይት እና ክምችት ሰራተኞች በቀጥታ በስማቸው የእህል ግዥ እንዲያከናውኑ በባንክ ገንዘብ የሚልክ ሲሆን ይህም ገንዘብ በስርዓቱ እና በወቅቱ ለሚፈለግበት ተግባር መዋሉን ማእከሉ እህሉን ገዝቶ ማስገባቱን የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

**በመጋዘኖች የሚቀመጡት እህሎች ድርጅቱ ባስቀመጠው የእህል ጥራትና ደረጃ መሰረት መሆኑን በተመለከተ፣**

8. የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እህል ሲገዙም ሆነ ሲያከማቹ ድርጅቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃ መመሪያ መሰረት ሊሆን ይገባል። ይህም የእህል ጆንያዎች አስተሻሸግን፣ በመጋዘን ውስጥ አደራደርን፣ የመጋዘኖች መለያ ኮድ አለጣጠፍን ሊጨምር ይገባል። በተጨማሪም ድርጅቱ ለእህል ማከማቻ የሚጠቀምባቸው መጋዘኖች የድንገተኛ እሳት ማጥፊያ መሣሪያ ሊኖራቸው ይገባል። የድርጅቱ የእህል ጥራት ቁጥጥር እና ክብካቤ አፈጻጸም መመሪያ በመጋዘኖች ውስጥ ያለው የእህል አያያዝ እና አደራደር ለእህል ተባይ መከላከል ተግባር አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 3 በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር የሚገኙ የእህል መጋዘኖች የእህል አደራደር የተዝረከረከ እና የተዘበራረቀ መሆኑ፤ በመጋዘኖቹ ወስጥ እህል ከመቋጠሪያ ዉጪ ፈሶ መታየቱ፣ በመጋዘኖቹ ውስጥ ባዶ የእህል መቋጠሪያ ጆንያዎች በብዛት ተከማችተው እና ተዝረክርከው መገኘታቸው፣ የድንገተኛ የእሳት ቃጠሎን ለመከላከል የሚያስችል የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች አለመኖሩ፣ በየመጋዘኖቹ ላይ የመጋዘን መለያ ኮድ አለመለጠፉ፣ በየመጋዘኖቹ የእህል ማስቀመጫ ፓኔሎች የሌሉ በመሆኑ እህል መሬት ላይ እንዲቀመጥ መደረጉ፣ በመጋዘን ቁጥር 11 ግቢ ውስጥ የግለሰቦች መኖሪያዎች ያሉበት መሆኑ፣ አእዋፋት ወደመጋዘኑ የሚገቡበት ሁኔታ መኖሮ አገልግሎት የማይሰጡ እና የተበላሹ ብዛት ያላቸው የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች በየመጋዘኖቹ ተተክለው የሚገኙ መሆኑ

9. በአሰላ፣ ጅማ፣ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የኦዲት ቡድኑ ለምልከታ በሄደበት ወቅት ምንም እህል በመጋዘኖች ውስጥ አለመኖሩ በአሰላ እና በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘን ውስጥ ለእህል ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒቶች አያያዝ የተዝረከረከ እና መድኃኒቶቹ በሰው እና በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉበት ሁኔታ ተቀምጠው መገኘታቸው

**ለእህል ጥራት ማረጋገጫ የሚውሉ የድርጅቱ መሳሪያዎችን በተመለከተ**

10. ድርጅቱ የሚገዛቸው እህሎች አስፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያሟሉ መሆናቸው በመጀመሪያ ሊያረጋግጥ ይገባል። ይህንንም ለማድረግ

እንዲያስችለው ዘመናዊ የእህል ጥራት ማረጋገጫ መሳሪያዎችን በበቂ ሁኔታ ሊያቀርብ እና በሚፈለጉበት የስራ ቦታዎች ሁሉ ሊያሟላ ይገባል፡፡ ነገር ግን በድርጅቱ የአምስት አመታት ስትራቴጂክ እቅድ (2000-2004 በጀት ዓመታት) ላይ እንደ ግብ ከተቀመጠው ነጥብ አንዱ ያረጁ የእህል ጥራትና ደረጃ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን በዘመናዊ መሳሪያዎች የሚተኩበት ዝርዝር ጥናት በማድረግ ከ2001 ጀምሮ እስከ 2004 ድረስ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚል ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የናዝሬት፣ የአሰላ፣ የባህር ዳር፣ የጅማ እና የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ የእህል ጥራት ማረጋገጫ መሳሪያዎች በተለይም ዘመናዊ የእህል እርጥበት መለኪያ እና የናሙና መለኪያ ሚዛን በዕቅዱ መሰረት ተገዝተው ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ግዥ ማእከላት አለመሰራጨታቸው፤ በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር በሚገኙት የእህል መጋዘኖች ውስጥ ያሉት የእህል ማበጠሪያ ማሽኖች እብዛኛዎቹ ያረጁና አገልግሎት እንደማይሰጡ መሆናቸው

**የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ በየጊዜው መከለሱን በተመለከተ፣**

11. ድርጅቱ የሚጠቀምበት የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ በየጊዜው ሊከለስና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ መመሪያው ሲከለስም በየጊዜው የሚደረጉ የአደረጃጀት ለውጦች እና የእህል ክብካቤ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን አለበት፡፡ ከዚሁ ጋር አብሮ ከመመሪያው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች መመሪያዎችና ደንቦችም አብረው ሊከለሱ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት አሁን እየሰራበት ያለው የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክምችት ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ የተዘጋጀው በ1986 ዓ.ም ሲሆን በአሁኑ ወቅት ካለው ተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታ ጋር እና የድርጅቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ጋር በተጣጣመ መልኩ ተከልሶ ወቅታዊ አለመደረጉ፤ በናሙና ከተመለከትናቸው የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአሰላ፤በጅማ፤ እና በባህር ዳር የእህል ጥራት ቁጥጥርና ክብካቤ የአፈጻጸም መመሪያ አለመገኘቱ ፡

**ወቅታቂ የእህል መረጃዎችን ዘመናዊ በሆነ መልኩ የሚለዋወጡበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ**

12. ድርጅቱ ወቅታዊ የሆኑ የእህል የገበያ ዋጋና ተዛማጅ መረጃዎችን

አጠናቅሮ ሊይዝ ይገባል፡፡ እነዚህንም መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ የመለዋወጫ ዘዴ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ጋር ሊለዋወጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለደንበኞቹም ሆነ ለባለድርሻ አካላት መረጃ የሚያስተላልፈበትና እራሱን የሚያስተዋውቅበት ድረ-ገጽ ሊኖረው ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ በአብዛኛው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ጋር የሚያገናኘው የኮምፒውተር ኔትወርክ የዘረጋ ቢሆንም በናሙና ከታዩት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በባህርዳር የኔትወርክ መስመሩ ያልተዘረጋ ሲሆን፤ በጅማ፤ በአዲስ አባባ፣ በአሰላ እና በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኔትወርኩ ቢዘረጋም ከዋናው መ/ቤት ጋር የየእለቱን የገበያ ሁኔታ በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ በመረጃ መረብ አማካኝነት አለመደረጉ፤

13. ድርጅቱ አጥንቶ ተግባራዊ ባደረገው አዲሱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ በረዥም ጊዜ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን በመጠቀም ሽያጭን ማከናወን የሚል እቅድ ቢኖረውም ድርጅቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተግባራዊ ከተደረገ ከ4 ዓመታት በኃላም በስራ ላይ አለመዋሉ፤ ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ በአሁኑ ጊዜ እየተጠቀመበት ያለውን ስታቲክ ድረ ገጽ ወደ ዳይናሚክ አለመለወጡ፤

**ለድርጅቱ ሰራተኞች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጠውን ሥልጠና በተመለከተ**

14. የእህል አያያዝና የምርት ጥራትን በተመለከተ ለሚመለከታቸው የመሰሪያ ቤቱ ባለሞያዎችም ሆነ የእህል አቅራቢ ህብረት ስራ ማህበራት በየዓመቱ ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በ2004 በጀት ዓመት ለ 240 ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት ብር 89,900 በጀት በእቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ለ13 ሰልጣኞች ብቻ ብር 3,129 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ ይህም አፈጻጸም በሰልጣኝ ብዛት ከእቅድ አንጻር 5 በመቶ በክፍያ አንጻር 3 በመቶ ብቻ መሆኑ፤ እንዲሁም በድርጅቱ የ2001-2004 እስትራቴጂክ እቅድ መሰረት የእህል አያያዝ እና የምርት ጥራትን በተመለከተ በየዓመቱ አንድ ስልጠና ለመስጠት እቅድ የተያዘ ቢሆንም ከ2002-2004 ዓ.ም ድረስ በ2004 ዓ.ም በእህል ጥራትና ቁጥጥር ህክምናና የመጋዘን አያያዝ እዲሁም በሰነዶች አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ከአሥሩም ቅርንጫፍ የስራ ሂደቶችና ከእህል ግዥና

ሽያጭ ወሳኝ የሥራ ሂደት ለተወጣጡ 27 ሰልጣኞች ለ3 ቀናት ከተሰጠ ስልጠና ውጭ የተሰጠ ምንም  ዓይነት ስልጠና አለመኖሩ፤

**ከአምራቾችና ከሸማቾች ማህበራት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣**

15. ድርጅቱ የተለያዩ እህሎችን ለሽያጭ ከሚያቀርቡለት የተለያዩ የህበረት ሥራ ዩኒየኖች  እና በየከተማው ገበያ ለማረጋጋት ከተቋቋሙ  የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር  የስራ ግንኙነት የሚፈጥርበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይህ ሥርዓትም ለድርጅቱ የሚያቀርቡት እህል ተፈላጊውን ደረጃ የሚያሟላ እንዲሆን ለማስቻል የሚሰጥ ድጋፍን ሊያካትት ይገባል፡፡  ድርጅቱ  በእያንዳንዱ ከተማ እየተቋቋሙ ካሉ ዩኒየኖች፣ የአምራቾችና የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ጠንካራና ጤናማ የስራ ግንኙነት የመፍጠር ተደራሽ ግብ ቢይዝም በመስክ የስራ ጉብኝት ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው  የህብረት ስራ ዩኒየኖች (ጋልማ ሁለገብ የገበሬዎች የህብረት ስራ ዩኒየን- አሰላ፤ ሊሙ አዳማ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን- አዳማ ፤ ጅሬን የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር- ጅማ፤ እንዲሁም መርከብ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን- ባህር ዳር) ለመረዳት እንደተቻለው ከድርጅቱ ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት በእህል ህክምና እና በገበያ ማረጋጋት ስንዴ እህል ግዥ ብቻ የተወሰነ መሆኑ፤ ድርጅቱ ከዩኒየኖቹ የእህል ግዥ የማያከናውን መሆኑ እና የተለያዩ የምክር እና ስልጠና ድጋፍ ለዩኔየኖቹ የማይሰጥ መሆኑን

**የገበያ ማረጋጊያ ስንዴ እህል አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ**

16. በገበያ ላይ ያለውን የስንዴ ዋጋ ለማረጋጋት ድርጅቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የዋጋ ማረጋጋት ሥራን በጥናት ላይ የተመሰረተና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ መንግስት (የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር) የገበያ  ዋጋን ለማረጋጋት  ከውጭ አገር ገዝቶ  ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባውን ስንዴ በመረከብ በየክልል በሚገኙ የድርጅቱ መጋዘኖች እና በዋናው መጋዘን ያከማቻል፡፡ ንግድ ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የስንዴና የዳቦ ስርጭት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ለሚመርጧቸው የዱቄት ፋብሪካዎች፣ አከፋፋዮች፣

የሸማቾች ማህበራትና ዳቦ ቤቶች እንዲደርሳቸው በተወሰነው መጠን እና በተተመነው ዋጋ መሰረት የእጅ በእጅ ሽያጭ እንደሚያከናውን በኦዲቱ ወቅት ታወቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሥር በሚገኙ መጋዘኖች ውስጥ ከባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀር ለዋጋ ማረጋጋት ሲባል ከውጭ አገር ተገዝቶ ለስርጭት የተዘጋጀ ስንዴ አለመኖሩ፣

17. የኦዲት ቡድኑ ከተለያዩ የሸማቾች ማህበራት፣ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየኖች እንዲሁም የዳቦና ዱቄት ማምረቻ ፋብሪካዎች በቃለመጠይቅ በሰበሰበው መረጃ በስንዴ ስርጭት ወቅት ንግድ ሚኒስቴር እና ንግድ ቢሮ በሚተምንላቸው ኮታ መሰረት ከኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ያለምንም ችግር እየወሰዱ መሆናቸውን ገልጸውልናል፡፡ የኦዲት ቡድኑ ለመስክ ጉብኝት በተለያዩ የድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በተዘዋወረበት ወቅት የማረጋጊያ ስንዴ በስፋት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች ውስጥ ባለመኖሩ እና አየተከፋፈል ባለመገኘቱ ህብረተሰቡ ከማረጋጊያው ስንዴ ምን ያህል መጠቀሙን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

18. በመሆኑም

- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በስሩ የሚተዳደሩትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከየግብርና ጣቢያዎች የሚሰበስቡት የሰብል ግምገማ መረጃዎችን ወጥነት ባለውና በመረጃ በተደገፈ መልኩ እንዲሰበስቡ በማድረግ እንዲሁም የእህል ግዥን በእህል ጥራት ደረጃው በመከፋፈል ግዥ የሚፈጸምበትን ስርዓት በመቅረጽ በየበጀት ዓመቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ ሊይዝና በየበጀት ዓመቱ የሚገዛውን የእህል መጠን እና አይነት ሊያሳድግ ይገባል፡፡
- የእህል ግዥ እና ሽያጭ ዋጋ የመወሰን ስልጣን የድርጅቱ የእህል ግዥ አፈጻጸም መመሪያን እና የመሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ ጥናትን መሰረት በማድረግ እና በማጣጣም ግልጽ የሆነ እና የእህል ግዥ እና ሽያጭ አፈጻጸምን ሊያጠናክር የሚችል የስልጣን ውክልና ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ለእህል ግብይት ሲባል ለግዥ ማዕከላት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በግለሰቦች ስም የሚላከው ገንዘብ በሚፈለገው ጊዜና ለተባለለት ዓላማ

መዋሉን ለመከታተል የሚያስችል ወጥ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ድርጅቱ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ የሚሳተፍባቸውን የእህል ንግድ ዓይነቶች በማሳደግ እና የገበያ እድልን በማስፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን እህሎች በተጠናከረ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ አለም አቀፍ የገበያ ሁኔታን በማጥናት እና ወደ ስራ ውስጥ በመግባት በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የውጭ ንግድ ሽያጭ ድርሻውን ከፍ በማድረግ የተቋቋመበትን ዓላማ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- የድርጅቱ የእህል ክምችት አያያዝና አጠባበቅን የተሻለ እና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል ድርጅቱ መጋዘኖቹን በበቂ እና ዘመናዊ በሆኑ የእህል ጥራት ማረጋገጫ መሳሪያዎች ማጠናከር እንዲሁም በእህል ጥራት ቁጥጥር ስራ ላይ ለተሰማሩ ባለሞያዎች ወጥነት ያለውና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠት የሚቻልበትን ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚጠቀምባቸውን የአሰራር መመሪያዎች ከተጠናው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ጋር በማጣጣም ሊከለሱና ወቅታዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ዋናውን መ/ቤት ከቅርንጫፍ መ/ቤቶች ለማገናኘት እና በቀላሉ መረጃዎች ለመለዋወጥ በከፍተኛ ወጪ የዘረጋውን የኔትወርክ መስመር ዝርጋታ ተግባራዊ በማድረግ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ሊያስጀምር ይገባል፡፡በተጨማሪም የዘረጋውን የመረጃ መረብ በማሻሻል በእቅድ እየተያዘ ተግባራዊ ያልተደረገውን የኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ ሊጀምር ይገባል፡፡
- ድርጅቱ መንግስታዊም ሆኑ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የሥራ ግኝኙነቱን ሊያጠናክርና ህገወጥ የእህል ንግድ ለመከላከል የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡
- ገበሬው ለአመረተው እህል አግባብነት ያለው ክፍያ እንዲያገኝ እንዲሁም የሚያመርተው ምርት ጥራት ኖሮት ለአለም ገበያ እንዲቀርብ ድርጅቱ በእህል ጥራት አያያዝ ዙሪያም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በየክልሉ ከተመሰረቱ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየኖች ጋር ተባብሮ የሚሰራበት ስርዓት ሊዘረጋና

ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ

በመሆኑም የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በእህል ግዢ፤ሽያጭ እና ክምችት አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.2 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታክስ መረጃ አያያዝንና አስተዳደርን በተመለከተ

**ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀትና አስተዳደር መኖሩን በተመለከተ፤**

19. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የገቢ አሰባሰብና የታክስ አወሳሰን ሂደት በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የተደገፈ የታክስ መረጃ አሰባሰብና፤ አደረጃጀት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች መረጃ በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ በዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀትና አስተዳደር ለመያዝ የሚያስችል የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተያዘ መረጃን የሚመዘግብና የሚቆጣጠር፤ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥርና የጣት አሻራ መመዝገቢያ እና የጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈልን የሚያግዝ አሲኩዳ የተባሉ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን የዘረጋ ቢሆንም በዘረጋው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በአግባቡ የግብር ከፋዩን መረጃ አሰባስቦ የመያዝ የማደራጀት እና የማስተዳደር ተግባሩን በቂ ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ አለማድረጉ

20. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የባህርዳር፣ የምዕራብ አዲስ አበባ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ እና የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤቶች የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) ሪከርድ ማኔጅመንት ሞጁል በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ አለማዋሉ፣ በማህደር ተከማችተው ያሉ የግብር ከፋይ መረጃዎችን በማጥራት ወደ ተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) ሙሉ በሙሉ በመመዝገብ እንዲገባ አለመደረጉ፤ በSIGTAS ላይ ያለው የግብር ከፋይ መረጃ በመዝገብ ቤት በማህደር ከተያዘው ጋር የማይናበብ መሆኑ፣

እንዲሁም በመዝገብ ቤት የተያዘው የግብር ከፋይ ማህደር በቂ ቦታና የፋይል ማስቀመጫ (ላተራል) ስላልተዘጋጀለት ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑ

**የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ**

21. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ግብር ከፋዮች መረጃ በየደረጃው መዝግቦ መያዝ፤ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበትን እያንዳንዱን ግብር ከፋይ በጣት አሻራ ላይ የተመሠረተ የግብር ከፋይ የመለያ ቁጥር (TIN) መስጠት ፤ እያንዳንዱ ግብር ከፋይም ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዳይኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ስርዓት አፈፃፀም መመሪያ 11/2001 በማውጣት አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ መለያ ቁጥር ሊሰጠው እንደማይችል ያስቀምጠ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡት ቅ/ፅ/ቤቶች 26 ግብር ከፋዮች በሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ተመዝግበው መገኘታቸው

**ግብር ከፋዮች የመክፈያ ጣቢያ ሲቀይሩ መረጃቸው የሚተላለፍ መሆኑን በተመለከተ**

22. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት/ ጣቢያ ሲቀይሩ በሰነድ ያለው መረጃ ሙሉ ለሙሉ መዘዋወሩ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና በSIGTAS ያለው የመክፈያ ጣቢያ መለያ ቁጥርም ወደ አዲሱ መቀየሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
23. በኦዲቱ ወቅት 62 ግብር ከፋዮች በተቋሙ ስር ከሚገኙት 10 የታክስ ማዕከሎች ውጭ ተመዝግበው የተገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 25 ግብር ከፋዮች “አዲስ አበባ ቫት” በሚባል የተመዘገቡ ሲሆን፣ 37 ግብር ከፋዮች “አዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን” በተባለ በተዘጋ ታክስ ማእከል የተመዘገቡ መሆኑ፤
24. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽቤት (ታክስ ማዕከሎች) በሚቀይሩበት ወቅት ፋይላቸው ከነሙሉ መረጃቸው ስለመዘዋወሩ ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋቱ እነዲሁም ደግሞ የዝውውር ሂደቱን ለማከናወን የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በጥቅም ላይ እንዲውል አለመደረጉ፡

**በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ መሆኑን በተመለከተ**

25. በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) በማዕከል ተመዝግቦ የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች (የታክስ ማእከል) ተመዝግቦ ከተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል፡፡

26. በማዕከል በተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በአምስቱ ቅርንጫፎች ያሉ ተብሎ ተመዘገቦ የተያዘው 29792 ግብር ከፋዮች ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አምስት የታክስ ማዕከላት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የተያዙት 21595 ግብር ከፋዮች ብቻ መሆናቸው፣ ይህም በማእከል በSIGTAS ተመዝግቦ ከተያዘው በ8197 የሚያንስ መሆኑ

27. ከላይ ከተጠቀሱት ግብር ከፋዮች ውስጥ በአምስቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በስራ ላይ ያሉ (Active) ተብለው የተያዙ 20047 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ በSIGTAS ላይ በሥራ ላይ ያሉ ግብራቸውን የሚያሳውቁ (active) ተብለው የተያዙት 28,287 ግብር ከፋዮች መሆኑ ይህም በ(active) ግብር ከፋይነት በSIGTAS ላይ የተመዘገቡት ግብር ከፋዮች ቁጥር በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ከያተዙት በ8240 ብልጫ ያለው መሆኑ፤ በባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ 37 ግብር ከፋዮች በSIGTAS ላይ ምዝገባቸው በሌላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት (የታክስ ማዕከል) ላይ ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ

**የግብር ከፋዮች የግዥ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /Data Base/ በማእከል መያዛቸውን በተመለከተ**

28. የተሟላ መረጃን መሰረት ያደረገ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ከሁሉም ግብር ከፋዮች እና ከሶስተኛ ወገን መረጃ ሰጪ አካላት የግዢ እና የሽያጭ ግብይት መረጃዎች ተሰብስበው እና ተደራጅተው በመረጃ ማእከል /ቋት/ ሊያዙ ይገባል፡፡ የግብር ከፋዮች የቅሬታ መረጃዎች እና የተሰጡ ውሳኔዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሁሉም ግብር ከፋዮች የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልኩ የማይሰበሰቡና የተሰበሰቡትም መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ወደ ማእከላዊው የመረጃ ቋት ተጠቃሎ አለመግባቱ፣

30. የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመታት የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ወደ መረጃ ቋት አለመግባታቸው

31. የግብር ከፋዮች መረጃ ለውሳኔ ሰጪዎችም ሆነ ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ በየሥራ መስክ እና ዓይነት በመለየት (ለምሳሌ በግብርና ዘርፍ፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፤ በኢንዱስትሪ ዘርፎች ወዘተ--) ተደራጅቶ አለመያዙ

32. ውዝፍ ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች፣ የሚያቀረቡትን ቅሬታና አቤቱታ የሚመለከቱ መረጃዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅረው አለመያዛቸው

33. መረጃው በሚመዘገብበት ወቅት ግብር ከፋይ ማቅረብ የሚገባቸው ዋና ዋና መረጃዎች እንደ የባንክ አካውንት፣ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የግብር እፎይታ ጊዜ ተጠቃሚ ከሆኑ ደግሞ እፎይታው የሚያበቃበት ጊዜ እንዲሁም ወቅታዊ አድራሻዎች በተሟላ ሁኔታ በSIGTAS አለመመዝገቡ፤

34. የግብር እፎይታ ጊዜ (Tax holiday) ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የእፎይታ ጊዜያቸው መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያበቃና ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ መረጃና ሌሎች መረጃዎች በተሟላ መልኩ ተደራጅተው አለመያዛቸውን ባለሥልጣኑ ባቋቋመው የአገር ውስጥ ታክስ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ቡድኑ መገለጹ፤

**የግብር ከፋዮዎች ሀብትና ንብረት መረጃ ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ**

35. ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ መረጃ እንዲኖር የሁሉም ግብር ከፋይ ሀብትና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ነገር ግን ባለስልጣን መ/ቤቱ በአጠናው የመሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ ጥናት የሁሉም ግብር ከፋይ ሀብት እና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ በተመለከተው መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፤

**ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረጉ መሆኑን በተመለከተ**

36. በመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ተደራጅቶ የተያዘው መረጃ እና በመዝገብ ቤት በማህደር (Hard Copy) የተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

በመዝገብ ቤት በማህደር ተይዘው የሚገኙ መረጃዎችን የማጥራት ተግባር እንዳልተከናወነ እና በSIGTAS ተመዝገበው የተያዙ የግብር ከፋይ መረጃዎች በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ የማይደረጉ መሆኑ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 608/2001 መሰረት ግብር ከፋዩ የሚያደረጋቸውን ማንኛውም ለውጦች በግብር ከፋይነት በተመዘገበቡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየቀረበ ማሳወቅ እንደሚገባው እና በየጊዜው የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች ተጠያቂ ሊደረጉ እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፤

**የታክስ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መዘጋጀቱን በተመለከተ**

37. ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ ለማሰባሰብ ፤ለማደረጀት እና ለማስተዳደር በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲና እስትራቴጂ መቅረጽ እና የተቀረፀውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች (ማንዋሎች) አዘጋጅቶ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃዎችን በአይነታቸው እየለየ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት እና ተንተኖ በማሰራጨት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም አገር አቀፍ የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ አለማዘጋጀቱ

**በፌዴራል፣ በክልል መንግስት እና በከተማ መስተዳደሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ መኖሩን በተመለከተ**

38. በፌደራል፤በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል ወጥነት ያለው የታከስ መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር እንዲኖር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ሊኖር ይገባል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በክልሎች እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ለመፈራረም በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ

**የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮችን በተመለከተ**

39. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች

በሙሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መርሃ- ግብር መሰረት መሳሪያውን መጠቀም አለባቸው፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዮት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች በባህርዳር፣በሀዋሳ፣ በምዕራብና በምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤቶች በSIGTAS ተመዝግበው ከተያዙት 29792 ግብር ከፋዮች ውስጥ 12090 ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚ ሲሆኑ 17702 (59.41%) ግብር ከፋዮች ተጠቃሚ አለመሆናቸው

**የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌርን በተመለከተ**

40. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌር በባለሥልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፡፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ያላገኘ ሶፍት ዌር የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች ካሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመከታተልና በመቆጣጠር ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር መጠቀም በህግ እንደሚያስጠይቅ በተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 47 ቁጥር 1 ላይ የተገለፀ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩ በከፍተኛ ግብር ከፋይነት የተመዘገቡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 14 ሆቴሎች ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው ሶፍትዌር እየተጠቀሙ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መረጃቸውን በአግባቡ ማስገባታቸውንና መረጃው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ቋት ጋር የተገናኘ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ እና በህጉ መሠረት እርምጃ አለመውሰዱ

41. በሂልተን እና በሸራተን አዲስ ሆቴሎች ከአገልግሎት ውጭ የተደረጉ 22 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመመሪያው መሰረት በአስመጪዎቹ ዘንድ መቀመጥ ሲገባው በሆቴሎቹ መጋዘኖች ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ

**የሽያጭ መሳሪያዎች ጥገናን በተመለከተ**

42. አቅራቢዎች የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማቅረባቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መስፈርት ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲበላሹ በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግ፣ አገልግሎት ላይ ያሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችም በየአመቱ መደበኛ ምርመራ

ሊደረግላቸው እና መሳሪያዎቹን ለማቅረብ ግዴታ የገቡት አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግና ግዴታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ አቅራቢዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችም ሆነ አቅራቢዎቹ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 133/1999 መሰረት መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉ ታውቋል፡፡

43. ግብር ከፋዩ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች ገዝቶ ከሚጠቀምባቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በአማካይ በዓመት 15670 የሚሆኑት በብልሽት ምክንይት ለጥገና የሚገቡ ሲሆን 7146 (46%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሲወጡ የቀሩት 8320 (54%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው እንደማይወጡ፣ አገልግሎት ላይ ከዋሉ ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 72964 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አመታዊ ምርምራ በተሟላ መልኩ እንደማይደረግላቸው እና ባለሥልጣን መ/ቤቱም በህጉ እና በገቡት ግዴታ መሰረት ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፣

**የንግድ ፍቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚቋረጥበት ስርዓትን በተመለከተ**

44. የንግድ ፈቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዮች ይጠቀሙበት የነበረው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አገልግሎት ከመስጠት የሚቋረጥበት እና መረጃው በምን መልኩ ወጥቶ መያዝ እንዳለበት የሚያሳይ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

**የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች መረጃን በተገቢው መንገድ ስለመመዝገባቸው የሚያደረግውን ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ**

45. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት መተላለፍ አለመተላለፋቸው በየታክስ ማዕከሉም ሆነ በዋናው መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

46. የሽያጭ መመዘግቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመሩበት

ጊዜ አንስቶ እስከ 2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለግብር ከፋዩ ከተሸጡት 82141 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ውስጥ 72964 (89%) አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 8755 (12%) ብቻ የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ፣ የተቀሩት 64209 (88%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፣ እና 5888 (12%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ከሲስተሙ ጋር ያልተያያዙ መሆናቸው፡

47. የአማራ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሥራቸው ያሉ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ክትትል የሚያደርጉ ቢሆንም መሳሪያዎቹ መረጃዎችን ወደ ዋናው ዳታ ቤዝ ማስተላለፍ አለማስተላለፋቸውን ግን ለማረጋገጥ በዋናው ዳታ ቤዝ የሚያዘውን መረጃ ለማየት የይለፍ ቃል(ፓስ ወርድ) ስላልተሰጣቸው ማረጋገጥ እንዳልቻሉ መገለጹ፤ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቅድሚያ ትኩረት ሲሰጥ የነበረው መረጃ የሚልኩ መሳሪያዎች የሚጨምሩበትን ስርዓት ማጠናከር እንደነበር፣ አቅራቢዎች መሳሪያዎቹ እዛው ባሉበት ቦታ መረጃ መላካቸው የሚያረጋግጡበት ዌብ - ፖርታል እንዲዘጋጅ ከማድረግ ጀምሮ ሳይልኩ እንዳይወጣ የሚያደርግ አሰራር በመከተል ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጃ ስለመላካቸው እያረጋገጠ እንደሚገኝ፣ ሆኖም የ(G*eneral* P*acket* R*adio* S*ervice*) (GPRS) ኔትወርክ ምልክት ወይም ሲግናል በማይኖርበት ወቅት፣ ከኢትዮ ቴሌኮም ወደ መረጃ ቋት የሚያገናኝ መስመር ብልሽት ሲያጋጥም፤ የመረጃ ቋት (Server) ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ፤ የሽያጭ መረጃ ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፤ በተጨማሪም የ(G*eneral* P*acket* R*adio* S*ervice*) የ(GPRS) ኔትወርክ አርባ በመቶ (40%) በአዲስ አበባ ስለማይሰራ በየጊዜው የሚያጋጥመውን የኔትወርክ መቆራረጥ ችግርን በተመለከተ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በተደጋጋሚ በመነጋገር ለመፍታት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ሊፈታ ያልቻለ ችግር መሆኑን፤ የተሸጠውና ሥራ ላይ የዋለው ልዩነት ደግሞ መሣሪያዎቹ አስፈላጊው ምዝገባ በቅጽ ተጠናቆላቸው በንግድ አድራሻቸው ተተክለው

ግን የቅጹ መረጃ ወደሽያጭ አጠቃቀም ሶፍትዌር እንዲገባ ባለመደረጉ የተፈጠረ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቀጣይነት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከየታክስ ማዕከሉ መሳሪያዎቹ መረጃ መላካቸውን የሚከታተሉበት ስርዓት እንደሚመቻችና መረጃዎቹን በቀጥታ እንዲጠቀሙ የይለፍ ቃል (ፓስወርድ) እንደሚሰጣቸው፣ እስከ አሁን ግን የታክስ ማዕከላቱ የሽያጭ መረጃዎች የሚከታተሉበት ስርዓት የሌላቸው በመሆኑ መረጃ ሲጠይቁ በታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል በሶፍት ኮፒ በማዘጋጀት ከመሳሪያዎቹ የተገኘ መረጃ እየተጠቀሰ ተጠናቅሮ እንደሚላክ መገለጹ

**ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን በተመለከተ**

48. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መለያ ቁጥር (TIN) ተሰጥቷቸው ተመዝግበው የንግድ ፍቃድ አውጥተው መክፈል የሚገባቸውን ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮችን ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መረጃቸው ሊደራጅ እና ሊያዝ፣ በተያዘው መረጃ መሰረትም ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ሁኔታው እየተጣራ መክፈል የሚገባቸውን ግብር እንዲከፍሉ ሊደረግ ይገባል፤

49. የንግድ ስራቸውን ማቆማቸው ወይም መዝጋታቸው የተረጋገጠ ግብር ከፋዮችም የተመዘገቡበትን መለያቁጥር (TIN) በማስመለስ ፋይላቸው ከሲስተሙም ሆነ ከማህደር ሊዘጋ ይገባል፡፡

50. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ቅ/ጽቤቶች መክፈል የሚገባቸውን ግብር ያላሳወቁ 1506 ግብር ከፋዮች ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጅት መረጃቸውን በየግብር ዘመኑ አደራጅቶ በመያዝ ያለባቸውን የግብር ዕዳ እንዲከፍሉ ክትትል እና ቁጥጥር አለመደረጉ፤

51. ሥራ አቁመዋል ተብለው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፋይላቸው የተዘጉ ተብለው ከተያዙት 3362 ግብር ከፋዮች ውስጥ ሥራ እንዳቆሙ በማዕከል ደረጃ የሚታወቁት እና የተዘጉ ተብሎ በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) ላይ የሚታዩት 1504 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 1858 ግብር ከፋዮች ግን በሥራ ላይ (active) እንደሆኑ የሚታይ መሆኑ፤

**ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ የሚረዱ መረጃዎች ተጠናቅረው መያዛቸውን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን በተመለከተ**

52. ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የሚረዱ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /ዳታ ቤዝ/ ሊያዙ፣ የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንተንና በማጠናቀር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለተጠቃሚዎች ሊሰራጭ፣ የተሰራጨት መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ለመከታተል እና ግብረ መልስ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡

53. የባለስልጣን መ/ቤቱ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎች የሚያዙባቸው እንደ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ መስብሰቢያ፣ የጉምሩክ ስነሥርዓት ለገቢ ዕቃዎችም ሆነ ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት የአሲኩዳ ሲስተም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሲሰጥ የሚመዘገብበትና የአሻራ ምዝገባ የመረጃ ቋቶችን ያደራጀ ቢሆንም እነዚህ የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface) ተደርገው አለመሰራታቸው

54. የተሰበሰበዉ መረጃ ተደራጅቶ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የጥራት ደረጃውን ለመገምገምና ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

55. በተበታተኑ የመረጃ ቋቶች የተያዘው መረጃም ሆነ ከሶስተኛ ወገን በተለያየ ዘዴ የተሰበሰበው መረጃን የመሰብሰብና ተንትኖ የማጠናቀር እንዲሁም የማሰራጨት ተግባር ከዋናው መ/ቤት በስተቀር በቅ/ፅ/ቤቶችና በክልሎች የማይከናወን መሆኑ፤

56. ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ክልሎች መረጃዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ መሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉ መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ግብረ መልስ የማይሰብሰብ መሆኑ፤

57. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ለክልሉ ግብር ከፋይ የሆኑ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ በአሲኩዳ እና በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የተያዙ መረጃዎችን መጠቀም አለመቻላቸውን፣

58. ክልሉን የሚመለከት የገቢ አስተዳደር መረጃዎችን ለመጠቀም ፓስወርድ ለመፍቀድና ለመከልከል የፌዴራሉ ፈቃድ ማስፈለጉ ፤ ለመጠቀም

ሲጠይቁም አፋጣኝ ምላሽ የማያገኙ መሆኑን፣

59. የአማራ ክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ደግሞ የሽያጭ መመዝገቢያና ሌሎች የዳታ መረጃዎችን አስተዳደር ለክልሎች አለመፈቀዱ በሥራቸው ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ እንደፈጠረባቸው መግለጻቸው

**የመረጃ አቅርቦት መስጫ ማዕከል መኖሩን በተመለከተ**

60. የመረጃ መስጫ ማዕከላትን በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በመክፈት ለግብር ከፋዩ ወይም ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ተገቢው ማብራሪያ ሊሰጥ ይገባል። ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት የመረጃ መስጫ ማዕከላት በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ያልተቋቋሙ በመሆኑ ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ የማይሰጥ መሆኑ

በመሆኑም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታክስ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል።

## 10.3 በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የካሳ ክፍያ አከፋፈልን በተመለከተ

**አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት በማድረግ አገር አቀፍ የካሳ አከፋፈል ቀመር እና የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

61. አዋጅ ቁጥር 455/1997ን መሰረት በማድረግ ለልማት ሥራ ለሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት ለሚከፈል የካሳ ግምት አገር አቀፍ ቀመር ሊወጣ ይገባል። ክልሎችም አዋጁንና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አለባቸው። በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የካሳ ግምት ለሚሰሩ ገማች ኮሚቴዎች እንዲደርስ ማድረግ እና በዚሁ መሰረት የካሳ ግምት ሊሰራ ይገባል። በዚህም መሰረት አዋጅ ቁጥር 455/1997ን ለማስፈጸም ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ስለሚከፈል ካሳ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቁጥር 135/1999ን) ያወጣ ቢሆንም በናሙና ከታዩት ሁለት ክልሎች ውስጥ አዋጁንና ደንቡን መሰረት በማድረግ የአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት የአፈጻጸም መመሪያ በመጋቢት 2003 ያወጣ ሲሆን፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

ክልል ግን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የአፈፃፀም መመሪያ አለማውጣቱ፤

62. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀድያ ዞን ሌሞ ወረዳ ለወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪሎቮልት የኃይል መስመር ዝርጋታ ለሚነሱት ንብረቶች የተቋቋመው የካሳ ገማች ኮሚቴ የወጣውን አገር አቀፍ ተመን መሰረት ሳያደርግ አስልቶ ብር 7,240,101 (ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ አንድ ብር) የካሳ ክፍያ ግምት በማቅረብ ክፍያ እንዲፈፀም የጠየቀ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ በአገር አቀፍ ቀመሩ መሰረት ክፍያው በጣም የተጋነነ መሆኑን በመግለጽ በድጋሚ በቀመሩ መሰረት ሂሳቡ እንዲሰላ በመጠየቁ በተደረገው ማጣራት የተገመተው የካሳ ክፍያ ወደ ብር 3,387,967 (ሦስት ሚሊዮን ሥስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሰባት ብር) ዝቅ መደረጉና ክፍያውም በዚሁ መሰረት መፈጸሙ፤

63. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዘግይቶም ቢሆን የካሳ ክፍያ የአፈፃፀም መመሪያ በ2003 ዓ.ም በማውጣት ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና መስጠቱን በኦዲቱ ወቅት የተገለጸ ሲሆን የደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ግን በ2004 ዓ.ም ረቂቅ የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጀ ቢሆንም የኦዲቱ ስራ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ እንዲጸድቅ አለመደረጉን የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መግለጹ፤

**የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር እና መመሪያ በየጊዜው ወቅታዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

64. የካሳ ክፍያ የአተማመን ቀመር በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሊዘጋጅ እና የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል። ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የአማራ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መስተዳደሮች ካሳ ክፍያን አስመልክቶ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ መገለጹ፤

65. በተጨማሪም የሚጠቀሙበት ቀመር ያለፉትን አምስት አመታት አማካኝ ዋጋ በመውሰድ መሆኑና የዋጋ ልዩነቱም በጣም የተራራቀ የሚያደርገው በመሆኑ በካሳ ክፍያ ወቅት ከፍተኛ ችግር የገጠማቸው

በመሆኑ ቀመሩ እንደገና ሊታይ እንደሚገባ መገለጹ

**የካሳ ክፍያ ንብረት ለመገመት ተገቢው ሙያ ያለው ኮሚቴ የተቋቋመና የገማች ኮሚቴ አባላት ስለካሳ ግመታ ገለጻ ወይም ስልጠና ያገኙ መሆኑን በተመለከተ፣**

66. ለልማት ሥራ የሚፈለገው መሬት የሚገኝበት የወረዳው ወይንም የከተማው አስተዳደር ለሚከናወነው የካሳ ግምት ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የሚገኙበት የካሳ ገማች ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ የሚቋቋሙት የካሳ ገማች ኮሚቴዎች አባላት ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት በአዋጅ ቁጥር 455/97 እና ደንብ ቁጥር 135/99 ላይ ገለጻ ወይም ስልጠና እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የጣና በለስ-ባህርዳር፣ ባህርዳር- ደብረማርቆስ-አዲስ አበባ እና የወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ 400 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላላፊ መስመር ከሚያልፉባቸው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያ እና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች እና የባህርዳር ከተማ መስተዳድር፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ የተቋቋሙት ገማች ኮሚቴዎች ከተለያዩ ዘርፎች የተወጣጡ ባለሙያዎች ቢሆኑም ካሳ ግመታን የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተመለከተ ገለጻ ወይም ሥልጠና ባለመሰጠቱ ህጎቹን በራሳቸው ጥረት በመረዳት የካሳ ግመታውን ይሰሩ እንደነበረ መግለጻቸው፤

**የካሳ ክፍያ ግምት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ፣**

67. ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚነሱ ባለይዞታዎች የሚከፈለው የካሳ ግምት በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ የካሳ ክፍያ ግምት ከመሰራቱ በፊት የፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናትና የሚያርፍባቸው ቦታዎች መልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር (Resettelement action plan) ሲጠናም ሆነ የካሳ ገማች ኮሚቴው በልማት የሚነሱ ንብረቶችን የግምት ሥራውን ሲሰራ በበቂ መረጃ ላይ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከተከለሱ ከካሳ ክፍያ ጋር የተያያዙ አላማጣ-መሆኒ- መቀሌ እና ቆቃ -ሁርሶ- ድሬዳዋ የ230 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክቶችና፣ የአሉቶ- ላንጋኖ ፕሮጀክት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን ስታትስቲካዊ መረጃ አለመጠቀማቸው፤ የኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት እና የገማች ኮሚቴ የካሳ ግምትም አንድ

አለመሆኑ፤

**ለልማት እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከት መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣**

68. ለልማት አገልግሎት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬትና በመሬቱ ላይ የሚገኙ ንብረቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት የከተማው ወይንም የወረዳው አስተዳደር ሊይዝ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህርዳር ከተማ መስተዳደር፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ ለኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ማስተላለፊያ ሥራ ለማከናወን የተነሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ የተጠናቀሩ መረጃዎች በከተማው ወይንም በወረዳው አስተዳደር ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

**መሬት ለልማት ሥራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበት ጊዜ እና የካሳው ግምት ለባለይዞታው በቅድሚያ መገለጹንና መሬቱ በወቅቱ መለቀቁን በተመለከተ፣**

69. መሬት ለልማት ስራ እንዲለቀቅ ሲወሰን መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜና የካሳውን መጠን የሚጠቅስ የማስለቀቂያ ትእዛዝና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ለባለይዞታው በጽሁፍ እንዲደርሰው ሊደረግ ይገባል፡፡ ለባለይዞታውም የሚሰጠው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ጊዜንም በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት ክልሎች መመሪያ ማውጣት ያለባቸው ሲሆን የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ጊዜ ግን ከ90 ቀናት ማነስ የለበትም፡፡ ካሳ የተከፈለው ባለይዞታም ካሳ በተከፈለው በ90 ቀናት ውስጥ ይዞታውን ለወረዳው ወይም ለከተማው መስተዳድር ማስረከብ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት ጣና በለስ- ባህርዳር፣ ባህርዳር - ደ/ማርቆስ - አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ቦታው ለልማት እንደሚፈለግና በአጭር ጊዜ ውስጥ ስራው የሚጀመር መሆኑ ለተነሺዎቹም ሆነ ለካሳ ገማች ኮሚቴዎች የተነገረው በድንገት መሆኑ፣ ለተነሺዎቹም በአዋጁ መሰረት ቢያንስ የ90 ቀን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ያለመሰጠቱንና ህብረተሰቡ ስለሚሰራው ሥራ በቂ ግንዛቤ እና ተሳትፎ እንዲኖረው አለመደረጉ፤

70. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ባህርዳር - ደ/ማርቆስ - አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል

ማስተላለፊያ መስመር ለልማት አገልግሎት ተብሎ ከይዞታቸው ለተነሱና ንብረት ለተጎዳባቸው ባለይዞታዎች በአዋጁ መሰረት በቅድሚያ ካሳ ሳይከፈላቸው የተነሱ መሆኑ

71. በ2004 በጀት ዓመት የካሳ ክፍያ ግምት ተሰርቶላቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የካሳ ክፍያ ያልተፈጸመላቸው ባለይዞታዎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የጉራጌ ዞን ምስቃን ወረዳ (ጃሌ 1ኛ ቀበሌ)፣ የሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ (ታች ሀምቢቾ፣ ሰቻ ሮማ እና ከምቢቾ ጎዶ ቀበሌዎች) መኖራቸው፤

72. ከዚህ በተጨማሪም የወላይታ ሶዶ-አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለመዘርጋት በወሰደው የቻይና ተቋራጭ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዲያ ዞን በሌሞ ወረዳ ውስጥ ለልማት አገልግሎት ተብለው ንብረት ለተጎዳባቸው ባለይዞታዎች ክፍያ ሳይፈጸም ቤትና ሰብላቸው በዶዘር እየታረሰ እንዲነሳ መደረጉ፣ የተገመተው የካሳ ክፍያም ሳይከፈላቸው አንድ ዓመትና ከአንድ አመት በላይ መቆየቱ፤

**ንብረትን የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪን የሚሸፍን ካሳ መከፈሉን በተመለከተ፣**

73. ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከልና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን ለማንሳት፣ ለማጓጓዝ እና መልሶ ለመትከል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን የሚሸፍን ካሳ ሊከፈል ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ካየናቸው ፕሮጀክቶች መካከል ባህርዳር-ደ/ማርቆስ-አዲስ አበባ እና ወላይታ ሶዶ - አዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ለልማት አገልግሎት ተብለው ከይዞታቸው ለተነሱና ንብረት ለተጎዳባቸው ባለይዞታዎች በአዋጁ መሰረት የካሳ ገማች ኮሚቴው የካሳ ክፍያውን ዋጋ ሲተምን ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት፣ ንብረቱን የማንሻ፣ የማጓጓዣ እና መልሶም የመትከያ ወጪዎችንም ከዋናው የንብረት ካሳ ክፍያ ጋር በመጨመር ግምቱን በመስራት ለተነሺዎች እንዲከፈላቸው አለመደረጉ፤

**ለልማት ሥራ የሚፈለገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ለአላቸው አካላት መድረሱን በተመለከተ፣**

74. ኮርፖሬሽኑ ለልማት አገልግሎት የሚፈልገውን መሬትና መሬቱ

የሚገኝበትን ስፍራ የሚገልጽ መረጃ በማዘጋጀት ሥራው ከመጀመሩ ቢያንስ ከአንድ አመት በፊት መሬቱን ለማስለቀቅ ሥልጣን ለአላቸው አካላት በመላክ ቦታው እንዲፈቀድ ወይም እንዲለቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው በአማራ ክልል የባህርዳር ከተማ፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን የባህርዳር ዙሪያና የይልማና ዴንሳ ወረዳዎች የጣና- በለስ--ባህርዳር 400 ኪሎ ቮልት እና የባህርዳር- ደብረማርቆስ 400 ኪ.ቮ. የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን የምስቃን ወረዳ፣ በሀዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ የወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት የሚያልፍበትን መስመር የሚያሳይ መረጃ አስቀድሞ እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤ መስመሩን የሚዘረጉት ኮንትራክተሮች የሚነሳበት ቦታ ላይ ምልክት እያደረጉና ቀለም እየቀቡ የካሳ ክፍያ ግምት እንዲገመት በማድረግ ሥራቸውን ለማስጀመር በተቻለ ፍጥነት ባለይዞታዎቹን በማስነሳት ኮሬፖሬሽኑ ስፍራው በጥድፊያ እንዲለቀቅ ያደረገ መሆኑ፤

75. የጣና በለስ - ባህርዳር የ400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታ መስመሩን ለመዘርጋት ሲባል በባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ካሳ ተከፍሎ ሰዎች ከተነሱ በኂላ መስመሩ በግንቦት ሃያ (ባህርዳር) አየር ማረፊያ ክልል ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ወደ 12 የሚጠጉ ምሰሶዎች ከተተከሉ በኂላ መስመሩ በአየር ማረፊው አካባቢ ማለፍ እንደሌለበት ተቃውሞ በመቅረቡ ድጋሚ የመስመር ለውጥ ተደርጎ ሌሎች ሰዎች እንዲነሱና ሌላ ተጨማሪ መጠኑን ማወቅ ያልቻልነው የካሳ ክፍያ እንዲፈፀም የተደረገ መሆኑ

**ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) የሚሸፈን መሆኑን በተመለከተ፡-**

76. ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለሚለቀቅ መሬትና ንብረት የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች (የኮሚቴ አባላት የአበል ክፍያ እና የጽህፈት ማሳሪያ የመሳሰሉ ወጪዎች) ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (በኮርፖሬሽኑ) ሊሸፈን ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ባህርዳር- ደብረማርቆስ- አዲስ አበባ 400 ኪሎቮልት ኃይል ማስተላፊያ ፕሮጀክት እና የወላይታ ሶዶ- አዲስ አበባ 400

ኪሎቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች የካሳ ክፍያ ለመገመት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች ቦታው ለልማት እንዲለቀቅለት በጠየቀው አካል (ኮርፖሬሽኑ) እንዳልተሸፈነ የገማች ኮሚቴዎቹ መግለጻቸው፤

**የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

77. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የባህር ዳር-ደብረማረቆስ-አዲስ አባባ ወላይታ ሶዶ -አዲስ አበባ 400 ኮሎ ቮልት የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክቶች የክልል መስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ የከተማና የወረዳ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እንደዚሁም የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴዎችም ሆነ ከካሳ ከፋዮች (ኮርፖሬሽኑም) ጋር ካሳ ክፍያን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ከክልሎችና ከልማት ፈጻሚ አካላት ጋር የምክክር መድረክ የሌላቸው መሆኑ፤

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኤልክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በካሳ ክፍያ አፈጻጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.4 በትራንስፖርት ባለሥልጣን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደርን በተመለከተ

**የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ደህንነቱ የተጠበቀ በጊዜ፣ምቾት፣አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን በተመለከተ**

78. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው፣ የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በጊዜ፣ ምቾት፣ አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ሊሆን ይገባል፡፡

79. ባለስልጣን መ/ቤቱ በህዳር 2004 ዓ.ም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች የአገልግሎት አሰጣጥ በክልሎች እና በአዲስ አበባ ከሚገኙ መናኸሪያዎች የተገልጋዮችን እይታ ለማወቅ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት መጠይቅ ከቀረበላቸው ውስጥ

- በቂ አገልግሎት መስጫ ቦታ አለመኖሩን (74%)፣

- የመናኸሪያ መገኛ ቦታ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምቹ አለመሆኑ (55%)፣
- መናኸሪያዎቹ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ የተደራጀ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ (82%)፣
- መናኸሪያዎች ለአካል ጉዳተኞች ለህፃናት ለእናቶች እና ለአረጋዊያን ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠረ አለመሆኑ (63.6%)፣
- መናኸሪያዎች ለሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ሆነው የተደራጁ አለመሆናቸው (82%)፣
- መናኸሪያዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ (91%)፣
- በአጠቃላይ በየመናኸሪዎች የሚሰጠው አገልግሎት ተገልጋዩን የማያረካ መሆኑን (75%) የገለጹ ቢሆንም ጥናቱን ተከትሎ የተወሰደ የእርምት እርምጃ ስለመኖሩ የባለስልጣኑ መ/ቤት መረጃ ባለማቅረቡ ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

80. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የባለስልጣኑ በድሬዳዋና የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናኸሪያዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ፣ በሐረሬ ክልል የሐረር ከተማ፣ የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ከተማ፣ ምዕራብ አርሲ ዞን የሻሸመኔ ከተማ፣ የአዲስ አበባ አነስተኛና መለስተኛ (አዲስ ከተማ) እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ውስጥ ተመሳሳይ ሞዴል ያላቸው አነስተኛና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች እንዲጭኑ ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ተጨማሪ መቀመጫዎች የጨመሩ፣ በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት ባለሥልጣኑ ካስቀመጠው የርቀት መጠን ያነሰ ሆኖ የተሰሩ በመኖራቸው ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ደህንነቱንና ምቾቱ ሳይጠበቅ የሚጓዝበት ሁኔታ መኖሩ፤

81. በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎችና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶች በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት በደረጃው ከተቀመጠው ያነሰ ሆኖ የተሰሩ መኖራቸው፣ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን የሚጥስ መሆኑ፤

**የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ቦታ መረጣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት መሆኑን በተመለከተ**

82. የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ግንባታዎችን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ሚሟላት የሚገባቸውን መስፈርትና ደረጃ ሊያወጣ፣ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ መናኸሪያዎችም በወጣው መስፈርት መሰረት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት ሊሰጡና አዳዲሶችም በዚሁ መሰረት ሊገነቡ ይገባል፡፡

83. በትራንስፖርት ባለስልጣን ሥር የሚገኘው የድሬዳዋ መናኸሪያ ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ መናኸሪያው በክረምት ወራት ኃይለኛ ዝናብና ጎርፍ ሲኖር አገልግሎት መስጠት ስለሚያቆም ሳቢያን በተባለው አካባቢ አዲስ መናኸሪያ ለመገንባት ለእምነቴ እንደሻው የሥራ ተቋራጭ በብር 37, 804,687.00፣ ለአልቲሜት ፕላን ፒ.ኤል.ሲ. አማካሪ አርክቴክት መሐንዲስ አማካሪ ድርጅት በብር 624,312.00 በድምሩ ብር 38,428,999.00 በመቅጠር ሥራ ማስጀመሩ፣ ተቋራጭ ድርጅቱ በውሉ መሰረት መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ግንባታውን ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ አጠናቆ መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ.ም እንደሚያስረክብ ውል ገብቶ ለሥራ ተቋራጩ ቅድሚያ ክፍያ ብር 13,042,617.01 እና ለተሰሩ ሥራዎች ክፍያ ብር 2,603,670.12 በድምሩ ብር 15,646,287.12 የተከፈለና ለአማካሪ መሐንዲሱ በየወሩ ብር 34,684 ሂሳብ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት ሐምሌ 2005 ድረስ እየተከፈለ ቢሆንም ለቢሮ አገልግሎት የሚሆነው ሕንፃ ግንባታ ከመጀመሩ በስተቀር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡበት የማቆሚያሥፍራ ግንባታ ሥራ አለመጀመሩ፣

84. በአዲስ አበባ ከተማ በምስራቅ መውጫ በር ላምበረት አካባቢ እና በምዕራብ መውጫ በር የአየር ጤና መናኸሪያዎቸ ግንባታቸው በ1995/96 በጀት ዓመት ቢጠናቀቀም ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፤

85. የአየር ጤና መናኸሪያ ወደ መናኸሪያው ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ከዋናው መንገድ የሚገነጠለው አስፋልት ጠባብ በመሆኑ ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎችም ሆነ ተሣፋሪዎችን ለሚያመላልሱ የከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ የከተማ አውቶብስና ታክሲዎች ማቆሚያና ማራገፊያ ቦታዎች የሌሉት መሆኑ፤

86. የሻሸመኔ እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ግቢያቸው አስፋልት ያልተነጠፈና አሸዋ የፈሰሰበት ሲሆን በተለይ የቃሊት መናኸሪያ አሸዋው በአፈር የተዋጠ ወጣ ገባ በመሆኑ ለተሽከርካሪዎች ተዘጋጅቶ የነበረው ለመኪና ማቆሚያ የተሰራው ፉካ በአፈር የተዋጠ መሆኑ፤

87. የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያዎች በ1969 ዓ.ም የተገነቡ በመሆኑ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት የማያሟሉ ከመሆኑ በተጨማሪ የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያ ከተሰራ ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት የማያውቅ መሆኑ፤

**የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች ለተጠቃሚዎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ሚሟላታቸውን በተመለከተ፣**

88. የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች በውስጣቸው መሰረታዊ አገልግሎቶችን (የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ መጸዳጃዎች፣ መጠለያ፣ የካፍቴሪያ ክበብ ወዘተ...) በሚሟላት ተጠቃሚዎች ያለችግር አገልግሎቶችን ሊያገኙ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ

- የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ የቃሊቲ እና የድሬዳዋ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ግቢ ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የቃሊቲ፣ የአስኮ እና የድሬዳዋ ከተማ፣ የሐዋሳ፣ የሻሸመኔ እና የአዳማ መናኸሪያዎች ለጠፉ ንብረቶች ማቆያ ቦታ እና የተሟላ የመፀዳጃ ቤቶች የሌላቸው መሆኑ፣
- የድሬዳዋ፣ የሐዋሳ እና የአዳማ መናኸሪያዎች የመንገደኞች ማረፊያና መጠበቂያ መጠለያ ቦታ ቢኖራቸውም መቀመጫ ወንበር የሌላቸው ሲሆን ፣ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች እና የሻሸመኔ መናኸሪያ ለተገልጋዮች የመጠለያ ቦታ የሌላቸው መሆኑ፣

**የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ**

89. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ መናኸሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት መሆን አለበት። በዚህም መሰረት ስለአገልግሎት አሰጣጡ ለተሳፋሪዎች መረጃ የሚሰጥበት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች መግቢያና መውጫ ቦታዎች፣ ሽኚ በማይገባባት ቦታ የዕቃ መግፊያ ጋሪዎች እና የሚዛን አገልግሎት በሁሉም መናኸሪያዎች መሟላት አለባቸው። ይሁን እንጂ

90. በአዲስ አበባ አገር አቋራጭና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ ባሉ መናኸሪያዎች ውስጥ ተሳፋሪዎች ወደ መናኸሪያ ሲገቡ ስለአገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖሩ፣

91. የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ መናኸሪያ ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ ያለው ቢሆንም ለረጅም ዓመታት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣ በሌሎች መናኸሪያዎች ውስጥ ደግሞ ቢል ቦርድ የሌለ መሆኑ፣

92. ከአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ በስተቀር በሌሎች ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተዘጋጀ የተለየ መግቢያ በር አለመኖሩ፤ ሽኚ በማይገባባቸው መናኸሪያዎች ደግሞ ደንበኞች ዕቃቸውን የሚገፉበት ጋሪ አለመኖሩ

93. በአስኮና ቃሊቲ መናኸሪያ ግቢ ውስጥ መብራት ባለመኖሩ መንገደኞች ለስርቆት አደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ መኖሩ፤ በቃሊቲ መናኸሪያ ውስጥ ለተገልጋዩ የሚዛን አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣ እንዲሁም ደግሞ መናኸሪያዎቹ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለያዩ አገልግሎቶች ወደሚሰጥባቸው ቦታዎች ለመንቀሳቀስ በሚመች መልኩ የተሰሩ አለመሆኑ፤

**የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተሰጣቸው ስምሪትና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣**

94. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለንበረቶችና ማህበራት በተሰጣቸው ስምሪትና ለርቀቱ በተመደበው ታሪፍ መሰረት መስራት አለባቸው። የስምሪታቸውን መስመርና የዋጋ ታሪፍ በግልጽ በሚታይ ቦታ ሊለጥፉ ይገባል። ይሁን እንጂ

95. በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የሻሸመኔ

ከተማ መናኸሪያዎች ስምሪት የሚወስዱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መናኸሪያ ውስጥ እያሉ የሚሄዱበትን መስመር እና የሚከፈለውን ዋጋ ታሪፍ አብዛኞቹ በውጭ በኩል ብቻ የሚለጥፉ ሲሆን ከመናኸሪያ ሲወጡ ግን በተለይ ሚኒባሶቹ የለጠፉትን ዋጋ አንስተው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፤

96. በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሐዋሳ እና በሻሸመኔ የከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች የሚሄዱበትን መስመር የሚሳይ ሰሌዳ (ታፔላ) ተሰርቶላቸው የሚለጥፉ ቢሆንም ለርቀቱ የሚያስከፍሉትን ዋጋ የማይለጥፉ መሆኑ፣

97. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለድጋፍ ሰጪነት በተጨማሪ የተመደቡት ኮድ 3 ሚኒባሶች የተመደቡበትን መስመርና የሚስከፍሉትን ዋጋ አብዛኛዎቹ የማይለጥፉ መሆኑ፣

98. ለህዝብ ማማላለሻ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ደረጃ የሌላቸውና ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 ሰሌዳ የወሰዱ ሚኒባሶች ጭምር የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ፣

99. የባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስምሪት መስመሮችን ርቀት እና የሚከፈለውን ዋጋ የሚያሳይ ሰሌዳ በከተማው የተለያየ ቦታ አሰርቶ ተክሎ የነበረ ቢሆንም ሰሌዳዎቹ ባልታወቀ ምክንያት መነሳታቸው፣

100. የአዲስ አበባ ከተማ የታክሲ ዞኒንግ ስምሪቱን በአግባቡ እንዲመሩ ኃላፊነት የተጣለባችው የታክሲ ባለንብረት ማህበራት ቢሆኑም ከሥርዓቱ ውጭ በሚሰሩና እየቆራረጡ በሚጭኑ፣ ከታሪፍ በላይ በሚያስከፍሉ፣ ወደ ስምሪት ስርዓቱ በማይገቡ ታክሲዎች ላይ እርምጃ የማይወስዱ መሆኑ፣

101. በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የታክሲዎች በሥራ ላይ አለመሰማራት፣ ከታሪፍ በላይ ማስከፈል፣ መስመር መቆራረጥ ችግሮች መኖሩ፣

102. በአዲስ አባባ በየተርሚናሉ የተደራጁ ተራ አስከባሪዎች ህግና ደንብ አክብረው አለመስራትና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እያቆራረጡ ሲጭኑም ሆነ ከታሪፍ በላይ ሲያስከፍሉ ያለመቆጣጠር፣ ችግሮች መኖራቸው፤

**የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ መሆናቸውን በተመለከተ**

103. የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣...) ምቹ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ ሲሰጡ ይህ የተሟላ መሆኑንና በዚሁ መሰረት አገልግሎት መሰጠቱን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ውስጥ የተመለከትናቸው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አመቺ መግቢያና መውጫ በር የሌላቸው መሆኑ፤ የባለሥልጣኑ የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መናኸሪያ ደግሞ አንድ በእጅ የሚገፋ ተንቀሳቃሽ መወጣጫ አሰርቶ ችግሩ ሲገጥም ወደ ተሽከርካሪው በማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፤

**ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለየደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን በተመለከተ፣**

104. የተለያየ ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተገልጋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ እንዲለያቸው ለተሰጣቸው ደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከደረጃ አንድ እስከ ሦስት ላሉት የተለያየ የመለያ ቀለም አዘጋጅቷል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በተመለከትናቸው መናኸሪያዎች ውስጥ የሚገኙት የአገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻዎች በሙሉ ለደረጃቸው የተሰጠውን መለያ ቀለም የተቀቡ ሲሆን፣ አንዳንድ መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች እና ሁሉም አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች (ሚኒባሶች) ግን የተሰጣቸውን ደረጃ ለመለየት የሚያስችለውን ቀለም አለመቀባታቸው፤

**የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እና አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን አሟልተው አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ**

105. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ተሽከርካሪዎችም ሆነ አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን

ተገዳኝ የሥራ መሳሪያዎችና ቁሶች አሟልተው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል። ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከትናቸው መናኸሪያዎች ውስጥ በአንዳንድ መለስተኛ እና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶች በመመሪያው መሰረት ለደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) የማይለብሱ መሆኑን፣ ለምሳሌ በድሬዳዋ መናኸሪያ ውስጥ በናሙና ከታዩት አሥራ ስድስት አነስተኛና መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚሰሩ አሽከርካሪዎችም ሆኑ ረዳቶቹ ከአንድ አሽከርካሪ በስተቀር ሌሎቹ መመሪያው ላይ የተገለፀው ቀለም ያለው ሸሚዝ፣ ሱሪም ሆነ ጃኬት አለመልበሳቸው፤

106. በሁሉም ደረጃ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አስገዳጅ ናቸው ተብሎ የተቀመጡ ቁሳቁሶችን፣ የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ከኋላው 730 ሚ.ሜ ስፋት፣ ጥራት ያለው ከጥጥ ጨርቆች የተሰራና በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ፣ የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ "ባለሳንቲም" ኘላስቲክ የለበሰ መሆን እንዳለበት እነዚህ ካልተሟሉ ፈቃድ እንደማይሰጥ መመሪያው ቢደነግግም

- በድሬዳዋ መናኸሪያ ውስጥ በናሙና ከታዩት 16 አነስተኛና መካከለኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ሁሉም የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያላቸው ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ የዘጠኙ (56%) ግን የመጠቀሚያ ጊዜቸው ያለፈ (አንዱ የመጠቀሚያው ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ ያለፈው መሆኑ፣
- ዘጠኝ ተሽከርካሪዎች (56%) ወዴት እንደሚሄዱ እና ምን ያህል ታሪፍ እንደሚያስከፍሉ የሚገልጽ ማስታወቂያ ያለጠፉ መሆኑን፣
- ሰባቱ (44%) ደግሞ ታሪፍ ያልለጠፉና የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያው ጊዜ ያለፈባቸው መሆናቸው፣
- አስራ ሦስቱ መጋረጃቸው ከጥጥ ያልተሰራ፣ አንዱ ጭራሹን መጋረጃ የሌለው፣ አስራ ሁለቱ መስፈርቱን ያሟላ የወለል ንጣፍ የሌላቸው መሆኑን
- ሥሪታቸው ለሌላ ተግባር የነበሩ ተሽከርካሪዎች ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት እንዲቀየሩ ፈቃድ ሲሰጣቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ

ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽካርካሪዎች ያወጣውን መስፈርት ሳያሟሉ ለታክሲ እና ከከተማ ውጭ እንዲያገለግሉ ሠሌዳና ደረጃ የሚሰጣቸው መሆኑ፤

**የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን መኖሩን በተመለከተ**

107. ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባው የፍጥነት ወሰን ሊኖረው እና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የካቲት 15/1961 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 361/1961 የወጣ ቢሆንም 45 ዓመት የሆነው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት መሆኑ፤

**ባለስልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ሥምሪትን ለመግታት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

108. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየቀኑ የሚፈፀሙ ሕገወጥ ስምሪቶችንና የሌሊት ጉዞዎችን ለማስቆም የሚረዱ የአሰራር ሥርዓቶችን ሊዘረጋና ይህንንም ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች በክልሎችና በባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ የካቲት 2005 ዓ.ም ሕገ ወጥ ስምሪትንና የሌሊት ጉዞ ለመግታት የሚያስችል አገራዊ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አውጥቶ ለቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ያሰረሰጨ ቢሆንም በናሙና ባየናቸው መናኸሪዎያችም ሆነ በናሙና በተመረጡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትራንስፖር ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ ምእራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ትንስፖርት ኤጀንሲ፣ በአዳማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት እና በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮዎች የሕገ ወጥ ሥምሪቱ በየመናኸሪያዎች በር ላይ ጭምር በግልፅ የሚከናወን መሆኑ ድርጊቱንም ለመከላከል በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ወጥ የሆነና ቅንጅታዊ አሰራር የሌለ መሆኑ፤

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ የሚያደርገውን ክትትል በተመለከተ**

109. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ ክትትል በማድረግ ወጥ የሆነና አስተማሪ ሊሆን የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ መጋቢት 2005

ዓ.ም በተሻሻለው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የተሽከርካሪ የጎላ ሰሌዳ በሚመለከተው አካል ከተፈታ በኋላ ቅጣቱን ሳይፈፅም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) መስራት እንደማይፈቀድለት፣ ይህንን ህግ ጥሶ የተገኘ አሽከርካሪ ላይ ብር 4000 ቅጣት እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሰረዝ ቅጣት እንደሚያደርስ የተቀመጠ ቢሆንም፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሚኒባሶች የጎላ ታርጋቸው ተነቅሎ የስምሪት ፍቃድ ተሰጥቷቸው ሲንቀሳቀሱ መታየቱ፣

110. በኦዲቱ ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ፣ በሐዋሳ፣ በሻሸመኔ እና በአዳማ በሚገኙ መናኸሪያዎች እና ከእነዚህ መናኸሪያዎች ስምሪት በሚሰጣቸው መስመሮች ላይ የጎላ ሰሌዳቸው የተፈቱ ሚኒባሶችና አውቶብሶች መኖራቸው፣ በአዲስ አበባ ከተማም የጎላ ሰሌዳቸው የተፈታ ታክሲዎችና በድጋፍ ሰጪነት የተሰማሩ ኮድ ሶስት ሚኒባሶች አገልግሎት ሲሰጡ በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት መቻሉ

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ**

111. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የራሱንም ሆነ ከስሩ ያሉ መናኸሪያዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑ፤ ወቅታዊና አገራዊ የትራንስፖርት መረጃዎችም በተሟላ መልኩ አለመያዙ፤

**በባለስልጣን መ/ቤቱ በሚወጡ አገራዊ ደንቦች መመሪያዎችና መስፈርቶች ላይ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ**

112. ባለስልጣን መ/ቤቱ የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለማሳደግ በሚወጡ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶች የተለያዩ ጥናቶችና የስራ እቅዶች የመሳሰሉት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና የተካተቱት የትራንስፖርት ቢሮዎች፤ኤጀንሲዎች እና ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ባለሥልጣን መ/ቤቱ በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በየጊዜው በሚወጡ አገራዊ

ስታንዳርዶች ላይ ለሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመስጠቱን መግለጻቸው፤

**የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማቋቋሙን በተመለከተ፣**

113. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከፍቶ ለፌደራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማድረግ አለበት፡፡ በዚህም መሰረት ባለሥልጣን መ/ቤቱ በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የከፈተ ሲሆን የአዲስ አበባውን በቁጥር ትባ/ዋዳ/287/11/02 ቀን 15/11/02 በተፃፈ ደብዳቤ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ውክልና መስጠቱ፤

114. ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ከባለሥልጣን መ/ቤቱ በተሰጠው ውክልና መሰረት እየሰራ ስለመሆኑ ክትትል አለማድረጉ፤የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውክልናውን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ አፈጻጸምም ሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አቅርቦ የማያውቅ ሲሆን የቅርንጫፉ ሂሳብ በባለሥልጣኑ አመታዊ ሂሳብ መግለጫ ውስጥም እንዲካተት የማይደረግ መሆኑ፤

በመሆኑም የመንገድ ተራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.5 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀምና ክትትል በተመለከተ፤**

ኤጀንሲው በስትራቴጂክ እና በአመታዊ ዕቅዱ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጀቶችን የመስክና የዴስክ ክትትል ሊያደርግ እና የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና የስራ ክንዋኔዎችን እና የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል። ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ መሰረት ክትትል ስለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት የቀረቡት የሶስት በጀት አመታት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ሲከለሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በመደበኛነት የመስክ ክትትል ግምገማ ለማድረግ ከ2003 - 2005 በጀት ዓመት ያለው የዕቅድ አፈጻጸም (39.3%)፣ (29.3%)እና (59%) በቅደም ተከተል ሲሆን የዕቅድ አፈጻጸሙ አነስተኛ መሆኑን እንዲሁም የዴክስ ክትትል (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማህደር መመርመርን) በተመለከተ በ2004 በጀት ዓመት 2060 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራትን የዴስክ ክትትል ለማድረግ አቅዶ 1549 (75%) መደረጉን እና የዴክስ ክትትል ከተደረገባቸው 1549 ድርጅቶችና ማህበራት ውስጥም 839ኙ (54%) የኦዲት ሪፖርት ያላቀረቡ ሲሆን 833ቱ (53.8%) ደግሞ ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት ያላቀረቡ መሆኑን እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት 2711 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ላይ የዴስክ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 2471 (91%) መደረጉን፣ እና

ከየዘርፉ አስተዳዳሪዎች (የየሴክተሩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች) ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያደረጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት በመደበኛነት ለዘርፍ አስተዳዳሪዎቹ የማያቀርቡ በመሆኑ በድርጅቶቹ ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል።

**ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ላደረጋቸው የክትትል ሪፖርቶች ግብረ መልስ መስጠቱን በተመለከተ**

115. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሊያካትት ይገባል። እንዲሁም በኤጀንሲው የዴስክና የመስክ ክትትል በታዩ ችግሮች ላይ በጎ አድራጎት

ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ መደረግ አለበት፡፡ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት 10 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ ሁለቱ በመስክ ክትትል የተደረገላቸው መሆኑን እና በቃል አስተያየት የተሰጣቸው መሆኑን ሲገልፁ 8ቱ ክትትል ያልተደረገባቸው መሆኑን፣ እንዲሁም ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል ለታዩ ችግሮች የማስተካከያ ግብረመልስ ሪፖርት ለድርጅቶቹ ስለመስጠቱ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በተለያዩ ጊዜያት የአሰራር ክፍተት በታየባቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ኤጀንሲው ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ እና በድርጅቶቹ እጅ ያለውና በህዝብ ስም የተሰበሰበው ሀብትና ንብረት ብክነት እንዳይደርስበት በማለት ለኤጀንሲው በተለያየ ጊዜ በተፃፉ በደብዳቤዎች ቢያሳውቅም በድርጅቶቹ ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ወይም ስለተሰጠው የመፍትሄ ሀሳብ ለቢሮው እንዳልተገለፀለት ለቢሮው ኃላፊዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅና ከተከለሱ የኦዲት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጭ በመመሪያው መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ፣**

116. ኤጀንሲው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጣው ወጪ ከ70 በመቶ የማያንሰውን ለዓላማ ማስፈፀሚያና ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ወጭ ማዋላቸውን፣ መመሪያውን ጠብቀው መስራታቸውን ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡ ይህንንም ተላልፈው በተገኙ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይንም ማህበራት ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

117. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በ2004 በጀት ዓመት በዴስክ ክትትል ካደረገባቸው 1549 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት መካከል 1250 (81%) እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ፋይላቸው ከተመረመረው 2471 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት መካከል 882 (36%) ለአስተዳደራዊ ወጭ ከ30 በመቶ በላይ የተጠቀሙ መሆኑ፤

118. በ2003 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 1210 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ 412 (34%)፣ በ2004 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 1549 ውስጥ 839 (54%)፣ በ2005 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 2471 ውስጥ 304 (12%) የኦዲት ሪፖርት ያላቀረቡ መሆኑ፤

119. ኤጀንሲው ታህሳስ 2003 ዓ.ም ባወጣው የክትትልና ድጋፍ ስራ መመሪያ (ጋይድ ላይን) መመሪያን ጠብቀው የማይሰሩ ድርጅቶች ላይ የቅጣት መጠን ቢያስቀምጥም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ህጉን አክብረው ባልሰሩት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው መመሪያን ሳይጠብቁ የሚሰሩ ድርጅቶች ችግሩ ሳይፈታ ፈቃዳቸውን በማደስ ወደስራ እንዲገቡ የተደረገ መሆኑ፤

**ኤጀንሲው ለገቢ ማስገኛ እና ለህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሰጣቸውን በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ፣**

120. በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለመሰማራት ከኤጀንሲው ፈቃድ ሊያገኙና እና ከሚመለከተው የመንግስት አካል የንግድ ፈቃድ ሊያወጡ ይገባል፡፡ ከገቢ ማስገኛ የሚገኘውን ገንዘብ እንቅስቃሴ ከበጎ አድራጎት ስራው የተለየ የሂሳብ መዝገብ ሊይዙ ይገባል፡፡ ከህዝብ በተለያየ መንገድ መዋጮ የሚሰበስቡ በጎ አድራት ድርጅቶች መዋጮ የሚሰበሰብቡበትን ዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ በማቅረብ ከኤጀንሲው ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡ የሕዝባዊ መዋጮ የማሰባሰቢያ ጊዜ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ከመዋጮው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም የገንዘብ እንቅስቃሴና የሀብት ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡ በገቢ ማስገኛ እና በሕዝባዊ መዋጮ የተሰበሰበው ገቢ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

121. ኤጀንሲው በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጥያቄ ሲያቀርቡ እየመረመረ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ፡-

- ኤጀንሲው በ2004 እና በ2005 በጀት አመት ለ68 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ፈቃድ የሰጠ ቢሆንም ፈቃድ የሰጣቸው ድርጅቶች (Income generating actitvity, IGA) በመመሪያው መሰረት መስራታቸውንና በአመቱ መጨረሻ የተለየ የሂሳብና የኦዲት ሪፖርት ማቅረባቸውን ክትትል አለማድረጉ፣

- የገቢ ማስገኛ ፍቃድ በገቢ ማስገኛ ሥራ (በIncome generating actitvity) መመሪያው የማይካተቱ ነገር ግን በወጪ መጋራት

(cost sharing) እያስከፈሉ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚመሩበት ግልፅና ወጥ የሆነ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

- በ2004 በጀት አመት ለ23 እና በ2005 በጀት አመት ለ26 በጠቅላላው ለ49 በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሰጠ ቢሆንም መዋጮውን ባከናወኑ በ3ወር ጊዜ ውስጥ ዝርዝር ሪፖርት ማቅረባቸውን የማይከታተል መሆኑ፤

- ከሕዝባዊ መዋጮ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉ የማይረጋገጥ መሆኑ፣

**ከውጭ ምንጭ ከ10 በመቶ በላይ ገቢ ማግኘት ስለማይችሉ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ**

122. ኤጀንሲው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጉ በሚፈቅድላቸው መሰረት የገቢ ምንጫቸውን 90 በመቶ ከሃገር ውስጥ ምንጭ እና ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ የማምጣት ህጉን አክብረው መስራታቸውን መከታተል እና እርምጃ መውሰድ አለበት። በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በ2004 በጀት ዓመት 60 እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት 59 በኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ስም ፈቃድ የወሰዱ ከ10 በመቶ በላይ የገቢ ምንጭ ከውጭ ያገኙ መሆናቸው በዴስክ ክትትል ቢደርስበትም ምንም አይነት እርምጃ፤ አለመውሰዱ፤

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፣**

123. ኤጀንሲው፣ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ክልል አስፈፃሚዎች የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው ወደ ትግበራ የገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ ሊያዘጋጅና ለየድርጅቶቹ ሊያሰራጭ ይገባል።በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት አምስት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች አራቱ (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር) እንዲሁም በናሙና ከታዩ አራት የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት መካከል በድሬዳዋ አስተዳደርና እና በሀረሪ ክልል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለመገምገም የሚያስችለው ወጥ የሆነ መመሪያም ሆነ ቼክ ሊስት

አለማዘጋጀቱ፤የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የአመቱን የአጋማሽ ግምገማ (Midterm evaluation) የማያከናውኑ ሲሆን የመጨረሻ የግምገማ ሪፖርት(Terminal evaluation) በሚደረግበት ጊዜ የገምጋሚዎቹ (የክልል አስፈፃሚ አካላት ሠራተኞች) የትራንስፖርትና የአበል ወጪዎች በተገምጋሚዎቹ (በበጎ አድራጎት ድርጅቶች) የሚሸፈን መሆኑ የግምገማ ሪፖርቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፤ በሀረሪ ክልል ውስጥ በሚገኙ 10 የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች በተደረገ የግምገማ ሪፖርት የተለያዩ ድርጅቶች በግቢያቸው ውስጥ ክሊኒክና የህክምና ባለሙያ የሌላቸው መሆኑ፣ ለህፃናት የተሟላ መዝናኛና መጫወቻ ስፍራ የሌለ መሆኑ፣ በየድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት መረጃ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ፣ ድርጅቶች ህፃናትን ተቀብለው ሌሎች አማራጮችን ሳይጠቀሙ በጉዲፈቻ እንደሚልኩ፣ ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር የሥራ ስምምነት የሌላቸውና ፈቃድም ያልተሰጣቸው፣ አድራሻቸው ሊታወቁ ያልቻሉ ድርጅቶች መኖራቸው፤

124. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የፕሮጀክት ስምምነት ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር የማይፈራረሙ በመሆኑ ከአንድ ክልል በላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ከየክልሎች ጋር ለመፈራረም የተገደዱ መሆኑን፣

125. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በጉዲፈቻ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ብቻ የሚፈራረሙ ሲሆን እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ክትትል ተደርጎባቸው የማያውቅ መሆኑ፣ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በታህሳስ 2005 ዓ.ም በአገሪቱ ያሉ 63 የጉዲፈቻ አገናኝ ኤጀንሲዎች የመመዘኛ መስፈርት አውጥተው ገምግመው ሪፖርት ያደረጉ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ በእያንዳንዱ ኤጀንሲ ምን ያህል ልጆች በጉዲፈቻ ወደ ተለያዩ አገራት እንደተላኩ፣ ከተላኩ ጊዜ ጀምሮ ያለ ታሪካቸው እና ያሉበት ሁኔታ ያልተገለፀ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት በጉዲፈቻ መልክ ከአገር የወጡ ልጆች በምን አይነት ሁኔታ እየኖሩ እንዳለ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማይታወቅ መሆኑ፤

**በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ ድርጅቶችን በተመለከተ፣**

126. ኤጀንሲው በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን አድራሻ በማፈላለግ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ

አለበት፡፡ኤጀንሲው ከመቋቋሙ በፊት 3982 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበው የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ በ2002 በዳግም ምዝገባ 1655 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ከቀሪዎቹ 2327 ድርጅቶችና ማኅበራት ውስጥ ዳግም ባልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አጣሪ ኮሚቴ ሲጣራ እስከ ሰኔ 2005 ድረስ

- 46 ድርጅቶች ዳግም ተመዝግበው የተገኙ ሲሆን 11 ድርጅቶች ቀደም ሲል በፍትህ ሚኒስቴር የተሰረዙ መሆናቸውን፣
- 6 ድርጅቶች ንብረታቸው ተጣርቶ ከአምስቱ ድርጅቶች ብር 34,009.85 ወደ ዲፓዚት አካውንት ገቢ መደረጉ እና አንዱ ድርጅት የባንክ አካውንቱ የታገደበት መሆኑን፣ 2 ማህበራት ተመሳሳይ አላማ ላለው ማህበር ንብረታቸው እንዲተላለፍ የተደረገ ሲሆን 3 ድርጅቶች ዳግም አለመመዝገባቸው ተረጋግጦ ንብረት በማስረከብ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣
- የተቀሩት 2259 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አድራሻ በማፈላለግ ንብረታቸውን ያላጣራ፣ ፈቃዳቸውንም ያላስመለሰ እና ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

**በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ህጋዊ ማዕቀፍ መኖሩን በተመለከተ**

127. ኤጀንሲው ክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡ይሁን እንጂ በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማእቀፍ ከአማራ ብሔራዊ ክልል በስተቀር በሌሎቹ ክልሎች አለመኖሩ፤

**ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፣**

128. ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት እና ለክልል አስፈፃሚ አካላት በአዋጁ፣ በደንቡ እና በወጡት መመሪያዎች እንዲሁም በሂሳብ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ኤጀንሲው ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት 2 ጊዜ፣ ለውጭ ኦዲተሮች የግማሽ ቀን ስልጠና የሰጠ ቢሆንም ይህ በቂ አለመሆኑን፣

129. በድሬዳዋ አስተዳደር እና በሀረሪ ክልል ውክልና በተሰጣቸው የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ኤጀንሲው ውክልና ከመስጠት ባለፈ ተቋማቱን የማብቃት፣ የማደራጀት፣ የማማከር፣ ተከታታይ የሆኑ ስልጠናዎች የመስጠት ስራ አለመስራቱ፤

130. በክልል አስፈፃሚ አካላት መመሪያዎችና ደንቦችን በአግባቡ ያለመረዳት ችግሮች መኖራቸው እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች አሰራር ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ባለማግኘታቸው የክትትልና የድጋፍ ስራውን በሚገባ እየሰሩ አለመሆኑ፤

**ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ (memorandem of understanding) ያለው መሆኑን በተመለከተ፤**

131. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር ተግባብቶና ተናቦ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ (memorandem of understanding) ሊፈራረም ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር በፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ፣ በጋራ የመስክ ክትትል አሰራር፣ በሪፖርት አቀራረብና ወዘተ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ሰነድ(mou) የሌለው መሆኑ፤

132. ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲና ከፌደራል የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው በየክልሎች ፕሮጀክታቸውን የሚተገብሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ስለሚሰሩት ስራ የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት መረጃ የማያገኙ መሆኑ፤

133. በኤጀንሲው ተመዝግበው የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ኤጀንሲው ወዲያውኑ እንደመዘገበ የማያሳውቃቸው ሲሆን ኤጀንሲው የድርጅቶችን ፈቃድ ከማደሱ በፊትም ከሚሰሩበት ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ወይንም አስተያየት የማይጠይቅ መሆኑ፤

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መረጃ አያያዝን በተመለከተ**

134. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መረጃ በተጠናቀረ መልኩ የእያንዳንዱን ድርጅት እንቅስቃሴ በሚያሳይ መልኩ ማለትም በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ አይነት፣ በሚያንቀሳቅሱት የካፒታል መጠን ወዘተ በዳታ ቤዝ ሊይዝ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የበጎ

አድራጎት ድርጅቶችን መረጃ በተጠናቀረ መልኩ በዳታቤዝ በተሟላ ሁኔታ የማይዝ መሆኑ፣

135. ፋይሎች በተገቢው ሁኔታ የማይያዙና የማይጠበቁ በመሆኑ ፋይሎቹ የተቀዳደዱና፣ በውስጣቸውም የሚገኙ መረጃዎች በቅደም ተከተል አለመቀመጣቸው፤ የበጎ አድርጎት ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ በተጠቃለለ መልኩ አለመያዙ፤

በመሆኑም ኤጀንሲው በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ የወጡ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎችን በማስፈጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.6 የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸምን በተመለከተ

### የግዢ ዕቅድ መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

136. በድርጅቱ ግዥ እንዲያከናውኑ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች በቅድሚያ የግዥ እቅድ በማዘጋጀትና የግዥ ስልት በመለየት በወቅቱ የተፈለገውን ግዥ በማከናወን፣ የዋጋ ቅናሽና የጥራት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ ዕቅድ የማይዘጋጅ መሆኑ፤

### በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በመለየት በጥቅል እንዲከናወን መደረጉን በተመለከተ

137. በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በቅድሚያ በመለየት በጥቅል እንዲከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡

138. በናሙና በታዩት በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ በከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከሲሚንቶ፣ ብረት እና ነዳጅ በስተቀር በድርጅቱ በርካታ ለኮንስትራክሽን የሚያገለግሉ እቃዎች በጥቅል የማይገዙ መሆኑን፣

139. ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት በፕሮጀክቱ የተፈጸሙ ግዢዎች በናሙና በታዩበት ወቅት አልፎ አልፎ ግዥዎች በመከፋፈል እና ከግዥ ጣሪያ በላይ የሚፈጸሙ መሆኑ ፤

140. በፕሮፎርማ መገዛት የሚገባቸው ግዥዎች አልፎ አልፎ ከተለያዩ ድርጅቶች ቢያንስ ከሶስት አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ ከአንድ አቅራቢ ብቻ በተሰጠ ፕሮፎርማ ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፤

**የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለሚመለከታቸው ክፍሎች መድረሱን እና ክፍያው በአቅራቢው ስም መፈጸሙን በተመለከተ**

141. በድርጅቱ ግዥን የሚፈቅዱና የሚያጸድቁ በግዥ መመሪያ መሰረት ሥልጣን የተሰጣቸው ኃላፊዎች የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲልኩ ኮፒዉ ለንብረት ክፍል፣ ለግዥ ክፍል እና ለመሳሰሉት ክፍሎች ሊደርስ እንዲሁም ክፍያው በአሸናፊው አቅራቢ ስም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በድርጅቱ ተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ፕሮጀክቶች የእቃዎች ግዢ የሚፈጸመው ከአዲስ አበባ ሲሆን ለሚፈጸሟቸው ግዢዎች ለክፍያ ይረዳ ዘንድ የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለፋይናንስ የሚደርስ ቢሆንም ቼክ የሚዘጋጀው ግን በአቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያዎች ስም በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ እስከ ብር 400,000.00 በግዢ ባለሙያዎች ስም የሚዘጋጅ መሆኑ፤

142. በድርጅቱ ለሚፈጸሙት ግዥዎች ክፍያ ሲፈጸም ቼክ ባሸነፈው አቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያዎች ስም ማዘጋጀቱ የድርጅቱን የግዥ መመሪያ ከመጣሱ በተጨማሪ ለጥፋት እና ለብክነት በር የሚከፍት መሆኑ፤

**ከኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ**

143. ድርጅቱ በኪራይ ከሚያሠራቸው መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ማግኘቱን ሥራው በሚመለከታቸው የቅርብ ኃላፊዎች ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር እየተደረገ በየወሩ ለዋና መ/ቤት ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ድርጅቱ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች በኪራይ ከመጠቀሙ በፊት አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ሊሰራ ይገባል፡፡ ሆኖም በተንዳሆ እና ከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በኪራይ የሚጠቀሙባቸው

መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሰሩበት ሰዓት ምዝገባ የሚከናወነው በሳይት ላይ በሚገኝ የቀን ሰራተኛ ሲሆን የኪራይ ገልባጭ መኪናዎች ምልልስ እና መሳሪያዎች የሰሩበት ሰዓት በብጣሽ ወረቀት ላይ የሚመዘገብ መሆኑ፤

144. የኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላልሰሩበት 2437.33 ሰዓት በአማካይ የክፍያ ስሌት መሰረት ብር 4,387,194.00 በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

### የግዥ ሥራዎች ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ መደረጋቸውን በተመለከተ

145. በድርጅቱ ፕሮፎርማ መሰብሰብና ማጠቃለያ ወይም ግምገማ የማከናወን፣ ግዥን ማከናወንና ርክክብ የማድረግ፣ የገቢ ደረሰኝ የማዘጋጀትና ሰነድ የማረጋገጥ ስራዎች እንደ አግባብነታቸውና የጠቀሜታ ደረጃቸው እየታየ ሥራን በማያጓትት ሁኔታ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ይሁን እንጂ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ ፕሮፎርማ መሰብሰብ እና ግዥውን የመፈጸም ሥራ በአንድ የግዥ ባለሙያ የሚሰራው ሲሆን፤ ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ ገቢ የማድረግ እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ንብረቶቹን ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በአንድ የንብረት ያዥ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፤

### እቃዎች ግምጃ ቤት ገቢ ከመደረጋቸው በፊት በሚመለከተው ባለሙያ እንዲረጋገጡ መደረጉን በተመለከተ

146. ድርጅቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኛቸውን ቋሚና አላቂ እቃዎች ሲረከብ በእስፔሲፊኬሽናቸው መሰረት መሆናቸው በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ ማደረግ እና አስፈላጊውን ምዝገባ ማከናወን ይገባል፡፡ በድርጅቱ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ንብረቶች ተገዝተው ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው መገዛታቸው በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማን (MAN) ለተባለ ገልባጭ መኪና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጥቶ የተገዙት 12 የፊት እና 12 የኋላ በድምሩ 24 ባሌስትራዎች (Leaf

Springs) ለመኪናው የማይሆን በመሆኑ ከሁለት ዓመት በላይ በግምጃ ቤት የተቀመጠ መሆኑ፤

**የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የተሟላ ማስረጃ የሚቀርብላቸው መሆኑን እና ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ መደረጉን በተመለከተ**

147. የድርጅቱ ቋሚ እና አላቂ እቃዎች በንብረት መጋዘን ገቢ እና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት ተገቢው የገቢ እና የወጪ ማስረጃዎች ሊሟላላቸውና በሚመለከተው ኃላፊ ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የድርጅቱ ንብረቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወጪ ከተደረጉ በኂላ በትክክል ለታቀደው ዓላማ የዋሉ ስለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

148. በተንዳሆ እና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሚንቶዎች፣ ብረቶች እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ከንብረት ክፍል በአንድ ፎርማን በጥቅል ወጪ ከተደረጉ በኂላ ሳይት ላይ ላሉት ለሌሎች ፎርማኖች የጠየቁትን ያህል ያለምንም መተማመኛ/ሰነድ/ የሚታደል ሲሆን ለፎርማኖች ስንት እንደታደለ እና ስንት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣ ከመጋዘን በጥቅል ወጪ የተደረገው የሲሚንቶ፣ ብረት እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ በትክክል የዋሉ ስለመሆኑ የሚታወቅበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤

**የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ**

149. የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ብልሽት ሲገጥማቸው የብልሽቱ መንስኤ እየተጣራ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ ተደርጎላቸው በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግ ይገባል፡፡

150. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለጥገና ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው ያልወጡ እና ከአራት ወራት በላይ የሆናቸው በቃሊቲ ጋራዥ 383፣ በተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 51 እና በከሰም ግድብ እና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 35 በጠቅላላው 469 የሆኑ የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፓ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች መኖራቸው፤

**አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች አቀማመጥ እና አወጋገድን በተመለከተ**

151. አገልግሎት የማይሰጡ የድርጅቱ ንብረቶች፣ ተሽከርካሪ መኪናዎች፣ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫ እቃዎች እና ኬሚካሎች በአግባቡ ሊቀመጡ እና በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከአገልግሎት የተመለሱ ንብረት ክፍል ተመላሽ መደረግ የነበረባቸው የተለያዩ ውፍረት ያላቸው በርካታ ባለ 8፣ ባለ 10፣ ባለ 14፣ ባለ 16፣ ባለ 20፣ ባለ 30 እና ባለ 32 ፌሮ ብረቶች በየፕሮጀክቶቹ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፤

152. ከዚህም በተጨማሪ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርጫፍ መ/ቤት ውስጥ ብዛት ያላቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 185 ዶዘሮች፣ ግሬደሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች፣ ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ጄነሬተሮች፣ ኮምፕረሰሮች፣ መበየጃ ማሽኖች፣ ለጥልቅ ውሃ ጉድጓድ የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ የሲሚንቶ ማቡኪያ ሚክሰሮች፣ ሲሚንቶ መጠቅጠቅያ፣ መሬት መጠቅጠቅያ፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ዲናሞዎች እና ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ በርካታ የኮንስትራክሽን መሳሪያ አካላትና እቃዎች፣ ለድርጅቱ አገልግሎት የማይስጡ መለዋወጫዎች እና ከአገልግሎት የተመለሱ አሮጌ መለዋወጫዎች መጋዘን አጣበው ፣ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

**የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ከንብረት መዛግብት ከወጪ ቀሪ ጋር የሚታረቅ መሆኑን እና ልዩነት ሲኖር እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ**

153. የድርጅቱ የንብረት ቆጠራ ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርዶች እና ከሂሳብ መዛግብት ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲታረቅ ማድረግ እና ልዩነት ሲኖረው ወቅታዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት አመታዊ የንብረት ቆጠራ በማድረግ ከንብረት መዛግብት ጋር የሚመዛዘን ቢሆንም በየአመቱ በተደረገው ቆጠራ በመብለጥና በማነስ የታዩት ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ ቀርበው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፤

**የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ የተደገፉ መሆናቸውን በተመለከተ**

154. የድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማግኘትና ለመለዋወጥ እንዲቻል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ሊደራጅና ሊጠበቅ ይገባል፡፡

በኦዲቱ በናሙና በተመለከትናቸው በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ አለመደራጀቱ፤

በመሆኑም የውኃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በግዢ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.7 በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ

**የግዥ ክፍሉ ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተደራጀ መሆኑን በተመለከተ፤**

155. የግዥ ክፍሉ በሚገባ ሊደራጅና ብቃት ባለው የሰው ኃይል ሊሟላ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ የግዥ ክፍል በሥራ ላይ ያሉ 11 ሰራተኞች የግል ማህደር ሲከለስ 6ቱ በሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛ መስፈርት መሰረት ተፈላጊውን ችሎታ የማያሟሉና ቦታው የሚጠይቀው የኮምፒውተር ዕውቀት የሌላቸው መሆኑ፤

**ግዢዎች በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት መፈጸማቸውን በተመለለከተ፤**

156. የድርጅቱ ግዥዎች በቅድሚያ በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት መፈጸም ሲኖርባቸው በ2003 በጀት አመት የብር 2,637,000 የኬሚካልና የአፓራተስ የግዥ አገልግሎት በመስጠት ብር 6,590,000 ገቢ ለማግኘት በጀት የተያዘና የታቀደ ቢሆንም አለመከናወኑን፣

157. በ2005 የዘጠኝ ወር የሥራ አፈፃፀም የውጭ ሀገር ግዥ ብር 21,702,000 ለመፈጸም ታቅዶ ምንም አለመከናወኑን፣ በተጨማሪም

በዚሁ በ2005 በጀት አመት ከኬሚካልና ከአፓራተስ ግዥ ብር 4,000,000 ገቢ ለማግኘት ታቀዶ ብር 885,000 ወይም (22%) ብቻ የተገኘ መሆኑ፤

**የግዥ ክፍሉ የግዥ እቅድና ክንውን መረጃ በመያዝ የግዢ ሥርዓቱን መገምገሙን በተመለከተ፤**

158. የግዥ ክፍሉ በየጊዜው የሚያዘጋጀውን የግዥ እቅድና ክንውን የተጠናከረ ማስረጃ በመያዝ የግዢ ሥርዓቱን መገምገም እና ፈጣን ማድረግ አለበት፡፡ ነገርግን በዚህ ረገድ የተሰራውን ሥራ የሚያመለክቱ ማስረጃዎችን ድርጅቱ ለማቅረብ አለመቻሉ፤

**ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች መሟላታቸውን እና ምርት አለመስተጓጎሉን በተመለከተ፤**

159. የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ በሆኑ ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች መሟላት የሚኖርበት ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት አንድ ምርት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በጥሬ ዕቃ እጥረት ምክንያት የሚቆም እና ምርቱ ከቆመ በኋላ የግዥ ጥያቄ የሚቅርብ መሆኑን፣ ሥራን በዝርዝር ቆጥሮ የመስጠትና ቆጥሮ የመቀበል የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ አለመቅረቡን፣ ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን መለዋወጫ ዕቃዎች አስቀድሞ በመለየት በወቅቱ ግዥ ባለመፈጸሙ የማምረቻ ማሽኖች የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰበት ሁኔታ መኖሩ፤

**ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን** (minimum & maximum stock level) **መቀመጡን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

160. በድርጅቱ አላስፈላጊ ክምችት እንዳይያዝ ወይም በቂ ክምችት ባለመኖሩ እጥረት እንዳይፈጠር በጥናት ላይ ተመስርቶ በየዕቃዎቹ ዓይነት ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን (minimum & maximum stock level) ሊቀመጥና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም፣ ጥናት ተደርጎ በየዕቃዎቹ አይነት ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠንን በመወሰን ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

**የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተፈላጊው መስፈርትና የውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በግልጽ መቀመጡን በተመለከተ፤**

161. የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ፣ ለአገልግሎትም ሆነ ለእቃ ግዢ ተፈላጊው መስፈርትና የውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በግልጽ ሊቀመጥ የሚገባ ቢሆንም፣ ከድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር

የተፈረሙ ሁለት ውሎች ውስ የተፈረመበት እና ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ በውሉ ላይ ያልተገለጸ መሆኑን፣ ከአንሞል ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር የተፈፀመው ውል ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀን ያልተገለጸ መሆኑን እና ከዚሁ የወረቀት አቅራቢ ድርጅት ጋር በ2003 ዓ.ም በተደረገ ውል የውል ማጠናቀቂያው እና ውል የተፈፀመበት ቀን ያልተጠቀሰ መሆኑ፤

**ድርጅቱ የጥቅል (bulk) ግዢ የሚፈጽም መሆኑን በተመለከተ፤**

162. ድርጅቱ በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች እና የአገልግሎት ግዥዎች በጥቅል (bulk) መፈጸም የሚኖርበት ቢሆንም፣ የአልሚኒየም ሽት ሜታል፣ ፓይነስ ጣውላ፣ ስኩየር ፓይፐ፣ ነጭ ፎርማይካ፣ ጣውላ፣ ቪናቪን ኮላ፣ ለማተሚያ ቤት የሚውል ጥቁር ቀለም፣ ለህትመት የፕሮሰስ ቢጫ ቀለም፣ ለማተሚያ አርት ፔፐር እና የመሳሰሉት በቁጥቁጥ ግዥ በተደጋጋሚ መፈጸሙ፤

**በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቅራቢዎች ውል የገቡበትን ዕቃ ገቢ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤**

163. በድርጅቱ ለሚመረቱ ምርቶች የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን አቅራቢዎች በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማቅረብ ባለመቻላቸው በሥራ ላይ ችግር ያስከተለበት ሁኔታ መኖሩ፤

**ድርጅቱ ገዝቶ ገቢ ያደረጋቸው ዕቃና መሳሪያዎች በግዢ ትዕዛዙ (Specification) መሰረት መሆናቸውን በተመለከተ፤**

164. ድርጅቱ ገዝቶ ገቢ ያደረጋቸው ዕቃና መሳሪያዎች በግዢ ትዕዛዙ (Specification) መሰረት መሆናቸው በቅድሚያ በሚመለከተው አካል (ባለሙያ) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ተገዝተው ገቢ ከተደረጉት መገልገያ ዕቃዎች ውስጥ በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ገቢ ያልሆኑ መኖራቸውንና ዕቃዎቹም ለምርቱ ችግር እየፈጠሩ መሆኑ፤

**ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ፤**

165. ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር ተገዝተው የሚመጡ ንብረቶችን የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶላቸው እቃ ግምጃ ቤት ገቢ ተደርገው አስፈላጊው ምዝገባ ሊከናወንላቸው የሚገባ ቢሆንም፣ ተገዝተው መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ደረሰኝ ሳይዘጋጅላቸው የሚቆዩበት ሁኔታ

መኖሩ እና አዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስም የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው ዕቃዎች መኖራቸው፤

**የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር መካሄዱን በተመለከተ፤**

166. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ማካሄድ እንዲሁም አዳዲስ ዲዛይኖችንና አሠራሮችን በመዘርጋት ሥራ ላይ ማዋል ሲገባው፣ ድርጅቱ የምርት ውጤት የሚሻሻልበትንና የሚያድግበትን ሁኔታ እንዲሁም የአሰራር ዘዴው በየጊዜው ካለው የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር አብሮ የሚራመድበትን መንገድ በማጥናት፣ ለድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ዕድገት ጠቃሚ ናቸው የሚባሉትን የማሻሻያ የጥናት ውጤቶች በመለየት ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ዙሪያ ክፍተት ያለበት መሆኑ፤

**ድርጅቱ ልዩ ልዩ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቱን በተመለከተ፤**

167. ድርጅቱ የመማርያና የማስተማሪያ መጻህፍትን ልዩ ልዩ ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ጽሑፎችን፣ ቻርቶችን፣ ካርታዎችንና ሥዕላዊ መግለጫዎችን እንዲሁም ለመዋለ ሕፃናት፣ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሊያመርት የሚገባ ቢሆንም፣ ለትምህርቱ ዘርፍ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ምርቶችን ለምሳሌ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ካርታዎች፣ ስዕላዊ መግለጫዎች የማያመርት መሆኑና፣ ለሽያጭ የሚሆኑ የሪፈረንስ መፃህፍት ተመርተው በበቂ ሁኔታ ለቅርንጫፉ የሚላኩበት ሁኔታ አለመኖሩ፤

**ድርጅቱ የሠራተኞችን ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደጉን በተመለከተ፤**

168. ድርጅቱ የሰው ኃይሉን በተለይ በግዥ፣ በምርት ሂደትና በስርጭት ላይ ያሉትን ሠራተኞች ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደግ ያለበት ቢሆንም፣ የግዥ ሂደቱን ለማሻሻል ለግዢ ክፍሉ ስልጠና የተሰጠበት ሁኔታ አለመኖሩ፤ በየሥራ ዘርፉ የሚያስፈልገው የስልጠና አይነት ቢለይም በታቀደለት መሰረት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲሰጥ አለመደረጉ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሀገር ውስጥ የህትመት ባለሙያዎችን የሚያሰለጥን ተቋም ባለመኖሩ የህትመቱ ሥራ

የሚከናወነው በልምድ ብቻ መሆኑ፣ በህትመት ሥራ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰራተኞች እና የጥገና ባለሙያዎች ለህትመት ከተገዙ አዳዲስ ማሽኖች ጋር ለመተዋወቅ ተገቢው ስልጠና ያልተሰጣቸው በመሆኑ ማሽኑ ተበላሽቶ መጠገን ባለመቻሉ ለረጅም ጊዜ ሳይሰራ የቆየበት ሁኔታ መኖሩ፤

**ድርጅቱ ምርቶችን በተገባው ውለታ መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፤**

169. ድርጅቱ ያመረታቸውን ምርቶች በገባው ውለታ መሰረት በጥራትና በጊዜ ገደብ ለደንበኞች ማስረከብ ያለበት ሲሆን በድርጅቱ ምርት ላይ የጥራት እና ምርትን በጊዜ ገደብ የማድረስ ችግር መኖሩ፤

**ድርጅቱ ምርቶቹን በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፤**

170. ድርጅቱ የሚያመርታቸው ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ተመርተው ለደንበኞች የማይቀርቡበት ሁኔታ መኖሩ፤

**የድርጅቱ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ መተከላቸውን በተመለከተ፤**

171. የድርጅቱ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ መተከል ሲኖርባቸው፣ የድርጅቱ ማተሚያ ቤትና ዋናው መ/ቤት በተራራቀ ቦታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ከፍተኛ የሥራ አመራር ችግር፣ የወጪ ጫና እና በሰው ኃይል አጠቃቀም ላይ ችግር ያስከተለ መሆኑ፤ ከዚህ በተጨማሪ መጽሃፍ ለማተም የህትመቱ ፅሁፍ ከሚቀረፅበት ከኮምፒውተር ክፍል አንስቶ እስከ ፕሌት ዝግጅት ድረስ በሽሮ ሜዳ በሚገኘው ማተሚያ ቤት ተዘጋጅቶ ወደ ዋናው መ/ቤት ማተሚያ ቤት ሄዶ እንደሚታተም እንዲሁም በዋናው ማተሚያ ቤት አራት አይነት ቀለም የያዘ ህትመት ታትሞ ወደ ሽሮ ሜዳ ማተሚያ ቤት በመውሰድ መጽሀፉ የሚዘጋጅ መሆኑ፤

**ድርጅቱ ከትምህርት ዘርፎች ጋር ግንኙነት መፍጠሩን እና ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት ግብረ መልስ መሰብሰቡን በተመለከተ፤**

172. ድርጅቱ ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከሚመለከታቸው የትምህርት ዘርፎች፣ የግልና የመንግስት ድርጅቶች፣ ተቋማትና መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የቴክኒክ ድጋፎችን በመለዋወጥ በጋራ መስራት እና ለሽያጭ ምርት እድገት የሚያደርገው አስተዋፅኦ በቂ አለመሆኑ፤ እንዲሁም ደግሞ

በሚሰጠው የግዢ አገልግሎት የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ለመሆኑ ግብረ መልስ የማይሰበስብ መሆኑ፤

**ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፤**

173. ድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳቡን በወቅቱና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልክ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን በ2002 በጀት አመት በውጭ ኦዲተሮች ከቀረበ ሪፖርት በመነሳት ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ2004 በጀት ዓመት ለማጣራት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ የፀደቀ ቢሆንም የተደረገ እንቅስቃሴ ባለመኖሩ፤ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም እየተንከባለለ የመጣ ብር 54,883,189.60 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፤

174. በድርጅቱ የሽያጭ መመሪያ የዱቤ ሽያጭ የሚጠይቅ ማንኛውም ሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በመንግስት በጀት የሚተዳደር ድርጅት አግባብ ባለው ኃላፊ የተፈረመና የድርጅቱ ማህተም ያለበት የሥራ ትእዛዝ አቅርቦ በቅድሚያ ዕዳ የሌለበት መሆኑ በፋይናንስ መምሪያ በጥንቃቄ ተረጋግጦ ዱቤው እንዲሰራ የሚያዝ ቢሆንም ዕዳ እንዳለባቸው እየታወቀ ለኦሮሚያ፣ ለሀረሪ፣ ለትግራይ እና ለአማራ ትምህርት ቢሮዎች፣ ዱቤ የተሰጠ መሆኑ፤

**ድርጅቱ ምርትና አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ሥራ ማከናወኑን እና ውጤቱን መገምገሙን በተመለከተ፤**

175. ድርጅቱ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች፣ በህትመት ውጤቶች፣ በሽያጭ ሠራተኞች፣ በባዛር፣ በኢግዚብሽንና በመሳሰሉት በመጠቀም ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቅ ሥራ ወጥ በሆነ መልኩ ማከናወን እና የተሰሩ የማስተዋወቅ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ ምርትና አገልግሎቱ ላይ የሚያደርገው የማስተዋወቅ ሥራ በቂ አለመሆኑ፤ በሽያጭ ጣቢያዎች ለሽያጭ መቀነስ በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ከድርጅቱ የአቅርቦት ማነስ፣ ጨረታዎችን ማሸነፍ አለመቻል እንዲሁም የሽያጭ ጣቢያዎች ባሉበት ከተሞች በራሪ ፅሁፎችን እና ሳምፐል በመጠቀም ገበያ የማስተዋወቅ በቂ ሥራ አለመካሄዱ ለፕሮሞሽን ሥራ አለመጠናከር እንደ ምክንያት መጠቀሱ፤ ድርጅቱ ያከናወናቸው ጥቂት የማስታወቂያ ስራዎች ያስገኙትን ውጤት በተመለከተ ግምገማ አለማድረጉ፤

**ድርጅቱ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤**

176. ድርጅቱ ፣ በውስጡ ካሉ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና ከውጪ ደንበኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ደንበኞች ስለምርቱ ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የዋጋ ዝርዝር፣ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችል የተሟላና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ሊደርግ ሲገባው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን ጠንካራ ለማድረግ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የሆነው የመረጃ መረብ በድርጅቱ አለመዘርጋቱ፤ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች እርስ በርሳቸው የሚገናኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

በመሆኑም የድርጅቱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በማድረግ፣ ከሀገሪቱ የትምህርት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እና መሰረታዊ የትምህርት መስፋፋት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንዲሆን ድርጅቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር በኦዲቱ ወቅት በትምህርት መሳሪያዎች ግዢና ስርጭት አፈጻጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.8 በግል ጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ

**ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለመከታተል በዕቅድ መያዙን በተመለከተ**

177. ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን የሚከታተል አካል/ክፍል/ ለሚያከናውነው ተግባራት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

178. ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በሰውና በእንስሳት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ ፤የግል የጤና ተቋማትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለመቆጣጠር ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም እቅዱ አለማካተቱ፤ የክልል ጤና ቢሮዎችም /አዲስ አበባ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ፣ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ ቁጥጥር ለማድረግ ዕቅድ ቢይዙም በዕቅዱ መሰረት ቁጥጥሩ  አለመደረጉ፤

**የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች የወጡና ለጤና ተቋማት የደረሱ መሆኑን በተመለከተ**

179. ከጤና ተቋሞች የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በሚኒስትር መ/ቤቱ እና በባለስልጣኑ መመሪያዎች ሊዘጋጁና ለየጤና ተቋማቱ ሊደርሱ ይገባል፡፡ ባለሥልጣኑም በመመሪያው መሰረት መተግበሩን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልሎች ለሚገኙ 42 የግል የጤና ተቋማት በሙሉ መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑ፤

180. ከዚህም በተጨማሪ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች በቀለም (colour) ተለይተው እንዲቀመጡ አለመደረጉ፣ በሰውና በእንስሳት ላይ በሽታን የሚያስተላልፉ አደገኛ ቆሻሻዎች ላይ አለም አቀፍ  የአደገኛነት ማስጠንቀቂያ ምልክት የማይደረግባቸው መሆኑ ፣ የቆሻሻ ማቃጠያዎች /ኢንስሌሬተሮች/ ወጥ የሆነ አሰራር የሌላቸው መሆኑ፤

**በጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፣**

181. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አደገኛነት አንፃር በጤና እና በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ በተመለከተ በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ የጽዳት ሰራተኞችም ሆነ ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚሰጥበት ስርዓት በጤና ቢሮዎች እና በየጤና ተቋማት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ የማይሰጣቸው ሲሆን በፅዳት ስራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ሥራቸውን የሚሰሩት ሲቀጠሩ በቃል በተሰጣቸው ኦሬንቴሽን ብቻ መሆኑ፤

182. የሜዲካል ቆሻሻ በሚመነጭባቸው የሕክምና መስጫዎች፣ የታካሚዎች መኝታ ክፍሎች እና ላቦራቶሪዎች ውስጥ የሚሰሩ ሞያተኞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሁም በአስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩ የጤና ተቋማት ሠራተኞች ቋሚ በሆነ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት እንዲያገኙ አለመደረጉ፤

183. ለሐኪሞች፣ ለነርሶች፣ ለላቦራቶሪ ቴክኒሺያኖችና ለፋርማሲስቶች ሜዲካል ቆሻሻን ከምንጬ/ከመነሻው/ ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችንና በአጠቃቀምና አያያዝ ላይ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እና ያለባቸውን ኃላፊነት እንዲያውቁት ለማድረግ የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ፤

**ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያዎች/ኢንስሌሬተርስ/ ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፣**

184. በግል የጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ክፍሎች የሚወጡ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያና ማቃጠያ /ኢንስሌሬተር/ በሁሉም የጤና ተቋማት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መሰራትና አገልግሎት መስጠት አለባቸው። የሚሰሩት የቆሻሻ ማቃጠያዎች ወጥነት ሊኖራቸውና ህክምና ከሚሰጥበትና ምግብ ከሚበስልበት አካባቢ 30 ሜ መራቅ አለባቸው።

185. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል ጤና ተቋማት ውስጥ የተሰሩት የቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያዎች ወጥነት የሌላቸው አንዳንዶቹ ትልቅ አንዳንዶቹ ደግሞ ትንሽ ሲሆኑ፣ በራቸው ጠባብ እና ቆሻሻን ለመገልበጥ የማይመቹ፣ የጪስ ማውጫቸውም አጭርና ረዥም ሆኖ የተሰሩ መሆናቸው፤

186. በአዳማ ከተማ አዳማ ሆስፒታል የተሰራው የቆሻሻ ማቃጠያ ትልቅ ቢሆንም አጠቃቀሙን ካለማወቅና ከቸልተኝነት ቆሻሻው መቃጠል ከነበረበት ከላይኛው ክፍል ውጪ በታችኛው ክፍል እና ከማጠራቀሚያው ውጪ የሚያቃጥሉ መሆኑ፤

187. በአዳማ ከተማ ተክሌ ጨለሞ ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻ ለማቃጠል የሚሆን ኢንስሌሬተር ስለሌለው በጉድጓድ የሚጠቀም መሆኑ፣ በአዋሳ ከተማ አሰፋ ጉበዜ መታሰቢያ ክሊኒክ እና በወላይታ ሶዶ አዲስ ጤና መካከለኛ ክሊኒክ ውስጥ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማቃጠያ የሚሆን ኢንስሌተር ባለመሰራቱ በርሜል ቆርጠው የሚጠቀሙ መሆኑ፤

188. በአዲስ አበባ በላንድ ማርክ ሆስፒታል ያለው ኢንስሌሬተር አነስተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ ከሆስፒታሉ ካፍቴሪያ 30 ሜ ያልራቀ መሆኑ፣ በድንበሯ ሆስፒታል ማቃጠያው /ኢንስሌሬተሩ/ ትንሽ መሆኑ፤ የልብስ ንፅህና/እጥበት/ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያው የራቀ መሆን ሲገባው

የሚታጠበው ከቆሻሻ ማቃጠያው አጠገብ መሆኑ እና ህክምና ከሚሰጥበት ክፍል 30 ሜ ያልራቀና በተጨናነቀ ቦታ መሆኑ፣ በቅድስተ ማርያም ከፍተኛ ክሊኒክ የተሰራው ማቃጠያ ትንሽ መሆኑና በቤቶች መካከል የተሰራ መሆኑን፣ በተክለሃይማኖት ሆስፒታል የቆሻሻ ማቃጠያው ቆሻሻን ለመገልበጥ በማይመች መልኩ የተሰራ መሆኑ፣ በዩርዳኖስ ሆስፒታል እና በኗላሽት ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻዎች ኢንስሌሬተሩ ውስጥ ሞልተው በመሬት ላይ ተዝረክርከው ሳይቃጠሉ መቀመጣቸው፤

189. በኪዩርና በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰሩ ዘመናዊ የቆሻሻ ማቃጠያዎችን በስራ ላይ ማዋላቸው ቆሻሻዎች በጤና ላይ ከሚያስከትሉት ጉዳት ለመከላከልና መርፌዎችን ለማቃጠልና ወደ አመድነት ለመቀየር በቂ ሙቀት ያላቸው በመሆናቸው ጥሩ ዘዴ ሆነው መገኘታቸው፤

190. በሌሎች በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግል የጤና ተቋማት የሚሰሩ የቆሻሻ ማቃጠያዎች አገልግሎት የሰጡ መርፌዎችን ለማቃጠል የሚበቃ ሙቀት/ኃይል/ ያላቸው ባለመሆናቸው አገልግሎት የሰጡ መርፌዎች በደንብ ሳይቃጠሉና ወደ አመድነት ሳይቀየሩ የሚቀሩ ከመሆኑ በተጨማሪ አመዱ ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር ተወስዶ በከተሞች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚደፋ መሆኑ፤

**ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን በተመለከተ፣**

191. በየጤና ተቋማት የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በየክፍሉ፣ በየኮሪደሩና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎች ሊሟሉ፤ ቆሻሻዎች በዓይነታቸው ተለይተው ወደ ማስወገጃ ቦታ በመውሰድ ሊወገዱ ይገባል፡፡ ይህ ለመደረጉ ባለስልጣን መ/ቤቱ እና የክልል ጤና ቢሮዎች ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ በኪዮር ሆስፒታል በህክምና መስጫ ክፍሎችም ሆነ በየኮሪደሩ በከለር የተለዩ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች እና ቆሻሻዎችን ወደ ሚወገዱበት ቦታ መውሰጃ ጐማ ያለው /ትራንስፖርት/ ማቴሪያል የሚጠቀሙ ሲሆን፤ በዮርዳኖስ ሆስፒታል የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎቹን ቀለም በመቀባት መጠቀም ቢጀምሩም ቀለሙ እየለቀቀ በመቸገራቸው የቆሻሻ እቀዎችን በከለር/በቀለም/ በመለየት መጠቀም ማቆማቸው፤ በዩርዳኖስ እና

በቤተዛታ ሆስፒታሎች እንዲሁም በሰናይ ከፍተኛ ክሊኒክ አደገኛና በሽታን ሊያስተላልፉ ይችላሉ የሚባሉ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) የሚል በመለጠፍ የሚጠቀሙ መሆኑ፤ይሁን እንጂ በሌሎቹ በናሙና በታዩት የጤና ተቋማት የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በከለር (አደጋን የማያስከትሉ በጥቁር ከለር፣ አደገኛና በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከደም ጋር ንክኪ ያላቸውና ስለታማ የሆኑ ነገሮች በቢጫ ከለር እና አደገኛ ብረት አዘል ንጥረነገሮች (heavy metals) በቀይ ከለር) እንዲለዩ አለመደረጉ፤

**በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ**

192. ከጤና ተቋማት የሚወጡ /የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በተመለከተ /የቆሻሻው ዓይነት፣ መጠን፣ የሚመነጩበት የስራ ክፍል፣ የሚቃጠሉበት ሰዓት … / በተመለከተ ተገቢው ሪከርድ/መረጃ የሚያዝበትና ሪፖርት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። በግል ጤና ተቋማት ላይ የቁጥጥር እና ክትትል ስራ ከተሰራ በኋላ የግብረ መልስ ሪፖርት ለየጤና ተቋሙ እንዲሁም ደግሞ የጤና ተቋሙ ስራውን ስለማስተካከሉ በሪፖርት ለጤና ቢሮው ሊያሳውቅ ይገባል። ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና በተመረጡ ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛ ክሊኒኮች እና መካከለኛ ክሊኒኮች በጤና ቢሮ የክትትል ስራ ስለመደረጉ የቁጥጥር እና ክትትል ስራው ውጤት እና መስተካከል ስለሚገባቸው ነገሮች የሚገልፅ ማስረጃ በጤና ቢሮዎች በኩል የማይሰጥ መሆኑ፤ የግል ጤና ተቋማትም የህክምና ቆሻሻን በተመለከተ የሚይዙትም ሆነ ለጤና ቢሮዎች የሚልኩት መረጃ አለመኖሩ፤

**የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት ባለሙያ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ**

193. በግል የጤና ተቋማት በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች/ባለሞያዎች/ ሊመደቡና ለስራቸውም የስራ ኃላፊነትና ተግባራት በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሊደርሳቸው ይገባል:: ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በጤና ባለሞያ ተለይቶ ሊወገድ ይገባል። የጤና ተቋማት በስራቸው የሳኒቴሽን እና ሃይጂን ባለሙያ /የስራ ክፍል ሊኖራቸው ይገባል፤

194. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከሐያት፣ ቤቴል፣ ተክለሐይማኖት፣ ላንድማርክ፣ እና ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታሎች፣ በአዳማ ከተማ አዳማ አጠቃላይ ሆስፒታል እና በኦሮሚያ ክልል ከአቅልሲያ መታሰቢያ ጠቅላላ ሆስፒታሎች በስተቀር በሌሎች በናሙና በታዩ ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች ውስጥ የህክምና ቆሻሻዎች በሳኒቴሽን እና የሃይጂን ባለሙያ እንዲለዩ የማይደረግ መሆኑ፤ የህክምና ቆሻሻዎችን ለሚያጸዱ የፅዳት ሰራተኞች በየተቋሙ የሚዘጋጅ የስራ መዘርዝር አለመኖሩ፤

**ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከጤና ተቋሙ ከመውጣታቸው በፊት የብክለት ደረጃቸውን እንዲቀንሱ ተደርገው የሚወጡ መሆኑን በተመለከተ፣**

195. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ስለታማ እና ጫፋቸው ሹል የሆኑ የህክምና ቁሶች በተገቢው ሙቀት ሊቃጠሉ ይገባል፡፡ ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ፍሳሾች ህብረተሰቡ ከሚጠቀምባቸው ስፍራዎች ከመለቀቃቸው በፊት ሊታከሙ ይገባል፡፡

196. የግል የጤና ተቋሞች በውሃ እና ፍሳሽ ቢሮ በላቦራቶሪ የጉዳት መጠናቸው ከመመርመሩ በፊት ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ በወንዞች እና በፍሳሽ ማስወገጃ ትቦዎች/በውሃና ፍሳሽ፣ በግለሰቦችና በተለያዩ ዘዴ የሚያስወግዱ መሆኑ፤

197. ስለታማ የሆኑ የህክምና ቆሻሻዎችም በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ በኪዩር ጠቅላላ ሆስፒታልና በቅዱስ ገብርኤል ጠቅላላ ሆስፒታል ኢንስሌሬተሩ የሚሰራው በኤሌክትሪክ እና በነዳጅ ሃይል በመሆኑ ስለታማ ቁሶችም አብረው የሚቀልጡ መሆኑ፤ በወላይታ ከተማ ከአንደት መካከለኛ ክሊኒክ በስተቀር በሌሎች በናሙና በተመረጡ የግል ጤና ተቋማት እነዚህ የህክምና ቆሻሻዎች በበቂ ሙቀት/አቅም/ ሳይቀልጡ ከጤና ተቋሙ ግቢ ውጭ የሚወገዱ መሆኑ፤

**የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋር የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን በተመለከተ፣**

198. ባለስልጣኑ እና የክልል ጤና ቢሮዎች የህክምና ቆሻሻን አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ከከተማ ማዘጋጃ ቤቶች እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡ በናሙና ተመርጠው በታዩ የጤና ተቋማት እንደተገለፀው ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከተቃጠሉ በኋላ

አመዱ ከሌሎች የሜዲካል ቆሻሻ ካልሆኑ ቆሻሻዎች ጋር ተደባልቀው ቆሻሻን ለሚያጓጉዙ አካላት በመስጠት የሚወገዱ መሆኑ፣

199. አመዱ ከህክምና ተቋሙ ውጭ በሚደፋበት ጊዜ የሚደፋበት ቦታ ማዘጋጃ ቤቱ ለደረቅ ቆሻሻ ባዘጋጀው ቦታ ላይ በመሆኑ ይሄም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊደርሱበት የሚችሉበትና የህክምና ቆሻሻዎች የተቃጠሉበት የሙቀት መጠን እና አመዱ ሊያመጣ የሚችለው የብክለት መጠን ስለማይታወቅ ለብቻው የማይቀበር መሆኑ፣

በመሆኑም በጤና ጥበቃ ሚ/ር የኢትዮጵያ የምግብ፤የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት የግል ጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.9 በስኳር ኮርፖሬሽን የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻምን በተመለከተ

**የስኳር ልማት ፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ**

200. ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳይ መሪ ዕቅድ (Master plan) በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

201. በስኳር ኮርፖሬሽን የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ደረጃውን የጠበቀና ከ4 ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የስኳር ኢንዱስትሪ መሪ ዕቅድ በ90 ቀናት፣ ደረጃውን የጠበቀና ከሁለት ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የተሟላ የስኳር ኢንዱስትሪ ስትራቴጂክ ዕቅድ በ90 ቀናት እና ደረጃውን የጠበቀና ከ2 ጊዜ በላይ ሊከለስ የማይችል የኦፕሬሽን ዕቅድና በጀት በ60 ቀናት መዘጋጀት አለበት፡፡

202. ሆኖም ኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የስኳር ኢንዱስትሪ መሪ ዕቅድ (Master plan) አለማዘጋጀቱ፤

203. መንግስት በነደፈውን የአምስት ዓመት ዕቅድ መሰረት የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች ከመቼውም ጊዜ የላቀ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲስፋፉና ያሉት የስኳር ፋብሪካዎችም የሚያመርቱት የስኳር ምርት

እያደገ የመጣውን የአገር ውስጥ ፍላጎት ማርካት ባለመቻሉ ይህንኑ ዕጥረቱን ለመቅረፍ እና የገቢ ምርቱን የሚተኩ የስኳር ፋብሪካዎችን በስፋት ለመገንባት የሚያስችል በኮርፖሬሽኑ (አገዳ ተክል ልማት፣ ፋብሪካ ግንባታ እና የመስኖ ልማት) የሚያሳይ የአምስት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

204. በኮርፖሬሽኑ የአምስት ዓመታት ዕቅድ (2003-2007 ዓ.ም) መሠረት አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች የአገዳ ተክል ልማት ዕቅድ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት 18,400 ሄክታር ሲሆን ክንውን 2,395 ሄክታር (13%)፤ በኦሞ ኩራዝ ዕቅድ 43,108 ሄክታር ሲሆን ክንውን 1,676.6 ሄክታር (4%) እና በወልቃይት እቅድ 8,608 ሄክታር ሲሆን ክንውን 539 ሄክታር (6.5%) መሆኑ፤

205. በአምስት ዓመታቱ የፋብሪካዎች ግንባታ ዕቅድ መሠረት (ከ2003 - 2005 ዓ.ም) የጣና በለስ ቁጥር አንድ እና ሁለት እስከ ጥቅምት 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውኑ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ ቁጥር አንድ 45% እና ቁጥር ሁለት 39% መሆኑ፣ በኦሞ-ኩራዝ የፋብሪካ ግንባታው እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ክንውን 42% መሆኑ፤ ወልቃይት እስከ ጥቅምት 2006 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲኖርበት ሥራው ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመጀመሩ፤

206. የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ እና የሌሎችም አዳዲስ ፕሮጀክቶች የአገዳ፣ የመስኖ እና የፋብሪካ ግንባታ ዕቅድ በኮርፖሬሽን ደረጃ ተዘጋጅቶ ለፕሮጀክቶቹ የሚላክ ሲሆን የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካላት ሊተገበሩት የሚገቡ ዝርዝር ሥራዎች በዕቅዱ ተካተው አለመዘጋጀቱ፤

207. ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ ሊያከናወን ያቀዳቸው ፕሮጀክቶች ግባቸውን እንዲመቱ ሥራውን የሚተገብሩት አካላት በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የማያሳትፍና ዕቅድ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ባለመሆኑ ዓመታዊ ዕቅዶች በዓመት ከሦስት ጊዜ በላይ የሚከለሱ መሆናቸውን እና የፕሮጀክቶቹ ዕቅድ አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ኮርፖሬሽኑን ተገቢ ላልሆነ ወጪ መዳረጉ፤

208. በተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት 5164.09 ሄክታር መሬት የለማ የሸንኮራ አገዳ

ምርት ዕድሜው በመራዘሙ ምክንያት እንዲወገድ በመደረጉ 102,440,145.00 ብር ፋብሪካው ማግኘት የሚገባውን ገቢ ማጣቱ፤

209. እቅዱ አግባብ ባለው ጥናት ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ እና ኮርፖሬሽኑ ለፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም አስፈላጊውን ዝግጅት፤ የተጠናከረ የፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር አለመድረጉን እና የፕሮጀክቶቹ ኮንትራት አስተዳደር ጠንካራ አለመሆኑ የሚያሳይ መሆኑ፤ ፡

210. ይህም ኮርፖሬሽኑ በአምስት ዓመታቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት በስኳር ልማቱ ዘርፍ የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ አዳጋች የሚያደርገው መሆኑ፤

**የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ**

211. የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የሚያስገነባቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራን በተመለከተ ሪፖርት በየወሩ ሊቀርብና በሪፖርቱ መሰረት ግምገማ ሊከናወን ይገባል፡፡ የሚቀርበውም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ተለይቶ በዝርዝርና ግልጽ በሆነ መልኩ ሊያሳይ ይገባል፡፡

212. ይሁን እንጂ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም የቀረበው የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች (ጣና በለስና ኦሞ ኩራዝ) የአፈጻጸም ሪፖርት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸሙን ለየብቻ በዕቅድ ከተያዘው ጋር በማነጻጸር በወሩ፣ በዓመቱ እና ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ምን ያህል እንደሆነ በልኬት እና በፐርሰንት የማይገለጽ መሆኑ፤

213. ኮርፖሬሽኑ ባጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የፕሮጀክቶች ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም ልዩነት ከ10% በታች ማድረስ የሚል ቢቀመጥም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ዶክመንቶች የዕቅድ አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

214. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት አለመጠናቀቃቸው፤ይህም በ2004 ዓ.ም 2000 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ አፈጻጸሙ 490 ሄክታር (25%) ሲሆን፣ በ2005 ዓ.ም የዘር አገዳ 800 ሄክታር እና የኮሜርሻል አገዳ 6200 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ የዘር አገዳ (ቲሹ ካልቸር) 626.8 ሄክታር

(78%)፤ የኮሜርሻል አገዳ 1123.92 ሄክታር (18%) በድምሩ 1750.72 ሄክታር የዕቅዱን (25%) ብቻ መሆኑ፤

215. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ስራዎች በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሰረት አለመጠናቀቁ፣ ይህም በ2004 ዓ.ም 3288 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ 1540 ሄክታር (47%) ብቻ መሆኑ፣ በ2005 ዓ.ም 3000 ሄክታር ታቅዶ ክንውኑ በሉላጋ ሳይት 120 ሄክታር፣

በጠጄቻ ሳይት 240 ሄክታር፣ በወሌንሶ ሳይት 270 ሄክታር፤ በወለንጪቲ ሳይት 20 ሄክታር፣ በድምሩ 650 ሄክታር (22%) ብቻ መሆኑ፤

216. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመስኖ ልማት በ2004 ዓ.ም 3750 ሄክታር ታቅዶ አፈፃፀሙ 412 ሄክታር (0.3%) ሲሆን በ2005 ዓ.ም ደግሞ የ10,000 ሄክታር (Sprinkler Irrigation) መስኖ ዘዴ እስከ 4ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ለማጠናቀቅ ታቅዶ በምዕራፍ አንድ ከተያዘው 1,366 ሄክታር (13.7%) ተገንብቶ በፍተሻ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤

217. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ማስፋፊያ ፕሮጀክት በ2005 ዓ.ም ውስጥ በጠጄቻ 300 ሄክታር፣ በወሌንሱ 600 ሄክታር፣ በወለንጪቲ 1510 ሄክታር፤በቦፋ 1710 ሄክታር በጠቅላላው 4120 ሄክተር የስፕሪንክለር የመስኖ መሰረተ ልማት ያለቀለት መሬት ለመረከብ ታቅዶ ክንውኑ በጠጄቻ 240 ሄክታር፣ በወሌንሶ 300 ሄክታር፣ በሉላጋ 120 ሄክታር፤ በወለንጪቲ 20 ሄክታር በድምሩ 680 ሄክታር (16.5%) ብቻ ሰርፌስ ኢሪጌሽን የተከናወነ መሆኑ፤

218. የጣና በለስ ቁጥር 1፤ ቁጥር 2 እና ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ስራቸው ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2005 ዓ.ም ድረስ የሲቪል ወርክ፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ኢሬክሽንና ኢንስታሌሽን ሥራዎች በማጠናቀቅ ለፍተሻ እና ለርክክብ ለማዘጋጀት የታቀደ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ዝግጅት፤ ዲዛይን፤ የፋብሪካ ማሺነሪ ማምረት ማቅረብ፤ የሲቪል ሥራዎች ብቻ የተሠራ መሆኑ እና አፈጻጸሙም እንደየቅደም ተከተላቸው 45%፤ 39% እና 42% ብቻ መሆኑ፤

219. ከዚህም በተጨማሪ በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በ2003 በበጀት ዓመቱ በነበረው የመስኖ ልማት መጓተት ምክንያት ቀድሞ 2,000 ሄክታር ልማትና ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የነበረው ተከላውን በመስኖ መጓተት መትከል እንደማይቻል ታምኖበት ዕቅዱ ወደ 230 ሄክታር ዝቅ ቢደረግም በተጨባጭ መትከል የተቻለው ግን 86 ሄክታር መሆኑ፤

220. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የወለንጪቲ ቦፋ የመስኖ ግንባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በ2005 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ የተያዘ ቢሆንም የፕሮጀክቱ መሰረተ ልማት ዝርጋታውን ለአገዳ ተከላ ኮንትራክተሩ አጠናቆ ስላላስረከበ የእርሻና የአገዳ ተከላ ዕቅድን ማሟላት አለመቻሉ፤

221. ከአገዳ ተክል ልማት፤ ከመስኖ ግንባታ እና ከፋብሪካ ግንባታ ክፍል ጋር የተቀናጀ እና የተጠናከረ የፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት በየዓመቱ ተደጋጋሚ የዕቅድ ክለሳ በማድረግ፤ የዕቅድ አፈጻጸም መጓተት፤ የወጪ መጨመር፤ የጊዜ መራዘም እና ሌሎች ሃብቶችንም በአግባቡ አለመጠቀምን ያስከተለ መሆኑ፤

**የፕሮጀክቶች የአዋጪነት ጥናትን በተመለከተ**

222. የአገዳ ተክል ልማትና የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ከፕሮጀክት ትግበራው በፊት ሊከናወንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

ኮርፖሬሽኑ ባጠናው እና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተቀናጀ ውጤታማና ተቀባይነት ያለው የፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም በተጨባጭ እየተከናወነ ያለው ግን የአዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ሳይጠና ወደ ስራ የተገባ መሆኑን፤

223. በጣና በለስ እና ኦሞ ኩራዝ ስኳር ፕሮጀክት የአገዳ ተክል ልማትና የመስኖ ልማት ወደ ትግባራ ከመገባቱ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ያልተከናወነ መሆኑን፤

**የፕሮጀክቶች የዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ**

224. ወደ ትግባራ ከመገባቱ በፊት የአገዳ ተክል ልማት፤ መስኖ ግንባታና የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል የፕሮጀክቶች ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ሊከናወን ይገባል።

225. ኮርፖሬሽኑ ባጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት ኮርፖሬሽኑ የአገዳ ተክልና መስኖ ልማት ዝርዝር ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅትና የቴክኖሎጂ መረጣ በማከናወን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ 25,000 ሄክታር ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ እንዳለበት የተገለጸ ቢኖርም በተጨባጭ ለአዳዲስ ስኳር ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባቱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ እንደማይከናወን ከሥራ ተቋራጮች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት መቻሉ፤

226. የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ወደ ትግባራ ከመገባቱ በፊት የዲዛይን ጥናት ባለመከናወኑ የአገዳ ተክል ልማት ፕሮጀክት አጠቃለይ ማሳ ውስጥ ሥራው በሚያከናውኑበት ወቅት የውሃ ማፋሰሻ (drainage structure) እና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ስራዎች በዲዛይን መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ መሆኑ፤ የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ወደ ትግባራ ከመግባቱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ጥናት (Detail Design Engineering) በመስኖ ግንባታ ላይ ባለማከናወኑ ምክንያት የዲዛይን ጥናቱ ከትግበራው ጋር ጐን ለጐን እንዲሰራ በመደረጉ ስራው በየጊዜው እንዲቀያየር ማድረጉ፤ ለዚህም እንደማሳያነት ለመጥቀስ ከSurface irrigation ወደ ርጭት መስኖ ዘዴ (Sprinkler)፤ ደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) በኮንክሪት ይገነባል የተባለው ወደ ጂኦሜንቤሬን (Geomebrane)[1] መቀየሩ እና በዚህም፤ ምክንያት በክረምት ወቅት በጐርፍ የተወሰደ መሆኑ፤

227. የጣና በለስ እና ኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር የዲዛይን ዝግጅት እና የቴክኖሎጂ መረጣ ጥናት ባለማከናወኑና ስራውንም ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ባለመዘረጋቱ የሚከተሉት ችግሮች መከሰታቸው፤

- ዋናው የመስኖ ውሃ ከጣና ወንዝ ከተቀለበሰበት (Head work) ጀምሮ እስከ ደለል ማስወገጃ (Sediment settling Basin) እንዲሁም ከዚያ በኋላ የሚገኘውም ካናል በደለል የተሞላ መሆኑ፤

[1] Geomebrane ማለት ለመስኖ መስሪያነት የሚያገለግል ጠንካራ ላስቲክ ነው፡፡

- ዋና የውሃ መውሰጃ ካናሎችን ከደለል ለመከላከል የሚያስችል የድሬኔጅ ስራ ባለመሰራቱ ካናሎቹ በደለል የተሞሉበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የዋናው ካናል (Head work) ላይ የተሰራው Gate Installation በኤሌክትሮ መካኒካል ችግር የካናሉ በሮቹ በትክክል የማይሰሩ መሆኑ፤
- ዋናው የመስኖ ካናል (Headwork) ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ 30 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ሲሆን ወደ ካናሉ የሚያስገባ ወጥ የሆነ መንገድ (Access Road) አለመኖር፤
- ባለ አምስት በር intake canal የውሃ ማስተንፈሻ (Escape canal) ባለመኖሩ intake canal በደለል የተሞላ መሆኑ፤

228. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን የተዘጋጀለት ቢሆንም በጥናቱ ላይ ከአዋሽ የተጠለፈው የመስኖ ዋና ቦይ ወደ 14.5 ኪ.ሜ የሚሆን በመጀመሪያው ጥናት በኮንክሪት እንደሚገነባ የተገለጸ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በGeomembrane ወደ 10 ኪ.ሜ. በላይ የሚሆን ያለ ጥናት መገንባቱ፤

229. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ማስፋፊያ ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ላይ የወለንጪቲ አካባቢ Primary canal 1 እና Primary canal 2 6240 ሄክታር በጥናቱ ቢካተትም በተለያዩ ምክንያቶች ስራው በመጓተቱ በአዲስ መልክ በተመረጡ አካባቢዎች ኡላጋ፤ ጠደቻ፤ ወሌንሶ እና Primary canal 3 (ቦፋ) አካባቢ 6600 ሄክታር መሬት ላይ የአዋጭነት ጥናትና የዝርዝር ዲዛይን (detail engineering design) ጥናት ባልተጠናበት ሁኔታ የማልማት ስራው እየተከናወነ መሆኑ፤

**የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ**

230. የፋብሪካ ግንባታ የስራ ሂደትን ለማጠናከር እና ውጤታማ የማሽነሪ ፋብሪኬሽን፤ የአቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታ፤ ማሽነሪ ተከላና ኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። ኮርፖሬሽኑ ባጠናውና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውስጥ ከሚመለከተው የስራ ሂደት ባለቤት ጋር የተቀናጀ ፕሮጀክትን

ለመምራትና የማስፈጸም አቅምና ብቃትን ለማጎልበት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በመዘርጋት ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

231. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በጣና በለስና በኩራዝ የፋብሪካ ግንባታ በኮርፖሬሽኑ በኩል ምንም አይነት የፋብሪካ ስታንደርድ ባለመኖሩ መካተት ያለባቸው ሥራዎች እንዲካተቱ ያልተደረገ ሲሆን በዲዛይን ሥራ ወቅት የሥራ ተቋራጩ በራሱ ያገኛቸውን ስታንደርዶች በመጠቀም እየሰራ መሆኑ፤

232. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክትና በጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) አለመኖሩ

233. በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለጣና በለስ ፕሮጀክቶች የሚያቀርበው ዕቃ ዘግይቶ በመቅረቡ በማሳ ቱቦ ቀበራ ስራ፤ በፓምፕ ተከላ ሥራና በስፕሊክለር ዝርጋታ ስራዎች ላይ መጓተት መፈጠሩ፣ የቱቦ አቅርቦቱ በአብዛኛው በሁሉም ሰከንዳሪ ካናል የተሟላ ሲሆን ነገር ግን (Fittings) ፓምፖችንና የፕላስቲክ ቧንቧ (PVC) ቱቦዎችን ለማገናኘት የሚያስችል እቃዎች እጥረት መኖሩ፤

234. በስኳር ልማት ፕሮጀክት አካል የሆኑት የመስኖ ልማት፣ የአገዳ ተክል እና የፋብሪካ ግንባታ ስራዎችን በትክክል እና ሥራዎችን በቅንጅት ባለመታቀዳቸውና አፈጻጸሙ ቅደም ተከተል ጠብቆ ባለመተግበሩ የአንዱ አፈጻጸም መዘግየት በሌላው ሥራ አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፤

235. በዚህም ምክንያት ጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት በ2003 በጀት ዓመት 2 ሺህ ሄክታር ልማትና ተከላ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በመስኖ ሥራ መጓተት ምክንያት የተከላው ሥራ በእቅዱ መሠረት መከናወን እንደማይቻል ታምኖበት ዕቅዱ ወደ 230 ሄክታር መውረዱ እና መትከል የተቻለው 86 ሄክታር ብቻ መሆኑ፤

236. እንዲሁም በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የማስፋፊያ ፕሮጀክት የወለንጪቲ ቦፋ የመስኖ እርሻ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በሥራ ተቋራጩ (በኮንትራክተሩ) በ2005 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ የተያዘ ቢሆንም የፕሮጀክቱን የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ለአገዳ ተከላ ኮንትራክተሩ

አጠናቆ ስላላስረከበ የእርሻና የአገዳ ተከላ ዕቅድን ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን፤

237. በተንዳሆ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት 5164.09 ሄክታር መሬት የለማ የሸንኮራ አገዳ ምርት ዕድሜው በመራዘሙ እንዲወገድ በመደረጉ 102,440,145.00 ብር ፋብሪካው ማግኘት የሚገባውን ገቢ ተገቢ ባልሆነ መልኩ ያሳጣ መሆኑ፤

**የፕሮጀክቶቹ ስራ በውሉ በተጠቀሰው ዋጋ እና ጊዜ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ**

238. የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራር ሥርዓት በመፍጠር የአዳዲስ ፋብሪካዎች ዲዛይን፣ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፣ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በውሉ መሰረት በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ በተቀመጠው ዋጋ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ባጠናውና እየተገበረ ባለው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራርና አደረጃጀት ሥርዓት በመፍጠር የአዳዲስ ፋብሪካን ዲዛይን፣ ማሽነሪ ፋብሪኬሽንና አቅርቦት፣ የግንባታ እና ኮሚሽኒግ ሥራ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ቢታቀድም በተግባር ግን ፕሮጀክቶቹ በውሉ ከተቀመጠ ጊዜ በላይ የወሰዱ መሆኑ፤

239. በስኳር ኮርፖሬሽን እና በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን መካከል በተደረገ የውል ስምምነት አስር የስኳር ፋብሪካዎችን ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ በተሟላ መንገድ (Turnkey)[2] ገንብቶና ኮሚሽን አድርጎ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ተዋውለዋል፡፡

240. በዚህም መሠረት ከሰም፣ በለስ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 መጋቢት 2003 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ ነሃሴ 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ፣ወልቃይት-ቁጥር1፣ ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 መስከረም 2004 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ መጋቢት 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ፣ ኦሞ ኩራዝ ቁጥር 3፣ ቁጥር 4፣ ቁጥር 5 እና ቁጥር 6 ጥር 2004 ዓ.ም ሥራው ተጀምሮ እስከ ሐምሌ 2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ስራው ግን በውል በተጠቀሰው ጊዜ አለመጀመሩ እና በተባለው ጊዜ አለመጠናቀቁ፤

[2] Turnkey፡- ውል ተቀባይ የሚገነባቸውን የስኳር ፋብሪካዎች ስራ ሁሉ (ከዲዛይን እስከ ኮሚሽኒንግና ሰው ኃይል ስልጠና ድረስ) አጠናቆ ለውል ሰጪ በቀጥታ ስራ የሚጀምር ፋብሪካ የሚስረከብ የተሟላ ስራ ማለት ነው፡፡

241. በወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና በ UTTAM Suerotech international Pvt ltd መካከል የስኳር ፋብሪካ ግንባታን ለማከናወን በተደረገ የውል ስምምነት ከ12/05/2000 ዓ.ም እስከ 13/05/2003 ዓ.ም በተሟላ መንገድ (Turnkey) ገንብቶ እና ኮሚሽን አድርጎ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ የተዋዋሉ ቢሆንም ግንባታው በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቁ፤ ከሚያዝያ 14 2005 ጀምሮ የሙከራ ምርት እንደ ጀመረና ሙሉ በሙሉ ርክክብ ያልተፈጸመ መሆኑ፤

242. የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአፈጻጸም ማንዋል ለግንባታ ሥራ አገልግሎት ግዥ የተፈረመው የውል ስምምነት የዋጋ ማስተካካያ እንደሚደረግ የሚፈቀድ ከሆነ፤ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ18 ወራት በላይ ሲሆን እና ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ12 ወራት በኂላ ማስተካከል እንደሚቻል ቢገልጽም ኮርፖሬሽኑ በተጨባጭ የዋጋ ማስተካከያ ያደረገባቸው የውል ስምምነቶች ግን ግንባታቸው 18 ወራት በታች መሆናቸው፤

243. በስኳር ኮርፖሬሽና በባቱ የኮንስትራክሽን አ.ማ መካከል በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመሬት ድልዳሎ (Land Leveling) የመሬት መሰንጠቅ አገልግሎት በ09/02/2005 ዓ.ም በተፈረመው የውል ስምምነት ከህዳር 1 እስከ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም አጠናቆ ለማስረከብ በ 25,818,740.00 ብር የተስማማ ሲሆን በ3/07/2005 ዓ.ም ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዋጋ መስተካከያ ብር 4,181,260.00 የ(16%) ለ1000 ሄክተር የግዥ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማሻሻያ መደረጉ፤

244. በስኳር ኮርፖሬሽና የኮንስትራክሽን ሥራዎችና የቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጀት መካከል የተደረገ የወል ስምምነት መሰረት በጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት የመሬት ድልዳሎ (Land Leveling) አገልግሎት በ09/02/2005 ዓ.ም በተፈረመው የውል ስምምነት ከህዳር 1-ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ስራውን አጠናቆ ለማስረከብ በ 25,818,740.00 ብር የተስማማ ሲሆን በ3/07/2005 ዓ.ም ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የዋጋ መስተካከያ ብር 4,181,260.00 የ(16%) ለ1000 ሄክታር የግዥ ስርዓት ባልተከተለ መልኩ ማሻሻያ መደረጉ፤

245. ስኳር ኮርፖሬሽንና ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን 10,000 ሄክታር ለማልማት በ2003 ዓ.ም ውል የተፈራረሙና ስራውንም ለማስጀመር 30% ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ሲሆን ተቋራጭ ድርጅቱ በተጨባጭ ያለማው 2000 ሄክታር ሲሆን የተቀረውን 8000 ሄክታር ስኳር ኮርፖሬሽን ለሌሎች ተቋራጮች የሰጠ መሆኑ፤ በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብም ካለማው የሄክታር መጠን ጋር ተመጣጣኝ አለመሆኑ፤

246. ለወንጂ ሸዋ ስኳር የመስኖ ማስፋፊያ ፕሮጀክት በመጀመሪያ በ13/10/2002 ዓ.ም የተፈረመው የኮንትራት ውል 6300 ሄክታር መሬት ለማልማት የተመለከተው ዋጋ 799,394,202.51 ብር ሲሆን በተለያየ ጊዜ በተደረገ የዋጋ ማስተካከያ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ በላይ ተጨማሪ ብር 957,767,481.12 (119.81% ጭማሪ) የግዥ ስርዓትን ባልተከተለ መልኩ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ መሆኑ፤

**የፕሮጀክት ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ**

247. የአገዳ ተክል ልማት፤ የመስኖ ግንባታ እና የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የተሰሩ ስራዎች በተቀመጠለት ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

248. ኮርፖሬሽኑ ሊያስገነባቸው ላቀደላቸው አስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች ሥራቸው በተጀመረበት ወቅት ጥራት የሚቆጣጠር አማካሪ ድርጅት አለመቀጠሩ፤

249. ለጣና በለስ ቁጥር 1፤ ቁጥር 2 እና ለኦሞ ኩራዝ ቁጥር 1 የፋብሪካ ግንባታ ስራቸው የተጀመረው መጋቢት 2003 ዓ.ም ሲሆን ኮርፖሬሽኑ አማካሪ ድርጅት የቀጠረው ሥራው ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በኂላ ሐምሌ 10 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑ፤

250. የጣና በለስና ኩራዝ ፋብሪካ ግንባታ (ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2006 ጥቅምት ወር ድረስ) በየደረጃው እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች (civil work) በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፐሲፊኬሽን መሰረት ስለመሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲስ አለመረጋገጡ፤

251. የአዳዲስ ፋብሪካዎች ግንባታ ከመጀመሪያው ጀምሮ ስራው በተቀመጠው የውል ስምምነት መሰረት ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የቴክኒክ ባለሞያ በፕሮጀክት ቦታው ላይ ያልተመደበ መሆኑ፤ እንዲሁም

የጣና በለስና ኩራዝ የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራዎች ከመጀመሪያ ጀምሮ (civil work) በተቀመጠለት ዲዛይንና እስፕሲፊኬሽን መሰረት እንዲከናወን የግንባታ ግብዓቶች (construction material input) የጥራት ማረጋገጫና የግብዓቶች መጠን መለኪያ ላብራቶሪ አለመኖሩ፤

252. የበለስ ስኳር ፕሮጀክት የመስኖ ግንባታን በተመለከተ የ10,000 ሄክታር የሚያለማው የመስኖ ርጭት አጣቃላይ የአቅርቦት እና የግንባታ ሥራውን የሚገልጽ የውል ስምምነት ሰነድ አማካሪ መሃንዲስ ለሆነው ለአማራ የዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ያልተሰጠ መሆኑ፣ አማካሪ መሃንዲሱ በውሉ ስምምነት ሰነድ መሠረት ሥራው ለመፈፀሙ የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፤

253. በወንጂ/ሸዋ፣ በጣና በለስና በኩራዝ የፋብሪካ፤ የአገዳ ተክል ልማት ሥራ በፕሮጀክቱ የጥራት ማረጋገጫ ማኑዋል (Quality Assurance Manual) አለመኖሩ፤

254. ኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ባለመቅጠሩ ምክንያት የፋብሪካ ግንባታ ከመከናወኑ በፊት ዝርዝር የፋብሪካ ዲዛይን ስራ በአማካሪ ድርጅት ያልተከናወነ ሲሆን ይህ በመሆኑም በጣና በለስና በኩራዝ የፋብሪካ የግንባታ ክንውን በምን ዓይነት የጥራት ደረጃ እንደሚገነባ የማይታወቅ መሆኑ፤

255. የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሚገባው ደረጃ በቦታው ተግኝቶ አፈጻጸማቸውን ከመገምገም ይልቅ በኮንትራክተሮች ሪፖርት ላይ ብቻ የተመረኮዘ ሪፖርትና ትንታኔ የሚደረግ ሲሆን የግንባታ ሥራው በተቀመጠለት ዲዛይን፤ ስፐስፊኬሽን እና በኮንትራት ዶክመንት መሰረት እየተከናወነ መሆኑ ለማረጋገጥ የሚደረገውን የግንባታ ጥራት ቁጥጥር እና ክትትል ስራ ውስብስብ የሚያደርገው መሆኑ፤ በጣና በለስ ስኳር ፕሮጅክት የአገዳ ተክል (Plant cane) የማዳበሪያ አጠቃቀም በጥናት የተረጋገጠ ስታንዳርድ የሌለው ሲሆን፤ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ የአገዳ ተክል (plant cane) የማዳበርያ አሰጣጥ ወቅታዊ አለመደረጉ፤

በመሆኑም የስኳር ኮርፖሬሽን በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 10.10 በጂአይዜድ የተከናወኑ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም

**የጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት አዘገጃጀት መመሪያ መኖሩን በተመለከተ**

256. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከናወኑ የጤና ተቋማት ግንባታ ስራዎች ከመጀመራቸው በፊት የፕሮጀክት አዘገጃጀት መመሪያ ሊኖረው እና በመመሪያው መሰረት ወጥነት ባለው መልኩ ለሚከናወነው የቅድመ ትግበራ ግምገማም ሆነ ለክትትል ስራው የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ሊሟላ፣ የእያንዳንዱ ሰራተኛ የስራ ድርሻ መዘርዝር፣ የዳይሬክቶሬቱ የስራ ሃላፊነትና ተግባር በጽሁፍ ሊዘጋጅ እና ጂ.ቲ.ዜድ ለየትኛው የስራ ክፍል ተጠሪ እንደሚሆን መገለጽ ይኖርበታል፡፡

257. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከናወኑ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክት በጥናት ላይ ተመስርቶ አለመዘጋጀቱ፤ ሰነዱ ባለመዘጋጀቱም የቅድመ ትግበራ ግምገማ አለመከናወኑ፤ ለትግበራ ለግምገማ እና ለክትትል ስራ የሚያስፈልገው የሰው ሀይል መሟላቱን የማረጋገጥ ስራ አለመሰራቱ፤ የስራ ድርሻ መዘርዝር አለመዘጋጀቱ፤ ስራውን በበላይነት የሚከታተለው ዳይሬክቶሬት የስራ ሃላፊነትና ተግባር እንዲሁም ጂ.ቲ.ዜድ ለየትኛው የስራ ክፍል ተጠሪ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ አለመዘጋጀቱ፤

**ለግንባታ ፕሮጀክት ሳይቶች የቅድመ አዋጪነት (pre-feasibility study) እና የአዋጪነት ጥናት (feasibility study) መከናወኑን በተመለከተ**

258. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና ተቋም ግንባታ የፕሮጀክት ሰነድ የቅድመ አዋጪነት (pre-feasibility study) እና የአዋጪነት ጥናት ( feasibility study) አለማከናወኑ፤

259. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና ተቋማቱን ለመገንባት ያሉትን አማራጮች በመከለስ የተሻለውን አማራጭ በመምረጥ ለስራው የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች በሚፈለገው ደረጃ በጥልቀት በመመልከት ወደ ስራ አለመግባቱ፤

**ለጤና ጣቢያ ግንባታ ሳይቶች መመልመያ መስፈርት መኖሩን እና የአካባቢ ግምገማ ጥናት መደረጉን በተመለከተ**

260. የጤና ተቋማቱ ግንባታ ፕሮጀክት የአካባቢ ግምገማ ጥናት (environmental impact assessment ) በማካሄድ ግልጽ የሆነ መመልመያ መስፈርት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መዘጋጀት እና ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው በማድረግ ሳይቶቹም በተቀመጠው

የምልመላ መስፈርት መሰረት የተመረጡ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

261. ለጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክት የአካባቢ ግምገማ ጥናት (environmental impact assessment) አለመደረጉ፤ ለጤና ጣቢያዎቹ የግንባታ ሳይቶች ግንባታዎቹ የሚያርፉበት ቦታን መምረጫ መስፈርት አለመኖሩ፤

262. ይህ በመሆኑም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የጢስ አባይ ጤና ጣቢያ ከአባይ ወንዝ ያለው እርቀት ከ 50 ሜትር የማይበልጥ በመሆኑ በክረምት ወቅት በአባይ ወንዝ የሚጥለቀለቅ መሆኑ፤ የወቾ ጤና ጣቢያ በደለላማ ቦታ ላይ የሰንጠማ ጤና ጣቢያ ደግሞ በረግረጋማ አካባቢ ላይ መገንባቱ፤

**የጸደቀ የፕሮጀክት ሰነድ እና የድርጊት መርሃ ግብር መኖሩን እንዲሁም የቁጥጥርና ክትትል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ**

263. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በጸደቀው የፕሮጀክት ሰነድ፣ በፕሮጀክት የድርጊት መርሃ ግብር፣ በቁጥጥርና ክትትል (monitoring & evaluation) መመሪያ (guideline) ግንባታው መከናወኑን፣ የፕሮጀክቱን የስራ ሂደት፣ ግብዓት፣ ውጤት/ስኬት በየጊዜው መከታተል አለበት፡፡

264. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለግንባታ ፕሮጀክቱ የድርጊት መርሃ ግብርም አለመዘጋጀቱ፣ የቁጥጥርና ክትትል (monitoring & evaluation) ስርዓት አለመዘጋቱ የፕሮጀክቱን ግንባታ በተመለከተ መመሪያ (guideline) አለመዘጋጀቱ፣ መደበኛ በሆነ መልኩ የፕሮጀክቱ የስራ ሂደት ላይ ክትትል አለመከናወኑ፣ እና ፕሮጀክቱም ያስገኘው ውጤት/ስኬት በየጊዜው አለመገምገሙ፤

**በፕሮጀክት ጥናት ላይ የቅድመ ትግበራ ግምገማ መከናወኑንና ከባለድርሻ አካላት ጋር ስምምነት ላይ መደረሱን በተመለከተ**

265. ለቅድመ ትግበራ ግምገማ የጤና ጣቢያ ግንባታ በቀረቡ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች ላይ የተመለከቱትን ክብደት የሚሰጣቸው (ስራዎች) በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ሊደረግባቸው እና የስምምነት ሰነድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

266. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት ላይ ሊሳተፉ የሚገባቸው ባለድርሻ አካላት በቅድሚያ የመለየት ስራ አለመስራቱ፤

ነገር ግን ለፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካል ከሆኑ የክልል ጤና ቢሮዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረመ ቢሆንም ከመፈራረም የዘለለ ነገር አለመስራቱ፤ ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ፡- የከተማና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤት፣ የክልል መስተዳድር አካላት እና ሌሎችም) ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር አለማድረጉ፤ ለባለድርሻ አካላት መሰጠት ያለበትን ኃላፊነት በመለየትና በቅድሚያ በመነጋገር በዝርዝር በጽሁፍ እንዲደርሳቸው አለማደረጉ፤

**አዲስ የሚገነቡ እና ማስፋፊያ የሚደረግላቸው ጤና ጣቢያዎች በውሉ ላይ መገለጻቸውን በተመለከተ**

267. ለእያንዳንዱ ግንባታ ሳይት ማስፋፊያ የሚያስፈልጋቸው እና አዲስ የሚገነቡ ጤና ጣቢያዎች ብዛት በውሉ ላይ በዝርዝር መገለጽ ይኖርበታል፡፡

268. ሆኖም የጤና ተቋማቱን በሚገነቡበት ቦታ ማስፋፊያ የሚያስፈልጋቸው እና አዲስ የሚገነቡ ጤና ጣቢያዎች ብዛት በመጀመሪያ በጂ.ቲ.ዜድ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል በተደረገው ውል ላይም ሆነ በድጋሚ በተደረገው የውል ስምምነት ላይ አለመገለጹ፤ እንዲሁም በመጀመሪያ በጂ.ቲ.ዜድ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል በተደረገው ውል ላይም ሆነ በድጋሚ በተደረገው የውል ስምምነት ላይ ነባር ጤና ጣቢያዎች የሚገኙበት ደረጃ በቀረበው ዋጋ ላይ የሚያመጣው ልዩነት አለመጤኑ፤

**ለጤና ጣቢያ የግንባታ ፕሮጀክት ዕቅድ መኖሩን በተመለከተ**

269. የጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ዝርዝር እቅድ እና የእቅድ አፈጻጸም መርሃ ግብር ሊኖረው፣ በመርሃ ግብሩ ላይም የወጪ ግምት፣ የተመደበ ሀብት፣ (የሰው ሀይልና ማቴሪያል) የቁጥጥር ስርዓት እና አዋጪነት ጥናት ሰነድ፣ የፕሮጀክቱ ሥራ የሚጀምርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን ሊገለጽ ይገባል፡፡

270. ሆኖም ለጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት አለመደረጉ፣ ለፕሮጀክቶቹ የሚሆኑ በአቅራቢያ የሚገኙ ግብአቶችን (Local materials) አስቀድሞ የመለየት ስራ አለመከናወኑ፣ ለግንባታው የተያዘው የወጪ ግምት የተሰጠው በቁርጥ ዋጋ ሲሆን ይህም በተፈቀዱ የመንግስት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ ያልተካተተ እና ለፕሮጀክቱ የተያዘው

የግንባታ በጀት ነባራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ በጂ.ቲ.ዜድ የመጨረሻ ሪፖርት መገለጹ፤

271. በጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት የተቀጠሩት 1 አለምአቀፍ የጥራት ተቆጣጣሪ፣ 1 አለምአቀፍ የፕሮጀክት አስተባባሪ፣ 7 የክልል ፕሮጀክት ማናጀሮች እና ሳይት ማናጀሮች ሲሆን ለአንድ የሳይት ማናጀር 18 ሳይቶች የሚሰጠው መሆኑ፣

272. ጂ.ቲ.ዜድ ባቀረበው የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ሪፖርት ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ የፕሮጀክቱን ስፋት፣ የሀገሪቱን መልካምድራዊ አቀማመጥ እና የሳይቶችን ተደራሽነት ከግምት ውስጥ ያላስገባ ከመሆኑም በላይ የተመደበው ባለሙያ በቂ አለመሆኑ፤

273. በአጠቃላይ ከፕሮጀክቱ ስፋት አንጻር ለስራው ትኩረት በመስጠት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት አለመደረጉ፤ የፕሮጀክት ማኔጅመንቱን ስራ ለጂ.ቲ.ዜድ ከመሰጠቱ በፊት ያሉ አማራጮች አለመዳሰሳቸው፤ ፕሮጀክቱን ለጂ.ቲ.ዜድ ከመስጠት ውጭ ሌላ የተሻለ መንገድ መኖሩ አለመረጋገጡ፤ ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራር ስርዓቶች አለመዘርጋታቸው፤

274. ጂ.ቲ.ዜድ ስራውን ለኮንትራክተር እየሰጠ ፣ የአማካሪነቱን ስራ እየሰራ፣ ክፍያ እያጸደቀ፣ ኮንትራክተሮች ስራውን ጥለው ሲወጡም የግንባታ ስራውን እያከናወነ ባለበት ሁኔታ የሚኒስትር መ/ቤቱ የቁጥጥር ስራውን በገለልተኝነት ሊያከናውን የሚቻልበትን መንገድ አለማመቻቸቱ፤

## ለጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት የምህንድስና ዲዛይን በሚኒስቴሩ በወጣው የጤና ጣቢያ ስታንዳርድ፣ ማንዋል፣ እስፔሲፊኬሽን መስፈርቶችን ማካተቱን እና ጥቅም ላይ ለሚውልበት ዓላማ የሚመጥን ስፋት ያለው መሆኑን በተመለከተ

### የተገነባው የጤና ጣቢያ ጥቅም ላይ ለሚውልበት ዓላማ የሚመጥን ስፋት ያለው መሆኑን በተመለከተ

275. ለጤና ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት የምህንድስና ዲዛይን የጤና ጥበቃ ሚኒስተር ባወጣው የጤና ጣቢያ ስታንዳርድ፣ ማንዋል፣ እስፔሲፊኬሽን መስፈርቶችን ማካተት እና የተገነባው ክፍል ወይም ቦታ ጥቅም ላይ ለሚውልበት ዓላማ የሚመጥን ስፋት ያለው መሆን አለበት።

276. በመስክ ጉብኝት ወቅት በከፋ ዞን ለጤና ጣቢያ የተሰሩ ብሎኮች በቂ ስፋት የሌላቸው ከመሆኑ በተጨማሪም ለጤና ጣቢያ ግንባታ የተዘጋጀው ዲዛይን የጥበቃ ማደሪያ ቤት፣ የነርሶች ማደርያ ቤት፣ ለቢሮ አስተዳደር ክፍሎች የሌለው መሆኑ፤ ከ 475 ጤና ጣቢያዎች ውስጥ 285 ሜዲካል ስቶር፣ 160 ኢንስሊኔተር፣ 153 ፕላሴንታ ፒት እና 198 አጥር ያልተገነባባቸው መሆኑ፤ ጤና ጣቢያዎቹ የተገነቡት በገጠራማ የሀገሪቱ ክፍል በመሆኑ ባለሙያዎቹ በአዳር ሥራ ለመስራት በማዋለጃ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን መጸዳጃ ቤት እና በግቢው ውስጥ የሚገኘውን የመጸዳጃ ቤት ውሃ ባለመኖሩ አገልግሎት መስጠት ስላልጀመረ ለማደሪያነት የሚገለገሉበት መሆኑ፤

## በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነው የጤና ጣቢያዎች ግንባታ ፕሮጀክት የአዋጪነት ጥናት፣ የምህንድስና ዲዛይን እና ለፕሮጀክቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ

277. የጤና ጣቢያዎች የህንፃው ክፍል ወይም አካል ተቀባይነት ባለው የህንፃ ዲዛይን ደንብ መሠረት ጥንካሬን፣ ተደላድሎ መተከልን፣ ለጥገና ሥራ አገልግሎት አመቺነትን፣ እንዲሁም ዘለቄታዊ አስተማማኝነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ሆኖ ዲዛይን ሊደረግ ይገባል፡፡

278. ይሁን እንጂ ለጤና ጣቢያዎቹ ግንባታ ዲዛይን ፕሮግራም ባለመኖሩ ግንባታው የተከናወነው በስታንዳርድ ፕላን በመሆኑ የአካባቢ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዲዛይን አለመዘጋጀቱ፤ ዲዛይኑን ለማዘጋጀት የአፈር ናሙና አለመወሰዱ፣ የሳይት ሁኔታ ጥናት አለመከናወኑ፣ እንዲሁም የተገነቡት ጤና ጣቢያዎች ዲዛይን ኮለን (ምሰሶ) የተሰራው ክላስ ቢ በሚባል በሆሎ ብሎክ ሲሆን ይህ አይነቱ ዲዛይን ለክትትልና ቁጥጥር የሚያስቸግር እና ጥራት ለሌለው ስራ(poor workmanship) የሚጋለጥ በመሆኑም ብዛት ላለው ሳይት እና እርቀት ላይ ላሉ ሳይቶች የማይመረጥ መሆኑ፤ በተጨማሪ የተሰራው ዲዛይን የውሃ ማስወገጃ አሸንዳዎች በአየር ላይ የተንጠለጠሉ መሆናቸው እና ግንባታው 2% እስሎፑን (ተዳፋቱን) ጠብቆ ያልተገነባ (በመስክ ጉብኝት ባየናቸው ለምሳሌ ጎሮ፣ ጅሩ ገመቹ) በመሆኑ ፔቭመንት (የህንጻው ዙሪያ የኮንክሪት ንጣፍ) ላይ በመፍሰስ ከማበላሸቱም በላይ ፍሳሹ ወደ ህንጻው የታችኛው ክፍል እንዲገባ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ በአጠቃላይ ዲዛይኑ

ከላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ህንጻው ጥራት፣ ጥንካሬ፣ ለጥገና አመቺነቱን እንዲሁም እድሜ (ዘለቄታዊ አስተማማኝነት) እንዳይኖረው ያደረገ መሆኑ፤

279. በአማካሪ መሀንዲሱ እና በጂ.ቲ.ዜድ መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ላይ የአፈር ምርመራ ናሙና እንደሚደረግና የሳይት ሁኔታ ጥናት እንደሚደረግ በዋጋ (በኮስት) ክፍፍል እና በቀረበው ቴክኒካል ፕሮፖዛል ላይ የተገለጸ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፤ በMH Engneering (በአማካሪው መሀንዲስ) እና በጂ.ቲ.ዜድ መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ላይ በመጀመሪያ ዙር ለሚገነቡ 220 ጤና ጣቢያዎች በቂ የሰው ሀይል በመመደብ የማጣጣም ፕላን (adaptation plan) በMH Engneering እንደሚሰራ እና በሁለተኛ ዙር ለሚገነቡት 221 ጤና ጣቢያዎች ደግሞ በጂ.ቲ.ዜድ መሀንዲሶች እንደሚታይ የተገለጸ ቢሆንም በዚሁ መሰረት አለመከናወኑ፤ የዲዛይን ፕሮግራም ባለመኖሩ በMH Engneering በቀረበውን ዲዛይን ላይ የፕሮጀክቱ ዋነኛ ባለድርሻ አካላት (የክልል ጤና ቢሮ ኃላፊዎች) በቀረበው ዲዛይን ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አለመደረጉ፤

280. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሰራው ስታንዳርድ ዲዛይን የአካል ጉዳተኞች መወጣጫ የሌለው ሲሆን፣ በተወሰኑ ጤና ጣቢያዎች ደረጃዎች በሚያስፈልጉባቸው ቦታዎች ላይ ደረጃ አለመሰራቱ፣ ከመሬት ከፍ ብለው በተገነቡ ቦታዎች ሰዎች ወድቀው እንዳይጎዱ የሚያስችል መከላከያ አለመኖሩ፤ ተጠቃሚዎች በዝናብ እና በፀሀይ ወቅት ከአንዱ ህንጻ ወደ ሌላው በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የሚተላለፉበት ሼድ (ከለላ) በዲዛይኑ ላይ አለመኖሩ፤

**በተገነቡ ጤና ተቋማት የፍሳሽ ማስወገጃ መዘጋጀቱን በተመለከተ**

281. ለተገነቡት የጤና ተቋማት በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መዘጋጀት አለበት፡፡ የጎርፍ ውሀ ከየትኛውም ቦታ ወደ ጤና ተቋማቱ ፍሳሽ ማስወገጃ እንዳይገባ መደረግ አለበት፡፡ ከጤና ተቋሙ የሚወጣ ፍሳሽ ከመፀዳጃ አገልግሎት መስጫዎች የሚወጣን ፍሳሽ ቆሻሻ ጨምሮ ወደ ማንኛውም የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ወይም በሌላ መልኩ ወደ ተገነባ የውሃ መስመር፣ ወንዝ፣ ምንጭ፣ ጎዳና ወይም ሌላ ስፍራ መለቀቅ የለበትም፡፡

282. ሆኖም የጤና ተቋማቱ ግንባታ የተከናወነው በገጠራማ የሀገሪቱ ክፍል ሲሆን በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴ የሌለ መሆኑ ታውቋል። ይኸውም በኦሮሚያ ክልል 6 ጤና ጣቢያዎች(ወቾ፣ ደነባ፣ ሰጠማ፣ ሶንቦ፣ ጅሩ ገመቹ እና ጎሮ)፣ በአማራ ክልል 5 ጤና ጣቢያዎች (አይምባ፣ ጎፍጭማ፣ ተዝካረ ማርያም፣ ዲማ እና ጢስ አባይ) እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 4 ጤና ጣቢያዎች (ዲንቢራ፣ ዲሪ፣ ባሺ እና ፎንኮ) በጠቅላላው በሶስቱ ክልሎች በተገነቡ 15 ሳይቶች ላይ የፍሳሽ መተላለፊያ ቦዮች ተዳፋት(ስሎፑን) ጠብቀው አለመገንባታቸው፣ በአቅራቢያውም ተስማሚ የሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ አለመኖሩን እና ተቀባይነት ባለው ሌላ መንገድ ፍሳሽ ማስወገጃ አለመዘጋጀቱ፤ በተጨማሪም ከጤና ተቋማቱ የሚወጣ ፍሳሽ ከመፀዳጃ አገልግሎት መስጫዎች የሚወጣን ፍሳሽ ቆሻሻ ጨምሮ ወደ ማንኛውም የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ወይም በሌላ መልኩ ወደ ተገነባ የውሃ መስመር፣ ወንዝ፣ ምንጭ፣ ጎዳና ወይም ሌላ ስፍራ ተቀላቅሎ የሚወጣ መሆኑ፤

**የጤና ጣቢያዎቹ የግንባታ ለሥራ ተቋራጮች በጨረታ መስጠቱን በተመለከተ**

283. ጂ.ቲ.ዜድ እያንዳንዱን የጤና ጣቢያ ግንባታ ለሥራ ተቋራጮች በጨረታ አወዳድሮ መስጠት አለበት።

284. በጂ.ቲ.ዜድ ከተከናወኑ 475 የጤና ጣቢያዎች ግንባታ ፕሮጀክት 51% የሚሆኑት ለሥራ ተቋራጮች የተሰጠው ያለውድድር እና ያለ ጨረታ መሆኑ፤ ለአንድ ኮንትራክተር ከሁለት እስከ ሰባት የጤና ጣቢያ መሰጠቱ፤

**የጤና ጣቢያዎቹ ግንባታ በውለታው መሰረት በተያዘለት ጊዜ፣ ወጪ እና የጥራት ደረጃ መጠናቀቁን በተመለከተ**

285. በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነ እያንዳንዱ የጤና ተቋም ግንባታ በጂ.ቲ.ዜድ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

286. ሆኖም የጤና ተቋም ግንባታ በውለታው መሠረት በተያዘለት የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አለመጠናቀቁ፤ በትግራይ ክልል አዲግራት ጤና ጣቢያ 1,332 ቀናት፣ በሱማሌ ክልል ለፊሳ ጤና ጣቢያ 1,193 ቀናት፣ በአማራ ክልል የመንገዘር ጤና ጣቢያ 983 ቀናት፣ በኦሮሚያ ክልል ቦንዳዎ ጤና ጣቢያ 982 ቀናት እና በደቡብ ክልል ዳራዲሜ ጤና ጣቢያ

955 ቀናት የዘገዩ ሲሆን በጂ.ቲ.ዜድ በተገነቡ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራ በተያዘለት ጊዜ ባለመጀመሩ በኦሮሚያ ከተገነቡት 169 ጤና ጣቢያዎች 113ቱ የዘገዩ መሆኑ፤

287. ከዚህ በተጨማሪ በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነ እያንዳንዱ የጤና ተቋም የመታያ ጊዜ( Warranty period) በውለታው መሠረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ሲኖርበት በጂ.ቲ.ዜድ ከተከናወኑ የጤና ተቋማት ውስጥ የግንባታ የጥራት ችግር ባለባቸው ላይ እና በተለያዩ ምክንያቶች በአፋር፣ በትግራይ፣ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ሕ/ብ/ብ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ ክልሎች በአጠቃላይ 158 ጤና ጣቢያዎች ላይ (የተጨማሪ ስራዎችን ሳይጨምር) በውለታው መሠረት በአንድ ዓመት የመታያ ጊዜ ውስጥ (Warranty period) ሥራው ባመጠናቀቁ የመጨረሻው ርክክብ አለመፈጸሙ፤

**የጤና ተቋማት ግንባታ በተያዘለት በጀት መጠናቀቅን በተመለከተ**

288. በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነ የጤና ተቋማት ግንባታ በኮንትራት ውሉ ላይ በተመለከተው ዋጋ መሠረት እና በተያዘለት በጀት መጠናቀቅ አለበት፡፡

289. የግንባታ ጥሬ ዕቃ ዋጋ ንረት በመከሰቱ ፣ በጀት በሚያዝበት ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት የነበረባቸው ጤና ጣቢያዎቹ የሚገኝበት የአፈር አይነት፣ ሳይቱ የሚገኝበት ርቀት፣ እና ሌሎች ምክንያቶች ከግምት ውስጥ ባለመግባታቸው የ144 ጤና ጣቢያዎች ግንባታ በተያዘለት በጀት መጠናቀቅ አለመቻሉ፤በአጠቃላይ በሁሉም ክልሎች ለተገነቡ ጤና ጣቢያዎች ከተያዘላቸው ዋጋ በላይ ብር 105,270,698.97 ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

**የጤና ጣቢያ ግንባታ በስታንዳርዱ፣ በዲዛይኑ እና ስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መሆኑን በተመለከተ**

290. በጂ.ቲ.ዜድ የተከናወነ የጤና ተቋም ግንባታ በታቀደው በጤና ጣቢያ ስታንዳርድ በተሰራለት ዲዛይን እና ስፔሲፊኬሽን መሰረት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ግንባታው መከናወን ይኖርበታል፡፡

291. በመስክ ጉብኝት ባየናቸው በኦሮሚያ ክልል ወቾ፣ ጅሩ ገመቹ፣ ጎሮ፣ ደነባ፣ ሰንቦ እና ሰጠማ በተገነቡ ጤና ጣቢያዎች ላይ የወለል መፈርፈር፣ የግርግዳ መሰንጠቅ፣ የበርና መስኮቶች መወላለቅና

አለመስራት፣ የበሮች ቁልፍ ፣ የእጅ መታጠቢያዎች ፣ የኤሌትሪክ መስመሮች እና የውሃ መስመሮች ባለበት ቦታ አለመስራት እና መስመሮች በተገቢው መንገድ በአግባቡ አለመዘርጋት፣ የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃዎች ተዳፋታቸውን ጠብቀው አለመገንባት፣ ከጤና ጣቢያው የሚወጣው ፍሳሽ አወጋገድ በተገቢው መንገድ ተጠንቶ አለመገንባቱ፣ የጣራ ማፍሰስ እና ሌሎችም ችግሮች መኖራቸው፤ በአማራ ብሄራዊ ክልል ባየናቸው አምስት ጤና ጣቢያዎች (ጢስ አባይ፣ ጎፍጭማ፣ ተዝካረ ማርያም፣ ዲማ እና አይምባ) እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ባየናቸው አራት ጤና ጣቢያዎች (ዲንቢራ፣ ዲሪ፣ ባሺ እና ፎንኮ) በአብዛኛው ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው መሆኑ፤ የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው 15 ጤና ጣቢያዎች የተከሰቱትን ችግሮች በጥገና ለማስተካከል እንዳልተቻለ ለመገንዘብ መቻሉ፤

292. በአጠቃላይ በጂ.ቲ.ዜድ ከተገነቡ 475 ጤና ጣቢያዎች ውስጥ በኦሮሚያ 26፣ በአማራ 28፣ በደቡብ 22፣ በትግራይ 10፣ በአፋር 6፣ በሱማሌ 1፣ በቤኒሻንጉል 10 ፣ እና በጋምቤላ ከተገነባው 1 በድምሩ በ104 ጤና ጣቢያዎች ላይ የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ፤፡ በመስክ ጉብኝት ወቅት በጤና ጥበቃ ከተገነቡት (በፒ.ኤም.ዩ) ተገንብተው የጥራት ችግር ካለባቸው መካከል አማላማ እና አዋሽ ቡኔ የጤና ጣቢያዎች ችግሮች በቀላል ጥገና ሊስተካከሉ የማይችሉ መሆናቸው፤

### የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ከመለቀቁ በፊት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መቀመጣቸውን በተመለከተ

293. በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በጂ.ቲ.ዜድ መካከል እ.ኤ.አ. በኦክቶበር/2006 በተደረገው የውል ስምምነት አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 7 ለግንባታው ቅድሚያ ክፍያ ብር 80,606, 670.00 ስምምነቱ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ወይም ከተፈጸመ በኂላ ከ14 ቀናት በፊት ወደ ጂ.ቲ.ዜድ ሂሳብ ገቢ መደረግ እንዳለበት እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሁለት ሩብ ዓመት የግንባታ ወጪን በመጀመሪያው ሶስት ወር ብር 60,455,003.00 በቀጣይ ሶስት ወር ብር 55,417,086.00 የወጪ መግለጫ/ SOE / ሪፖርት ጠይቆ ሲቀርብለት ሥራ ላይ ያልዋለ ገንዘብ ካለ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለጂ.ቲ.ዜድ ገንዘብ እንደሚተላለፍ ተገልጿል፡፡

294. ከዚህ በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጂ.ቲ.ዜድ ጋር በገባው ውል መሰረት ለኮንስትራክሽን ማኔጅመት ክፍያ እና የግንባታ ክፍያ የሚፈጸመው በሶስት ጊዜ ሲሆን በመጀመሪያ ዙር፣ በሁለተኛ ዙር (የፕሮጀክቱ ስራ 60% ሲጠናቀቅ) እና የመጨረሻውን ክፍያ የሚፈጽመው የክፍያ ሰነዶች ሲቀርቡለት በ30 ቀናት ውስጥ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በውሉ ላይም በየደረጃው የስራ ማስፈጸሚያ ገንዘብ ለጂ.ቲ.ዜድ ከመልቀቁ በፊት ማሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ዝርዝር መስፈርቶችና ግዴታዎች ተቀምጧል፡፡

295. ይሁን እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ ለጂ.ቲ.ዜድ ክፍያ ለመፈጸም የሚቀርብለትን ሪፖርት የሚገመግም ቢሆንም ስራው የደረሰበትን ደረጃ ግን በሳይቶች በመገኘት የማረጋገጥ ስራ አለማከናወኑ፤

**ለፕሮጀክቱ የተገዙ ንብረቶች በመንግስት የግዢ ህግ መሰረት መሆኑን እና ንብረቶቹም ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ መተላለፋቸውን በተመለከተ**

296. በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ጂ.ቲ.ዜድ መካከል በተደረገው ስምምነት ላይ ለፕሮጀክቱ የሚገዙ ንብረቶች በአገሪቱ የግዥ ህግ መሰረት እንደሚሆኑ እና ለፕሮጀክቱ የተገዙ ንብረቶች በሙሉ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መ/ቤት ይተላለፋል የሚል ቢሆንም፤ የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው (በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደቡብ ክልል ጤና ቢሮዎች) በተገኘው ማስረጃ መሰረት ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የተረፉ ንብረቶች ርክክብ አለመደረጉ፤ የሚኒስቴር መ/ቤቱም የፕሮጀክቱ ንብረቶች በሙሉ በተገቢው መንገድ መመለሳቸውን አለማረጋገጡ፤

297. በውል ስምምነቱ መሠረት ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመላሽ እንደሚደረጉ የተገለጸ ሲሆን ጂ.ቲ.ዜድ ለዞንና ለክልሎች ማስረከቡ ከውለታው ውጪ መሆኑ፤ በተጨማሪም ጂ.ቲ.ዜድ ለክልል ጤና ቢሮ እና ለዞን ጤና መምሪያ የፕሮጀክቱ ተራፊ ንብረቶች ያስረከበበት ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም ክልሎች ደግሞ አለመረከባቸውን መግለጻቸው በንብረት ርክክቡ ላይ ግልጽ የሆነ አሰራር አለመኖሩን የሚያመለክት መሆኑ፤

298. በመሆኑም የጤና ተቋማት ግንባታ በተያዘላቸው ወጪ፣ጊዜና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቀው ለህብረተሰቡ ተፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችሉ ፣

በመሆኑም  የጤና ጥበቃ ሚ/ር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በጂአይዜድ አማካኝነት በተከናወኑ የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.11 <u>በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድን በተመለከተ</u>

**ከዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ የሚረዳ የአሰራር ሥርዐት መዘርጋቱና እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

**ቆሻሻን ለማስወገድ የተቀናጀ አሠራር ሥርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣**

1. ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ጉዳት እንዳያመጣ ለማምከንና ለማስወገድ የሚያስችለውን የተቀናጀ የአሰራር ስርዐት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ለዚህም መመሪያ ሊያወጣና ተገቢውን ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፡፡

2. ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ደረቅ፣ ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎች ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ እንደ አግባብነቱ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማስወገድ የሚያስችለውን ወጥ የሆነ የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ የአሰራር ስርአት አለመዘርጋቱ፤

**ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ**

3. ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ፣ በአመት ምን ያህል ቆሻሻ ከዩኒቨርሲቲው እንደሚያመነጭ እና በምን አይነት መንገድ መሰብሰብ፣ መያዝ፣ መጓጓዝና መወወገድ እንዳለበት የሚያሳይ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ አለማዘጋጀቱ፤

**እንደ የቆሻሻው አይነት እና ባህሪ ቆሻሻን የማስወገድ ግንዛቤ በሰራተኞች፣ በተማሪዎችና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ዘንድ እንዲኖር መደረጉን በተመለከተ**

4. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማለትም እንደ ቆሻሻው አይነት እና ባህሪ በመለየት የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝና የማስወገድ ስራን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖርና ስራው በዚሁ መሰረት እንዲከናወን ሊያደርግ ይገባል፡፡

5. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድን በተመለከተ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ተከትሎ ማለትም ደረቅ፣ ፈሳሽ እና አደገኛ

የሆኑትን ቆሻሻዎች በአይነትና በባህሪ በመለየት ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድን በተመለከተ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎችና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲኖር እና በዚሁ መሠረት ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ሁኔታ እንዲፈጠር አለማድረጉ፤

6. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት፣ የጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አራት ኪሎ ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲቲትዩት፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ፣ የንግድ ስራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት እና ደብረ-ዘይት የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ደረቅ፣ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎችን በአይነት እንዲሁም በባህሪ አደገኛ የሆኑትን፣ በመለየት እንዲወገዱ የማይማይደረግ መሆኑ፤

**በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች ከሚገኙ ቢሮዎች፣ ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤቶች እና ምግብ ቤቶች የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ማስወገድን በተመለከተ፣**

<u>**ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ማድረጉን በተመለከተ**</u>

7. እንደሚመነጩት የቆሻሻ አይነቶች ለማጠራቀሚያ፣ ለማጓጓዣ እና ማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሊሟሉ ይገባል።

8. ዩኒቨርሲቲው እንደሚመነጫቸው የቆሻሻ አይነቶች ለማጠራቀሚያ፣ ለማጓጓዣና ለማስወገጃ የሚያሰፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟሉ አለመሆኑ፤ሆነው አልተገኙም።

9. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የዩኒቨርሲቲው ቅርንጫፎች የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ፣የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲትትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክትና ደብረዘይት እንስሳትና ግብረና ኮሌጅ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማከማቻ ገንዳ የሌላቸው መሆኑ፤

<u>**ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሁኔታዎችን ያመቻቸ መሆኑን በተመለከተ**</u>

10. በዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ ቆሻሻዎችን እንደገና በመጠቀም ለኃይል፣ ለማዳበሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚቻልበትን ሁኔታ ሊመቻች ይገባል።

11. ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸው የሽንት ቤት ፍሳሾች፣ የምግብ ትርፍራፊዎች እና ሌሎችም እንደገና መልሶ በመጠቀም ለሃይል፣ ለማዳበሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉበት አሠራር ወጥ በሆነ መልኩ አለማመቻቸቱ፤

12. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በአካል ከታዩት የጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ት/ቤት፣የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ፣ የንግድ ስራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክትና ደብረ-ዘይት የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ለሃይል ለማዳበሪያና ለሌሎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ፤

<u>**የደረቅ ቆሻሻ ሲጓጓዝ እና ሲከማች እንዲሸፈን እና በወቅቱ እንዲነሳ ማድረጉን በተመለከተ**</u>

<u>**ቆሻሻዎች ሞልተው ሳይዝረከረኩ በየወቅቱ እንዲነሱ ማድረግን በተመለከተ**</u>

13. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻው በየወቅቱ መነሳቱ ሊረጋገጥ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ቆሻሻዎች የሚይዙ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሲንቀሳቀሱ እንዲሸፈኑ ሊያደረግ ይገባል፡፡

14. በዩኒቨርሲቲው ስር በሚገኙ እና በኦዲቱ በናሙና ከታዩ በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ ንግድ ስራ ኮሌጅ የሚመለከታቸው የስራ አካላት ቆሻሻ በየጊዜው እንደሚነሳ የገለጹ ቢሆንም፣ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ቆሻሻ የሚዝረከረክና በወቅቱ የማይነሳ ሲሆን፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክት ፣ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምነና ግብርና ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ ቆሻሻ በብዛት ሜዳ ላይ ተጥሎ ተዝረክርኮ የሚታይ መሆኑ፤ እንዲሁም ቆሻሻን የሚይዙ ማጠራቀሚያዎች ሲጓጓዙ ቆሻሻ እንዳይዝረከረክ፣ አከባቢን እንዳያበላሹና እንዳይበክሉ እንደሸፈኑ አለመደረጉ፤

15. የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ዋናው መርህ ቆሻሻን ከሚመነጭበት ቦታ ብዛቱን እና አደገኝነቱን መቀነስ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻው ከሚመነጭበት ቦታ የሚቀንስበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

16. ሆኖም አደገኛ ቆሻሻ ከሚመነጭበት ብዛቱንና አደገኛነቱን ለመቀነስ ተገቢው ጥረት አለመደረጉ፤

17. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ እና የንግድ ስራ ት/ቤት የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች በብዛት በክሊኒክ ውስጥ ተከማችተው መገኘታቸው፤፡

18. በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከምርምር ቤተ ሙከራዎች የሚወጡ ምርምር የተደረገባቸው ኬሚካሎች በመጋዘንና በቤተሙከራዎች ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

<u>ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ</u>

19. ከዩኒቨርሲቲው ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ ፍሳሽ እና ሌሎች ቆሻሻዎች ከመወገዳቸው በፊት በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

20. በኦዲቱ እንደታየው፤ ከዩኒቨርሲቲው ማስተማሪያ ምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ከመግባታቸው በፊት የያዙት ጎጂ ንጥረ ነገር በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ አስፈላጊው ጥንቃቄ የማይደረግ መሆኑ፤

21. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የተፈጥሮ ሳይንስና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ወደ ፍሳሽ ቱቦዎች የሚለቀቁ መሆኑ፤

<u>ከክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ሥፍራ የተዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ</u>

22. ዩኒቨርሲቲው ከክሊኒኮች ለሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ሥፍራ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

23. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የአዲስ አበባ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ደብረ ዘይት እንስሳትና ግብርና ኮሌጅ እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ ክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ስፍራ የሌላቸው መሆኑ፤

**<u>ከምግብ ቤቶች የሚመነጨትን ከምግብ ጋር የተያያዙ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከተ</u>**

24. ዩኒቨርሲቲው.ከምግብ ቤቶች የሚመነጩ ከምግብ ጋር የተያያዙ ደረቅ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ማለትም የሚሰበሰበውን ቆሻሻ በቀላሉ ለመለየት በሚያስችል መልኩ ሊሰበስብ፣ ሊያጓጉዝና ሊያስወገድ ይገባል።

25. ከምግብ ቤት የሚመነጩ ከምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ደረቅ ቆሻሻዎች ለብቻ ተለይተው የሚሰበሰቡ የሚጓጓዙ ቢሆኑም የሚከማቹትና የሚወገዱት ግን ለብቻ አከባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ አለመሆኑ፤

26. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ፣በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ እና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተረፈ ምግብ ከደረቅ ቆሻሻዎች ተለይተው እንዲከማቹና እንዲወገዱ የማይደረግ መሆኑ፤ በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ ፣በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ፣በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ፣በአቃቂ ሀገር ልማት ፕሮጀክተ ፣ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩትና የተፈጥሮ ሳይንሰ ኮሌጅ በምግብ ዝግጅት ወቅት የሚመነጩ ቆሻሻዎች ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ተለይተው እንዲከማቹ በማድረግ እንዲወገዱ የማይደረግ መሆኑ፤

**<u>የደረቅ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የተገነቡ እና አስፈላጊውን ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ</u>**

27. የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ደረጃን መሠረት በማድረግ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ሊገነቡ እና አስፈላጊው ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግላቸው ይገባል።

28. በናሙና በታዩት የዩኒቨርስቲው ግቢዎች ለደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተገነቡ ማቃጠያዎች አስፈላጊው ክትትል እና ጥገና በወቅቱ ባለመደረጉ በጉዳት ላይ መሆናቸውና የተወሰኑትም ደግሞ ማቃጠያ የሌላቸው መሆኑ፤

29. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ የደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ እና የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት አንስቲትዩት የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ያላቸው ቢሆንም፣ ደረጃውን ጠብቀው የተገነቡ አለመሆናቸው፤ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ እና አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲትትዩት የቆሻሻ ማቃጠያ ያልገነቡና ቆሻሻ ሜዳ ላያ የሚያቃጥሉ መሆኑ፤እንዲሁም ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ የቆሻሻ ማቃጠያው በር ተገንጥሎ የተጣለና የተሰባበረ፤ የኢትዮጵያ አርቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ማቃጠያው ግንድ የወደቀበትና የተሰባበረ መሆኑ፤ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተሰባበረና አስፈላጊው ክትትልና ጥገና ያልተደረገለት መሆኑ፤

<u>በዩኒቨርሲቲው የሚከረፋ ሽታ እንዳይኖር ማድረግን በተመለከተ</u>

30. የሚከረፋ ሽታ ምንጮች ላይ ቁጥጥር ሊያካሄድ ይገባል፡፡

31. የሚከረፋ ሽታ ምንጭ በአከባቢና በዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት በዩንቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ፤

32. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተማሪዎች መኖሪያ፣ከሆስፒታሉ ላበራቶሪ፣ ከቤተ ሙከራዎች፣ ከምግብ ቤቶችና ከሽንት ቤት የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በአንድ ላይ ተከማችተው በአከባቢ ላይ መጥፎ ሽታን የፈጠሩ መሆኑ፤ እንዲሁም ከሆስፒታሉ የሚወጡ አደገኛ ኢንፌክሽን ሊያስከትሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችና ተረፈ ምግቦች በገንዳ ላይ የሚጣሉ ሲሆኑ፣ በተማሪዎች መኖሪያ አከባቢ ላይ የሚከረፋ ሽታ የፈጠሩ መሆኑ፤

33. በተጨማሪም የኢትዮጵያ አርክቴቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ግቢው ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦ ከከተማው ዋና መስመር ጋር ያልተገናኘ በመሆኑ ፍሳሽ ቆሻሻው ግቢ ውስጥ እየፈሰሰ በአከባቢው

ላይ መጥፎ ሽታን የፈጠረ መሆኑ፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ተረፈ ምግብ ተከማችቶ ተጥሎ በአከባቢው ላይ መጥፎ ሽታ የፈጠረ መሆኑ፤

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን በመሰብሰብ፤በማከማቸት፤ በማጓጓዝና በማስወገድ ረገድ በታዩት የአሰራር ድክመቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው የኦዲት ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.11 የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችትና ሥርጭት አፈጻጸም

### የምርት ማሳደጊያዎች በጥራት፣ በወቅቱና በዝቅተኛ ዋጋ ለአርሶ አደሩ መቅረቡን በተመለከተ

34. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭ እና ሥርጭት ማዕከላት (ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) እና በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን)፣ መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ/ደጋጊና፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ጥራት ያላቸው የምርት ማሳደጊያዎች ወቅቱን ጠብቀው እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ የማይቀርቡ ሲሆን የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከማዳበሪያ ውጪ ላሉ ግብዓቶች የሚደረገው የዋጋ ተመን ወጥ በሆነ መልኩ የትርፍ መጠን (profit margin standard) አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማደረጉ፤

### በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት መከናወኑን በተመለከተ

36. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት ሊያከናውኑ ይገባል፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በበደሌ ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ በሚገኙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች፣ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሁለት ዩኒየኖች (አምቦና በቾ)፣አራት መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ እና ያያ ጀቦ) ፣ በአማራ ክልል በታዩ ሶስት ዩኒየኖች (መርከብ፣ፀሐይ እና ጎዛምን) እና 3 መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት(ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ከማዳበሪያ ውጪ ያሉ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው በመሆኑ ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የእነዚህን ድርጅቶች ዋጋ እና ጥራት ከግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ዋጋ ጋር ለማነጻጸር እንዲሁም የትኞቹ ግብዓቶች ገበያ ላይ ተፈላጊነት አላቸው የሚለውን ለመለየት የሚያስችል፣ በምርት ማሳደጊያዎች ላይ ወቅቱን የጠበቀ የገበያ ጥናት የማያደረግ መሆኑ፤

<u>*ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፡-*</u>

38. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሚከናወነው ዓመታዊ የምርት ማሳደጊያዎች ግዥ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን በፍላጎት ጥናት ላይ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

39. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት በደሌ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢያዎች አርሶ አደሮች፣ ኢንቬስተሮች፣ የእርሻ ልማቶች ወ.ዘ.ተ የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያዎች መጠን ያሳወቁበት (ፍላጎት የተሰበሰበበት) መረጃ ተጠናቅሮ ሳይያዝ ካለፈው አመት የግብዓት ፍላጎት መጠን በመነሳት ግዥ የሚፈጽሙ መሆኑ፤

40. እንዲሁም በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ/ደጋጊና፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) መህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ፍላጎት መጠን እና

አይነት በልማት ሰራተኛው አማካኝነት ከእያንዳንዱ አርሶ አደር ተሰብስቦ በየደረጃው በሚገኙ እና ከአመራር አካላት በተዋቀረ ኮሚቴ ጸድቆ በግብርና ጽ/ቤቶች እየተጠናቀረ ለግብርና ሚ/ር ተልኮ በዚሁ መሰረት ግዥው ሊፈጸም ሲገባው በነኚህ በናሙና በታዩት ማህበራት ሥር የሚገኙ 69 አርሶ አደሮች ተጠይቀው 35 አርሶ አደሮች የምርት ማሳደጊያዎችን ፍላጎት በየቀበሌው በሚገኙ ልማት ሰራተኞችም ሆነ በሌላ አካል አለመጠየቃቸውን መግለጻቸው፤

## <u>የምርት ማሳደጊያዎች መጠናቸውን ጠብቀው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ስለሚደረገው ቁጥጥርና ክትትልን በተመለከተ</u>

41. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ከክብደት በታች (Under Weight) የግብርና ግብዓት ከወደብ ወደ መሀል አገር እንዳይጓጓዝ በተለይም ተጠቃሚው ወደ ሆነው አርሶ አደር በቀጥታ እንዳይደርስ እንዲሁም ሾፌሩ ጭነት በጫነበትና ዕቃውን ወይም ጭነቱን ባስረከበበት ሰነዶች መካከል የባከነ ንብረት ወይም ልዩነት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

42. ከላይ በተጠቀሱት እና በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና መሰረታዊ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ከክብደት በታች (Under Weight) 50 ኪ.ግ. መሆን ሲገባቸው የማዳበሪያው ከረጢት ሳይፈታ ከ44- 49 ኪ.ግ. የሆኑ የምርት ማሳደጊያዎች ለአርሶ አደሮች የሚደርሱ መሆኑ፤ በመጋዘን ውስጥ ለሚከሰቱ የግብዓቶች ፍሳሽ (ጉድለት) መጠን በየአመቱ ተጠናቅሮ በመረጃነት አለመያዙ፤ እንዲሁም ከክብደት በታች የሆኑ ማዳበሪያዎች ክትትል እየተደረገባቸው ወዲያውኑ ለሌላ ብክነት ሳይጋለጡ ሪባግ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

43. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ16 ሐምሌ 2005 ዓ.ም ከግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት በተጻፈው ደብዳቤ ሾፌሮች 9,381.56 ብር የማዳበሪያ ጉድለት ያለባቸው ስለመሆኑ ለትራንስፖርት ዳይሬክቶሬቱ የተጻፈ ደብዳቤ እና በ01/07/05 ዓ.ም

የኮንቦልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ሾፌሮች ያጎደሉትን 1,214.86 ከድርጅቱ ሂሳብ የቀነሰ መሆኑን ቢያመለክትም ድርጅቱ ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉ፤

**<u>በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች የሚቀመጡበትን ሥርዓት በተመለከተ</u>**

44. በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘን ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል፣ የመጋዘኑን ንጽህና ለመጠበቅ እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ ሊደረደሩ ፣ በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰቡ ግብዓቶች በተለየ ሥፍራ ፣ ሳይበላሹ እና ሳይጎዱ የሚቀመጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም በሚወጡበት ወቅት አወጣጡ በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ የገባው ቀድሞ ሊወጣ ይገባል፡፡

45. በናሙና ተመርጠው በታዩት በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል የሚገኙ ሰባት መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በመጋዘኖች ውስጥ የተከማቹ የምርት ማሳደጊያዎች በመጋዘኖቹ ተዘዋውሮ ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና ለአወጣጥ አመቺ በሆነ መንገድ የተደረደሩ አለመሆኑ፣ እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ ሽያጭና ሥርጭት ጣቢዎች፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ መርከብ፣ ፀሐይ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) በመጋዘኖች በጥራት ችግር ምክንያት የተሰበሰቡ ግብዓቶች በተለየ ሥፍራ እንዲቀመጡ አለመደረጉ፤ እና ከላይ በተጠቀሱት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ግብዓቶቹ በሚወጡበት ወቅት አወጣጣቸው በረድፍ በረድፍ ሆኖ ቀድሞ የገባው ቀድሞ እንዲወጣ አለመደረጉ፤

**<u>የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘን አያያዝ፣ ጥራት እና የመገልገያ መሳሪያዎችን በተመለከተ</u>**

46. የምርት ማሳደጊያዎች መጋዘኖች ሕንጻ አሰራር ጥራታቸውን የጠበቁ ሆነው በየጊዜውም ክትትል ተደርጎ ተገቢው ጥገና ሊደረግላቸው እና

በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የመገልገያ መሳሪያዎችም በመጋዘኖቹ ውስጥ ተሟልተው ሊገኙ እንዲሁም የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ ሁኔታ በሚመለከተው ኃላፊ በየጊዜው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

47. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሥር በሚገኙ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከአራቱ(ነቀምት፣ በደሌ፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች በሶስቱ (ነቀምት፣ በደሌ እና ባህር ዳር) ጣቢያዎች ፣ ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ ፀሐይ፣ መርከብ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ከግብርና ግብአቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንብረቶች(የማዳበሪያ ከረጢቶች፣ ጀሪካን፣ ካርቶኖች፣ በርሜሎች፣ ማገዶዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ ሌሎች ግብዓቶች ተቀላቅለው (ብረት ነክ/ቢቢኤም የእርሻ መሳሪያ እና ማዳበሪያዎች…) በክምችት መጋዘን ውስጥ ተጣበው እንደተቀመጡ እና ንብረቶቹም ተሸጠው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም መወገድ ያለባቸው እንዲወገዱ አለመደረጉ፤ እንዲሁም በመጋዘን ውስጥ የሚያስፈልጉ የመገልገያ መሳሪያዎች አለመሟላታቸው፤ እና የመጋዘን ሕንጻ አሰራር ጥራቱ የተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው ክትትል በማድረግ ተገቢው ጥገና እንደማይደረግለት መሆኑ፤

## <u>የሚወገዱ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸውን የግብርና ግብዓቶች አያያዝ በተመለከተ</u>

48. በማንኛውም ምክንያት በማዕከል እና በሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት መጋዘኖች ሊወገዱ የሚገባቸው፣ ለተጠቃሚ ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብአቶች ዝርዝር ሊያዝና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

49. በኦሮሚያ እና አማራ ክልል በሚገኙ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘኖች የሚወገዱ፣ ለተጠቃሚው ቀርበው እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም

አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው የግብርና ግብዓቶች ዝርዝር መረጃ ተጠናቅሮ እንዲያዝ እና ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ እንዲሰጥበት አለመደረጉ፤

<u>ድርጅቱ ፣ የግብርና ሚ/ር እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ማዕከላት የሚያካሂዱዋቸውን የሽያጭ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ</u>

50. የግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት እና የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የሽያጭ ጣቢያዎች የሚያካሂዱዋቸውን የግብዓቶች ሽያጭ ከብክነት እና ከምዝበራ ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

51. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ የድርጅቱ የሽያጭ ጣቢያዎች በሽያጭ ሰራተኞች አላስፈላጊ ብክነት እና ምዝበራ እንዳይፈጸም ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት በስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉን መገንዘብ መቻሉ፤ለማሳያ፡- በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የሽያጭ ጣቢያዎች የሚሰሩትን ሥራ እንዲሁም የሚሸጡበትን ሥፍራ በመቆጣጠር ለይቶ አለማወቃቸውን፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአማራ ክልል በናሙና ተመርጠው በታዩ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት ያለ ዋስትና ለአርሶ አደሮች የግብዓት ማከማቻ መጋዘን እና ገንዘብ የመሰብሰቡን ሂደት እንዲያስተዳድሩ እየተደረገ አንድ አርሶ አደር እስከ ብር 1,626,033.62 የመዘበረ ቢሆንም ያለው ንብረት ከዚህ ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ በእስር እንዲቀጣ እና ወደፊት ንብረት ሲያፈራ እንዲከፍል በሚል ውሳኔ የተሰጥበት ሁኔታ፤

<u>የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭትና ክምችት አፈጻጸም ሪፖርትን በተመለከተ</u>

52. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና በሌሎች አስፈጻሚዎች የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የግብዓት ግዥ፣ ክምችት፣ ሥርጭት እና ሽያጭ እንቅስቃሴ በወር፣ በሩብ ፣ በግማሽ አመትና በአመት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ግብዓቱ አይነት በቀን

ወይም በሳምንት ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡

53. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት በሚገኙ ማከፋፈያ መጋዘኖች ሥለተደረገው ሽያጭ በማጠቃለል ሊሸጥ የታቀደው ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሳይሆን ሽያጭ በብዛት በሚከናወንበት ወቅት ብቻ የተሸጠውን መጠን የሚያሳውቁ መሆኑን እንጂ ቀጣይነት ባለው መልኩ በወር፣ በሩብ፣ በግማሽ አመት እና በአመት ሪፖርት የማያዘጋጁ መሆኑ፤

## <u>የምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑን በተመለከተ</u>

54. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች የሥርጭት ፕሮግራም ሊዘጋጅ በተዘጋጀውም የሥርጭት ፕሮግራም መሠረትና ተጠቃሚዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ በመመርኮዝ የግብርና ግብዓት ሥርጭት ሊፈጸም፣ የሚያንጉዝበትን የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የጣቢያዎችን ዝርዝር የያዘ የስርጭት ፕሮግራም ተጠናቅሮ ሊያዝ እና ሥምሪት የወሰደው ሾፌርም በተሰጠው ስምሪት መሰረት ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ በተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

55. በናሙና በታዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ፣በኦሮሚያ እና አማራ ክልል የሚገኙ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት የሥርጭት ጊዜ፣ መጠንና የያዘ የሥርጭት ፕሮግራም እንደማያዘጋጁ እና መረጃዎቹንም አጠናቅረው የማይዙ መሆኑን፣ እንዲሁም በምስራቅ ጮራ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር አንድ መኪና ዳፕ ማዳበሪያ ተጠይቆ አንድ መኪና ዩሪያ ማዳበሪያ እንዲረከቡ መደረጉን ፣ ከላይ በተጠቀሱት እና በናሙና በታዩት የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት የምርት ማሳደጊያዎች ከጠየቁት ቁጥር በላይ ወይም በታች የሚላክላቸው መሆኑን ለኦዲቱ ቡድኑ መግለጻቸው፤

56. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በሀገር ውስጥ ለሚደረገው የከባድ መኪና ተሽከርካሪዎች ጉዞ ከመነሻው እስከ መድረሻ ይፈጃል ተብሎ የተወሰነው የጉዞ ሰሌዳ መመዘኛ (standard) ተዘጋጅቶ ተሽከርካሪው መድረሱን እና የባከነ ጊዜ አለመኖሩን ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

**የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች በስርጭት አውታሮች፣ በአከባቢ እና በገበያ ሁኔታ የሚለዩ መሆናቸውን በተመለከተ**

57. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ መለየት ይኖርበታል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች እንዲሁም በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በታዩት ባህር ዳር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎንደር፣ አምቦ፣ ወሊሶ፣ በደሌ እና ነቀምት የሚገኙ የግብርና እና የህብረት ሥራ ማህበራት ጽ/ቤቶች ይሸጣል ተብሎ የተገመተው ግብዓት በሥርጭት አውታሮች (Distribution Channels) እና በገበያ ሁኔታ/ በአከባቢና በመሳሰሉት/ የሚለዩበት ሁኔታ ስለመኖሩ ቢገልጹም የምርት ማሳደጊያዎቹ ዓይነት ዝርዝር እና የሚፈለጉበት ቦታ በመረጃነት ተጠናቅሮ አለመያዙ/አለመገኘቱ፤

**የምርት ማሳደጊያዎችን ማስተዋወቅ እና የሽያጭ አውታሮችን ማስፋፋትን በተመለከተ**

59. የምርት ማሳደጊያዎች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት የሚገኙ ግብዓቶች ወደ ደንበኛው ቀርበው ሊተዋወቁ፣ በምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ሥርጭት እና ክምችት ዙሪያ ለተሰማሩ ሠራተኞች ሙያቸውን ለማሻሻል እንዲችሉ ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው፣ ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት ያሉበትን ሥፍራ ሊጠቁሙ የሚችሉ ማስታወቂያዎች ሊኖሩ እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ኢኮኖሚያዊ የማከፋፈያና የሽያጭ አውታሮችን ሊዘርጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

60. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት ዩኒየኖች (አምቦ፣ በቾ፣ መርከብ፣ ፀሃይ እና ጎዛምን) እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት (ሙቱሉ፣ ደጋጊና፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) የግብዓቶች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት በክምችት በሚገኙ የምርት ማሳደጊያዎች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ የማይሰራ መሆኑ፣

61. በግብዓት ማከማቻ መጋዘን ለሚሰሩ ሰራተኞች የምርት ማሳደጊያዎች አያያዝ እና አጠቃቀም ሁኔታን በተመለከተ ሥልጠና አለመሰጠቱ፤

62. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና ከታዩት አራቱ ጣቢያዎች በሁለቱ (በባህር ዳር እና በበደሌ) ፣በናሙና ተመርጠው ከታዩት አምስት ዩኒየኖች በአንዱ (ጸሃይ) እና የህብረት ሥራ ማህበራት ( ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ) ሙሉ በሙሉ የጣቢያዎቹን ሥም የያዙ ማስታወቂያዎች ወይም ምልክቶች የሌሉ ሲሆን በቀሪዎቹ ጣቢያዎች ደግሞ የቆዩ እና በደንብ የማይታዩ እና የማይነበቡ መሆኑ፤

63. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በየጊዜው ልዩ ልዩ የሽያጭ ሥልቶችን በመንደፍ የሽያጭ መጠኑ እንዲጨምር እና የድርጅቱ ትርፋማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ የሽያጭ አውታሮችን ያልዘረጋና በየጊዜው እንዲሻሻሉ አለማድረጉ፤ ለምሳሌ በ2004 እና 2005 በጀት ዓመታት የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መሰረት ድርጅቱ በ2004 ዓ.ም ያስገኘው ትርፍ 35,378,193 ሲሆን በ2005 ዓ.ም ግን 16,126,271.34 መሆኑ፤

**<u>የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች ዱቤ ሽያጭን በተመለከተ</u>**

64. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና የህብረት ሥራ ኤጀንሲ የተፈቀደውን የክሬዲት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በአመት ውስጥ በዱቤ ሊሸጥ የታቀደው የግብዓት ዋጋን ሊተምኑና ለመሰብሰብም ፕሮግራም ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

65. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከ2004- 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በድርጅቱ የክሬዲት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፤ በአማራ ክልል በ15 ዩኒየኖች አማካኝነት ለአርሶ አደሮች በዱቤ የተሰራጨ እና ያልተሰበሰበ የምርት ማሳደጊያዎች ብር 706,792,927.56 መሆኑን መረጃ ቢያመለክትም ይህን ብድር የግብርና ጽ/ቤቶች፣ የህብረት ሥራ ጽ/ቤቶች፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት በቅንጅት ወቅቱን ጠብቀው የማያስመልሱ መሆኑ፤

<u>ለሚሸጡ የምርት ማሳደጊያዎች የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ብዛት መመዘኛ ደረጃ መዘጋጀቱን በተመለከተ</u>

66. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ ዩኒየኖች እና መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ… ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) ሊያዘጋጁና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ሊዘረጉና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ጣቢያዎች እንዲሁም በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በታዩት ባህር ዳር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎንደር፣ አምቦ፣ ወሊሶ፣ በደሌ እና ነቀምት የሚገኙ ዩኒየኖች እና የህብረት ሥራ ማህበራት ለሚሸጡ የግብርና ግብዓቶች ወይም ዕቃዎች፤ የፈሳሽ፣ የስባሪ ወይም የብልሽት ወዘተ… ብዛት መመዘኛ ደረጃ (Standard) አለመዘጋጀቱን እና ከዚህ ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ወይም የቅጣት አሠራር ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤ እንዲሁም በነዚህ መጋዘኖች የሚገኙ ሰራተኞችም ለተረከቧቸው ግብዓቶች ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ የሚደረጉ መሆኑ፤

<u>ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ ግብዓቶች ትኩረት መስጠትን በተመለከተ</u>

68. ከማዳበሪያ ውጭ ላሉ የግብርና ግብዓቶች ትኩረት ሊሰጥ እንዲሁም ሽያጭና ሥርጭትን አስመልክቶ የማዕከሉ ሰራተኞች መፈጸም ስለሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡

69. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በናሙና በታዩት አራቱ (በደሴ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች ያሉት ግብዓቶች ውስን መሆናቸውን እና የላብራቶሪ እቃዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች የተለያዩ የጓሮ አተክልቶች፣ የእንስሳት መደሃኒቶች፣ የአበባ ማዳበሪያዎች … በጣቢያዎቹ የሌሉ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት በተካሄደው የመስክ ጉብኝት ለማረጋገጥ መቻሉ፤፤ እንዲሁም በነዚህ አከባቢዎች የሚገኙ ዩኒየኖች ፣ ማህበራት፣ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች እና የግብርና ጽ/ቤቶችም ሌሎች ግብዓቶች በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እንደሚቀርቡ የማያውቁ መሆኑ፤

## የምርት ማሳደጊያዎች እጅ በእጅ ሽያጭ ባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ

70. በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ በተከሄደበት ጣቢያዎች፣ ዩኒየኖች እና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት ባንክ ካለ በዕለቱ እና ባንክ ከሌለ ሠራተኛው የሰበሰበውን ጥሬ ገንዘብ በካዝና በማስቀመጥ በሶስት ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ባንክ በመሄድ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

71. ሆኖም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የሽያጭና ሥርጭት ማዕከላት(በደሴ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን በዕለቱ ባንክ ገቢ እንደሚደረግ ቢገለጽም በየቀኑ የተሰበሰበው መረጃ ባንክ ከገባበት(slip) ጋር ተነጻጽሮ ለማቅረብ አለመቻሉ፤

72. በበቾ፣ አምቦ፣ መርከብ፣ ጸሃይ እና ጎዛምን ዩኒየኖች እንዲሁም ሙቱሉ፣ ቁርሲቲ አረዳ ሌቃ፣ አዋሽ ቡኔ፣ ያያ ጀቦ፣ ምስራቅ ጮራ፣ መራዊ እና ወንቃ መሰረታዊ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ሲከናወን የተሰበሰበውን ገንዘብ እስከ አንድ ወር ድረስ በአርሶ አደሩ እጅ የሚቆይ መሆኑ፤

## የምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት፣ ክምችት እና ስርጭት በቅንጅት መፈጸሙን በተመለከተ

73. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የግብዓት አቅርቦት፣ ክምችት እና ሥርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ ኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አራቱ (በደሴ፣ ነቀምት፣ ባህር ዳር እና ወረታ) ጣቢያዎች ከግብርና ጽ/ቤቶች እና የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት እየሰራ አለመሆኑ፣ ከማዳበሪያዎች እና ፀረ-አረሞች ውጪ በሌሎች ግብዓቶች ላይ ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከንግድ ባንክ ጋር ከሲፒኦ ጋር በተያያዘ ቶሎ ወደ ድርጅቱ አካውንት የማዘዋወሩን ሥርዓት ለማፋጠን በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፤፡ ይህም አንድ አንዴ ድርጅቱ የዋጋ ለውጥ በሚያደርግበት ወቅት ባለሀብቶቹ ያስገቡት ገንዘብ ወደ ድርጅቱ ሂሳብ ቁጥር ባለመተላለፉ በባለሀብቶቹ ላይ ተጽኖ ስለሚያሳድር ከድርጅቱ እምነት እንዲያጡ ማድረጉ፤

<u>**የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የሚያጓጉዙ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ**</u>

75. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪ መኪናዎችን ኢኮኖሚያዊ በሆነ እና ውጤት በሚያስገኙበት ሁኔታ ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ ከ2004- 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ አብዛኛው የድርጅቱ የጭነት ተሽከርካሪዎች በኪሳራ እንዲቀሳቀሱ መደረጉ፤ ይህም በ2005 ዓ.ም 15 ተሽከርካሪዎች ብር 1,770,341.96 እና በ2004 ዓ.ም ብር 1,855,825.22 ኪሳራ ያሳዩ መሆኑ፤ እንዲሁም መወገድ የሚገባቸው 12 ተሽከርካሪዎች እና 13 ተሳቢ በየካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲወገዱ የቀረቡ ቢሆንም እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ያልተወገዱ መሆኑ፤ ከዚህ በተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የደርሶ መልስ ጭነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤ እንዲሁም በድርጅቱ ተሽከርካሪዎች ላይ የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ከሌሎች የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ጋር በማቀናጀት በግብዓት ማመላለስ የጨረታ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ አለመደረጉ፤

77. በመሆኑም የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት

እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በግዢ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.12 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ተግባር አፈፃፀምን በተመለከተ

<u>የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ሰነድ እንዲሁም የኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፣</u>

78. ባለስልጣኑ የተቋቋመበትን ዓላማዎች መሰረት ያደረገ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ፖሊሲና ስትራቴጂውንም ለማስፈፀምየሚያስችሉ ሰነዱን መሰረት ያደረጉ ማንዋሎች/መመሪያዎች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ አፈጻጸሙም በተቋም ደረጃ በየአመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡

79. ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረፅ በግንቦት 2002 ዓ.ም. እንዲፀድቅ በማድረግ፤ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂውን በአግባቡ ለማስፈፀም እንዲቻል ሰነዱን መሰረት ያደረጉ የአሰራር ማንዋሎች/መመሪያዎች/ ለማዘጋጀት እንዲሁም ከኦዲት ጋር ተያያዥ የሆኑ የተለያዩ ስልጠናዎች ለመስጠት ጠቅላላ ዋጋው ብር 2,670,439.42 የሆነና ዝግጅቱ በመጋቢት 2004 ዓ.ም. የሚጠናቀቅ የታክስ ኦዲት ማኔጅመንት እና ማንዋል ዝግጅት ፕሮጀክት በመስከረም 2004 ዓ.ም. ያፀደቀ ቢሆንም፣ የታክስ ኦዲት አፈፃፀም መመሪያ/ማንዋል/፣ የታክስ ኦዲት ጋይድ ላይን፣ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር መመሪያ፣ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ጋይድ ላይን እንዲሁም የኢንቨስትጌሽን ኦዲት ማንዋሎች ስራ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ተዘጋጅቶ አለመጠናቀቁና ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ፤

80. በመሆኑም ቅ/ጽ/ቤቶች በቀድሞ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እየተባለ በሚጠራበት ወቅት (በ1998 ዓ.ም.) በተዘጋጀ እና ወቅታዊ ባልተደረገ የኦዲት ማንዋሎች ከተለያዩ የግብር አዋጆችና ደንቦች ጋር በማያያዝ እየሰሩ የሚገኙ መሆኑን፤በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት፣ የምዕራብ እና ምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች መረጋገጡ፤

**የታክስ ኦዲት ተግባር ያስገኘውን ፋይዳ መገምገምን በተመለከተ፣**

81. የታክስ ኦዲት ያስገኘውን አስተዋፅኦ ከሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት በመለየት ሊለካ በሚችል መልኩ ለማቀድ፣ አፈፃፀሙንም ለመገምገምና ለማሻሻል የሚያስችል የታክስ ኦዲት መርሆዎችን/ tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት ሊዘጋጅና እያንዳንዱ የኦዲት ስራ እንዲሁም አጠቃላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የኦዲት ተግባር ሊገመገም ወይም ሊመዘን ይገባል፡፡

82. በባለስልጣን መ/ቤቱ አገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መነሻ በማድረግ በተዘጋጀው የ2003-2007 በጀት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በዕቅድ ዘመኑ ተግባራዊ ከሚያደርጋቸው ግቦች እና ስትራቴጂክ እርምጃዎች መካከል በፈቃደኝነት የሚከፈለውን የገቢ ድርሻ በየዓመቱ በ7% እንደሚያድግ እና ሕገ-ወጥ ንግድና ታክስ ማጭበርበርን በተመለከተ ደግሞ በየዓመቱ በ10% እንደሚቀንስ ታቅዷል፡፡

83. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጁት የ2004 እና የ2005 በጀት ዓመታት ተቋማዊ የታክስ ኦዲት ዕቅድ ሰነዶች በተከለሱበት ወቅት እንደ ተቋም በየበጀት ዓመታቱ ከተያዘው የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ዕቅድ ግብ ውስጥ የኦዲት ውጤታማነት መለኪያዎች ተብለው የተቀመጡት፡- ተቋሙ በየግብር ዘመኑ እደርስበታለሁ ብሎ በውጤት ተኮር ዕቅድ የያዘውን የገንዘብ መጠን ግብ ለማሳካት በኦዲት የሚገኝ ተጨማሪ ግብር/ታክስ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ማድረስ፣ በአንድ ኦዲተር የሚገኘውን ተጨማሪ ግብር/ታክስ ማሳደግ፣ ከአንድ ማህደር የሚገኘውን ተጨማሪ ግብር/ታክስ እንዲያድግ አድርጐ መፈፀም እና በኦዲት የተገኙ ተጨማሪ ግብርና ታክስ ሙሉ በሙሉ እንዲሰበሰቡ ማድረግ የሚሉት ብቻ መሆናቸው፤

84. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች  በቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባርን የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፈል ከማድረግ አንፃር በዕቅድ ዘመኑ ከተቀመጡት ዒላማዎች (Targets) እና

የአፈጻጸም መለኪያዎች አንፃር እንደማይታቀድ፤ ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት/ፋይዳም የማይገመገም መሆኑ፤

**የግብር/ታክስ ኦዲት ስራዎች ዕቅድ እና አፈፃፀምን በተመለከተ፣**

85. በታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂው ላይ የተቀመጠውን የታክስ ኦዲት መርህ /tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የረዥም፣ መካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ተቋማዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ እና ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል። ቅ/ጽ/ቤቶችም የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ ሊያዘጋጁና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል። የዕቅድ አፈጻጸሙም በየወቅቱ ሊገመገም ይገባል። በግምገማው ውጤት መሰረትም ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

86. በኦዲቱ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂውን መሰረት ያደረገ አንድ ወጥ ተቋማዊ ዕቅድ አሳታፊ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ የተደረገ ቢሆንም፣ ቅ/ጽ/ቤቶች የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃ በተከለሰበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት በተቋም ደረጃ የተቀመጠው ዕቅድ ከ848 ግብር ከፋዮች ውስጥ 544(64%) ማህደራትን አጠቃላይ ኦዲት፣ ልዩ ኦዲት እና ውስን ኦዲት ማድረግ ሲሆን፣ ነገር ግን በቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት ዕቅድ ላይ 213 አጠቃላይ ኦዲት ብቻ ታቅዶ 190(22%) ብቻ ማከናወኑ፤
- ✓ በተጨማሪም በቅ/ጽ/ቤቱ የህግ ማስከበር እና የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደቶች እንደየቅደም ተከተላቸው 2 ልዩ ኦዲት እና 158 የዴስክ ኦዲት የተከናወነ ሲሆን፣ በጠቅላላው በበጀት ዓመቱ የ350 ግብር ከፋይ ማህደራት ኦዲት የተከናወነ

መሆኑ፤ ይህም በቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኙት ግብር ከፋዮች ውስጥ 41% ብቻ የሸፈነ መሆኑ፣

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ በተቋም ደረጃ በቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኙ 864 ግብር ከፋዮች ውስጥ የ835(97%) ማህደራትን በአጠቃላይ ኦዲት፣ ልዩ ኦዲት እና ውስን ኦዲት ለማድረግ ቢሆንም፣ በቅ/ጽ/ቤቱ ዕቅድ ላይ ግን 170 አጠቃላይ ኦዲት፣ 10 ልዩ ኦዲት እና 480 የዴስክ ኦዲት በድምሩ 660 የግብር ከፋይ ማህደራትን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 149 አጠቃላይ ኦዲት፣ 5 ልዩ ኦዲት እና 331 የዴስክ ኦዲት በድምሩ 485 የግብር ከፋይ ማህደራት ማለትም 56 በመቶውን ብቻ ኦዲት ያከናወነ መሆኑ፣
- ✓ ኦዲት የሚደረገውን የግብር ዘመን በተመለከተ ደግሞ የዋናው መ/ቤት ዕቅድ መሰረት ያደረገው የአንድ ግብር ከፋይ ኦዲት የሁለት ግብር ዘመንን ቢሆንም፣ በቅ/ጽ/ቤቱ ዕቅድ የአራት ግብር ዘመንን በሁለት ኦዲተር ኦዲት ለማድረግ የታቀደና አፈጻጸሙ ግን እስከ ስድስት የግብር ዘመን የሚሸፍን መሆኑ፤

87. ቅ/ጽ/ቤቶች እንደ አንድ ተቋም የተዘጋጀውን ወጥ የሆነ የኦዲት ዕቅድ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑ፤

**<u>ኦዲቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን እና በኦዲት ዓይነቱ የተያዘ የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

88. የግብር ከፋዮች ደረጃን፣ የኦዲት አይነት እንዲሁም የንግዱን እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ የኦዲት የጊዜ ተመን/ ስታንደርድ/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለኦዲት የተመሩ የግብር ከፋይ ማህደራት/ፋይሎች/ ኦዲት በተቀመጠው የጊዜ ዕቅድ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ኦዲትም በተቀመጠው የኦዲት ጊዜ ተመን ውስጥ ስለመከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

89. በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣን መ/ቤቱ ለእያንዳንዱ የኦዲት አይነት እንዲሁም በየቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ ግብር ከፋዮችን ደረጃ በመለየት ስታንደርድ ያዘጋጀ ቢሆንም በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የምዕራብና የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች እያንዳንዱ የተጠናቀቀ ኦዲት የወሰደው ጊዜ፣

የተከናወነው የኦዲት አይነት እና ሌሎች መረጃዎችን ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ በማጠናቀር በስራ ሂደቱ እንዲያዝ የሚደረግ ስለመሆኑ እና የኦዲት ቡድን አስተባባሪውም ሆነ የስራ ሂደቱ እያንዳንዱ ኦዲት በታቀደለት ወቅት እና የጊዜ ተመን እየተከናወነ ስለመሆኑ በየወቅቱ ክትትል በማድረግና አፈፃፀማቸውን በመገምገም ተገቢውን እርምጃ የሚወሰድ ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

90. በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከቀረቡት መረጃዎች እና በናሙና ከታዩት የግብር ከፋይ የኦዲት ፋይሎች ኦዲቱን ለመጀመር የሚፃፈውን የደብዳቤ ቀን እና የኦዲት ውሳኔው የመጣበትን ቀን በማነፃፀር በቅ/ጽ/ቤቱ ከተከናወኑ ኦዲቶች ውስጥ አንዳንድ አጠቃላይ ኦዲቶች በዕቅድ ከተያዘው ጊዜ በላይ ከ34-358 ቀናት የወሰዱ መሆኑን ለመረዳት መቻሉ፤

<u>**ለኦዲት የሚመረጡት ግብር ከፋዮች ግልጽነት ባለው መንገድ እንዲመረጡ ማድረግን በተመለከተ፣**</u>

**ሀ. የግብር ከፋይ ማህደራትን ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

*91.* የግብርና ታክስ ኦዲት ስራዎችን ተገቢና ምቹ በሆነ መልክ ለማደራጀት፣ ለመመደብና ለመገምገም እንዲሁም ግብር ከፋዩን በእኩልነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የአሰራር ስርዓት በአግባቡና ወጥ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ስለመደረጉ በዋና መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡

92. ግብር ከፋዮች ለኦዲት የሚመረጡበት ሂደት የታክስ ኦዲትና የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት ያደረገ እንዲሆን በደብዳቤ ቁጥር 1-0/7/1 ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. ከዋናው ዳይሬክተር መመሪያ የተላለፈ ሲሆን መመሪያውም የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ የስጋት ደረጃ ለመለየት የሚያስችሉ አራት የስጋት መመዘኛ መስፈርቶችን ያካተተ ሆኖ በየቅ/ጽ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ቢያንስ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር ማህደራት እንደ ስጋት ደረጃቸው መመረጥ እንዳለባቸው መገለጹ፤፣

የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በመመሪያው መሰረት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ኮሚቴውን በማቋቋም የግብር ከፋይ ማህደራትን በመምረጥ የሚሰራ መሆኑ፤

93. ይሁን እንጂ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከተለያዩ ክፍሎች 5 ሰዎች ተመድበው በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የሚደረጉ ማህደራትን በማንዋል መርጠው ለኦዲት አስተላልፈው ኦዲት የተደረገ ሲሆን፣ በ2005 በጀት ዓመት ግን የግብር ከፋይ መረጃ የማጥራት ስራ ተጠናክሮ ተሰርቶ በሲግታስ መምረጫ መሰረት በሲስተም ብቻ እንዲሰራ በመባሉ ከዚህ ወቅት ጀምሮ ይህን ስራ የሚሰራ ኮሚቴ የሌለ መሆኑ፣ ነገር ግን በጥቅምት 2006 ዓ.ም ከዋናው መ/ቤቱ በተላለፈ መመሪያ መሰረት ኮሚቴው በቅ/ጽ/ቤቱ በድጋሚ በመቋቋም ላይ እንደሚገኝ መገለጹ፤፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግን በተለያዩ ስብሰባዎች እና በጥናት ሰነዶች ላይ የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫ ተብለው ከተለዩት አንዱ በየቅ/ጽ/ቤቶች የሚቋቋመው ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን የሚመርጠው ኮሚቴ ነው በመባሉ ምክንያት ቅ/ጽ/ቤቱ የመራጭ ኮሚቴውን አለማቋቋሙ

94. በተቋቋመው አካል የሚከናወነውን የግብር ከፋይ ማህደራትን ለታክስ ኦዲት የመምረጥ ሂደት ለመምራት የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የመራጭ ኮሚቴውን ተግባርና ሃላፊነት በተመለከተ ቅ/ጽ/ቤቱ፣ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና በስጋት ስራ አመራር መሰረት የ2003 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና በቀጣይ መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ባዘጋጀው የግምገማ ሰነድ ላይ ያስቀመጠ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግን ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን ለመምረጥ የተቋቋመ ኮሚቴ ባለመኖሩ ኮሚቴው የሚሰራበት የአሰራር መመሪያ አለመዘጋጀቱ፤

95. በመሆኑም በቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት/ኦዲት ኬዝ/ የመምረጥ ተግባር ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው እንዲሁም ወጥ በሆነ መልኩ እየተከናወነ አለመሆኑ፤

**ለ. ለታክስ ኦዲት የመምረጫ መስፈርቶች የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተጠናቅረው የሚያዙና የግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ የሚለይ መሆኑን በተመለከተ፣**

96. የግብር ከፋዮች መረጃ (profile) እንዲሁም በታክስ ኦዲትና ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂው መሰረት ለታክስ ኦዲት የመምረጫ መስፈርቶች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሰባሰብ አጠናቅሮ በመያዝ የስጋት መምረጫ መስፈርቶቹን አቀናጅቶና አዋህዶ ጥቅም ላይ በማዋል የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ስጋት ደረጃ በማለት በግልጽ በማስቀመጥ በየበጀት ዓመቱ ደረጃ እንዲይዙ ሊደረግ እና በየበጀት ዓመቱ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮች ሊመረጡ ይገባል፡፡

97. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የከፍተኛ ግብር ከፋዮችን መረጃ በማጠናቀር እና መረጃውን በመተንተን በስጋት ደረጃ የመለየት ሥራዎችን እንደሚሰራ የገለጸ ሲሆን የምስራቅ እና ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በቅ/ጽ/ቤቶቹ የመራጭ ኮሚቴ ያልተቋቋመ በመሆኑ መረጃዎች በኮሚቴው ተደራጅተው የተቀመጡበት ሁኔታ አለመኖሩ፤ ቀደም ሲል ኦዲት የሚደረጉ ማህደራት በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት የሚከናወን መሆኑን፣ ነገር ግን በ2005 በጀት ዓመት የግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ለመወሰን እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው በመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት በተለዩት እና በተላኩት የመረጃ ማስተካከያ ነጥቦች ላይ ሙሉ በሙሉ የመረጃ ማጥራት ስራ ተሰርቶ መጠናቀቁን የገለጹ ቢሆንም በቅ/ጽ/ቤቶቹ የቀረቡ መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

**በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት፤**

- በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲደረጉ የመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸው እና በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት አስተያየት ተሰጥቶባቸው

ለየኦዲት ቡድኑ የተደለደሉ የ206 ግብር ከፋዮች ዝርዝር ቢኖርም፣ ከግብር ከፋዮቹ ስም ዝርዝር እና የግብር ከፋይ መለያ ውጭ የተሰጣቸው የስጋት ደረጃ አለመጠቀሱ፣

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት 190 ግብር ከፋዮች ውስጥ በስጋት መስፈርት መሰረት የተመረጡት 100 ግብር ከፋዮች ብቻ መሆናቸውንና ቀሪዎቹ 90 ግብር ከፋዮች ግን በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲደረጉ የመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸው እና በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት አስተያየት ተሰጥቶባቸው ለየኦዲት ቡድኑ ከተደለደሉት የ206 ግብር ከፋዮች ዝርዝር ውስጥ ያልተገኙ መሆኑ፣
- በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ በበጀት ዓመቱ ኦዲት እንዲደረጉ የተመረጡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ፣ ሲግታስ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን በስጋት መስፈርት መሰረት የሚመርጥበት ሞጁል ከነሐሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ በመስራቱ በቅ/ጽ/ቤቱ ከተመዘገቡት 864 ግብር ከፋዮች ውስጥ የ718 (83 በመቶ) ግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ተሰጥቷቸው የወጡ መሆኑንና ሲስተሙ የስጋት ደረጃ ውጤት ከሰጣቸው 718 ግብር ከፋዮች ውስጥ 75 የመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋሞች በኦዲት የማይካተቱ እና 50 ግብር ከፋዮች ቀደም ሲል ኦዲት የተደረጉ ተቀንሶ ቀሪዎቹ 593 ግብር ከፋዮች በሶስቱም የኦዲት አይነቶች ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ መሆኑን፣
- የሲግታስ የስጋት ደረጃ ካልተሰጣቸው 146 ግብር ከፋዮች ውስጥ 67 ግብር ከፋዮች በዕቅድ ተካተው አጠቃላይ 660 ግብር ከፋዮች ለኦዲት የተመረጡ መሆኑ፣
- ለ2006 የበጀት ዓመት ለኦዲት የተመረጡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ በስጋት መስፈርት መሰረት ለመምረጥ ተሞክሮ የሲግታስ ውስንነት በመኖሩ በቅ/ጽ/ቤቱ ካሉት አጠቃላይ 991 ግብር ከፋዮች ውስጥ የስጋት ደረጃ የወጣላቸው የ254 ግብር ከፋዮችን ብቻ ሲሆን፣ የቀሩት 737 ግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ግን ማየት አለመቻሉ፤

- በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ከመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ለቅ/ጽ/ቤቱ ከተላኩት

ግብር ከፋዮች ውስጥ ብዛታቸው 325 ድርጅቶች ታክስ ማዕከላቸው ምዕ/አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ነው ከሚለው በስተቀር በትክክል ስለመሆናቸው ያልተጣራ እና ከተላኩት የቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከፋዮች ዝርዝር ውጪ የሆኑ እና በመረጃ ማጥራቱ ስራ ያልተካተቱ ብዛታቸው 2028 የሆኑ ግብር ከፋዮች መኖራቸው፤

- በተጨማሪም ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ከመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተላለፈው መመሪያ መሰረት መረጃ የማጥራት ስራዎቹ በሶስት ክፍሎች የሚከፈሉ ሲሆን፣ እነርሱም፡- ከግብር ከፋዮች አጠቃላይ መረጃ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የማጥራት ስራ፣ ከግብር ከፋዮች የተፈፀመላቸው የግብር/ታክስ ተመላሽ ምዝገባ ስራ እና ከግብር ከፋዮች የኦዲት ታሪክ (ኦዲት ኬዝ) ጋር በተያያዘ የመረጃ ምዝገባ ስራዎች የተገለፁ ቢሆኑም፣ ከተገለፁት ሶስቱ የመረጃ ማጥራት ክፍሎች ውስጥ የግብር ከፋዮች አጠቃላይ የምዝገባ መረጃ ጋር የተያያዘው ስራ ብቻ የተሰራ መሆኑ፤
- በመሆኑም በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሚገኙ ለሁሉም ግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ እንዳልተሰጣቸው እና በየበጀት ዓመታቱ ለኦዲት የተመረጡት ግብር ከፋዮችም ባላቸው የስጋት ደረጃ ውጤት መሰረት ግልጽነት ባለው መንገድ ስለመመረጣቸው ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የጠራና የተደራጀ መረጃ (profile) አለመያዙ፤

**<u>በየበጀት ዓመቱ ለኦዲት የተመረጡ ግብር ከፋዮች ዝርዝር መረጃን በማጠናቀር ለዋናው መ/ቤት እንዲተላለፍ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

98. ቅ/ጽ/ቤቶች በየበጀት ዓመቱ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን በመለየትና ለቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ሪፖርት በማቅረብ፤ ከቅ/ጽ/ቤቱ የሚሰጡ ግብዓቶችን አካቶ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን መረጣ በማጠናቀቅ ዝርዝር መረጃውን ኦዲቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ለዋናው መ/ቤት ለታክስ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት እና ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች ወቅቱን ጠብቆ ሊተላለፍ ይገባል። የዋናው መ/ቤትም በተላለፈለት መረጃ መሰረት ስራው ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል።

99. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መራጭ ኮሚቴው አጠቃላይ ሪፖርቱን እና የተመረጡትን ዝርዝር አባሪ በማድረግ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ እንደሚያስተላልፍ፤ በተጨማሪም ለዋናው መ/ቤት የታክስ መረጃ ማደራጃና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መረጃ እንዲሰበሰብ ሲባል ዝርዝሩ የሚላክ መሆኑን፣ ለሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ግን በዝርዝሩ ወይም በእያንዳንዱ ፋይል ላይ የሚወስዱት እርምጃ ስለሌለ የመረጣ ኮሚቴው ሪፖርት(የመረጣውን ሂደት እና በየኦዲት አይነቱ የተመረጡትን ብዛት የሚያሳይ) መረጃ የሚላክ መሆኑን የገለጹ ሲሆን የምዕራብ እና የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ግን ለጥያቄያችን ምላሽ አለመስጠታቸው፤

100. ይሁን እንጂ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከ2002-2005 ባሉት በእያንደንዱ የበጀት ዓመታት ኦዲት እንዲደረጉ የተመረጡት የግብር ከፋይ ማህደራት፣ የተመረጡበት ምክንያት/የተለየ ስጋት፣ የተሰጣቸው የስጋት ደረጃ እና እንደ የስጋት ደረጃው የተወሰደውን እርምጃ (action) ማለትም የተከናወነውን የታክስ ኦዲት ዓይነት ወይም ሌሎች ተግባራት የሚያሳይ ተጠናቅሮ የተያዘ ዝርዝር መረጃ በቅ/ጽ/ቤቶቹም ሆነ በዋናው መ/ቤት ተጠይቆ ለማቅረብ ባለመቻላቸው የዋናው መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወነውን የታክስ ኦዲት ተግባር ባግባቡ ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤ በተጨማሪም በተቋም ደረጃ የጠራና የተደራጀ የታክስ ኦዲት መረጃ እንደማይያዝ ለማረጋገጥ መቻሉ፤

<u>**ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**</u>

101. የኦዲት ስራ አፈፃፀም ደረጃውን የጠበቀና የንግዱን እንቅስቃሴ ተከትሎ ክህሎቱ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት በተቋም ደረጃ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት የግብር ከፋይ ማህደራትን ለኦዲተሮች

ሊመሩ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

102. በኦዲቱ ወቅት በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ለታክስ ኦዲት የተመረጡ የግብር ከፋይ ማህደራት በስራ ሂደቱ ስር ለሚገኙ የቡድን አስተባባሪዎች እንዲሁም የቡድን አስተባባሪዎችም በተዋረድ በስራቸው ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ኦዲተር(ኦዲተሮች) የሚደለደልበት ወይም የሚከፋፍልበት የስራውን ውስብስብነት፣ ግብር ከፋዩ የተሰማራበትን ዘርፍ፣ የቡድኑን ወይም የኦዲተሩን እውቀትና ክህሎት ወ.ዘ.ተ መሰረት ያደረገ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው ወጥ የሆነ መስፈርት የሌለው መሆኑ፤

**<u>ከኦዲት ኬዝ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣</u>**

103. ኦዲት እንዲደረጉ ከተመረጡ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

104. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በአጠቃላይ ዓመታዊ እና ወርሀዊ የኦዲት እቅድ ሲዘጋጅ እቅዱም ሆነ የድርጊት መርሀ ግብሩ በተዋረድ በየደረጃው እየተዘጋጀ በቡድኑም ሆነ በስራ ሂደቱ የሚጸድቅና ክትትሉም የሚከናወን መሆኑን፣ በተጨማሪም በየሳምንቱ እና በየወሩ የየቡድኑ እንዲሁም የሥራ ሂደቱ እቅድ አፈጻጸም እንደሚገመገም ለዚህም የቢ.ኤስ.ሲ.(ባላንስድ ስኮር ካርድ) እቅድ፡ የድርጊት መርሀ ግብር በየቀኑ እያንዳንዱ ኦዲተር የሚሰራው ስራ እየተያዘ የሚገመገምበት አሰራር መኖሩን መግለጻቸው፤

105. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ፣ በቡድን አስተባባሪ ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር እንደሚዘጋጅ እና በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት ኦዲት ሲጀመር ለእያንዳንዱ ኦዲት፣ ኦዲት ፕሮግራም በማዘጋጀት ለስራ ሂደቱ እንደሚቀርብ፣ ነገር ግን የተቋሙ ዋና ስራ ኦዲት ባለመሆኑ በተቋሙ ከዚህ በላይ የስራ ሂደቱን አልፎ

እንደማይሄድና የስራ ሂደቱ በፕሮግራም መሰረት መሰራቱን አይቶ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ እንደሚፈርም መገለጹ፤

106. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የተከናወኑ ኦዲቶች የስራ ወረቀት በተከለሰበት ወቅት ኦዲቱ በአግባቡ መከናወኑን ለመከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስት እና በየደረጃው የተደረገውን የኦዲት ክለሳ/audit review/ የሚያሳይ ማስረጃ ለማግኘት አለመቻሉ፤፡

107. በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከ2002-2005 በጀት ዓመታት የተከናወኑ ኦዲቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ የታክስ ኦዲት ቡድን ለቡድኑ የተመሩትን እያንዳንዱን የግብር ከፋይ ማህደራት በተሰጣቸው የስጋት ደረጃ መሰረት ቅደም ተከተል በማውጣት ኦዲት የሚያደርግበትን ጊዜ/ኦዲቱ የሚጀመርበት እና ኦዲቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ/፣ ኦዲቱ በማን እንደሚከናወን፣ የኦዲት ሂደት እና ሌሎች የኦዲት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የተዘጋጀ እና የፀደቀ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር/ኦዲት ፕሮግራም እንዲሁም የኦዲት ቡድን አስተባባሪውም ሆነ የስራ ሂደቱ እያንዳንዱ ኦዲቶች በታቀደላቸው ወቅት፣ የጊዜ ተመን እና የኦዲት ሂደት መሰረት የተከናወኑ ስለመሆኑ የተደረገ ክትትል እና የአፈፃፀም ግምገማን የሚያሳይ የተጠናቀረ ማስረጃ ተጠይቆ አለመቅረቡ፤

108. በመሆኑም የተከናወኑት ሁሉም ኦዲቶች የስጋት ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ ቅደም ተከተል የወጣላቸው፣ በወጣው ቅደም ተከተል መሰረትም ኦዲቱ የተከናወነ እንዲሁም ስራው መች እንደተሰራ፣ በማን እንደተሰራ፣ የት እንደተሰራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ እና ትኩረት የተሰጣቸው ጭብጦች በተገቢው መጠን የተዳሰሱ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

<u>የሚከናወኑ ሁሉም ኦዲቶች ወጥነት ያላቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ለኦዲት ስራው አጋዥ የሆኑ ፎርማቶችን ማዘጋጀትን በተመለከተ፣</u>

109. እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበት አሰራሮች በኦዲት ስራ ወረቀቶች የተደገፉ እንዲሁም በኦዲተሮች የተዘጋጁት መግለጫዎችና ሌሎች ሰነዶች ተፈርመው ከኦዲት ውጤቱ ማጠቃለያ ጋር ለስራ ሂደቱ

ሊቀርቡ ይገባል፡፡ የኦዲት ስራ ወረቀቶቹም ባግባቡ ሊደራጁ (ግልፅ እና የተሟሉ) እና በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችሉ መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ ሊደረጉ ይገባል፡፡

110. በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት፤ በቅ/ጽ/ቤቱ ለተከናወኑት ለእያንዳንዱ ኦዲት የሚዘጋጁት የኦዲት ሥራ ወረቀቶች በኦዲት ተደራጊው ግብር ከፋይ ማህደር ላይ ተያይዘው እንደሚቀመጡ ነገር ግን ለእያንዳንዱ ኦዲት የሚዘጋጅና የሚያዝ የኦዲት የስራ ወረቀት ማህደር/ፋይል አለመኖሩ፤ የተሟላ ኦዲት ሊይዛቸው የሚገቡ የኦዲት ሥራ ወረቀቶች/ፎርማቶች የማይታወቁ ሲሆን፣ ይህንን ችግር ለመቅረፍም በቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅተው ለቅ/ጽ/ቤቱ እንዲሁም ለዋናው መ/ቤት ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የቀረቡ ቢሆንም፣ በተቋም ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የኦዲት ማንዋል እየተዘጋጀ በመሆኑ እስካሁን ተግባራዊ አለመደረጉን መግለጻቸው፤

111. የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ቅ/ጽ/ቤቱ አሁን ወደሚገኝበት ሕንፃ ከተዛወረበት ጀምሮ (ከሐምሌ/2003 ዓ.ም.) አንድ ክፍል በማዘጋጀትና የጽ/ቤት ረዳት በመመደብ የኦዲት የስራ ወረቀቶች በኃላፊነት እንዲያዙ መደረጉን የገለፁ ሲሆን፣ የኦዲት የስራ ወረቀቶችን ወጥነት በተመለከተ በቅ/ጽ/ቤቱ በተካሄደው የ2005 በጀት ዓመት የስራ ሂደት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ወቅት ችግሮች መኖራቸው የታየ በመሆኑ በቀጣይ ይህን ለማስተካከል እንደ ሪፈረንስ የሚያገለግል አንድ የኦዲት የስራ ወረቀት በ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት ለማዘጋጀት እየሰሩ እንደሚገኙመገለጹ፤

112. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ የኦዲት ስራ ወረቀቶች በየጊዜው እየተቀየረ አስተያየት የሚሰጥባቸው ሳይሆኑ ከማንዋል ጋር አብረው የተቀረፁ እና በስራ ላይም እየዋሉ መሆኑን፣ ኦዲተሮችም ለእያንዳንዱ ስራ በዚያው አግባብ መስራታቸው ክትትል

እንደሚደረግና እንደሚረጋገጥ በተጨማሪም የተሰራባቸው የኦዲት የስራ ወረቀቶች የሪፖርት አካል መሆናቸው ኦዲት በተደረጉ የግብር ከፋይ ፋይሎች/ማህደሮች ውስጥ፣ ኦዲቱን ባከናወኑ ኦዲተሮች፣ በቡድን መሪ እና በስራ ሂደት ኮፒዎች ተሰራጭተው እንደሚቀመጡ መገለጹ፤

113. በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች እና የኦዲት መስሪያ ወረቀቶች በናሙና በተከለሰበት ወቅት ወጥነት የሌላቸው እና ባግባቡ ተጠቃቅሰው፣ የመዝገብ ቁጥር እንዲሰጣቸው እና ተመዝግበው እንዲቀመጡ አለመደረጉ፤ የኦዲት ሪፖርቶችና የስራ ወረቀቶች ይዘት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በተመለከተ ክትትል ለማድረግ ኃላፊነት በተሰጣቸው ሰዎች በየደረጃው የተደረገ የማረጋገጥ ስራ ስለመሰራቱ የሚያስረዳ ማስረጃአለመገኘቱ፤

114. በመሆኑም እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበትን አሰራሮች ተከትሎ የተከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ካለመቻሉ በተጨማሪ የኦዲት ስራ ወረቀቶችም ማህደር ተዘጋጅቶላቸውና ባግባቡ ተደራጅተው (ግልፅ እና የተሟሉ) በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችል መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ አለመደረጉ ፤

<u>**ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣**</u>

115. በታክስ ኦዲት ወቅት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ መረጃዎቹም በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

116. በታክስ ኦዲት ወቅት ከግብር ከፋይ ከሚቀርብ መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት

አስቀድመው ተጠናቅረው እንደማይያዙ ወይም እንደማይሰበሰቡ እና በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆኑ፤

117. በተጨማሪም ተቋሙ የሶስተኛ ወገን መረጃ በመጠቀም የሚያከናውናቸው የአሰስመንት ሥራዎች ውጤታማ እንደሆኑ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በቅ/ጽ/ቤቶቹ በየበጀት ዓመታቱ የሶስተኛ ወገን መረጃን በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ በማዋል የተገኘ ተጨማሪ ግብር/ገቢ መረጃ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ፤

**<u>በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

118. በተከናወኑ የኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተገቢው እርምጃም ስለመወሰዱ በየደረጃው (በዋና መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

119. በኦዲቱ ወቅት ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የኦዲት አይነቶችን በማከናወን ተጨማሪ ግብር/ታክስ፣ ወለድ እንዲሁም መቀጫ ውሳኔ በማውጣት ለግብር ከፋዮች እንዲደርሳቸው ያደረጉ መሆኑ፣ ለአብነትም በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002-2005 በጀት ዓመታት ዘጠኝ ወር ድረስ ብር 2,025,438,108.21 ተጨማሪ ፍሬ ግብር/ታክስ እና ብር 2,923,323,143.86 ወለድና መቀጫ በድምሩ ብር 4,948,761,252.07 የተወሰነ መሆኑ፤፡

120. ግብር ከፋዮች የመቀጫ ይነሳልኝ አቤቱታ ባቀረቡት መሰረት ከተጣለው የመቀጫ መጠን በ2002 በጀት ዓመት የ378 ግብር ከፋዮች ከተወሰነው ጠቅላላ ብር 54,411,310.83 ውስጥ ብር 45,104,015.21 (83 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 9,307,295.62 (17 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ የፀና መሆኑን፣ በ2003 በጀት ዓመት ደግሞ የ1052 ግብር ከፋዮች ከተጣለው የመቀጫ መጠን ብር 103,514,519.8 ውስጥ ብር 84,488,177.73 (82 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 19,026,342.7 (18 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ የፀና መሆኑ፤

121. በመሆኑም በታክስ ኦዲት ተጨማሪ የሚወሰነው ግብርና ታክስ አሰባሰብን በተመለከተ በአንድ በጀት ዓመት የተወሰነው ግብርና ታክስ

ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ ቀርቦበት እንዲስተካከል ውሳኔ ከተሰጠው በኃላ በታክስ ኦዲት ተስተካክሎ በሚወጣው ውሳኔ ማስታወቂያ መሰረት የሚሰበሰብ እና/ወይም የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል የሚገባበት በመሆኑ አሰባሰቡ ከአንድ ግብር ዘመን ወደ ቀጣይ ግብር ዘመን እንደሚዞርና በተጨማሪም በፍሬ ግብር ላይ የተጣለው መቀጫ በአስተዳደራዊ ሁኔታ የሚነሳ በመሆኑ በታክስ ኦዲት የተወሰነው በሙሉ እንደማይሰበሰብ ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፤

122. በተጨማሪም በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2002-2005 በጀት ዓመታት በሦስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ላይ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ውስጥ ስንቱ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ በኮሚቴው በተሰጠው የውሳኔ ዓይነት እንዲሁም በስራ ሂደቱ የተደረገ ማስተካከያ/የተወሰደ እርምጃ/ መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳተፈ የተተነተነና ተጠናቅሮ የተያዘ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ባለመቻሉ በቅ/ጽ/ቤቶቹ በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ/ በእያንዳንዱ ኦዲት እና በግብር ዘመኑ በኦዲት የተገኙ ተጨማሪ የግብርና ታክስ ውሳኔዎች ገቢ መሆናቸውን/ ስለመወሰዱ በየደረጃው (በቅ/ጽ/ቤቶች እና በዋና መ/ቤት) ክትትል የሚደረግ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

<u>**የግብርና ታክስ ቅሬታ አቀራረብና አፈታትን በተመለከተ፣**</u>

123. በኦዲት ውጤት ከግብር ከፋይ ጋር ስምምነት ያልተደረሰባቸው እና ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ የቀረቡ ውሳኔዎች በቢ.ፒ.አር ጥናቱ ላይ በተቀመጠው 5 ቀናት የጊዜ ገደብ ምላሽ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

124. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጀው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የግብርና ታክስ ቅሬታ አቀራረብና አፈታትን በተመለከተ የሚቀርቡ የአቤቱታ ጥያቄዎች በ5 የሥራ ቀናት ውሳኔ እንደሚያገኙ ቢቀመጥም በከፍተኛ ግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤት በተለያየ ወቅት ኦዲት ተደርገው በኦዲት ውሳኔው ላይ ቅሬታ ከቀረበባቸው የግብር ከፋይ አቤቱታዎች መካከል በኦዲቱ ወቅት በናሙና

በየበጀት ዓመቱ ከተመረጡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ ስለመሰጠቱ በሚጣራበት ወቅት በ2003 ከ53 እስከ 433 ቀናት እና በ2004 ከ50 እስከ 155 ቀናት  የወሰዱ አቤቱታዎች መኖራቸው፤

125. በተጨማሪም በምዕራብ አዲስ አባባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት ለቅሬታ መልስ ለመስጠት የፈጀው ጊዜ በተሰጣቸው የግብርና ታክስ ውሳኔ ላይ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ያቀረቡ ግብር ከፋዮችን ጉዳይ ሲፈተሽ ከታች በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው ነው፡፡

| **አቤቱታው የፈጀው ጊዜ** | **የግ/ከ ብዛት** | **በመቶኛ** | |
|---|---|---|---|
| **በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔያገኙ** | 1 | 0.15% | |
| **ከ6 ቀናት እስከ 6 ወር** | 413 | 63% | |
| **ከ6 ወር እስከ 2 አመት** | 200 | 30.4% | |
| **ከ 2 አመት በላይ** | 36 | 5.5% | |
| **ያልተረጋገጠ** | 8 | 1% | |
| **ድምር** | 658 | 100.00% | |

126. በመሆኑም ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የግብር ከፋዮችን እርካታ መፍጠር ካለመቻሉ በተጨማሪ ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረጉና በባለስልጣን መ/ቤቱም መሰብሰብ ያለበት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ማድረጉ፤

**<u>ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ማድረግን በተመለከተ፣</u>**

127. በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እና በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ /የአፈጻጸም እንዲገቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

128. በኦዲቱ ወቅት ከአቤቱታ አጣሪ እንዲሁም ከቴክኒክ ኮሚቴ እንዲስተካከሉ የሚወሰኑ እና ወደ ታክስ ኦዲት የሚመለሱ ውሳኔዎች በምንያህል ግዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለባቸው የተቀመጠ የጊዜ ስታንዳርድ እንደሌለና ማስተካከያ ያልተደረገባቸው ውሰኔዎች እንደሚገኙ፣ በተጨማሪም ማስተካከያ የተደረገባቸውም፤ የተደረገውን

ማስተካከያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ፣ የግብር ዓይነት፣ በየበጀት ዓመታቱ ተለይተው በቅድመ ኦዲት ከተወሰነው ጋር ማነጻጸር በሚያስችል መልኩ ተጠናቅሮ አለመያዙ፤

**በኦዲት ውሳኔ መሰረት የሚገኙ ውዝፍ ዕዳዎችን ማስተዳደርን በተመለከተ፣**

129. የውዝፍ ዕዳውን እድሜ እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በመጠቀም ሊሰበሰቡ የሚችሉ እና የማይችሉ ዕዳዎችን በመለየት፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ/በተለይ የቅርብ ዕዳዎችን/ ላይ በማተኮር ሀብትና ንብረት እስከመያዝ የሚደርስ እርምጃ በመውሰድ ውዝፍ የግብር ዕዳ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

130. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው ውዝፍ ዕዳ ብር 671.26 ሚሊዮን ውስጥ ብር 615.81 ሚሊዮን በአቤቱታ አጣሪ እና ብር 0.60 ሚሊዮን በግብር ሰሚ ጉባኤ እየታየ ያለ መሆኑን፣
- በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው ውዝፍ ዕዳ መጠን ብር 1.58 ቢሊዮን ውስጥ ብር 1.43 ቢሊዮን በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እና ብር 0.81 ሚሊዮን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እየታየ ያለ መሆኑን፣
- በ2005 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወር መጨረሻ ከነበረው የውዝፍ ዕዳ መጠን ብር 1.59 ቢሊዮን ውስጥ ብር 731.86 ሚሊዮን በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ፣ ብር 0.57 ሚሊዮን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና ብር 422.983 ሚሊዮን በቴክኒክ ኮሚቴ እየታየ ያለና ብር 297.97 ሚሊዮን ደግሞ ወደ ሌዠር የተላለፈ መሆኑን፤

131. በመሆኑም በየበጀት ዓመቱ ከሚከናወኑ የኦዲት ውሳኔዎች አብዛኛዎቹ ወደ አቤቱታ እንደሚሄዱ እና አፋጣኝ ምላሽ ተሰጥቷቸው ወደ አሰባሰብ በወቅቱ እንዲገቡ የማይደረግ መሆኑ፤

**የኦዲት ጥራትን ከማስጠበቅ አንፃር የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ፣**

132. እያንዳንዱ ኦዲት በሚካሄድበት ጊዜ ከጅምሩ አንስቶ፣ ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አፈፃፀሙ ተቀባይነት ባለው የኦዲት አካሄድ መርህ

እና የአሰራር ማንዋሉ መሰረት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይገባል። በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወኑ የታክስ ኦዲቶችን የጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቶቹ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቶቹ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ ለምን እንዳቀረቡና ለቅሬታው መቅረብ ምክንያት የሆነውና ውሳኔው ለማን እንደተሰጠ በየኦዲቱ እየተተነተነ ወጥነት ባለው መልኩ መረጃ ሊያዝ ይገባል።

133. ይህ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን ለማጣራት የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡- በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የኦዲት ጥራትን በተመለከተ የኦዲት ጥራት የማረጋገጥ ተግባር የሚከናወነው በዋናው መ/ቤት የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ሲሆን ይህንን በተመለከተ Quality Assurance Audit Manual በዝግጅት ላይ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ግን ማንኛውም የኦዲት ሥራ ሲከናወን የኦዲት ማንዋሉን፡ የግብር አዋጆችንና ደንቦችን እንዲሁም በተለያየ ጊዜ የወጡ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን መሆኑን፤ ይኸውም በየደረጃው በቡድንም ሆነ በስራ ሂደቱ እየተረጋገጠ ውሳኔው የሚወጣ መሆኑን ፤ በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ከዓመታዊ ዕቅድ እስከ ዓመታዊ ዕቅድ ክንውን ድረስ ኦዲቱ ጥራቱን ጠብቆ መሰራቱን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን እና በበቂ ሁኔታም መሰራቱን ለማረጋገጥ በውስጥ ኦዲትና ማኔጅመንት በሚሰየመው አካል/ኮሚቴ እንደሚታይ መገለጹ፤

134. ይሁን እንጂ በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በ2002 በጀት ዓመት ከቀረቡ 1035 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 282 አቤቱታዎች በድምሩ 1317 አቤቱታዎች ውስጥ ውሳኔ ያገኙት 879 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 165ቱ(19 በመቶው) አቤቱታዎች ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱየተወሰነ (የፀደቀ)፣ 33ቱ (4 በመቶው) ለግብር ከፋዩ የተወሰነ(የተሻረ) እና 681ዱ(77 በመቶው) አቤቱታዎች

ደግሞ ለባለሰልጣን መስሪያ ቤቱ እና ለድርጅቱ በጋራ(እንዲስተካከል) የተወሰነ ሲሆን፣ የ438ዎቹ አቤቱታዎች ደግሞ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣

- በ2003 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከቀረቡ 723 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 343 አቤቱታዎች በድምሩ 1066 አቤቱታዎች ውስጥ 385ቱ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል 110ቹ (28 በመቶው) ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተወሰነ(የፀና)፤ 57ቱ(15 በመቶው) ለግብር ከፋዮቹየተወሰነ(የተሻረ) እና 218ቱ (57 በመቶው) ደግሞ በጋራ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱና ለግብር ከፋዩ(እንዲስተካከል) ሲወሰን ቀሪዎቹ 27ቱ አቤቱታዎች ደግሞ በበጀት ዓመቱ በተካሄደው የግብር ከፋች ድልድል መሰረት ወደ ምስራቅና ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ሲዛወሩ 654ቱ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣
- በ2004 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ ከቀረቡ 468 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 487 በድምሩ 955 አቤቱታዎች መካከል 898ቱ አቤቱታዎች ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 258ቱ (29 በመቶው) ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/የፀደቀ፤ 422ቱ (47 በመቶው) በጋራ ለግብር ከፋዮቹና ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/እንዲስተካከል እና 218ቱ (24 በመቶው) ለግብር ከፋዩ/የተሻረ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 57ቱ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣ በአቤቱታ አጣሪ እጅ ያለው በድርጅት ሲገለፅም 28 ድርጅቶች (ብር 801,364,824.00) መሆኑ፤
- በ2005 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወር ከቀረቡ 255 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 291 በድምሩ 546 አቤቱታዎች መካከል 196ቱ አቤቱታዎች ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 122ቱ (62 በመቶው) ለቅ/ጽ/ቤቱ/የፀና፣ 61ዱ (31 በመቶው) ለግብር ከፋዩ/የተሻረ እና 13ቱ (7 በመቶው) ለባለስልጣኑና ግብር ከፋዩ በጋራ/እንዲሻሻል ሲወሰን ቀሪዎቹ 350ዎቹ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ወር እንዲተላለፍ መደረጉ፤
- በተጨማሪም በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በ2005 በጀት ዓመት ቅሬታ ተገብቶባቸው እንዲስተካከሉ ውሳኔ ከተሰጣቸው መካከል

በናሙና ከተመረጡት 29 ግብር ከፋዮች ውስጥ የሁለት ግብር ከፋዮች የቀድሞው ውሳኔ በኦዲተሮች ትክክል መሆኑ የተረጋገጠ ፣ የ9 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ጠቅላላ ብር 138,012,716.46 የተሻረ፣ የ12 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ደግሞ ከነበረው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ብር 802,293,162.76 ወደ ብር 393,377,402.14 ማለትም በብር 408,915,760.62 ልዩነት ዝቅ እንዲል ተደረጎ የተወሰነ እና የ3 ግብር ከፋዮች ከቀድሞው ውሳኔ በብር 96,799,267.65 በብልጫ እንደተወሰነ መረጋገጡ፤

- በየበጀት አመታቱ የሚከናወኑ እያንዳንዱ የኦዲት ውሳኔዎች በግብር አዋጆች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎች፤ የታክስ ኦዲት ማንዋሎች እንዲሁም ተቀባይነት ባላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሠረት ጥራታቸውን ጠብቀው ባለመከናወናቸው አብዛኞቹ የኦዲት ውሳኔዎች ወደ አቤቱታ እንዲሄዱና ማስተካከያ የሚደረግባቸው መሆኑ፤
- በመሆኑም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታክስ ኦዲት የአሰራር ስርዓት እና አፈጻጸም ረገድ በታዩ ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.13 በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ፤ አሻሻጥ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ማጠቃለያ ሪፖርት

<u>ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ ምርቶች አያያዝና የመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን በተመለከተ፣</u>

135. የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለብልሽት ሊጋለጡ የሚችሉ የግብርና ምርቶችን አሠባሠብ አያያዝና በመጋዘን አቀማመጥ ሁኔታን አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ በቅድሚያ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በ 2005 ዓ.ም በመጋቢት ወር ገበያ ለመቅረብ የደረሰ የሸንኩርት ማሳ መነቀል የነበረበት ከ 1 ወር በፊት ቢሆንም፣ በወቅቱ ባለመነቀሉ 250 ኩንታል የሚሆን ሽንኩርት በማሳው ላይ እያለ መበላሸቱ፤

136. በተመሳሳይ ሁኔታ ማዕከሉ በማሳ ላይ የደረሱ ምርቶች መቼ ተሰብስበው ለገበያ ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ እንደሚችሉ በጥናት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ባለመስጠቱ በጾም ወቅት ተፈላጊ የነበሩ ምርቶችን ለፋሲካ በዓል ጥቂት ቀናት ሲቀረው ከምርቱ ተረካቢዎች ጋር አስፈላጊውን ትዕዛዝና ቀብድ ሳይቀበል በቁጥር 1012 የጥቅል ጎመን ምርቶች ከማሳ ላይ እንዲሰበሰቡ በመደረጉ ምርቱ ገዢ በማጣቱ በብልሽት ምክንያት እንዲወገድ በመደረጉ ሊገኝ ይችል የነበረውን ብር 3542.00 /ሦስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ብር/ ገቢ መታጣቱ፣

137. በዝዋይ ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እርሻ ልማት ማሳ ላይ በ2005 ዓ.ም ከተመረተው ጥቅል ጎመን ውስጥ በቁጥር 1225 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አምስት/ ሳይሸጥ በመቅረቱ እና በመበላሸቱ ብር 4195 /አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አምስት ብር/ ገቢ መታጣቱ፣

138. በሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል የተበላሹ እና መሸጥ የማይችሉ የቲማቲም ምርቶች ከማሳ መለቀማቸው እና ምርት አቅራቢው ለሽያጭ በሚያመችና አዋጪ በሆነ መልክ ምርቶችን አደራጅቶ ባለማቅረቡ እና የሽያጭ ሰራተኛው ምርቱ እየተሸጠ አለመሆኑን ቢያሳውቅም፣ ያልተሸጠ ምርት እያለ ምርት አቅራቢው ምርት ስለሚያቀርብ ምርቱ እየተበላሸ ለብክነት በመጋለጡ በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጥ እና አልሸጥ ካለም ተወግዶ ለአሳማዎች መኖ የሚውል መሆኑ፣

139. የደረሱ ምርቶችን ማዕከሉ ለሽያጭ ማዋል ባለመቻሉ የቲማቲም ምርት በማሳው ላይ እየበሰበሰ መርገፉና ለብክነት መዳረጉን፣ የመሸጫው ሱቅ ውስጥ ሰፋፊ ቀዳዳዎች በመኖራቸው ምርቱ በአይጥ እና በተባይ የሚበላ መሆኑ፣ የምርት መሸጫው ሱቅ ጣሪያው ዝናብ የሚያስገባ በመሆኑና ምርቱ ለብልሽት መዳረጉ፣፣ የምርት መሸጫው ሱቅ ከበሩ ስር ክፍት በመሆኑ ለስርቆት የተጋለጠ መሆኑ፣ መጋዘኑ የአይጥ ጎሬ በመሆኑ ምርቱን እያበላሹ መሆኑ ከማሳ ላይ የምርቱን ግዜ ጠብቆ አለማስነቀል መሠረታዊ ችግሮች መሆናቸው፣

140. ከዚህ በተጨማሪም በሸዋሮቢት ማረሚያ ቤት የግብርና ምርቶች ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ከሶስት አመት በፊት ጊዜው ያለፈበት አደገኛ

ኬሚካል (Bayleton 25 WP) ከተለያዩ ምርቶች (ቲማቲም፤ ማንጎ፤ በቆሎ…..ከመሳሰሉት) ጋር መቀመጡና በምርቱ ላይ እና በመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤ ኬሚካሉ እንዲወገድላቸው የመጋዘኑ ሠራተኞች ለማረሚያ ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃል በተደጋጋሚ እንደጠየቁና መልስ ማጣታቸውን፤ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለጹ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅትም ችግሩ አለመፈታቱን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ የሰጠው ወይም ያሳተመው መሆኑን በተመለከተ፤**

141. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ማዕከላት ከውስጥ ገቢ የሚሰበስቡትን ገንዘብ ገቢ የሚያደርጉበት ደረሰኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም ፍቃድ በሰጠው ደረሰኝ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

142. በኦዲቱ ወቅት በመስክ ስራ ከታዩት የዝዋይ፤ የሸዋሮቢት ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል እና የድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከል  የውስጥ ገቢ የሚሰበሰበው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ደረሰኝ  ቢሆንም፣ ማዕከላቱ ለሚያካሂዱት የግብርናና ሌሎች ምርቶች ሽያጭ ለገዢዎች ደረሰኝ የማይሰጡ መሆኑ

143. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገንዘብ መቀበያ ደረሰኙ ላይ ታክስ የሚል ቀደም ብሎ የተጻፈ ጽሁፍ ስለሌለ፤ የከፈለበት ምክንያት የሚለው ቦታ አጠገብ ላይ በእጅ ጽሁፍ “ታክስ” የሚል በማስገባት የምርቱ ዋጋ ላይ 5% በመጨመር የሚያስከፍሉ ሲሆን  ለዚህም ታክስ ምንነት  እንዲያስረዱ ተጠይቀው ማስረጃ ማቅረብ አለመቻላቸው፤

**በማዕከላት ከምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረጉን በተመለከተ፤**

144. በማዕከላት በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም፡-

145. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የመስክ ስራ፤ የመረጃ ክለሳና ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ በዝዋይ እና በሸዋሮቢት

ተሐድሶና ልማት ማረሚያ ማዕከል በምርት ሽያጭ የተሠበሠበው ገንዘብ በዕለቱ በባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤ በዝዋይ ከ1/07/2005 እስከ 8/07/2005 ከሽያጭ የተሰበሰበ ገቢ በ 9/07/2005 ማለትም ከሳምንት በኂላ ብር 28,074.00 (ሃያ ስምንት ሺ መቶ ሰባ አራት) ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

**በማዕከላት ከምርት አሠባሰብ እስከ ሽያጭ ሂደትን የመከታተያ ስርዓትን በተመለከተ፤**

146. የምርት ማቅረቢያ ማዘዣ ምርት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፤ ደረጃ ፤ መጠን ፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ ማዕከላት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

147. በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ከማሳ እንዲሰበሰብና ለሽያጭ ርክክብ እንዲዘጋጅ የምርት ዓይነት ፤ ደረጃ ፤ መጠን ፤ የአቅርቦት እለትና ሰዓት ፤ የርክክብ ቦታ እና ተረካቢ በዝርዝር የሚመዘገብበት የማረሚያ ቤቱ ቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሠጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ቅጽ/ካርድ የሚጠቀሙበት የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ፤

**የማረሚያ ቤቱን ምርት ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ፤**

148. የማዕከላት አምራቾች የሚሸጡትን ምርቶች አይነትና የሽያጭ ፕሮግራም ለደንበኞች በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስታወቂያ መለጠፍና እንደአስፈላጊነቱ በሚዲያ ሊያስነግሩ ይገባል፡፡

149. ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ ማዕከላት ለደንበኞች ምርቱን ለመሸጥ የማስተዋወቅ ስራ አለመሰራታቸው እና የምርት አሻሻጥ፤ ተግባራትና ዘዴዎቹ ግልጽ አለመሆናቸው፤

**የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ማዘጋጀቱን እና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፤**

150. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው ማዕከላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያው ዓላማ መሠረት ማዕከላቶች ትርፋማና በገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የማረሚያ

ቤቶች አስተዳደር ለግብርና ምርት አሰባሰብ አቀራረብና አሻሻጥ ተፈጻሚነቱ በአስተዳደሩ ስር ለሚገኙ ለዝዋይ፤ ለድሬዳዋ እና ለሸዋሮቢት ማረሚያ ቤቶች እንዲውል መመሪያ አውጥቶ ለማዕከላቱ ቢያሰራጭም ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ አለማደረጉ፤

151. በናሙና የተመረጡ የማዕከል ኃላፊዎችም ሆኑ ከምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብ እስከ አሻሻጥ ድረስ የተሰየሙት ኮሚቴዎች የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የተሃድሶ ልማቱ አገልግሎት አላማ ማረም እና ማነጽ ነው እንጂ "ትርፋማ እንዲሆን አይደለም" የሚል አመለካከት ያላቸው መሆኑ፤

**<u>በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የውስጥ ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፤</u>**

*152.* የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ማዕከላት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ በተመለከተ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ጽ/ቤት ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ፤

**በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጻ ቅጾች መጠቀምን በተመለከተ፤**

153. በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾች፡- የዋጋ ተመን የሚወጣላቸው ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 001፤ የዋጋ ተመን ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽና ቃለ ጉባኤ ቅጽ 002፤ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶች መጠየቂያ ቅጽ 003፤ የተተመኑ ምርቶች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረጊያ ቅጽ 004፤ የዋጋ ማሻሻያ ተመን የተጠየቀባቸው የምርት ዓይነቶች ማሳወቂያ ቅጽ 005፤ በዋጋ ማሻሻያ ተመን ምክንያት ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ የሆኑ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 006፤ የተበላሹ ምርቶች ማሳወቂያ ቅጽ 007 እና የተበላሹ ምርቶች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ማሳወቂያ ቃለ ጉባኤ ቅጽ 008 በማረሚያ ቤት አምራቾች በጥቅም ላይ ሊውል ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ በዝዋይ እና በድሬዳዋ ሁሉን አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ማዕከላት በምርት አሰባሰብ፤ አቀራረብና አሻሻጥ ሂደት የሚያገለግሉ ቅጾችን የማይጠቀሙ መሆኑ፤

**ሁሉም ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቶች አስተዳዳሪ ሪፖርት ማቅረባቸውን በተመለከተ፤**

154. የምርት ዋጋ ተማኝ፤ የምርት አስረካቢ እና የምርት አስወጋጅ ኮሚቴዎች በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ ማዕከላት በየወሩ የክንውን አፈጻጸማቸውን በጽሁፍ ለማረሚያ ቤቱ አስተዳዳሪ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ

በመሆኑም የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.14 በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ

**የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን አግባብ ባለው ደረሰኝ የሚሰበስቡ መሆኑን በተመለከተ**

155. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን ሲሰበስቡ፣ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባሳተመው ወይም ገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንዲታተም በፈቀደው ተከታታይ ቁጥር ባለው ደረሰኝ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ገቢውም መሰብሰብ የሚገባው ቋሚ /ተገቢው ዋስትና ባለው/ ሠራተኛ ብቻ ሊሆን እንደሚገባው እና የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠር እና ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲቻል በየዕለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በየቀኑ ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

156. ይሁን እንጂ በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ አዳማ ዩኒቨርሲቲ እና ባህርዳር ሥር የሚገኙ የውስጥ ገቢ ማመንጫ ተቋማት የገቢ ደረሰኞች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያሳተማቸው ወይም ፈቃድ የሰጣቸው ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አለመሆናቸው፤ የገቢ ማመንጫ ተቋማቱ የሚጠቀሙባቸውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ የሚያጣራ፣ መዝግቦ የሚይዝና የሚከታተል አካል አለመኖሩ እና በገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚሠሩ

የገቢ ሰብሳቢዎች ዋስትና የሌላቸው ሠራተኞች መሆናቸው፤ የውስጥ ገቢ አሰባሰቡ የሪፖርት አደራረግ ሥርዓት ሲታይ፣ በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣በባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የተሰበሰበውን ገቢ ለመቆጣጠር እና ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲቻል በየዕለቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለዚሁ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በየቀኑ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤

**የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ ባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን በተመለከተ**

የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ሊያደርጉ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

157. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር የሚገኙ 28 የገቢ ማመንጫ ተቋማት፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ 9 የገቢ ማመንጫ ተቋማት፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 7 የገቢ ማመንጫ ተቋማት እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲ 22 የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሰበሰቡትን የውሰጥ ገቢ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የማያደርጉ ወይም በመ/ቤቱ ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተፈቀደና በተከፈተ የገቢ መሰብሰቢያ ባንክ ሂሳብ ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፤

158. በጅማ እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እውቅና በራሳቸው ስም በተከፈተ የባንክ አካውንት የሚያስቀምጡ ሲሆን፣ በተለይ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሞዴል ፋርማሲ ቁጥር አንድ እና ሁለት፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ ኢንተርፕራይዝ እና የማህበረሰብ ትምህርት ቤት የገቢ ማመንጫዎች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3 የመንግሥት መ/ቤቶች የባንክ ሂሳብ የሚከፈተው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም እርሱ በሚሰይመው ወይም በሚወክለው ባንክ እንደሚሆን ከተጠቀሰው የአሠራር መመሪያ ውጭ ገቢያቸውን የሚያስቀምጡ መሆኑ፣ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች በሶስቱ

ማለትም (አዲስ አበባ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት የሚሰበስቡትን ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፤

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብን አስመልክቶ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ**

159. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

160. ይሁን እንጂ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለትም (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች) የውስጥ ገቢ አስተዳደር ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ መመሪያዎችን በማስተዋወቅ (awareness) ፣ ስልጠና በመስጠት እና ስለውስጥ ገቢ አተገባበር ስርዓት በአካል በመገኘት ሙያዊ እገዛ አለማድረጉ፤

**የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዳዲስ ዋጋ እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በተመለከተ**

161. በፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማጸደቅ አለባቸው፡፡ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማትም አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡

162. በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ አራት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ በሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው የማያጸድቁ መሆኑ፤

እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ሥር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግ ለውጥን በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሀሣብ ለተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ሳያሳውቁ በራሳቸው የሚያከናውኑ መሆኑ፤

163. **የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ**

164. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያን ወጥ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ወይም ተቋማቱ እንዲያዘጋጁ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

165. በናሙና ተመርጠው በታዩት አራት የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመዘርጋት የሚያስችል የውስጥ ገቢ መመሪያ ወጥ በሆነ መልኩ አለመዘጋጀቱ፤ ተቋማቱም እንዲያዘጋጁ እገዛ አለመደረጉ

**የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ዕቅድ አዘገጃጀት እና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ**

166. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በውስጥ ገቢ በጀት ኮድ ቁጥር 1900 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፀድቆ እና ተመዝግቦ ከተመደበላቸው በጀት በላይ ሊጠቀሙ አይገባም፤ እንዲሁም ገቢውን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ከሚሰራው ሥራ ጋር በማጣጣም በየወሩ የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ እቅድ አዘጋጅተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

167. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የተመደበላቸው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር የማይጣጣም ሲሆን፣ በየወሩም የተከፋፈለ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ የማያዘጋጁ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይህን ያህል በጀት ይጽደቅልኝ ብሎ ገ/ኢ/ል/ሚ/ርን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ከውስጥ

ገቢ የተጠቀመውን መጠን ሙሉ በሙሉ የማያሳውቅ እና በሪፖርቱ ውስጥም የማያካትት መሆኑ፤

የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያገኙትን አስፈቅደው የሚጠቀሙ መሆኑን እንዲሁም በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ መፈጸሙን በተመለከተ

168. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከውስጥ ገቢ የሚያገኙትን የተለያዩ ገቢዎች አስፈቅደው ሊጠቀሙ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው ሊፈጸሙ ይገባል፡፡

169. በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች ስር የሚገኙ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከውስጥ ገቢ ያስገኙትን ሳያስፈቅዱ የሚጠቀሙ ሲሆን በውስጥ ገቢ የሚከናወኑ ግዥዎችም፣ የግዥ መመሪያና የፋይናንስ ደንብን ተከትለው የማይፈጸሙ መሆኑ፤

**የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ ግዥ መፈጸማቸውን በተመለከተ**

170. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ የገበያ ጥናት ሊያካሂዱ እና ለግዥ ሰራተኞች የሚሰጠው ቅድመ ክፍያ ጣሪያ ሊወሰን ይገባል፡፡

171. በአዲስ አበባ፣ ጅማ እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማመንጫ ተቋማቱን ጥቅም ከማስከበር አንጻር በአቅርቦቶች ላይ የዋጋ መጋነን ሲታይ፣ የገበያ ጥናት የማይደረግ ሲሆን ለግዥ ሰራተኛ የሚሰጡት ቅድመ ክፍያም በየተቋማቱ ወጥ ያልሆነ እንዲሁም በየገቢ ማመንጫዎች አይነት የተለያየ መሆኑ፤

**የዩኒቨርሲቲዎቹ የውስጥ ገቢ ማመንጫ ተቋማት አደረጃጀትን በተመለከተ**

172. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ፣ የአሰራር ሥርዓት ያላቸው በዚሁ ሥርዓት የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡

173. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ ፣ ባህር ዳር፣ አዳማ እና ጅማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢን የሚሰበስቡ ድርጅቶች በዩኒቨርሲቲው መዋቅር ውስጥ በግልጽ የታቀፉ እና የአሰራር ሥርዓት ያላቸው ባለመሆናቸው ምክንያት ለተመራቂ ተማሪዎች በየአመቱ በራሳቸው ገቢን እያስተዳደሩ እንዲጠቀሙበት የገቢ ማመንጫዎችን

በባለቤትነት እንደሚሰጡ፣ ለግለሰብ ጭምር የገቢ ማመንጫ ተቋማቶቹን በነጻ የሚሰጡ መሆኑ፣ የገቢ ማመንጫ የሥራ ሂደት እያንዳንዱ የገቢ ማመንጫ ያስገኘውን ገቢ ለይቶ አለማወቁ፤ እንዲሁም የገቢ ማመንጫዎቹ ውል ሰጪ በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎች /ሰሻል፣ ግዥ፣ ቤቶች ልማት፣ የተማሪዎች አገልግሎት እና የተማሪዎች ህብረት/ መሆናቸው፤

**<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን የሚያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ</u>**

174. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያሳውቁ፤ ገቢና ወጪን በበጀት ኮድ 1900 ሊመዘግቡ እንዲሁም በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አስደርገው ለሚመለከተው የበላይ አካል ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

175. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ፣ ጅማ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ ዩኒቨርሲቲዎች የውስጥ ገቢ ምንጫቸውን ብዛት እና የሚያስገኙዋቸውን የገቢ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማያሳውቁ ሲሆን ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡትን እና ወጪ ያደረጉትን ሙሉ በሙሉ በበጀት ኮድ 1900 የማይመዘግቡ መሆኑ፤

**<u>የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ</u>**

176. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጉና አግባብነት በሌላቸው የአሰራር ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃዎችን ሊወስዱ ይገባል፡፡

177. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫዎቹን ውል ፈጽመው የተከራዩ ተከራዮች ከውሉ አላማ ውጪ በተጨማሪ ተለጣፊ ሱቅ በመሥራት፣ የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ፣ የኮምፒዩተር አገልግሎት፣ የፑል ጨዋታ አገልግሎት እየሠጡ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥር የሚገኙና በውጭ አካል (Outsource የተደረጉ) አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የገቢ ማመንጫዎች በጨረታ አግባብ ወይም ተጫርተው አሸንፈው እና በዚህም ላይ ተመስርቶ የኮንትራት ውል የተሠጣቸው ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ ወይም ሰነድ

ከፋይላቸው ጋር ያልተያያዘ መሆኑ እየታወቀ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

178. በጅማ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ ተቋማት ሥር የሚገኙ ንብረቶች በአግባቡ በመጠለያ ሥር እንዲያዙ ወይም መወገድ ያለባቸው እንዲወገዱ አለመደረጉ፣ ሞዴል ፋርማሲዎቹ የቁጥ ቁጥ ግዥ የሚፈጽሙ መሆኑ፤

179. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በገቢ ማመንጫው ስር የሚገኘው የከብት እርባታ ከ2003- 2005 ዓ.ም ያሉ የከብቶች ብዛት እንዲሁም በህይወት ያሉና የሞቱን በመለየት መረጃዎች አለመያዛቸው፣

180. በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በውል የተከራዩ የገቢ ማመንጫዎች በውሉ መሰረት ጊዜውን ጠብቀው ኪራይ እንዲከፍሉ አለመደረጉ

181. በጅማ ከ10 ገቢ ማመንጫ በስድስቱ፣ አዳማ እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች በሁሉም የገቢ ማመንጫ ተቋማት ከ2003- 2005 ዓ.ም የተገኘውን ትርፍ/ኪሳራ፣ የነበራቸውን የካፒታል መጠን እንዲሁም የወጣው የገንዘብ መጠን አለማወቃቸው እየታወቀ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ

**በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡና የሙያ ሥነ ምግባር የሚያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ**

182. በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ እንዲሁም የሙያ ሥነ-ምግባርን እንዲያውቁ የተደረጉና የሚተገብሩ ሊሆን ይገባል፡፡

183. ሆኖም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአዲስ አበባ፣ በጅማ፣ በባህር ዳር እና በአዳማ ዩኒቨርሲቲዎች በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በተቋሙ መዋቅር መስፈርት መሰረት የተመደቡ አለመሆናቸው፤ እንዲሁም የሙያ የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲያውቁት እና ተግባራዊ እንዲያደርጉት አለመደረጉ፤

**የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን በተመለከተ**

184. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኪራይ ገቢ አሰባሰብና የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች የመንግሥትን መመሪያ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

185. ይሁን እንጂ የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ መመሪያ ቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 መሰረት አለመሆኑ፤ የውስጥ ቁጥጥርን ለማጠናከር የሚያስችል የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003ን ተግባራዊ አለመደረጉ፤

186. የኪራይ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) ፤ ዩኒቨርስቲዎቹ በሚፈጽሙት ውል መሠረት የውል ሰነዱ ጊዜው እንዳለቀ ያለ ምንም ተጨማሪ ማስታወቂያ ውል ተቀባይ ከዩንቨርሲቲው የተረከባቸውን አስረክቦ እንደሚለቅ የተዋዋሉ፣ ቢሆንም አብዛኞቹ ተከራዮች የውል ጊዜያቸው ያለፈ መሆኑ እንዲሁም የዋጋ ተመናቸውም በየጊዜው እየተጠና እንዲሻሻል እና ተከራዮች ጊዜያቸውን ጠብቀው እንዲከፍሉ አለመደረጉ፤

**የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ማቅረባቸውን በተመለከተ**

187. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወቅቱን ጠብቀው ሊያቀርቡ እና ከውስጥ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ሂደቶች በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡

188. በናሙና ተመርጠው በታዩት አራቱ ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር እና አዳማ) በሁሉም የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በአመቱም መጨረሻ የማያቀርቡ መሆኑ፤ እንዲሁም ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥራ ክፍሎች (የፋይናንስ

አስተዳደር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር፣ የገቢ ማመንጫ፣ የተከታታይ ትምህርት፣ የተማሪዎች አገልግሎት...) በቅንጅት አለመስራታቸው፤

189. በመሆኑም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችሉ በኦዲቱ ወቅት በውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስዱ እንዲደረግ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.15 በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት የሚገነቡ ግንባታዎች እና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች አስተዳደርን በተመለከተ

**አዋጅ ደንብና መመሪያ በተመለከተ፣**

190. ድርጅቱ የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት እንዲያስችለው የመቋቋሚያ አዋጁና ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮች በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ሊያስፀድቅ እንዲሁም ድርጅቱ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ግንባታ እና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር እንዲያስችለው የወጣውን ደንብ መሰረት በማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣና መመሪያውን ተግባራዊ ሊያደረገ ይገባል፡፡

191. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ድርጅቱ ዘግይቶም ቢሆን የተሰጠውን ሃላፊነትና ተግባር በብቃትና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት እንዲያስችለው የመቋቋሚያ አዋጁና ደንቡ እንዲሻሻልለት ያጋጠሙትን ችግሮ በጥናት አስደግፎ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በእንቅስቃሴ ላይ ቢገኝም በወቅቱ እንዲሻሻልለት አለመደረጉ
- ድርጅቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የግንባታ መመሪያዎች ቢጠቀምም መቋቋሚያ ደንቡን መሰረት ያደረገ እና የድርጅቱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የራሱ የግንባታ የአፈፃፀም መመሪያ አለማውጣቱ፤
- ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የካቲት 1999 ዓ/ም የወጣ መመሪያ ቢኖርም በስራ ላይ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑ ድርጅቱ ጥናት አድርጎ

ክፍተቶችን ለማስተካከል በሂደት ላይ ቢገኝም በዚህ ዘርፍ የተፈጠሩ ከፍተኛ ችግሮችን በወቅቱ ለመፍታት ያስችለው ዘንድ መመሪያው በወቅቱ እንዲሻሻል አለማድረጉ፤

**ድርጅቱ የተሟላ የሰው ሃይልና አደረጃጀት ያለው መሆኑን በተመለከተ ፣**

192. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ የሰው ሃይል ሊኖረው ይገባል፡፡

193. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ መዋቅር የተፈቀደው ቦታና የሰው ሀይል ሲታይ ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅሩን መሰረት ያደረገ በቂ እና የተሟላ የሰው ሃይል የሌለው መሆኑ፤

**ኤርፖርቶች ለመገንባት በቅድሚያ የሚደረግ የአዋጪነት ጥናት ስለመኖሩ በተመለከተ፣**

194. በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች በአዋጪነት ጥናት ላይ እንዲመሰረቱ እና በጥናቱ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

195. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተገነቡ እና በመገንባት ላይ ያሉ ኤርፖርቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የመልካአ ምድራዊ አቀማመጥ ወዘተ መሰረት ያደረገ የአዋጭነት ጥናት አለመደረጉ፤

196. ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው ኤርፖርቶች መሪ ዕቅድ/Master Plan/ ሊኖራቸው እና በክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ የተገነቡም ሆነ የሚገነቡ የማስፋፍያ እና አዳዲስ ግንባታዎች የኤርፖርቱን መሪ ዕቅድ /Master Plan/ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

197. ድርጅቱ ከሚየስተዳድራቸው አስራ ሰባት ኤርፖርቶች ውስጥ ስምንት ኤርፖርቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /Title Deed/ ፣ አስራ ሁለት ኤርፖርቶች የመሬት አጠቃቀም ፕላን/Land use plan/ እና መሪ ዕቅድ/Master Plan/ የሌላቸው መሆኑ፤

**የድርጅቱ ግንባታዎች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና የኮንትራት ዋጋ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ**

198. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ እና ገንዘብ ተገንብተው ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

199. የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ / **በቀናት**/ እና ገንዘብ /**በብር**/ ተገንብተው ስለመጠናቀቃቸው ሲታይ ፣ በድርጅቱ የተገነቡ እና በመገንባት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በዕቅድ ከተያዘላቸው ገንዘብ ከብር 3,151,187.27 /15%/ እስከ ብር 17,936,899.42 /34%/ እና ጊዜ ከ65 /15%/ ቀን እስከ 559 /266%/ ቀን ድረስ የወሰዱ መኖራቸው፤

**የተጠናቀቁ ግንባታዎች ርክክብ የተደረገላቸው እና በተገባላቸው ውል መሠረት ስለመሰራታቸው እንዲሁም በታዩ ግድፈቶች ላይ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፣**

200. ግንባታቸው የተጠናቀቁ መሰረተ ልማቶች ጊዚያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኂላ የመጨረሻ ርክክብ ሊደረግና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

201. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በድርጅቱ በናሙና ከታዩ አብዛኞቹ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የድርጅቱ መሰረተ ልማቶች በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶች /Defects/ ካሉ በመለየት እና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ጊዚያዊ ርክክብ ከተደረገላቸው ቀን ጀምሮ 365ኛውን ቀን ጠብቆ የመጨረሻ ርክክብ አለማድረጉ፤
- እንደዚሁም የአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ግንባታ ጊዚያዊ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ365 ቀናት በኂላ የመጨረሻ ርክክብ በማድረግ በውሉ መሰረት ተግባራዊ ያልተደረጉና የታዩ ግድፈቶችን /Defects/ በመለየት ድርጅቱ ህጋዊ እርምጃ በወቅቱ ሊወስድ ባለመቻሉ፡-
  - የህንፃው ጣሪያ በክረምት ወቅት ዝናብ የሚያንጠባጥብ በመሆኑ መንገደኞች፣ ሰራተኞች፣ ተከራይተው በንግድ ተሰማርተው የሚገኙ ነጋዴዎች ለ10 አመታት ያህል በፍሳሽ ከመቸገራቸው በተጨማሪ አብዛኛው የኤርፖርቱ ተጠቃሚዎች የውጭ ዜጎች በመሆናቸው በአገር ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳደሩ፣

- ድርጅቱ ህንፃውን የመጨረሻ ርክክብ ሳያደርግ ለ10 አመታት ያህል በመጠቀሙ፣ በግንባታ ወቅት የታዩ ግድፈቶችን በወቅቱ እንዲስተካከሉ ማስደረግ ያልቻለ በመሆኑ፣ በግንባታ ወቅት አማካሪ ድርጅት የነበረው በተለያየ ጊዜ የድርጅቱን ስም በመቀያየሩ ለማግኘት አለመቻሉ እና የስራ ተቋራጩ ብዙ ወጪ በማውጣት ጥገና ቢያደርግም መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ ባለመቻሉ ምክንያት ድርጅቱ የታዩት ግድፈቶችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ወደ ህግ ቢወስደው ሊያሸንፍ የሚችልበት እድል የጠበበ በመሆኑ ከተቋራጩ ጋር መደራደርን በመመምረጡ የህንፃውን ጣሪያ ሙሉ ለሙሉ ለመቀየር በግርድፉ ከሚየስፈልገው USD 3,210,570.00 ውስጥ 60% 1,926,342 USD እንዲሸፍን የተገደደ መሆኑ፤

**ኤርፖርቶች አስተማማኝ ደህንነት ያላቸውና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን በተመለከተ**

202. ድርጅቱ ለአይሮፕላኖች፣ ለመንገደኞችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝና ቀልጣፋ የኤርፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

203. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ሁሉም ኤርፖርቶች ውስጥ የሚገኙ አይሮፕላኖች፣ መንገደኞች እና ሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚየስችል በተሟላ መልኩ የዙሪያ አጥር፣ ደረጃውን የጠበቀ በቂ የጥበቃ ማማ፣ አገልግሎት የሚሰጥ የለሊት የዙሪያ አጥር መብራት፣ ጥራታቸውን የጠበቁ የፍተሻ አገልግሎት የሚሠጡ ማሽኖች፣ ለሚያርፉና ለሚነሱ አውሮፕላኖች የተሟላ የሜትሮሎጂ አገልግሎት እና የእሳት አደጋ ማጥፊያና መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፤

**የድርጅቱ ግንባታዎች ደረጃቸውን የጠበቁና በውሉ መሰረት እየተገነቡ መሆናቸውን በተመለከተ፡-**

204. በድርጅቱ የሚገነቡ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች በግንባታ ኮንትራት ውሉ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ መሰረት መግንባታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

205. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የጋምቤላ፣ የባህርዳር ኤርፖርቶችና የድርጅቱ ዋና መ/ቤት ግንባታዎች አፈጻጸም ሲታይ **በተሟላ መልኩ**

በግንባታ ኮንትራት ውል ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ መሰረት ግንባታቸው አለመጠናቀቁ፤

**ግንባታቸው ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መሰረተ ልማቶች ስርአትና፣ ቀጣይነት ባለው መንገድ፣ ጥገናና እድሳት እየተደረገላቸው መሆኑን በተመለከተ**

206. ድርጅቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ሊኖረውና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ በማውጣት ጥገናና ዕድሳት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

207. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ግንባታቸው የተጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የኤርፖርት መሰረተ ልማቶች የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ እድሳት እየተደረገላቸው አለመሆኑ፤

**ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን በተመለከተ**

**ድርጅቱ ያከራያቸው የኪራይ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የተቀመጠላቸው የኪራይ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ለጨራታ የሚቀርቡ ስለመሆናቸው በተመለከተ**

208. ድርጅቱ ለመኪና ማቆሚያ በየሁለት ዓመቱ፤ ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረጥ ነፃ ሱቆች፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቂያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመቱ እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ መደረግ አለበት፡፡

209. ይሁን እንጂ ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቂያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን

የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችኝ እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ ለማድረግ ጨረታ ቢወጣም ተከራዮች ባነሱት ክስ ምክንያት ተግባራዊ አለመደረጉ፤

**ተከራይ የኪራይ ውሉ ሳያከብር ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉን በተመለከተ**

210. ድርጅቱ ተከራይ የገባውን የውል ስምምነት ከጣሰ፣ ወይም የተከራየውን ይዞታ በንፅህና ካልያዘ፣ ተከራይ ውሉን ማቋረጥ ከፈለገ፣ ተመሳሳይ አሳማኝ ምክንያት በጽሑፍ ካቀረበ፣ ድርጅቱ ውል እንዲታደስ ለደንበኛው የውል እድሳት በጊዜ ገደብ አስታውቆ ምላሽ ካልሰጠው፣ ተከራይ በ3 ወራት ውስጥ የሚፈለግበትን ኪራይ አጠናቆ ካልከፈለ፣ ወይም ደርጅቱ ይዞታውን ለሌላ ተግባር ከፈለገው በነበረው ውል መሠረት ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡

211. ይሁን እንጂ ኤሮኖቲካል ላልሆኑ የገቢ ምንጮች በወጣው መመሪያ መሰረት ለሱቆች ፣ለምግብና መጠጥ በተርሚናል ውስጥ፣ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ፣ ለመጋዘን፣ለሃንጋር በኤርፖርቱ አስተዳደር የተገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለሱቅ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ለምግብና መጠጥ በተከራይ የሚገነባ፣ ለባዶ ቦታ ቢሮ በተከራይ የሚገነባ እና ለማስታወቅያዎች /የንግድ፣የመንገድ ዳር ወዘተ/ በየአምስት ዓመት እንደ አዲስ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ነባር ተከራዮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ጨረታ በማውጣት እንዲከራዩ ለማድረግ ጨረታ ቢወጣም ተከራዮች ባነሱት ክስ ምክንያት ተግባራዊ አለማድረጉ፤

**በጨረታ መከራየት ያለባቸው የድርጅቱ የኪራይ ቦታዎች የጨረታ ህጉን ተከትለው እየተከራዩ ስለመሆናቸው በተመለከተ**

212. ድርጅቱ ከአየር ትራንስፖርት ሥራ ጋር በተያያዘ ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቢሮ አገልግሎት ከሚጠቀሙባቸው ቢሮዎችና ካውንተሮች፣ ትናንሽ መጋዝኖች እና ሁለት ጊዜ የጨረታ ማስታወቅያ ወጥቶላቸው ተጨራቾች ላልቀረቡላቸው የኪራይ ይዞታዎች በስተቀር ሌሎቹን የጨረታ ህጉን ተከትሎ በጨረታ እንዲከራዩ ማድረግ አለበት፡፡

213. ይሁን እንጂ በኦዲቱ፤

- ለንደን ካፌ በ21/03/03 በቁጥር BIAA/7-54/3 በተጻፈ ደብዳቤ በመጀመሪያ የውል ስምምነት ላይ 109.9 ስኩ/ሜ. በአዲሱ ተርሚናል በጨረታ ያሸነፉበት ቦታ 2C2 ለስናክና ሬስቶራንት አገልግሎት የሚል መሆኑ ፣ሕዳር 08 /2003 ዓ.ም. በቁጥር PMD-8/05/03 በተጻፈ ደብዳቤ የቀረጥ ነፃ ሱቅ መደብር የውል ስምምነት ሳይኖራቸው ጊዜያዊ የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ቦንድድ መጋዘን 103 ካሬ ሜትር ቦታ መስጠቱ፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ 109.9 ካሬ ሜትር ቦታውን ይጠቀሙበት የነበረው ለስናክና ሬስቶራንት አገልግሎት ብቻ ሆኖ ሳለ ከሰኔ 29/ 2004 በቁጥር PMD- 8/22/04 በተጻፈ ደብዳቤ ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም. እስከ መስከረም 30 ቀን 2005 ድረስ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ ተብሎ የኪራይ ውል እድሳት መደረጉ፣
- ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በጨረታ አሸንፎ እ.ኤ.አ. July 24/2006 ውል የፈረመበትን 58.72 ካ.ሜ ይዞታ ለአልኮል መጠጦች መሸጫ አገልግሎት የተከራየው ቦታ ድርጅቱን ሳያስፈቅድ ይዞታውን ከተከራየበት ጊዜ አንስቶ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ አገልግሎት እየተጠቀመበት እንደሆነ የካቲት 21/1999 ዓ.ም ለኤርፖርቶች ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ በፃፈው ደብዳቤ ለመረዳት እንደተቻለና ድርጅቱ ተከራዩ ውሉን መጣሱን ገልጾ ህጋዊ እርምጃ መወሰድ ሲገባው ሐምሌ 1/1999 ዓ/ም የኮርፖሬት ማርኬቲንግ መምሪያ ኃላፊ አገልግሎቱን ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ በመለወጥ ለአንድ ዓመት ውሉ እንዲታደስ ማድረጋቸው እና እስከ አሁን ድረስ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- ዲና ልኡልሰገድ እ.ኤ.አ በ18/8/06 በጨረታ አሸንፈው ለቁንጅና ሳሎንና ማሳጅ አገልግሎት ውል የፈረሙበት 53.05 ካ.ሜ ይዞታ ለ4 ዓመታት በዚሁ የአገልግሎት ዘርፍ የውል እድሳት ሲከናወን የቆየ ቢሆንም ደንበኛዋ በ11/9/02 አዲስ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ከተከራዩበት የንግድ ዘርፍ ውጪ ውሉን በመጣስ ዲና የተዘጋጁ ልብሶች መሸጫ በሚል የንግድ ዘርፉን ቀይረው ሲሰሩ ቆይተው በ2003 በተደረገ የውል እድሳት የልብሶችና ጫማዎች ሱቅ ተብሎ የታደሰ መሆኑ በመጨረሻ በ2004 ውል እድሳት ደግሞ በተከለሰው

ታሪፍ መሠረት የሀገር ባህል ልብሶች መሸጫ በሚል የታደሰ መሆኑ፤

- የቦሌ ዓለምአቀፍ ኤርፖርት የመንገደኞች መግቢያ ትኬት የጨረታ ሁኔታ በኦዲቱ ወቅት ሲታይ፤- የድርጅቱ ጨረታ ኮሚቴ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ/ም የተደረገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር ኢኤድጨኮ 225/ 101 መሠረት በቅድሚያ ኮሚቴው በጨረታ መክፈቻው ላይ ለተገኙ ተጫራቾች ስለተጨማሪ እሴት ታክስ የማብራሪያ ፅሁፍ እንደደረሳቸው ያረጋገጠ መሆኑንና በመቀጠልም ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች  የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጨምር በብር 4,510,000 የጨረታ ዋጋ ወስዶ እንዲሰራ ኮምቴው በሙሉ ድምጽ መስማማቱንና ለዋናው ስራ አስከያጅ የውሳኔ ሃሳብ ያቀረበ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የመግቢያ ትኬት ሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን፣ በተከራይ ግዴታዎች ንዑስ አንቀፅ 2.1 ላይ በዓመት ብር 4,510,000 ተከራይ ለመክፈል መስማማቱን ተገልፆ በንዑስ አንቀጽ 2.4 ላይ ግን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጨምር፤ በመንግስት የሚፈለጉ ማናቸውም አይነት ክፍያዎች በሙሉ ለሚመለከተው የመንግስተት አካል መክፈል ያለበት በእራሱ በተከራይ ነው ተብሎ በመገለጹ ከጨረታ ኮሚቴ ውሳኔ ውጭ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል በመደረጉ፤-
  - መክፈል ያልነበረበትን በተከራይ ስም የ9 ወር ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 441,195.66 / 49021.47 * 9/ ያለ አግባብ መክፈሉ
  - በ2002 ዓ/ም ድርጅቱ በመግቢያ ትኬት ሽያጭ አገልግሎት ውል ማሻሻያ በማለት  በአንቀጽ 2 በንዑስ አንቀጽ 2.1 ላይ ከጨረታ ኮሚቴው ውሳኔ ውጭ ተከራዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይጨምር ብር4,510,000 እንዲከፍል መደረግ ሲገባው ወደ ብር 3,921,739.13 እንዲቀንስ መደረጉ፤፡ ይህ ደግሞ ድርጅቱ ከተከራዩ ማግኘት የነበረበትን ብር 588,260.87 እንዲያጣ እና ተከራዩ ያለ አግባብ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረጉ፤
- እንደዚሁም ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ከሚያስገኙ በክልል ኤርፖርቶች ከሚገኙ ተከራዮች በጎንደር አፄ ቴዎድሮስ

በጨረታ 13 ያለጨረታ 31 ፣ በመቀሌ አሉላ አባነጋ በመነሻ ዋጋ 21፣ በጨረታ 3 ፣ በአርባ ምንጭ በመነሻ ዋጋ 6፣ በጨረታ 3 ፣ ባህርዳር ግንቦት 20 በመነሻ ዋጋ 40 ፣ በጨረታ 1፣ በላሊበላ በጨረታ 9፣ በድርድር 23 እና በአክሱም አፄ ዮሐንስ በመነሻ ዋጋ 36፣ በጨረታ 3 በድምሩ በጨረታ 32፣ ያለጨረታ 31 ፣ በድርድር 23 እና በመነሻ ዋጋ 103 የተከራዩ መሆኑ ይሁንና በጨረታ ተከራዩ የተባሉት ለተከራዮች ጥሪ የተደረገው በኤርፖርት አካባቢ በኮምፒዩተር በተጻፈ ጽሁፍ በመለጠፍ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ መሆኑ መገለጹ፣ ሁሉም የአካባቢው ህብረተሰብ በሚያየው ቦታ የተለጠፈ ስለመሆኑና ለስንት ቀናት እንደቆየ ለማወቅ አለመቻሉ፣ እንዲሁም በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት በጋዜጣ እንዲወጡ ያልተደረጉ በመሆናቸው ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል በማያስችል እና ህግን ያልተከተለ መሆኑ፤

**በክልል ኤርፖርቶች በድርድር የሚከራዩ ቦታዎች በመመሪያው መሰረት የድርድር ኮሚቴው ቦታውን ለተከራዩ ከማስረከቡ በፊት ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቁን በተመለከተ**

214. በድርድር የሚከራየው ቦታ በክልል ኤርፖርቶች ከሆነ ከስድስት ወራት እስከ አንድ አመት ለሚሆን ጊዜ የኤርፖርት ሀላፊዎች የሚያቀርቡትን መነሻ መሰረት በማድረግ የድርድር ኮሚቴው ለተከራዩ ውል አዋውሎ ቦታውን ከማስረከቡ በፊት ውሉን ለዋና ሥራ አስኪያጁ አቅርቦ ማስፀደቅ አለበት፡፡

215. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመቀሌ አሉላ አባነጋ ኤርፖርት 3 እና በላሊበላ ኤርፖርት 23 የኤርፖርት ይዞታዎች በድርድር የተከራዩ መሆናቸው፤፡ የመቀሌ ኤርፖርት ስራ አስኪያጅ ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የክልል ስራ አስኪያጆች በራሳቸው ማፅደቅ እንዲችሉ የስልጣን ውክልና እንደተሰጣቸው ቢገልፁም የተሰጣቸው የስልጣን ውክልና በድርድር ለሚከራዩ ሳይሆን በግልፅ ጨረታ ለሚከራዩ መሆኑ፤

**ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች ጥናት በማድረግ በየአመቱ ተመጣጣኝ ኪራይ ጭማሪ እየተደረገ ስለመሆኑ በተመለከተ**

216. ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የወቅቱን የዋጋ

ግሽበት /Inflation/ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ከተደረገ በተመጣጣኝ በየዓመቱ ኪራይ መጨመር አለበት፡፡

217. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ከአንድ ዓመት በላይ የውል ቆይታ ጊዜ ላላቸው ይዞታዎች የኢንቨስትመንት ወጪዎች ግምት ውስጥ ያስገባ፣ የወቅቱን የዋጋ ግሽበት /Inflation/ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ እና በመንግስት የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ /Devaluation/ ስለመኖሩ በማየት በ10 ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ ያደረገ ቢሆንም ተከታታይነት ባለው መልኩ እና ተመጣጣኝ የኪራይ ጭማሪ አለማድረጉ፤

**ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ**

218. ድርጅቱ የአከራይ እና የተከራይ ውልን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

219. ይሁን እንጂ፡-

- ተከራዮች የሚገለገሉበት ቦታዎች ስፋት መጠን ከድርጅቱ ጋር በተዋዋሉበት የአከራይ እና ተከራይ ውል መሠረት መሆኑን ድርጅቱ ክትትልና ቁጥጥር አያደረገ አለመሆኑ፤ በተርሚናል አንድ /መናፈሻ/ በናሙና ከታዩት ስድስት ደንበኞች ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በድምር 1822.41 ካ/ሜ እንደሆነና ድርጅቱ በአመት ብር 1,783,672.00 እያጣ መሆኑ፣ በተርሚናል ሁለት /ዲፓርቸር/ በናሙና ከታዩት ሰባት ደንበኞች ከውሉ ውጭ ክፍያ ሳይከፍሉ የሚገለገሉበት ቦታ በድምር 145.58 ካ/ሜ እንደሆነና ድርጅቱ በአመት ብር 714,142.10 ከሁለቱም ተርሚናሎች በናሙና ከታዩት ቦታዎች በዓመት በድምሩ ብር 2,497,814.80 እያጣ መሆኑ፤
- ድርጅቱ ለንደን ካፌና ሳተላይት ሬስቶራንት ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም 110 ካ.ሜ ባዶ የመጋዘን ቦታ በካሬ ሜትር በብር 1,100.00 መከራየት ሲገባቸው በኪችን ዋጋ በካሬ ሜትር በዓመት ብር 812 ሂሣብ ተወስኖ ለ5 አመታት ፀንቶ የሚቆይ የኪራይ ውል በመፈራረሙ ምክንያት ደንበኛው የመጋዘን ቦታን በኪችን ዋጋ ከተከራዩበት ቀን ጀምሮ የታሪፍ ክለሳ እስከተደረገበት እስከ ሰኔ

30/2003 ዓ.ም ድረስ  በካ.ሜ በብር 1100 ሂሣብ እንዲከፍሉ ባለመደረጉ፣ ድርጅቱ ሊያገኝ ይችል የነበረው ብር 81,839.00 ማጣቱ፤

- የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የኪራይ ተመን ለውጥ  የተደረገ ቢሆንም  በኩሽና ኪራይ ዋጋ ላይ ለውጥ አለመደረጉ፣ ነገር ግን ቀደም ብሎ የኩሽና ኪራይ ተመን ብር 812 የሆነበት ምክንያት የዋናው ይዞታ (የሬስቶራንቱ) ተመንን በ2/3 በማብዛት (1218X2/3) ስለሆነ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የኩሽና ኪራይ ዋጋም የዋናው ይዞታ ታሪፍ 2/3 ሊሆን ሲገባው  የገበያ ልማት ዳይሬክቶሬት በጥናቱ ውስጥ ስላላካተተው ተግባራዊ አለመደረጉ፣ ይህ የኩሽና ይዞታ እንደሌሎቹ ይዞታዎች ሁሉ ታሪፍ ባለመስተካከሉ ምክንያት የሎው ስፖት እና ሎንደን ካፌና ሬስቴራንት የተባሉትን 2 ድርጅቶች በናሙና ሲታዩ ድርጅቱ በ2004 በጀት ዓመት ብቻ  ሊያገኘው  ይገባ  የነበረ  ብር 221,990.76 ገቢ ማጣቱ፤
- በሌላ በኩል የታሪፍ  ክለሳ ተግባራዊ የተደረገው ከሐምሌ 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም የለንደን ካፌና ሬስቶራንት 103 ካ.ሜ ይዞታ በአዲሱ ታሪፍ መሠረት ውል የታደሰው ከህዳር 1/2004 እስከ ጥቅምት 30/2005 በመሆኑ በአዲሱ ታሪፍ  ለካሬሜትር ብር 4100 መሠረት ሊከፍሉበት የሚገባው  የ103 ካ.ሜ ቦታ ለ4 ወራት በቀድሞው ታሪፍ ብር 1100 ሂሣብ በመታደሱ ድርጅቱ  ሊያገኘው ይገባ የነበረ ብር 12,000 ማጣቱ፤
- ድርጅቱ ይዞታዎችን ሲያከራይ ደንበኞች በይዞታዎቹ ላይ ጉዳት ቢያደርሱ ለማስተካከያ የሚሆን ገንዘብ (Pledge) ውል ሲፈርሙ ወይም ኮንትራታቸው ሲታደስ እንዲያስይዙ የሚያስገድድ ቢሆንም ጉዳዩ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የተወሰኑ ተከራዮች ማስያዝ ካለባቸው የገንዘብ መጠን ያነሰ  እንዲያስይዙ ሲፈቀድ ሌሎች ደግሞ ከነጭራሹ ሳያስይዙ በመቆየታቸው ታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም መጨረሻ በተወሰደ መረጃ መሠረት ከ2 ሚሊዬን ብር በላይ በወቅቱ መያዝ የነበረበት  የመያዣ ገንዘብ መኖሩ፤

**<u>ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ</u>**

220. ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኔቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

221. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ ኤርፖርቶችን ለመገንባትና ኤሮኖቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከክልል ኤርፖርቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

222. በመሆኑም የኤርፖርቶች ድርጅት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በኤርፖርቶች ግንባታ፤ የፋሲሊቲዎች አጠቃቀምና ደህንነት አጠባበቅ ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.17 በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ

**የመድኃኒት አቅርቦትና ክትትልን በተመለከተ**

223. ተመጣጣኝና ተገቢ የመድኃኒት ክምችትና እና ያልተቋረጠ አቅርቦት የሚኖርበት ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የመድኃኒት ብክነት እና እጥረት እንዳይደርስ ለመከላከል የተጠናከረ የመድኃኒት ክምችትና ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

224. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የመንግስት ሕክምና መስጫ ተቋማት እንደታየው፤ የመድሃኒት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም፣ አሁንም የአቅርቦት መቆራረጥና ክፍተት መኖሩ በተለይ የኬሚካሎችና ላብራቶሪ ሪኤጀንቶች (Chemicals and lab-reagents) አቅርቦት ከፍተኛ እጥረት መኖሩ፤ በተጨማሪም በናሙና በታዩት በሁሉም (17) ጤና ተቋማት ኤጀንሲው የተጠየቁትን መድሃኒቶች ሙሉ ለሙሉ ማቅረብ እንዳልቻ የገለፁ ሲሆን፤ በፌለገ-ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል በ1/2/2006 ዓ.ም በተደረገ ጉብኝት በሆስፒታሉ መድሃኒት

ማከማቻ መጋዘን 42 አይነት አስፈላጊ መድሃኒቶች ምንም ክምችት አለመገኘቱ፤

**የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖችን በተመለከተ**

225. ለመድኃኒት አያያዝ አመቺ የሆኑና ለየአካባቢው የአየር ጠባይ የሚስማሙና የተደራጁ ዘመናዊ መጋዘኖች በሁሉም ክልሎች ሊቋቋሙ ይገባል። የመረከቢያ፣ የማከማቻና የማስረከቢያ መጋዘኖች የተለያዩ መሆን አለባቸዉ።

226. ኤጀንሲው አስራ አንድ የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ያሉት ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ አራት በኦሮሚያ፣ ሶስት በአማራ፣ አንድ በደቡብ፣ አንድ በትግራይ፣ አንድ በድሬዳዋ እንዲሁም አንድ በአዲስ አበባ ሲገኙ የተቀሩት ክልሎች፤ ማለትም ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ እና አፋር የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘን የሌላቸው መሆኑ፤

227. በናሙና ተመርጠው ከተጎበኙ 17 የመንግስት ጤና ተቋማት መካከል የአስሩ ተቋማት መድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች ዘመናዊና ለአካባቢው አየር ጠባይ ተስማሚ ተደርገው የተሰሩ አለመሆናቸው፤፡

228. በናሙና የታዩት የጅማ፣ የነቀምቴ፣ የባህርዳር እና የደሴ ቅርንጫፎች የማስረከቢያና የመረከቢያ ቦታ የተለያዩ ባለመሆናቸው በአንድ ቦታ ተደራራቢ ስራዎች እንዲከናወኑ ማድረጉ፤ በተለይም በጅማ እና ደሴ ቅርንጫፎች ከፍተኛ የመድሃኒት ማከማቻ የቦታ ጥበት ያለበት መሆኑ፤

229. ለመረከቢያ፣ ለማከማቻና ለማስረከቢያ መጋዘኖች አገልግሎት የሚውሉ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች (የሙቀት መለኪያዎች፣ ፎርክሊፍት፣ ጋሪ፣ ፓሌት፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶች ወዘተ) መሟላት አለባቸው።

230. በናሙና ከታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች አብዛኛዎቹ ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ያልተሟሉላቸው መሆኑ በኦዲቱ በታዩ የኤጀንሲ ቅርንጫፍ መጋዘኖች ላይም ተመሳሳይ ችግር መኖሩ፤ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና በጳውሎስ ሆስፒታል ለመድሃኒት ክምችት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች የሌሏቸው ሲሆን፤ በጅማ፣ ደሴና ባህርዳር የኤጀንሲው ቅርንጫፎች ግብዓቶቹ ሙሉ ለሙሉ አለመሟላታቸው፤፡

231. ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ቁልፍ ባለው የብረት ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል መቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት ባለሙያ እጅ መሆን አለበት፡፡

232. በኦዲቱ ተመርጠው በናሙና ከታዩት 17 መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በ15 ተቋማት የመድሃኒት መጋዘኖች ውስጥ ለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የተለየ ሳጥንም ሆነ የተለየ ባለሙያ አለመኖሩ፤፡ በተጨማሪም በኤጀንሲው የጅማ ቅርንጫፍ የሚገኘው የተለየ ሳጥን ቁልፍ የተበላሸ መሆኑ፤

**የመድሃኒቶችን ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ**

233. በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በመንግስታዊ የሕክምና መስጫ ጤና ተቋማት የሚኖረዉ የክምችት መጠን ከሚፈለገዉ በታች ወይም በላይ እንዳይሆን ወይም በአጠቃላይ ከክምችት ጠፍቶ ችግር እንዳይፈጠር የክምችት መጠን አመላካቾች (Average monthly consumption, Minimum stock level, safety stock Level) በየደረጃዉ (በማዕከልና በቅርንጫፍ መጋዘኖች እንዲሁም በጤና ተቋሞች) በሥራ ላይ ማዋል አለባቸዉ፡፡

234. በናሙና ከታዩ መንግስታዊ ጤና ተቋማት መካከል በቦንጋ ፣ በጋምቤላ፣ በኡኬ፣ በጢጣ እና በጉቴ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በጥቁር አንበሳና ጳውሎስ ሆስፒታሎች የመድሃኒት መጠን አመላካቾቹ ስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤

**የመድሃኒት ቆጠራ ሪፖርትን በተመለከተ**

235. ማንኛዉም በኤጀንሲዉ የሚገኝ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያዎች ክምችት ቆጠራ በበጀት ዘመኑ ማብቂያ ሊደረግ እና የቆጠራው ዉጤትም ከሐምሌ 30 በፊት ተጠቃሎ ሪፖርት ሊቅረብበት ይገባል፡፡

236. በኦዲቱ የታዩት የጅማ፣ ነቀምቴ፣ ባህርዳር፣ ደሴ እና አዲስ አበባ ያሉ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የ 2005 ዓ.ም ቆጠራ ሪፖርት አጠቃለው ለማዕከል አለማቅረባቸው፤

**ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል መድሃኒት አወጋገድን በተመለከተ**

237. በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አግባብ ባለው መንገድ የሚወገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

238. በጤና ተቋማትና በኤጀንሲው ቅርንጫፎች በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ለማይውሉ መድኃኒቶች በህብረተሰቡና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገዱ የተዘረጋ ወጥ የሆነ ስርዓት ባለመኖሩ፣ በናሙና በታዩት የኤጀንሲው ቅርንጫፎችና ጤና ተቋማት ጥቅም የማይሰጡ መድሃኒቶችና ሕክምና መገልገያዎች ጉድጓድ ተቆፍሮ እንዲቃጠሉ የሚደረግ መሆኑ፤

**የመድሃኒቶች ማስወገጃ የጊዜ ሰሌዳና የህክምና መሳሪያዎች ክምችትን በተመለከተ**

239. በመድሃኒትና ሕክምና መገልገያዎች ክምችትና ስርጭት መመሪያ እንደተቀመጠው በማዕከልና ቅርንጫፍ መጋዘኖች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶች በየሩብ አመቱ መጨረሻ የተቆጣጣሪው ባለስልጣን ተወካዮች ባሉበት እንዲወገዱ የማስወገጃ ሰርተፊኬት (Disposal certificate) በወቅቱ እንዲቀርብ ክትትል መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ለተጠቃሚው ቀርበው ለ5 ዓመት እንቅስቃሴ ያላሳዩ ወይም አዝጋሚ እንቅስቃሴ ያላቸው (በሚፈለገው መልኩ ለተጠቃሚው አገልግሎት የማይሰጡ) የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር ለሚመለከተው አካል እየቀረበ እንዲወገዱ ወይም በክምችት እንዲቆዩ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

240. በናሙና በታዩት የነቀምት፣ የጅማ፣ የባህርዳር፣ የደሴ እና የአዲስ አበባ የኤጀንሲው ቅርንጫፎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈ መድኃኒቶችን ለማስወገድ ቋሚ የሆነ የማስወገጃ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ፤ በጋምቤላ፣ በደሴ፣ በፈለገ ህይወት ሆስፒታሎች እንዲሁም በኤጀንሲው የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ የተለያየ አይነት ያላቸው የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ጥቅም ሳይሰጡ እና በኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

**ለመድሃኒቶች ብልሽት መንስዔዎችን መለየትና እርምጃ መውሰድን በተመለከተ**

241. የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ በማወቅ ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡

242. በኦዲቱ በታዩት አምስት የኤጀንሲው ቅርንጫፎችም ሆነ 17 የመንግስት ጤና ተቋማት በስራቸው የሚወገዱትን መድኃኒቶችና የሕክምና

መገልገያዎች ጥቅም ላይ የማይውሉበትን ምክንያትና መንስኤ ለማወቅ የተደረገ ጥናት አለመኖሩ፤

**ለመድሃኒቶች ብልሽት መንስዔዎችን መለየትና እርምጃ መውሰድን በተመለከተ**

243. ለጤና ተቋማት ወጪ የሚደረገው መድኃኒትና የሕክምናመገልገያዎች ወደ ተቋማቱ ለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

244. ለመደበኛ የግዥ መድሃኒቶች ኤጀንሲው መድሃኒቶቹ ወደ ጤና ተቋማቱ ለመድረሳቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት የሌለ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት በአዲስ ህይወት ሆስፒታል በ2002 ዓ.ም ብር 110,000፣ በአሶሳ ዞን ጤና ፅ/ቤት በ2001 ዓ.ም ብር 197,575፣ በአባይ ጤና ጣቢያ በ2003 ዓ.ም ብር 38,429፣ በባህርዳር አስተዳደር ጤና ፅ/ቤት በ2003 ዓ.ም ብር 23,436፣ በማሻ ጤና ጣቢያ በ2005 ዓ.ም ብር 46,000 እና በገንጂ ጤና ጣቢያ በ2005 ዓ.ም ብር 113,702 የሚያወጡ መድሃኒቶች ወደ ጤና ተቋማቱ ሳይደርሱ ሊጭበረበሩ ሲሉ ተይዘው ጉዳዩ በህግ እንዲታይ የተደረገ መሆኑ፤

**የመድሃኒቶች ማጓጓዝ ሂደትን በተመለከተ**

245. ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶች ለመንግስት ጤና ተቋማት የሚቀርብበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

246. ኤጀንሲው መድሃኒቶችን ወደ ጤና ተቋማት የሚያሰራጨው በመድሃኒት አያያዝ ዙሪያ ትምህርት ባልወሰዱ ሹፌሮች አማካይነት መሆኑ፤

**መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማት ማጓጓዝን በተመለከተ**

247. የማዕከል መጋዘኖችና ቅርንጫፎች አገልግሎት ለሚሰጧቸው የመንግስት ጤና ተቋማት በሚወጣው የስርጭት ፕሮግራም መሰረት እስከ ተቋማቱ በማጓጓዝ ማስረከብ አለባቸው፡፡

248. ቅርንጫፎች መድሃኒቶችን እስከ ጤና ተቋማቱ በማጓጓዝ ማስረከብ ቢኖርባቸውም፣ ለመደበኛ መድሃኒቶች እና የፀረ ኤችአይቪ ኤድስ ክትትል ለማይሰጡ ጤና ተቋማት መድሃኒቶችን እስከ ተቋማት የማጓጓዝ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

**መድሃኒቶችን በጤና ተቋማት ፍላጎት መሰረት ማቅረብን በተመለከተ**

249. ለጤና ተቋማት የሚደረገው የመድኃኒት ክፍፍል የጤና ተቋሙ በሚልከው የመድኃኒት ፍላጎት መሰረት መሆን አለበት፡፡

250. በናሙና ከታዩት መንግስታዊ የህክምና መስጫ ተቋማት መካከል በነቀምት ቅርንጫፍ ስር የጉቴ ጤና ጣቢያ፣ የኡኬ ጤና ጣቢያ አና የነቀምቴ ሪፈራል ሆስፒታል እንዲሁም በጅማ ቅርንጫፍ ስር የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የአጋሮ ጤና ጣቢያ፣ የሰርቦ ጤና ጣቢያ፣ የቦንጋ ጤና ጣቢያ፣ የጋምቤላ ጤና ጣቢያ እና የጋምቤላ ሆስፒታል የሚላክላቸው መድሃኒት ፍላጎታቸውን መሰረት ከማድረግ ይልቅ በግዴታና አገልግሎት ማብቂያቸው የቀረቡ መድሃኒቶች የሚለክላቸው መሆኑ፤ በደሴና ባህርዳር ቅርንጫፍ ግልጋሎት የሚያገኙ ጤና ተቋማትም ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው መሆኑ፤

**የመድሃኒቶች ማጓጓዣ ስርዓትና የመድን ሽፋንን በተመለከተ**

251. ኤጀንሲው መንግስታዊ ጤና ተቋማት ላይ በሚያደርገው ጉብኝትና ምልከታ መሰረት የተጠናከረ የማጓጓዣ አገልግሎት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

252. በኦዲቱ እንደታየው ለኤጀንሲው ቅርንጫፎች የተመደቡት የመድሃኒት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ቅርንጫፎቹ መድሃኒት ከሚያሰራጩላቸው ጤና ተቃማት ብዛት ጋር ሲነፃፀር እጅግ ያነሰ መሆኑ፤

253. ከማዕከል መጋዘኖች ወደ ቅርንጫፎች ፤ ከቅርንጫፎች ወደ ማዕከል እና በቅርንጫፎች መካከል ለሚደረጊዉ የመድኃኒቶች ዝዉዉር በጉዞ ወቅት ለሚከሰት አደጋ እንደ አስፈላጊነቱ እና አመቺነቱ የመድን ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

254. ከቅርንጫፎች ወደ ማዕከል፣ ከቅርንጫፍ ወደ ቅርንጫፎ እና ከቅርንጫፍ ወደ ጤና ተቋማት ለሚደረግ የመድሃኒት ዝውውር የመድን ሽፋን የሌለው መሆኑ፤

**የመድኃኒት አያያዝ፣ አስተዛዘዝ እና አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠርን በተመለከተ**

255. የመድኃኒት አስተዛዘዝ፣ ዕደላና አጠቃቀም እንዲሁም በመድኃኒት ጎጂ ባህሪያት ዙሪያ የባለሙያ ክህሎት የሚጎለብትበት ተከታታይ ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

256. በኦዲቱ እንደታየው በኤጀንሲው በመደበኛነት የሚሰጠው የ IPLS (Integerated Pharmaceuticals Logistics Supply) ስልጠና ትኩረት የሚያደርገው የመድሃኒት አያያዝና አቀማመጥ ላይ ሲሆን፣ በመድሃኒት አስተዛዝ፣ ወጪ አደራረግ እና ግንዛቤ መፍጠር ላይ ከመድኒት መጋዘን ውጪ የሚሰሩ የሕክምና ባለሙያዎችን ክህሎት በማዳበር ዙሪያ ክፍተት መኖሩ፤

257. የኤጀንሲውን ራዕይ ለማሳካት በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይነት ያለው ትምህርት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

258. በኦዲቱ ተመርጠው በታዩት የጅማ፣ ነቀምቴ፣ ባህርዳር፣ ደሴ እና አዲስአበባ ባሉት የኤጀንሲው ቅርንጫፎች በመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰራ ሥራ አለመኖሩ፤

**በመድሃኒት ክምችትና ስርጭት ዙሪያ ኤጀንሲው ያለውን የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት እና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ**

259. የመድኃኒት ፍላጎት ለመተንበይ፣ ብክነትና እጥረትን ለመከላከል የሚያስችል የተጠናከረ የመረጃ ኔትዎርክ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

260. ኤጀንሲው አጠቃላይ የመደሃኒቶችን ክምችትና ስርጭት ለመከታተል እንዲያስችለው በቅርንጫፎችና ጤና ተቋማት የተቀናጀ የመድሃኒትና መገልገያዎች ክምችትና አቅርቦት ስርዓትን (Integrated Pharmaceuticals Logistics and Supply System- IPLS) ዘርግቶ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም ስርዓቱ በመረጃ ኔትዎርክ የተያያዘ ባለመሆኑ ቅርንጫፎች የጤና ተቋማትን የመድሃኒትና መገልገያዎች ክምችትን ለመቆጣጠር የሚያስችል አለመሆኑ፤ በተጨማሪም በናሙና ከታዩ ጤና ተቋማት መካከል ጋምቤላ፣ ኡኬ፣ ጉቴና አጋሮ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በጳውሎስና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች የ IPLS ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

261. በመሆኑም ኤጀንሲው በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በመድኃኒት እና የህክምና እቃዎች ግዢ፤ ክምችትና ስርጭት ረገድ በታዩ የአሰራር

ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.18 በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ *በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብን በተመለከተ*

**1. በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር መመርያ ስለመኖሩና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ስለመሆኑ፤**

262. በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ የጸደቀ የአሰራር መመሪያ ሊኖር ፣ ሂሳብ አሰላሉ መመሪያውን የተከተለና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

263. ይሁን እንጂ በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ አሰባሰብና አሰላልን በተመለከተ ኤጀንሲው ለሂሳብ አሰላል የሚጠቀመው የሽያጭ ውልና በተለያየ ጊዜ የጸደቀ የአሰራር መመሪያ ቢኖረውም አንድ ወጥ የሆነና ተቀናብሮ የጸደቀ አለመሆኑ እንዲሁም አሰላሉን የሚያግዝ ዘመናዊ ሶፍትዌር የሌለው መሆኑ፤

**ድርጅቶቹን የገዙ ባለሃብቶች የገቡትን ውል ተፈጻሚ ባያደርጉ ጉዳያቸውን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ ስለመቀመጡ፤**

264. ኤጀንሲው በተራዘመ ክፍያ ለሚሸጣቸው ድርጅቶች የሚያዘጋጀው ውል አስፈላጊ የውል ግዴታዎችን መያዝና በውሉ መሰረት ባይፈጸም ጉዳዩን ወደ ህግ ለመውሰድ የሚያስችል የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

265. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ሁሉም የልማት ድርጅቶች ፣ የሚፈለግባቸውን አመታዊ ክፍያ በገቡት ውል መሰረት ባይፈጽሙ ጉዳያቸው ወደ ህግ የሚሄድበት የጊዜ ገደብ በውሉ ውስጥ አለመካተቱ፤

**2. <u>በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግን ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት ለመሰብሰብ የሚያስችል በኤጀንሲው የተዘረጋ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ</u>**

266. በተራዘመ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ቀሪ ሂሳብ አልሚዎቹ በገቡት ውል መሰረት እንዲከፍሉ ኤጀንሲው በቂ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግና በወቅቱ መክፈል ላልቻሉትም መክፈል ያልቻሉበትን ምክንያት አጥንቶ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

267. በተራዘመ ክፍያ የልማት ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች የሚፈለግባቸውን ቀሪ ሂሳብ በወቅቱ እንዲከፍሉ ኤጀንሲው የሚያደርገው ክትትል ስለመኖሩ በኦዲቱ ሲጣራ ፣

268. አመታዊ የክፍያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት እንዲፈጽሙ ለማስታወስ በደብዳቤ ፣ ቦታው ድረስ ሄዶ በመነጋገርና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ከሠነዶችና ለባለሀብቶች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

269. በተጨማሪም ቀሪ እዳን ከመክፈል አንጻር በታዩ ችግሮች ዙሪያ ለባለሀብቶች መጠይቅ በመበተን ኤጀንሲው ጥናት ማድረጉን ህዳር 2005 ዓ.ም ከቀረበ ሪፖርት መረጃ ተገኝቷል፡፡

270. ይህም ሆኖ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽመው ውል ከገቡ በኋላ ቀሪ ክፍያቸውን በገቡት ውል መሰረት ያላጠናቀቁ ድርጅቶች ስለመኖራቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ እስከ ህዳር 30/2006 ዓ.ም. ድረስ መጠናቀቅ የነበረበት ከሃያ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ እና ከሁለት እስከ አምስት አመት የዘገየ ሂሳብ ብር 362,394,242.11 (ሶስት መቶ ስድሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) እና ፓውንድ 300,318.06 (ሶስት መቶ ሺህ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ከዜሮ ስድስት ፓውንድ) በፋይናንስ ሌጀር ተመዝግበው ከሚገኙ ባለሀብቶች የሚፈለግ ነገር ግን በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ፤

271. በመሆኑም በናሙና ከተመረጡት አስራ ስምንት ድርጅቶች ውስጥ በንጽጽር ከፍተኛ እዳ የተመዘገበባቸውን ስድስት ድርጅቶች በመለየት የግል ማህደሮቻቸውን በመከለስና ለባለሀብቶቹ ቃለመጠይቅ በማቅረብ እዳቸውን በወቅቱ ያልከፈሉበትን ምክንያትን ለማወቅ በተደረገው ማጣራት፤

- የቦሌ ቡልቡላ ጠጠር ማምረቻ ድርጅት ባለሀብቱ አክስዮን ማህበሩን ሲገዛ ፣ በአክስዮን ማህበሩ ስም የተመዘገቡ የመሬት ይዞታዎችን የመጠቀም መብት ለገዢው የተላለፈለት ቢሆንም ፣ ለጠጠር ማምረቻ እንዲሆን የተረከበው ቦታ ለኮንዶሚኒየም ግንባታ በመዋሉ በዚሁ ጉዳይ ክርክር ላይ መሆኑን፣

- አዲስ አበባ ራስ ሆቴል ፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከቀረቡት የንብረት ዝርዝሮች ውስጥ በንብረት ርክክብ ወቅት በብልጫ ለተገኘ የርክክብ ልዩነት ክፍያ ብር 7,745,069.00 ባለሀብቱ እንዲከፍል ኤጀንሲው ጥያቄ ቢያቀርብም ብር 4,959,895.00 ባለሀብቱ ሆቴሉን ከመረከቡ በፊት ለተወሰኑ የመኝታ ክፍሎች እድሳት የወጣ በመሆኑና ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት ክፍሎቹ የታደሱ መሆናቸውን አይቶ በመሆኑ የእድሳት ወጪው ሂሳብ እንደማይመለከተው ጥያቄ ያቀረበ መሆኑ፣
- ኢትዮጵያ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ ፣ ለምርት የሚሆኑ በርካታ ግብዓቶችን ከገዛ በኂላ ለማምረት የመብረት ኃይል አቅርቦት እጥረት ያጋጠመው መሆኑ፣
- ኮኮብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት በጨረታ ሰነዱ ላይ በዝርዝር የተቀመጡና የንብረት ርክክብ ቆጠራ ሲደረግ ያልተገኙ ንብረቶች በመኖራቸው ባለሀብቱ ድርጅቱን ሲጫረት ይኖረኛል ብሎ የገመተውና የተረከበው ንብረት ባለመጣጣሙ ልዩነቱ ከእዳዬ ላይ ይቀነስልኝ በሚል ለኤጀንሲው የሚያቀርባቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ምላሽ ያላገኘ መሆኑ፤
- የኮኮብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካን ፣ የሀዋሳ ዱቄት አክስዮን ማህበርን እና የታቦር ሴራሚክ አክስዮን ማህበርን የገዙት አንድ ባለሀብት ሲሆኑ ባለሀብቱ ድርጅቶቹን ሲጫረቱ ባቀረቡት ቢዝነስ ፕላን መሰረት ሰላሳ በመቶ የራሳቸውንና ሰባ በመቶ ከባንክ ለስራ ማስኬጃ በሚያገኙትን ብድር ሰርተው ሂሳቡን ሊከፍሉ ታሳቢ በማድረግ ሲሆን ፣ ነገር ግን ውሉ ባለሀብቱ የመጨረሻውን ሂሳብ ከፍለው ሳይጨርሱ በድርጅቶቹ ላይ የባለቤትነት መብት እንደማይኖራቸው ስለሚጠቅስ፣ ባለሀብቱ ለስራ ማስኬጃ ብድሩን ከባንክ ባለማግኘታቸው ክፍያውን በወቅቱ መክፈል ያልቻሉ መሆኑ፣

272. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በሰጡት መልስ ከድርጅቶቹ የሚፈለገው ቀሪ እዳ እንዳለ የሚታወቅ መሆኑንና ገንዘቡን ለማሰባሰብ በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥረት ተደርጎ ከአቅም በላይ የሆኑትን በህግ ክትትል እየተደረገ የሚገኝና በዚሁ መሰረት ከተጠቀሱት 30 ድርጅቶች ውስጥ 7ቱ በፍርድ ቤት በክስ ላይ የሚገኙና

ወደአፈጻጸም የተሸጋገሩ ሲሆን 23ቱ ደግሞ የክስ ሂደታቸው ተጀምሮ በህግ የተያዘ መሆናቸው፣

3. **<u>የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በተመለከተ</u>**

273. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በጨረታ ለመሸጥ በሚያቀርባቸው የጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎችን ትክክለኛነት ሰነዱ ለባለሀብቱ ከመቅረቡ በፊት ማረጋገጥ አለበት፡፡

274. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ አስራ ስምንት ድርጅቶች መካከል የንብረት ርክክብ በሚደረግበት ወቅት የንብረት ቆጠራው በጨረታ ሰነዱ ላይ ከቀረበው የንብረት ዝርዝር ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጉድለት የታየባቸው ሁለት ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆኑ ፣ እነርሱም

- የኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ በቁጥር 464 የቢሮ መገልገያ እቃዎች፣ 5 ማሽነሪዎች፣ 487 ቁልሶች እንዲሁም 7 ተሽከርካሪዎች በርክክብ ወቅት በተደረገው ቆጠራ ያልተገኙ መሆኑ
- የአዲስ አበባ ራስ ሆቴል በጨረታ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ በቁጥር አንድ ሚትስቡሽ መኪና 12 ኩንታል የመጫን አቅም ያለው ፣ 1 ቁልስ ፣ 159 የቢሮ እቃዎችና የመገልገያ መሳሪያዎች ፣ 12 የወዳደቁ ንብረቶች ፣ ሁለት ማሽነሪዎች በርክክብ ወቅት በተደረገው ቆጠራ ያልተገኙ መሆናቸው ፤ በኤጀንሲው ከሚገኝ የድርጅቶቹ ሰነዶች መረጋገጡ፡

275. በተጨማሪም ለተገኘው የንብረት ርክክብ ጉድለት ባለሀብቶቹ በጨረታ ሰነድ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተው በብልጫ የተገኙትን ንብረቶች ልዩነቱን እንዲከፍሉ ከተጠየቁት ሂሳብና ከቀሪ ክፍያቸው ላይ ማካካሻ እንዲደረግላቸው ቢጠይቁም፣ በጉድለት ለተገኙ ንብረቶች ተመላሽ እንዲሆን ወይም ማስተካከያ እንዲሰራ በውል ስምምነቱ ስላልተካተተ ማስተካከያውን ለመስራት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩ መገለጹ፤

**በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተጠናቀረ ዝርዝር መረጃ በኤጀንሲው ስለመኖሩ**

276. በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች መረጃ እና ማስረጃ በአግባቡ ተሰብስቦ በኤጀንሲው በመረጃነት የሚጠበቅበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል::

277. በኦዲቱ ወቅት የተገኘው የሰነድ ማስረጃ ከ1987-1997 ባሉት አስር አመታት 213 ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ወደ ግል ሲዛወሩ 3.13 ቢሊዮን ብር እና ከ1998-2003 ደግሞ 97 ድርጅቶች እና ቅርንጫፎች ወደ ግል ሲዛወሩ 5.6 ቢሊዮን ብር በድምሩ ባለፉት አስራ ስድስት ዓመታት 310 የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በጨረታ ሽያጭና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ግል ተዛውረው ብር 8.7 ቢሊዮን ገቢ እንደተገኘ ያሳያል፡፡

278. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጥቅል ማስረጃ ቢቀርብም ፣ በአጠቃላይ የተሸጡትን 310 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሟላ ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ በኤጀንሲው ማግኘት የልተቻለ መሆኑ፤

279. የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ለጉዳዩ በሰጡት መልስ ኤጀንሲው በመስከረም 2004 ዓ.ም ባዘጋጀው ብሮሸር ላይ የተቀመጠ ጥቅል ወደ ግል የተዛወሩ የልማት ድርጅቶች ብዛትና ለኦዲቱ ስራ ተጠይቆ በተሰጠ የድርጅቶቹ ዝርዝር መካከል የተፈጠረ የቁጥር ልዩነት መንስኤ አንድ ገዢ የገዛቸው እና በተለያየ ቦታ የሚገኙ ቅርንጫፎች አንድ ላይ የተመዘገቡ መሆኑን መግለጻቸው፤ በተጨማሪም በኤጀንሲው ከሚታተም መጽሄት (ዜና ፕመልድተኤ 2005) የተገኘ የድርጅቶች ዝርዝር መረጃ የቀረበ መሆኑ፣

280. በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ ላይ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ በኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ በተራዘመ ክፍያ የተሸጡና የሚጠበቅባቸውን ክፍያ የጨረሱ ድርጅቶች ዝርዝር ለኦዲት ስራው አለመቅረባቸውን እንደማያውቁ ገልጸው ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ባዘዙት መሰረት በደብዳቤ ቁጥር 30/ሐ8/4/59/2006 በቀን ጥር 20/2006 በዲፈርድ ክፍያ ከተሸጡ የልማት ድርጅቶች ውስጥ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ የ48 የልማት ድርጅቶች ዝርዝር የቀረበልን ቢሆንም የኦዲቱ ጊዜ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቀረበው ማስረጃ ላይ ዝርዝር ትንተና ለመስራት ያልተቻለ መሆኑ፤

በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ድርጅት በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በጨረታ የተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ሂሳብ አሰባሰብ ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች

ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 10.19 የወይራ ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር የሚሰጠውን የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት፣ የተለያዩ ግዢዎችን፣ የንብረት አስተዳደርንና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

**የአክሲዮን ማህበሩ ዕቅድ እና ክንውንን በተመለከተ፣**

281. አክሲዮንማህበሩ በፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት በጥናት ላይ የተደገፈ ዕቅድ ሊኖረውና ዕቅዱንም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

282. አክሲዮን ማህበሩ በፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ዕቅድ ያቀደ ቢሆንም፣ ዕቅዱ ግን በስታንዳርድና በገበያ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ፣ በተሽከርካሪ ወርሃዊና ዓመታዊ ምልልስ፣ በተጓጓዘ ጭነትና በተሰራ ሜትር ኪዩብ በኪሎ ሜትር ዕቅዱን አለማሳካቱ፤

**አክሲዮን ማህበሩ ጊዜን በቆጠበ መልኩ ነዳጅ መጫንና ማራገፍ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

283. አክሲዮንማህበሩ ጊዜን በቆጠበ መልኩ ነዳጅ መጫንና ማራገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና በመርሃ ግብሩም መሰረት መፈጸሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

284. አክሲዮን ማህበሩ ጊዜን በቆጠበ መልኩ ነዳጅ እየጫነና እያራገፈ አለመሆኑ፤ በዓመት አንድ ተሽከርካሪ በመጫንና በማራገፍ ሂደት አማካይ የጊዜ ቆይታ ለእያንዳንዱ ሞዴል ተሽከርካሪ ምን ያህል እንደሆነ አለማጠናቱ፤፣ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ መመሪያና መለኪያ የሚሆን ስታንዳርድ የሌለው መሆኑ፤

**ለሁሉም የከባድ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መጠናትን በተመለከተ፣**
**የተሽከርካሪዎች ምልልስ አፈጻጸም ክትትልን በተመለከተ፣**

285. የተሽከርካሪዎች ምልልስ በዕቅዱ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ባሉት ዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች(OBC እና GPS) መረጃዎችን በተገቢው በመጠቀም አፈጻጸማቸውን ሊገመግም ይገባል፡፡

286. ማህበሩ ስምሪቱን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቶ ስራ ላይ ባዋላቸው በOBC እና GPS መሳሪያዎች የሚጠቀም መሆኑ ቢታወቅም በነዚህ መሳሪያዎች አጠቃቀምና ክትትል አፈጻጸም ላይ ከሚጠበቀው በታች እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ተሽከርካሪዎች ላይ በተገጠመ GPS መሰረት በቀን 2 ጊዜ በየቡድኑ የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ሊታይ ይገባል ተብሎ በመመሪያ መልኩ ቢጸድቅም ከሁለት ቀናት በላይ ክትትል ሳይደረግ እንደሚቆይ ለመገንዘብ መቻሉ፤ ከአክሲዮን ማህበሩ ተሽከርካሪዎች ግማሹ OBC ግማሹ GPS የተገጠመላቸው ሲሆኑ፣ በነዚህ መሳሪያዎች በመጠቀም ተገቢውን ቁጥጥር በሚፈለገው ሁኔታ እየተከናወነ አለመሆኑ፤

**የደህንነት አልባሳት አጠቃቀም ክትትል መደረጉን በተመለከተ፣**

287. የደህንነት አልባሳት አጠቃቀም ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሳ የደህንነት አልባሳት አጠቃቀም ክትትል የማይደረግበት መሆኑ ሊረጋገጥ መቻሉ፤

288. የደህንነት አልባሳት አጠቃቀም ክትትል እየተደረገ እንዳልሆነ፣ የደህንነት አልባሳት አጠቃቀም በሁሉም መልኩ አንሶ እንደታየና ሴፍቲ እንደስራ አካል ተወስዶ አለመስራት ችግር እንዳለ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፣ በቅርቡ በተደረገው ለሊብያ ኦይል ኢትዮጵያ የሴፍቲ ኦዲት የአክሲዮን ማህበሩ ደረጃ ወርዶ መገኘቱ፤

## 2. <u>የጥገና ጋራዦች በቂና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በተመለከተ፣</u>

289. የጥገና ጋራዦች በቂና ደረጃቸውን(ስታንዳርዳቸውን) የጠበቁ ሊሆን ይገባል፡፡

290. ይሁን እንጂ፤ በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሳና የኦዲት ቡድኑ በአካል ጉብኝት ወቅት ባደረገው ምልከታ ደረጃውን የጠበቀ በማንኛውም የአየር ሁኔታ(በዝናብና በጭቃ) እንደልብ መስራት የሚያስችል ጋራዥ አለመኖሩ፤ የተሽከርካሪዎች የጥገና ቦታዎች አመቺ አለመሆናቸው፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለጥገና የሚያስፈልጉ ዘመናዊ ማሽነሪዎች የሌሉት መሆኑ፤

## 3. <u>በድንገተኛ አደጋ ወቅት አደጋን ለመከላከል ያለውን ቅድመ ዝግጅት በተመለከተ፣</u>

291. በአክስዮን ማህበሩ በሚገኙ ጋራዦች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮችና የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያዎች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ ሊቀመጡ ይገባል፡፡

292. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ መረጃ በሰበሰበባቸው በአክስዮን ማህበሩ በሚገኙ ጋራዦች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮችና በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያዎች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ እንዲቀመጡ አለመደረጉ፤

293. በተለይም በአክሲዮን ማህበሩ ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ያለው ጋራዥ በአደጋ ጊዜ እርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የስልክ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ አለመቀመጣቸውን፣ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያዎችም የሌሉት መሆኑን፤ ይህም ለጋራዡ የተዘጋጀ ቦታ (ሃንገር ) ባለመኖሩ ምክኒያት መሆኑ እና አደጋ ቢነሳ የሚያስከትልውን አስከፊ ጥፋት ለመከላከል አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጠር የሚችል መሆኑ፤

4. <u>የትራንስፖርት ሰነዶች ርክክብ በተመለከተ፣</u>

294. የትራንስፖርት ሰነዶችን ከስምሪት ሱፐርቫይዘሮች በየቀኑ ርክክብ መፈጸም ይገባል፡፡

295. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሣና በመስክ ጉብኝት ወቅትም ካገኘነው መረጃ የተወሰኑት ነገር ግን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን የያዙ ሰነዶች ከስምሪት ሱፐርቫይዘሮች በየዕለቱ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑ፣ ርክክቡ የሚከናወነው ያለሰነድ መሆኑንና የጭነት ማዘዣዎች ቅደም ተከተላቸው ተጠብቆ የማይሰሩ መሆኑ፤

296. አሽከርካሪዎች ወደ አዲስ አበባ ሳይገቡ ወደ ክልሎች ስለሚመላለሱ በተሽከርካሪዎች እጅ መስመር ላይ ስለሚዘገዩ የትራንስፖርት ሰነዶች ላይ በየዕለቱ ርክክብ አለመፈጸሙንና ርክክቡ የሚከናወነው ያለማረካከቢያ ሰነድ መሆኑን እንዲሁም የጭነት ማዘዣዎች ቅደም ተከተላቸው ተጠብቀው እንደማይሰሩ፤ በአብዛኛው በየዕለቱና በየሁለት ቀኑ በሰነድ የተደገፈ ርክክብ የሚፈጸም ቢሆንም የተወሰኑት ግን በወቅቱ ርክክብ የማይደረግባቸው መሆኑ፤ የትራንስፖርት ሰነዶች በየቀኑ ለዋናው መ/ቤት ለመላክ እንደሚከብድና አንዳንድ ጊዜ የጭነት ትዕዛዝ የታዘዘባቸው የጉዞ እና የገንዘብ ክፍያን የሚገልጹ ሰነዶች በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከ ሳምንት የሚቆዩ መሆኑ፤

## 5. የአክስዮን ማህበሩን ግዢ ስርዓትን በተመለከተ፣

### የአክስዮን ማህበሩን የጥቅል (bulk) ግዢ ስርዓትን በተመለከተ፣

297. ግዢዎች በፍላጎት ላይ የተመሠረቱና ዓመታዊ የግዢ ዕቅድ ወጥቶላቸው የዋጋ ቅናሽ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል በጥቅል እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡

298. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው አክስዮን ማህበሩ ዓመታዊ እቅድ ቢኖረውም የመለዋወጫ እና ጎማ ግዢ የተከናወነው በዕቅዱ መሰረት ሳይሆን በቁጥ ቁጥ ግዢ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ አክስዮን ማህበሩ የዋጋ ቅናሽ ተጠቃሚ እንዲሆን በጥቅል ግዢ እየፈጸመ አለመሆኑ፤

### በአክስዮን ማህበሩ የሚፈጸሙ ግዥዎች የግዥ ሥርዓትን ጠብቀው የሚከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፣

299. በአክስዮን ማህበሩ የሚፈጸሙ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የጎማና የመለዋወጫ ዕቃ ግዢዎች የተፈለገውን ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ ሊሆን ይገባል፡፡

300. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሣ በአክስዮን ማህበሩ የሚፈጸሙ አንዳንድ የመለዋወጫና የጎማ ግዢዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው፤

301. በ2004 በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ማጠቃለያ እና በማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ 046/04 ላይ እንደተገለጸው አክሲዮን ማህበሩ ከገዛቸው ጎማዎች መካከል የጥራት ችግር (የማኮፍኮፍ ወይም የመፈንዳት) የታየባቸው ጎማዎች በበጀት ዓመቱ ከተገዙት መሃል በብዛት የሚገኙ መሆኑ፤

### የገበያ ዋጋ ዳሰሳ (market survey) ጥናት ማድረግን በተመለከተ፣

302. አክስዮን ማህበሩ የመለዋወጪያ ዕቃዎችን የሀገር ውስጥና የውጪ አገር ግዢ ሲፈጽም የዋጋ መቆጣጠሪያ ስልት የገበያ ዋጋ ዳሰሳ (Market Survey) ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

303. በኦዲቱ ወቅት በተደረገው የዶክመንት ክለሣ አክስዮን ማህበሩ የመለዋወጫ እቃዎችን የሀገር ውስጥ ግዢ ሲፈጽም የዋጋ መቆጣጠሪያ

ስልት የገበያ ዋጋ ዳሰሳ (Market Survey) ለማድረጉ ማስረጃ አለመኖሩ፤፡

**እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው የገበያ ዋጋ ዝርዝር (price list) የሚከለስ መሆኑን በተመለከተ፣**

304. መለዋወጪያ ዕቃዎችና ጎማ ሲገዛ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር (Price List) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

305. ሆኖም በኦዲት ወቅት ለፋይናንስ ግዥና አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች በተደረገ ቃለ መጠይቅ የመለዋወጫ ዕቃዎችና ጎማ ሲገዛ በየስድስት ወሩ የተከለሰ የገበያ ዋጋ ዝርዝር (Price List) ቢዘጋጅም ተግባራዊ የማይደረግ ሲሆን ከአሮጌ ተራ የእቃዎች ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፤

**የአክሲዮን ማኅበሩን ንብረት አስተዳደር በተመለከተ፤**

**የተሸከርካሪ መረጃ ስምሪት፣ አያያዝ እና ጥገናን በተመለከተ፤**

**የተሸከርካሪን የህይወት ታሪክ፣ የስምሪት እንቅስቃሴና ገቢና ወጪ የሚያሳይ ማህደር መኖሩን በተመለከተ፣**

306. የተሸከርካሪና የተሳቢ የህይወት ታሪክ፣ የጥገና፣ የስምሪት እንቅስቃሴና የሚያስገቡት ገቢና ያስከተሉት ወጪ በጎን ቁጥርና ሰሌዳ ቁጥር የሚያሳይ የተዘጋጀ ማህደር ሊኖር ይገባል፡፡

307. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሣ ለእያንዳንዱ ተሸከርካሪና ተሳቢ በጎን ቁጥርና ሰሌዳ ቁጥር የተዘጋጀ የጥገና ማህደር እንጂ የስምሪት እንቅስቃሴን፣ የህይወት ታሪካቸውን የሚያሳይና የተሸከርካሪ ገቢና ወጪ መረጃ የያዘ ማህደር አለመኖሩ፤

**የተሸከርካሪዎችን ጥገና በተመለከተ፣**

308. በየጥገና ጋራዡ ለጥገና የቀረቡለትን ተሸከርካሪዎች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠግነው ሊወጡ ይገባል፡፡

309. ይሁን እንጂ አንዳንድ ተሸከርካሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥገናቸው እንደማይከናወን በዶክመንት ክለሣ ወቅትና ለስራ ኃላፊዎች በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

310. ስለሁኔታው የአክስዮን ማህበሩ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከ2004 ዓ.ም በኋላ የሲኖ ተሸከርካሪዎች የዲፈረንሺያል፣ የካምቢዮና የሞተር ብልሽት በከፍተኛ ሁኔታ በማጋጠሙ አንዳንድ ተሸከርካሪዎች ለበርካታ ጊዜያት እንደሚቆሙና ለምሳሌም የጎን

ቁጥራቸው 21-026፣ 21-030 እና 21-040 የሆኑ ተሸከርካሪዎች ከ4 ወራት በላይ በሞተር ብልሽት ምክኒያት መቆማቸውን፣እንዲሁም የጎን ቁጥሩ 21-001 ሚሌ ላይ ለአንድ ዓመት በጊር ቦክስ ምክንያት የቆመ መሆኑና ከ50ዎቹ መኪኖች ግማሾቹ ወደ ስራ ከገቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጊር ቦክሳቸው(ካምቢዮ) ተበትኖ  የተገጠመላቸው መሆኑ፤

**የቋሚ ንብረት ምዝገባ መከናወኑን በተመለከተ፣**

311. አክስዮን ማህበሩ የተሟላ የቋሚ ንብረት ምዝገባ ሊያከናውን ይገባል፡፡

312. በኦዲት ወቅት በተካሄደ የዶክመንት ክለሣ የአክስዮን ማህበሩ ቋሚ ንብረት መዝገብ ለነባር ንብረቶች የእቃው ዓይነት፣ መለያ ቁጥር፣ የተገዛበት ቀንና ዋጋ፣ የእቃ አቅራቢው አድራሻ፣ ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ(የስራ ክፍል እና እየተጠቀመበት ያለው ሰራተኛ) ከሚሉት በስተቀር ሌሎች በማኑዋሉ የተቀመጡ መረጃዎችን አሟልቶ በሚይዝ መልኩ የተዘጋጀ አለመሆኑ፤፣ አዲስ እየገቡ ያሉ ንብረቶችም ያልተመዘገቡ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

**ለአክስዮን ማህበሩ ጥቅም የማይሰጡ ንብረቶችን ህግንና ደንብን በጠበቀ መልኩ መወገዳቸውን  በተመለከተ፣**

313. በተለያዩ ምክንያት ለአክስዮን ማህበሩ ጥቅም የማይሰጡ ንብረቶች ህግንና ደንብን በጠበቀ መልኩ በወቅቱ ሊወገዱ ይገባል፡፡

314. ሆኖም በተለያዩ ምክንያት ለአክስዮን ማህበሩ ጥቅም የማይሰጡ ንብረቶች ህግንና ደንብን በጠበቀ መልኩ በወቅቱ እንዲወገዱ አለመደረጉ፤

315. አንድ በርሜል HD 80 W-140 የሆነ የተበላሸ ዘይት ለረዥም ጊዜ በእቃ ግምጃ ቤት መቆየቱ፤ ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ የማይውሉና ጊዜ ያለፈባቸው የብር 483,457.24 የመለዋወጫ ዕቃዎች እንዲወገዱ አለመደረጉ፤

316. በመሆኑም  የወይራ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በትራንስፖርት አገልግሎት አፈጻጸም፤ የግዢና ንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

## 10.20 የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ የማእቀፍ ግዢን በተመለከተ

**የአገልግሎቱ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን በተመለከተ፤**

የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስችል የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም (Human and Institutional Capacity) ሊኖረው ይገባል፡፡

317. አገልግሎቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ እና የውል አስተዳደር የስራ ሂደቶች በመዋቅሩ ከተፈቀደለት 56 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. 30 (54በመቶ) በሥራ መደቡ ላይ ሰው ያልተመደበባቸው ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው 234 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. 127ቱ (54 በመቶ) ሰው ያልተቀጠረባቸው ክፍት መደቦች ያሉተ መሆኑ፤

**የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ፤**

318. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች  የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

319. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች  የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን በተሟላ ሁኔታ የማያረጋግጥ መሆኑ፤ ፍላጎት አሰባስቦ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት ተፈራርሞ በራሱ ዕቅድ መሰረት ግዥ የማይፈፅም መሆኑ፤ ነገርግን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት  ሚኒስቴር ትዕዛዝ ሲመጣለት ብቻ ግዥ የሚፈፅም መሆኑ፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የደንብ ልብሶች፣ የኤሌትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እና የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎች ግዢዎችን ለመንግስት መ/ቤቶች አለመፈጸሙ፤

**የባለበጀት መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ መለየትና ማደራጀትን በተመለከተ፤**

320. አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን /Common user items/ በተመለከተ በኤጀንሲው የተወሰኑትን የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ሊያሰባስብ እና በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ በተለያየ ምድብ/ሎት/ ሊለይ እንዲሁም ከገበያ ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት ማደራጀት አለበት፡፡

321. አገልግሎቱ በ2003 ዓ.ም. ለ2004ና ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤ ከመጋቢት ወር በፊት ቀድሞ መላክ ሲገባው የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤውን የላከው ማሰባሰብ ከነበረበት ጊዜ ከ2-8 ወራት ዘግይቶ የተላከ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም. ለ2006 በጀት ዓመት ግዥ ፍላጎት ደግሞ የካቲት 27/2005 ዓ.ም. የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት እንዲያሳውቁት የጠየቀ ቢሆንም ከመጋቢት1 ጀምሮ ፍላጎት የሚያሰባስብበት ጊዜ ስለሆነ የመንግስት መ/ቤቶችም በ3 ቀናት ውስጥ ከዕቅዳቸው በመነሳት ፍላጎታቸውን ሞልተው ለመላክ በቂ ጊዜ ስላላገኙ በተባለው ጊዜ ፍላጎት መላክ ባለመቻላቸው የግዥ ሂደቱ እንዲጓተት ማድረጉ፤ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት በገበያ ጥናት መሰረት ዕቃው በገበያ ላይ ስለመኖሩ በማረጋገጥ አለማደራጀቱ፤

**የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

322. አገልግሎቱ ባሰባሰበው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዢ ፍላጎት መሰረት የግዢ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት የታወቁትን የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የግዢ ፍላጎቶችና ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዢ ዘዴ በመምረጥ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ ሊያመላክት እንዲሁም በመርሐ-ግብር በማስደገፍ ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

323. ይሁን እንጂ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከ2003-2005 ዓ.ም በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ የግዥ ዕቅድ አለማዘጋጀቱ፤ ይህም በመሆኑ

ከ2003-2005 ዓ.ም. ድረስ በመርሐ-ግብር የተደገፈ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዢ ዕቅድ ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው አለማሳወቁ፤

**መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተጠንቶ ግዥ ስለመከናወኑ**

324. በደንብ ቁጥር 182/2002ና በአዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አጥንቶ በሚልከው መሠረት ግዥ ሊያከናውን ይገባል፡፡

325. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሚወሰን የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ እቃዎች የግዥ ውል ከመፈራረም ውጭ የዕቃ ግዥ የማያከናውን ሲሆን፤ ለአገልግሎት ግዥም(ለጥገና፣ ለፅዳት፣ ለጥበቃ፣ ለመድህን ዋስትና ግዥዎች) የግዥ ውል እንደማይፈራረም እና ግዥም የማያከናውን መሆኑ መጠይቅ ከቀረበላቸው 12(100%) መ/ቤቶች እንዲሁም በሰርቬይ መጠይቅ ከመለሱት 21መ/ቤቶች (88%) ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፤፡ በተጨማሪም የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጁ መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ተመሳሳይ ፍላጎት አለማጥናቱ፣ የዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር አለማውጣቱ እና ለአገልግሎቱ አለማሳወቁ፤

**በሚፈለገው ጊዜና መጠን የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በማከናወን ለተጠቃሚዎች ስለማድረስ፤**

326. በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚ አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

327. በአገልግሎቱ ከቀረቡ የመ/ቤቶች የግል ማህደር በናሙና እንደታየው በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ግዥዎች ላይ 19 የመንግስት መ/ቤቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ተከታትሎ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ፤ እንዲሁም 6 የመንግስት መ/ቤቶች ሌላ አሸናፊ አቅራቢ

ድርጅት ጋ ተመድበው መግዛት እንዲችሉ አገልግሎቱን ጠይቀው ክምችት እንደሌላቸውና ዕቃዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚያስገቡ እና መ/ቤቶቹም ተከታትለው ግዥ እንዲፈፅሙ የበጀት ዓመቱ መጨረሻ አካባቢ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶቹ በአሳወቀው መሰረት መ/ቤቶቹ ዕቃ አቅራቢዎች ጋ የግዥ ትዕዛዝ ሰጥተው ተከታትለው ለመረከብ ጥረት ቢያደርጉም ዕቃ በመጋዘናቸው ውስጥ ባለመኖሩ የበጀት አመቱ ለመጠናቀቅ 2 ሳምንት እስከሚቀረው ድረስ እቀዎቹን ለመ/ቤቶቹ አለማቅረባቸው፤ ለረጅም ጊዜ በመመላለስ እቃዎቹን ማግኘት ባለመቻላቸውም የግዥ ትዕዛዙን የሰረዙ መ/ቤቶች መኖራቸው፤

**የአገልግሎቱ የግዥ ሂደት ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ፤**

328. አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱ ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ በገበያው ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚገኝበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገና ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን ሊወስን ይገባል፡፡

329. የመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቢሆንም በአገልግሎቱ አብዛኛውን ጊዜ መ/ቤቶች ግዥ እንዲፈፅሙ የሚደረገው የበጀት ዓመቱ 1ኛ ሩብ ዓመት ካለፈ በኂላ በመሆኑ፤ አገልግሎቱ ከ2004-2005 ዓ.ም. የግዥ ሂደቱን ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት/ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ በማድረግ የግዥ መፈፀሚያ ጊዜ አለመወሰኑ፤

**የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ማግኘቱን ስለማረጋገጡ**

330. በግዥ መመሪያው መሠረት አገልግሎቱ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ሊያገኝ እና ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የማዕቀፍ ግዥዎችን በዓለም አቀፍ የግዢ ጨረታ መግዛት አለበት፡፡

331. ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ ከ2003-2005 ዓ.ም. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀሙ በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና

አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተቀባይነት ማግኘቱ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ በ2004 ዓ.ም. ለብር 28,173,094.00 የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እና በ2005 ዓ.ም. ለብር 355,021,356.23 በአገልግሎቱ ባለሙያዎች ተገምግሞ በሥራ አመራር ቦርድ የጸደቀ መሆኑ፤ እንዲሁም አገልግሎቱ በ15/9/2004 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ እስከ 100 ሚሊዮን ለሚሆኑ ግዥዎች የግዥ ኮሚቴ በማቋቋም ግዥው እንዲጸድቅ የወሰነ ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመት ከ100 ሚሊዩን ብር በላይ የሆኑትን ግዥዎች በሥራ አመራር ቦርድ ብቻ በማፀደቅ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤

332. በተጨማሪም አገልግሎቱ ከመመሪያ ውጭ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም. ከ10,000,000 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዥ በዓለምአቀፍ ግልጽ ጨረታ መግዛት ሲገባው፣ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከ9 ድርጅቶች ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**አገልግሎቱ የተጫራቾችን ብቃት እና የስራ አፈፃፀም ማረጋገጡን በተመለከተ፤**

333. በአገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ሊረጋገጥና እንዲሁም ነባር የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር የበፊት የሥራ አፈጻጸማቸው መታየት ይኖርበታል፡፡

334. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን መፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ወጥ በሆነ መልኩ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመገምገሚያ መስፈርት መሰረት የቅድመ ቴክኒክና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ (prelimenarey and technical evaluation) ተደርጎ ለመረጋጋጡ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

335. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ተወዳድረው ያለፉ የ9 ተጫራቾች ፋይል ሲታይ የ2004 በጀት ዓመት የጨረታ ሰነድ ተሟልቶ ያልቀረበ ሲሆን፤ ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ የቴክኒክ ግምገማን በተመለከተ በመ/ቤቱ የተቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ገምግመው ሪፖርት ቢያደርጉም የቴክኒክ ገምጋሚ ኮሚቴው ካስቀመጠው ውጤት ውጪ ውጤታቸው ከ90% በታች መሆኑ እና ቴክኒካሊ እንደወደቁ እየታወቀ ተጫራቾቹ

በፋይናንስ ግምገማ እንዲካተቱ በማድረግ በአጠቃላይ የቴክኒክና የፋይናንስ ግምገማ ላይ አሸናፊ ሆነው ዕቃ እንዲያቀርቡ በቃለ ጉባኤ መወሰኑ እንዲሁም ግምገማ ሲደረግ የተጫራቾች ውጤት ከ40% ምን ያህል እንዳገኙ ሪፖርት ቢደረግም ውጤቱን በማሻሻል ከተጫራቾቹ በአጠቃላይ ውጤት ማለፍ የሌለባቸው ተጫራቾች እንዲያልፉ መደረጉ፤ከዚህም በተጨማሪ አገልግሎቱ በ2004 ዓ.ም. አሸናፊ የነበሩትን ሁለት አቅራቢ ድርጅቶች በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም፣ የበፊቱ የሥራ አፈጻጸማቸውን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በ2005 ዓ.ም እነዚሁ ድርጅቶች በድጋሚ አሸናፊ ሆነው እንዲያቀርቡ መደረጉ፤

**በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ የክፍያ ሁኔታ ስለማመቻቸቱ እና አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የእርምት እርምጃ ስለመውሰድ፤**

336. በግዥና ውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ መሰረት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ ዕቃውን ከተረከበ በኋላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ሊያመቻች ወይም እንዲመቻች ሊያደርግ እና የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታዎችን ተቀብሎ እንደየደረጃው ከሁለት እስከ አሥር ቀናት ውስጥ ምላሽ ሊሰጥ እንዲሁም ከተገልጋዮች የቀረበው ቅሬታ ወይም አቤቱታ ተጣርቶ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በአገልግሎቱ የተቀመጡትን የእርምት እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

337. አገልግሎቱ ተጫራቾች አወዳድሮ ግዥ በመፈፀም ዕቃ መረከብ ያልጀመረ ከመሆኑም በላይ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ እንዲረከቡ ባዘዘው መሰረት ዕቃ ለሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ ከተረከቡ በኋላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ያላመቻቸ መሆኑ፤በተጨማሪም አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ትዕዛዝ እየሞላችሁ ክፍያውን በመፈፀም እቃ እንድትረከቡ በማለቱ እና አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ባለማመቻቸቱ በናሙና ከተመረጡ 11 የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ 9ኙ ከአገልግሎቱ ጋር ውል ለተዋዋሉ አሸናፊ ድርጅቶች ክፍያ የፈጸሙት በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ከተገለፀው ውጭ

ዕቃውን ተረክበው ሞዴል 19 ከመቁረጣቸው በፊት ዩኒቨርስቲዎች፣ የሚኒስቴርና ባለስልጣን መ/ቤቶች የፋይናንስ ግዥና አሰራርን በመተላለፍ ለገንዘቡ ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ ከብር 50,000 በላይ በቼክ ከብር 74,476.24 እስከ ብር 3,030,859.26 ክፍያ በመፈፀም ግዥ ያከናወኑ መሆኑ፤እንዲሁም የዕቃ ርክክብ ሳይፈፅሙ ፣ሞዴል 19 ሳይቆርጡና ካለዱቤ ሽያጭ/credit invoice/ በባንክ አካውንት ዝውውር በአንድ ጊዜ ግዥ ብቻ ለአንድ አቅራቢ ድርጅት 8 የመንግስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 18,141,902. ቅድመ ክፍያ የፈፀሙ መሆኑ፡

338. እንዲሁም 3 መ/ቤቶች ደግሞ ኮምፒተሮችን፣ ፎቶ ኮፒ ማሽንና ፕሪንተር ለመግዛት በትራንስፈርና በቼክ ቅድመ ክፍያ ብር 420,875.00 ለአቅራቢ ድርጅቶች የፈጸሙ ሲሆን ከነዚህ መ/ቤቶች ውስጥ በተሟላ መልኩ ዕቃውን ባለመረከባቸውና በጀት ዓመቱ በመጠናቀቁ የፈፀሙት ክፍያ እንደተሰብሳቢ የተያዘባቸውና በጀቱ የተቃጠለባቸው መኖራቸው፤

339. በሌላ በኩል ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የተለያዩ ዕቃዎችን በጥራትና በወቅቱ ባለማቅረባቸው ለአገልግሎቱ ቅሬታ ላቀረቡ 8 መ/ቤቶች ከግዥ መመሪያ ውጪ ከ12 እስከ 25 ቀናት ዘግይቶ ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑ፤ ለ6 መ/ቤቶች ደግሞ ምንም ምላሽ ያልሰጣቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በናሙና ከታዩ አምስት የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ 4ቱ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች መ/ቤቶች ዕቃ ባለመረከባቸው እና የዋጋ ማስተካከያን በተመለከተ ለአገልግሎት መ/ቤቱ ቅሬታ አቅርበው፤ ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑን፤

**አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የተሟላ መረጃ መያዛቸውና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ስለመከታተሉ እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ስለማድረጉ፤**

340. አገልግሎቱ የሚፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ የአቅራቢው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣ የግዢ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብና ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ አቅራቢው ድርጅት በውሉ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ሊከታተል እና ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ሊያደርግ እንዲሁም ለማዕቀፍ ስምምነት ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ሊይዝ፣ ሊያስተዳድር

እና በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ ገንዘቡን ሊወርስ ይገባል፡፡

341. አገልግሎቱ በ2004ና 2005 ዓ.ም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በተደረገው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ ወይም የሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር እንዲሁም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት አለማካተቱ፤ በዚህ ዙሪያ በናሙና ከታዩ 5 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ ለ2 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች አገልግሎቱ የመ/ቤቶችን ዝርዝር ውሉን ከተፈራረመ ከ2 ወር በኋላ ቢያሳውቃቸውም ከ2003-2005 ዓ.ም. በተፈፀመው የግዥ ውል ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝር በወቅቱ ባለመካተታቸው 5ቱም የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ለስንትና ለየትኞቹ መ/ቤቶች ዕቃ ማቅረብ እንዳለባቸው ቀድመው እንዳያቅዱ ያደረጋቸው መሆኑ፤

342. አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በማዕቀፍ ስምምነቱ ውልና በውሉ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀሙ መሆናቸውን በመከታተል ለመንግስት መ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ ድጋፍ ያላደረገ ሲሆን፤ የማዕቀፍ ግዥን በተመለከተ አገልግሎቱ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና መ/ቤቶችን የሚከታተልበት ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ባለመፍጠሩና በውሉም ላይ ባለማካተቱ እንዲሁም የራሱ የሆነ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በውለታው መሠረት ባልፈጸሙ አቅራቢዎች ላይ ተከታትሎ በወቅቱ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ አለመውሰዱ፤

343. አገልግሎቱ የውል ማስከበሪያ ገንዘብን በ2004 ዓ.ም በወቅቱ ያላደሰ፣ በአግባቡም ያልያዘና ያላስተዳደረ መሆኑ እንዲሁም በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን በማረጋገጥ ለሁሉም አቅራቢ ድርጅቶች ወጥ በሆነ መልኩ የግዥ ውል ማስከበሪያ ገንዘብ የመውረሻ ሥርዓት አለመኖሩ፤፤ የተያዘው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ መጠን ትክክል ስለመሆኑ ከአገልግሎቱም ሆነ ከድርጅቱ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

**የግዥ ውሎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የያዙ መሆናቸውን እና በመግለጫው መሰረት ግዥ ስለመፈፀሙ፤**

344. አገልግሎቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ/Specification/ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣን ወይም እንደግዢው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በጨረታ ሰነዱ ዝርዝር ውስጥ ለማካተት ጠንካራ የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ በቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የተገለፀው የዕቃው ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ ዲዛይን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱንና ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆኑን የውሉ አንድ ክፍል በማድረግና የአቅርቦቱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊያውል እና በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች በታወቀ መ/ቤት የናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸውና እንዲረጋገጥ ሊያደርግ እንዲሁም ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው Specification መሰረት መቅረቡን ሊመረምር ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ከምርመራ በኋላም አስፈላጊው የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡

345. አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ በአዘጋጀበት ጊዜ በተሟላ መልኩ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣንን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ደረጃ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለዕቃው ደረጃ ዝርዝር አለመገለፁ፤ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲና አግባብ ካላቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቴክነክ ፍላጎት መግለጫን(specification) በተመለከተ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱና ተግባራዊ አለማድረጉ፤፤ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለ351 የቢሮ ዕቃዎች ደረጃ እንዲዘጋጅለት በደብዳቤ የደረጃዎች ኤጀንሲን ከጠየቀው ውስጥ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ ለ219 ዕቃዎች ደረጃ ተዘጋጅቶ በኮሚቴ ታይቶ መፅደቁ ቢታወቅም ለተቀሩት 132 ዕቃዎች(ለምሳሌ ኮምፒውተርና አክሰሰሪ፣ የፅዳት ዕቃዎች እና የመሳሰሉት) ደረጃዎች ተዘጋጅቶ ያልፀደቀ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ሲታይ አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 ዓ.ም ለዕቃዎቹ (እስክብርቶና እርሳስ፣ የፋይል ማቀፊያና ቶነሮች) ደረጃ

ሳይዘጋጅላቸው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተቱ፤ ይህ በመሆኑ መ/ቤቶች በ2005 ዓ.ም. የግዥ ሂደት ወቅት ከፋይል ማቀፊያና ከሁለት ዓይነት ቶነሮች በስተቀር ሌሎቹ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ዕቃዎች የቀረበላቸው መሆኑ፤

346. በተጨማሪም አገልግሎቱ ከ2004-2005 ዓ.ም ከ9 አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በተዋዋለው ውል የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ክፍል ውስጥ ስለዕቃው ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆኑን አለማካተቱ፤

347. በሌላም በኩል አገልግሎቱ በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች በታወቀ መ/ቤት የቅድመ ናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸውና እንዲረጋገጥ በማድረግ በኢትዮጵያ ተስማሚነትና ምዘና ድርጅት የናሙና ፍተሻ እየተደረገ የሚገኝ ቢሆንም በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈለጉ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ ቅድመ ናሙና ፍተሻ እየተደረገላቸው አለመሆኑ፤ በተጨማሪም ከ2004-2005 ዓ.ም. በኮምፒውተርና ተጓዳኝ ዕቃዎች በተፈፀመው ግዥ የናሙና ፍተሻ ስለመደረጉ አገልግሎቱ ማስረጃ የሌለው መሆኑ፤

348. አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው Specification መሰረት መቅረቡን አለመመርመሩ፤ በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን አለማመቻቸቱ፤ከዚህ በተጨማሪ ከምርመራ በኋላ በተሟላ መልኩ አስፈላጊውን የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም አለማድረጉ፤ ይህም በመሆኑ ግዢዎች አስቀድሞ በተቀመጠው Specification መሰረት ለመሆኑ አስፈላጊውን ምርመራ ሳይደረግበት ክፍያ ፈጽመው ከ Specification ውጪ ዕቃ የተረከቡ መ/ቤቶች መኖራቸው፤

**አገልግሎቱ የሚፈራረመው የግዥ ውል የገበያ ጥናትና መረጃን የተመረኮዘ መሆኑን በተመለከተ፤**

349. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና ለክልል መንግስታት በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት ሊሰጥ፣ ለማዕቀፍ ስምምነት ግዢ የሚፈራረመውን የውል ዓይነትና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ሊወስን እና አገልግሎቱ ከግዥና

ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ የዕቃዎች ዋጋ ጥናት መሰረት ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ሊያረጋግጥና ማስተካከያዎችንም ሊያደርግ ይገባል፡፡

350. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለአብዛኛዎቹ የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ግዥ ውል ስምምነት ከመፈጸም ውጭ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት አለመስጠቱና ከ2004-2005 ዓ.ም ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የተፈራረመውን የዕቃዎች ውል ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ አለመወሰኑ፤ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ የማዕቀፍ ግዥ ሲፈፀም የቀረበው ዋጋ መጋነኑንና አለመጋነኑን የሚገልፅ የዋጋ ጥናት ሳይደረግበት ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤ በአገልግሎቱም የተደራጀ የገበያ ጥናት ቡድን የሌለው መሆኑ፤ በዚህ ዙሪያ በመግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲም ሆነ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዕቃዎች የዋጋ ዝርዝር የሌላቸው መሆኑ፤

351. በተጨማሪም አገልግሎቱ የዕቃዎች የገበያ መረጃ ስለሌለውና ወጥ በሆነ መንገድ በየበጀት ዓመቱ የመ/ቤቶችን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ገንዘብ በጀት የሚመለከተውን አካል ስለማይጠይቅ እስከ 2005 ዓ.ም ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥ መጠን መመጣጠኑን በማረጋገጥ ማስተካከያዎችን አለማድረጉ፤

**በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ጊዜና የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ ስለመካተቱ፤**

352. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኂላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ በማመላከት ማስተካከያ ሊያደረግ እንዲሁም ሰነዱ ላይ በማዕቀፍ ስምምነት የሚገዛውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር፣ የማስረከቢያ ቦታ፣ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜና መጠን፣ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ፣ አፈፃፀሙንና የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲካተት ሊያደርግ ይገባል፡፡

353. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ቢያመላክትም የዕቃዎች የዋጋ ጥናት ባለመዘጋጀቱ ዋጋ ሲጨምር እና ሲቀንስ ለዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችም ሆነ ለመንግስት መ/ቤቶች የዋጋ ለውጥ አለማድረጉ፤ ይህም በመሆኑ መ/ቤቶች ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ ፍላጎታቸውን ባሳወቁት እቃዎች ላይ አቅራቢ ድርጅቶች ዋጋ ከልሰን እስከምናዘጋጅ በቀድሞው ዋጋ አናስተናግዳችሁም በማለት ማቅረብ እንደማይችሉ በመግለፃቸው ምክንያት እስከ ነሐሴ 28 ቀን 2005 ዓም መፍትሄ አለማግኘታቸው፤

354. እንዲሁም በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ባወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ ያላካተተ መሆኑ፤፤አቅራቢዎች ዕቅዳቸው ላይ ችግር የፈጠረባቸውሲሆን ፍላጎት ያላሳወቁ መ/ቤቶች ዕቃ የሚረከቡ መሆኑ ይህ ደግሞ አቅርቦት ላይ ችግር እንዳስከተለባቸውና በቀጥታ መ/ቤቶች ጋር ሄደው ተረከቡ ለማለትም ሆነ ለማስገደድ እንዳላስቻላቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ የድርጅታቸውን የአቅርቦት ዕቅድ እንዳያስተካክሉ ማድረጉ፤

**ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ስለመግዛትና ጥቅል ግዥ በመፈፀም ጥቅም ስለመገኘቱ**

አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዛ እንዲሁም ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ተመሳሳይ ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ እና ያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ሊታወቅ ይገባል፡፡

355. በኦዲቱ ወቅት ከ2004-2005 ዓ.ም አገልግሎቱ በፈፀመው የግዥ ውል ወቅት ሰፊ የገበያ ጥናት የተደረገባቸው እቃዎች በሚፈለገው ጊዜና መጠን በተሟላ ሁኔታ ለመንግስት መ/ቤቶች እንዲቀርቡ ያላደረገ በመሆኑና ለመ/ቤቶች ከተገዙት ዕቃዎች ውስጥ የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀቶች፣ ቶነሮች፣ ኘሪንተሮችና የፋይል አቃፊ ላይ የጥራት ችግር የገጠማቸው መሆኑ፤ እንዲሁም 3 የመንግስት መ/ቤቶች 360 ዴስክ ቶፒ ኮምፕውተር በመግዛት ከአገልግሎቱ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በብልጫ ብር1,989,034 የከፈሉ መሆኑና ዋጋውም

ተመጣጣኝ አለመሆኑ፤ ይህም በመሆኑ የመንግስት መ/ቤቶች ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም እያስገኘላቸው አለመሆኑ፤

356. በተጨማሪም አገልግሎቱ ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ስለማስገኘቱ ሲታይ፤ የመንግስት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በአገልግሎቱ በኩል ግዥ እንዲፈፅሙ ቢደረግም አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም በአገልግሎቱ ተሰርቶ የማያወቅ መሆኑ፤በዚሁ መሰረት አገልግሎቱ በ2004 በጀት ዓመት በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉትን ዕቃዎች ለይቶ ለሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች በወቅቱ የግዥ ፍላጎት ባለመጠየቁና ባለማሰባሰቡ፣ የጨረታ ሂደት ጨርሶ ባለማሳወቁ እና የግዥ ሂደት ማካሄድ የማይችልባቸውን ቀድሞ ባለማሳወቁ እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ፍላጎት የጠየቀበትን ሁሉንም ግዥ አንድ ላይ ባለማከናወኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት 9 መ/ቤቶች በግላቸው በብር 121,642,598.47 ግዥ በመፈፀም፣ ለጨረታ ማስታወቂያ ብር 225,225.79ና አገልግሎቱ ከገዛበት ዋጋ በላይ በብልጫ በብር 158,704.68 በመገዛቱ በጋራ ከሚፈለጉ አገልግሎቶችና ዕቃዎች ጥቅል ግዢ ሊያስገኝ የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በበቂ ሁኔታ ያላስገኘ መሆኑ፤

### አገልግሎቱ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና ግንዛቤ መፍጠሩን በተመለከተ፤

357. አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ ለመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት ሊያደርግ፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ከመንግስት መ/ቤቶችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖረው እና በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡

358. በደንብ ቁጥር 184/2002 እና በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አገልግሎቱ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መረጃ መረብ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማጠናቀር

ለህዝብ ይፋ ያላደረገ መሆኑና ለማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ ባለበጀት መ/ቤቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ እንዲያውቁት አለማድረጉ፤ በኦዲቱ ወቅት በአካል ከተሄደባቸው 16 የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ለ11ዱ(69%)፣ ከአገልግሎት መ/ቤቱ ከተገኘው 46 የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ የግል ማህደር እንደታየው ለ44ቱ(96%) አገልግሎቱ ለ2004ና 2005 በጀት ዓመት ግዥ ውሉ ከተፈራረመ በኋላ ከ1 ሳምንት እስከ 6ወር በመዘግየት የአሸናፊ ተጫራቾች ስም፤ አድራሻ፣ የዕቃው ዓይነትና ዋጋ በደብዳቤ ከማሳወቅ ውጪ የግዥ ውል ኮፒ ለመ/ቤቶቹ በመላክ እንዲያውቁት አለማድረጉ፤

359. ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ መመሪያዎችንና የግዥ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚረዳ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት ለመዘርጋት ቢያቅድም እስከ 2005 ዓ.ም ተግባራዊ በማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ለመንግስት መ/ቤቶችና ለአቅራቢ ድርጅቶች በወቅቱ መረጃዎች እንዲደርሱ አለማድረጉ፤ በዚህ ዙሪያ ከተጠየቁት 12 መ/ቤቶች 12ቱም እና የሰርቨይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 24 መ/ቤቶች ውስጥ 13ቱ እና ከ 5 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች በተገኘው ማስረጃ መሰረት የሚፈልጉትን የግዥ መረጃዎች በሚፈለገው ጊዜና በተቀላጠፈ ሁኔታ በወቅቱ አለማግኘታቸው፤

360. በሌላም በኩል አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አለማድረጉ

በመሆኑም የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በማእቀፍ ግዢና አፈጻጸም ረገድ በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 11. <u>የልዩ ኦዲት ስራዎች</u>

በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች ትህዛዝና በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ የተከናወኑትም ልዩ ኦዲቶች፣

1. አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የብድር ሂሳብ ክርክር
2. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ
3. የምህራብ አርሲ ዞን ገቢዎች ጽ/ቤት ተ.እ.ታ ክርክር
4. በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የዳያስፖራ ፕሮጀክት ሂሳብ
5. አ.አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት
6. የኢትዮጵያ ጤናና ስነምግብ ኢኒስቲዩት
7. በትምህርት ሚ/ር የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ዕቃዎች ጉድለት ሂሳብ
8. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን
9. ኑ-ጻ ኃ/የተ/የግል ማህበር
10. ባሰፋ ኃ/የተ/የግል ማህበር
11. ሞኔት ኃ/የተ/የግል ማህበር
12. ኤቲትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር
13. ኬኬ ኃ/የተ/የግል ማህበር
14. ሚፍሃም ኃ/የተ/የግል ማህበር
15. ፍጹም ገ/መድህን አጠቃላይ አስመቸጪና ላኪ
16. ጂ ኤች ሴሚክስ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ናቸው፡፡

## 12. <u>ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እርምጃ ያልተወሰዱ መ/ቤቶች</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:– በ22 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 33 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦችና በየመ/ቤቶቹ በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ክፍል ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል፡፡

## 13. <u>መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች</u>

መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፣ በተጋረጡበት አንዳንድ ተግዳሮቶች ምክንያት ያሰበውን ያህል ውጤት ማስገኘት አልቻለም፡፡ በሥራ ላይ እየተፈታተኑን ከሚገኙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ያደገ በሆንም ኦዲቱን በሚፈለገው ጥልቀትና ጥራት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ ለመቅጠር ባለመቻሉና ከፍተኛ ልምድ ያለቸው ነባርም ሆኑ አዲስ ተቀጣሪ ሠራተኞች ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱን በመልቀቃቸው እስከ አሁን በተገኙ ውጤቶች ቀጣይነትና ሊሠሩ በታቀዱት ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ሥጋት ፈጥሯል፡፡ የችግሩን አሳሳቢነት በማሳየትና በማስረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢደረግም እስከ አሁን ድረስ መፈትሔ ሊገኝ አልቻለም፡፡

በኦዲት ተደራጊዎች ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር በአብዛኛው መሻሻል ያሳየ ቢሆንም ቁጥሩ በማይናቅ መ/ቤቶች አሁንም ያለመተባበር (በወቅቱ የሥራ ቦታ አለማመቻቸትና መረጃ አለመስጠት) ችግሮች የሚታዩ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ካለፈው የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ በተለየ ሁኔታ 91(68.93%) የሚሆኑት (ከ132 መ/ቤቶች ውስጥ 91 መ/ቤቶች ከመስከረም 30/2006 በኃላ ሂሳባችውን የዘጉ ሲሆኑ፣ ዝርዘሩን በአባሪ ሁለት ይመልከቱ) የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ዘግይተው በመዝጋታቸው የዘመኑን የኦዲት ሥራ በወቅቱ እንዳናጠናቅቅፍ ፣የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በመርሀ-ግብራችን መሠረት እንዳንጀምርና

ዓመታዊ ሪፖርታችንንም በወቅቱ ለማዘጋጀት ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖብን አልፏል፡፡ ኦዲቱን ከማቋረጥ ይልቅ የየመ/ቤቶቹን የበላይ ኃላፊዎች በተደጋጋሚ በማነጋገር ችግሩን በማስታመም የዘመኑን ኦዲት የማጠናቀቅ ኃላፊነታችንን የተወጠን ቢሆንም ጉዳዩ የሕግ ጥሰት በመሆኑ ለወደፊቱ እንዳይደገም መ/ቤቶች ከወዲሁ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ሂሳባቸውን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ ባስቀመጠው የሕግ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዘግተው ለኦዲት ማቅረብ እንደሚኖርባቸው፣ ለሁሉም መ/ቤቶች በወቅቱ ሂሳባቸውን ዘግተው የማያቀርቡትን ተቀብለን ኦዲት እንደማናደርግ በግልጽ አሳውቀናል፡፡

በአብዛኛው መ/ቤቶች የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍሎች አሁንም በማዋቅር፣ በክህሎትና በዕውቀት በሚገባ ባለመደረጀታቸውና አንፃራዊ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ባለመደረጉ ወይም ባለመፈቀዱ የውጪ ኦዲቱ ከውስጥ ኦዲት ሥራ ማግኘት የሚገባውን ባለማግኘቱ ሰፊ ሥራ እንዲሠራ መገደዱ፣

ሌላው አሁንም ያልተሻገርነው ችግር በርካታ ኦዲት ተደራጊዎች ከመ/ቤታችን በሚላኩ የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና በሚሰጡት  የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ተገቢውን እርምጃ የማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ይህ ጉዳይ ውሎ አድሮ ተጠያቂነትን ሊያስከትል አስቀድው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ቢወስዱ ተመራጭ ነው ፡፡ በም/ቤቱም በኩል የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## 14. <u>ማጠቃለያ</u>

በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የኦዲት ሽፋኑን 100% ደርሷል፡፡ የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 100% እና የክዋኔ ኦዲቱም 20 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዶ ሁሉም  ሲጠናቀቁ ሌሎች በዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ 6 ክዋኔ ኦዲቶች ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ስለሆነ፣ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡

በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም፣ በኦዲቱ ሂደት በየመ/ቤቱ በተደጋጋሚ የሚታዩት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ ተዘጋጅቶ፣ የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት በ17 ጥራዝ ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፣ ም/ቤቱ በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴናሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በተጨማሪም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የሠነድ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፣ እንደዚሁም ከመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችና በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን፣በተለይም ኦዲት ተደራጊዎች በጊዜ ገደብ የታጠረ የማስተካከያ መርሀ-ግብር መንደፍና የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦችን ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ የም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች የክትትልና ቁጥጥር ፕግሮራም በመንደፍና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመታገዝ የግድፈቶቹን መንስኤዎች በማጣራት ከሥረ መሠረቱ ለማስወገድ የተጀመረው አሰራር የበለጠ ተጠናክሮ ሊሠረበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከርና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግልን እንጠይቃለን፡፡

# የ2005 በጀት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች

# ኦዲት አፈጻጸምና  ዋና ዋና ግኝቶች

## 1. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሰቦች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ያስደርጋል ፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርት መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች በደብዳቤ እንዳስፈላጊነቱ ማሳሰቢያ በመስጠት ውጤቱን ከሌሎች  የመንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## 2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2005 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት

### 2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲሆን  የመንግሥት የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዘ የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው ክትትል እንዲያደርጉና አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

አንድ የፋይናንስ ኦዲት ከተከናወነ በኋላ ሁለት ዓይነት ሪፖርቶች ማለትም አጭርና ረዥም /ዝርዝር/ ሪፖርት ተዘጋጅተው ይቀርባሉ፡፡

በአጭር ሪፖርት የሚሰጡ አስተያየቶች ዋና ዓላማ በአንድ ድርጅት ተዘጋጅተው የቀረቡ የሂሣብ መግለጫዎች በአለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ በቂ በሆነ ናሙና /በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ/ በመጠቀም ኦዲት ከተደረጉ በኋላ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ ሁኔታ ማሣየት ወይም አለማሳየታቸውን በመግለፅ ኦዲተሩ አስተያየት የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡

በረጅም ሪፖርት ላይ የሚሰጡ አስተያየቶች በኦዲቱ ወቅት የተደረሰባቸውን የገንዘብና የንብረት ጉድለቶች፣ የቁጥጥርና የአሠራር ድክመቶች በመጠቆም እነዚህን ጉድለቶችና ድክመቶች ለማስወገድ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በመግለጽ የማሻሻያ ሃሣብ የሚሰጥበት ነው፡፡

## 2.3 የሥራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2005 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛቸውና ያከናወናቸዉ የሂሣብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

| ተራ ቁ. | መግለጫ | የ2005 በጀት ዓመት | | የ2004 በጀት ዓመት ክንውን |
|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | |
| 1 | የአምራች ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ | 159 | 149 | 158 |
| 2 | የአገልግሎት ሰጪና የማከፋፈያ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ | 76 | 80 | 76 |
| | 1. ድምር | 235 | 229 | 234 |

ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት ወጪ የሆኑት 229 ሪፖርቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው 115፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው 95፤አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው 12 እና የልዩ ሪፖርቶች 7 ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የ2005 ክንውን በሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር በ6 ሪፖርቶች በቁጥር የሚያንስ ሲሆን ከ2004 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነፃፀር በ5 ሪፖርት ወይም በ 2.14% ማነስ አሳይቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን 13 ረቂቅ የኦዲት ሪፖርቶች ለኮርፖሬሽኑ አስተያየት እንዲሰጥበት ቢላክለትም ምላሽ ባለመስጠቱ የተነሳ ሪፖርቶቹ በወቅቱ ወጪ ባለመሆናቸው ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽናችን የኢትዮጵያ ስኳር ኢንደስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አ.ማ ሂሳብን እያጣራ ሲሆን፤ከዚህም በበጀት ዓመቱ ብር 697,495.00 ገቢ አግኝቷል፡፡

## 2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ

በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ የሠራተኛው ብዛት 113 የነበረ ሲሆን፣ በ2005 በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ 33 በድምሩ ከ146 ሰራተኞች ውስጥ በጡረታ የተገለሉ 4 እና በፈቃዳቸው የለቀቁ 30 በመሆኑ፤ በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ 112 ሠራተኞች እንደነበሩ ታውቋል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ፕሮፌሽናል ኦዲተሮች 69 ፣ አስተዳደርና ፋይናንስ 37 እና አንድ የትምህርትና ስልጠና ሠራተኞች ሲሆኑ ፤ በፆታም ሲታይ 64 ወንድና 48 ሴት በድምሩ 112 ናቸው።

## 2.5 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንደኛው የኦዲት ሙያ በይበልጥ የሚዳብርበትንና አገሪቷ በዚህ ሙያ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት በእንግሊዝ አገር ከሚገኘው አሶስዬሽንስ ኦፍ ሠርቲፋይድ አካውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የድርጅቱ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ በገንዘብና በጊዜ እንዲሁም በመጻሕፍት እየረዳ 17 ሠራተኞችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአገር ውስጥ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በትርፍ ጊዜአቸው ለሚማሩ ሰራተኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተገቢውን ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

የኦዲት ሙያ ያለ ቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፤ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሠጠው ሥልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

### 2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

የኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከሂሳብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡

በ2005 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፤ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የ2005 የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን**

| መግለጫ | ገቢ<br>ብር | ወጪ<br>ብር | ያልተጣራ ትርፍ /ከታክስ በፊት/ብር |
|---|---|---|---|
| ዕቅድ | 14,787,155.00 | 8,397,324.00 | 6,389,831.00 |
| ክንውን | 15,517,846.00 | 8,219,536.00 | 7,298,310.00 |
| ክንውንበመብለጥ /በማነስ/ | 730,691.00 | (177,788.00) | 908,479.00 |

**የ2005 የዕቅድ ክንውን ከ2004 ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡**

| የበጀት ዓመት | ገቢ<br>ብር | ወጪ<br>ብር | የተጣራ ትርፍ<br>ብር |
|---|---|---|---|
| **2005** | **15,517,846.00** | **10,409,030.00** | **5,108,816.00** |
| **2004** | **13,998,601.00** | **9,841,546.00** | **4,157,055.00** |
| **ልዩነት በመብለጥ** | **1,519,245.00** | **567,484.00** | **944,761.00** |

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የ2005 የገቢና ወጪ ክንውን ከ2004 ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

3. <u>በ2005 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች</u>

በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 82 ሲሆኑ በኢትዮጵያ መንግስትና በውጭ መንግስታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 150 በድምሩ 214 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርቡ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው፡፡

በእነዚህ ሪፖርቶች የተሰጠው በኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) የቀረበበት 105፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (**Qualified** opinion) የቀረበበት 99፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) የቀረበበት 9 እና የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት 1 በድምሩ 214 ናቸው፡፡

4. <u>የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

በ2005 በጀት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብለው በኦዲተሮች አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታ እና ከሁለት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1 አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው

አቋም ሊወሰድበት የማይቻል (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ የቻሉ ዋና ዋና ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው መ/ቤት

ከ1999 እስከ ሰኔ 30/2002 ዓ.ም የተጠናቀቀው የዩኒቨርሲቲው ዋና መ/ቤት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሰኔ 30/2002 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የነዳጅና ቅባት ሂሳብ ብር 2,166,940.00 በቂ የቆጠራ ግምገማ ባልተደረገበት፣ ስለትክክለኛነቱና አሳማኝነት ማረጋገጫ ያልተሰጠ ሲሆን ማስተካከያ የሚደረግበት ከሆነ በሂሳበ መግለጫው ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፣
- በጽዳት ዕቃዎችና የጽሕፈት መሳሪያዎች ሂሳብ ላይ ለታየው ኔጋቲቭ የሂሳብ ሚዛን ብር(2,044,870.00) ምንም ምክንያት ያልተሰጠውና በሂሳብ መግለጫው ሚዛን በተመለከተው ክምችት ሂሳብ ብር 4,141,053.00 ላይ ለመድረስ ይኸው ሂሳብ ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ፣
- በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ የተመለከተው ሂሳብ ብር 28 ሚሊዮን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በትክክል ስለመኖሩ፣የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ባለመዘጋጀቱ ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥም የሚያስችል ሌላ ዘዴ ወይም ማረጋገጫ ባለመገኘቱ፣
- በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ የብር 16 ሚሊዮን ኔጋቲቭ ሚዛን እንዴት ሊከሰት እንደቻለና ይኸው ሂሳብ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ሂሳብ ላይ ለማድረስ ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ማግኘት ባመቻሉ፣
- በሂሳብ መግለጫው በተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ በድምሩ ብር 9.5 ሚሊዮን በባንክ ገቢ(deposit) ከዓመት በላይ በገቢ

ሳይያዝ (outstanding) እንደቆየ በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ ትክክለኛ ገቢ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ሂሳብ ብር 68.17 ሚሊዮን ለበርካታ ዓመታት ሳይከፈል የቆየ በመሆኑ፣ ለምን ሳይከፈል እንደቆየ በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ ትክክለኛ ተከፋይ ወይም ዕዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- በዩኒቨርሲቲውና በተባባሪ ተቋማት (Associated Institution) መካከል ስለሚደረጉ የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ምንም የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ በነዚሁ ተቋማት አለ ተብሎ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጫ ማግኘት ባለመቻሉ፣
- በየፈንድ ሂሳብ መካከል የሚታየውን የተከፋይ እና ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በማጣጣት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ዜሮ ሚዛን ማሳየት ሲገባው የተጣራ ተከፋይ ብር 23.33 ሚሊዮን በሰኔ 30/2002 ዓ.ም ተመልክቷል። ከዚህም በላይ ብር 2,297,049.00 ለካፒታል ፈንድ ተከፋይ ተብሎ ለበርካታ ዓመታት የቆየና በዩኒቨርስቲው ምዝገባ ሊደረስበት ያልተቻለ ከመሆኑም በላይ ምንም ማብራሪያ ሊሰጥበት ባለመቻሉ፣
- ከ1999 እስከ 2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ለዩኒቨርሲቲው የተለቀቀ በጀት ምን ያህል እንደሆነ ለተጠየቀው ከሚ/ር መ/ቤቱ ምንም ማረጋገጫ (Conformation) ባለመሰጠቱ፣
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጥበቃ ሥር የሚገኝ የዩኒቨርሲቲው ወርቅ በግምት ዋጋው ብር 17 ሚሊዮን የሆነ በዩኒቨርስቲው ሂሳብ በሀብትነት ባለመያዙ፣

ከላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊያስከትሉ በሚችሉ የመረጀ ክፍተት የተነሳ በዩኒቨርሲቲው በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

ይኸው ሪፖርት ለመ/ቤታችን እንደደረሰ በተገኙት ግኝቶችና በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ዩኒቨርሲቲውና የአ.አ ዩኒቨርሲቲ ስራ

አመራር ቦርድ የወሰዱት የማስተካከያ እርምጃ እንዲገለጽልን ለዩኒቨርሲቲው የቦርድ ሰብሳቢ በቀጥታና ለዩኒቨርሲቲው በግልባጭ ለፃፍነው ደብዳቤ ምላሽ አልተሰጠንም፡፡

4.1.2 <u>በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ</u>

ከ1999 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ 30/2002 የተጠናቀቀው የፋኩልቲው ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የቀረበው የኦዲት አስተያየት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ነው::

- በፋኩልቲው አመዘጋገብ በርካታ ስህተቶችና ግድፈቶች በመኖራቸው በሂሳብ መግለጫዎች የተመለከቱትን የሂሳብ ሚዛኖች ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከቱት ተሰብሳቢነቱ እና ተከፋይ ሂሳቦች ተቀፅላ ሌጀር (Subsidiary ledger) ባለመዘጋጀቱ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሰኔ 30/2002 ዓ.ም በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የተሰብሳቢ ብር 8,438,938.00 ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረድ የቆየና ስለትክክለኛነቱ አሳማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ባለመዘጋጀቱ የልዩነቱ መንስዔ ያልተገለፀ የብር 2,760,255.00 በባንክ መዝገብ እና የባንክ ሂሳብ ሚዛን መካከል ልዩነት መኖሩ፣ እንዲሁም በሰኔ 30/2002 በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ብር 42,228.00 በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መግለጫ ያልተደገፈ ስለሆነ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሰኔ 30/2002 የሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ ብር 3,692,087.00 በረጅም ጊዜ የቆየ እና ከዚያ ወዲህም ያልተወራረደ በመሆኑ የፋኩልቲው ትክክለኛ ዕዳ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በተለያዩ የፋኩልቲው የፈንድ ሂሳቦች መካከል (Inter fund balances) የሚታየው ዝውውር ሚዛን ዜሮ መሆን ሲገባው የተጣጣ ዴቢት ሚዛን (Net off) ብር 2,999,991.00 የሚያሳይ በመሆኑ፣ ዝውውሩ በሙሉ፣ በትክክል እና በወቅቱ አለመመዝገቡን የሚያሳይ

ከመሆኑም በላይ ብር 82,871.00 ለረዥም ጊዜያት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ የሌለው መሆኑ፣

- ለፋኩልቲው ከ1999 እስከ ሰኔ 30/2002 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተመደበው በጀት ላይ ምን ያህል እንደተላለፈለት በቀጥታ ማረጋገጫ (Confirmation) ባለመስጠቱ እና

ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሊያስከትሉ በሚችሉት የመረጃ ውስንነት የተነሳ በፋከልቲው የተዘጋጀው የገቢ፣ የወጪ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻላቸው መሆኑን በመጥቀስ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

ይኸው ሪፖርት ለመ/ቤታችን እንደደረሰ በተገኙት ግኝቶች ላይ ፋኩልቲውና የአ.አ ዩኒቨርሲቲ የወሰዱትን የማስተካከያ እርምጃ እንዲገለጽልን ለዩኒቨርሲቲው የቦርድ ሰብሳቢና ለዩኒቨርሲቲው በግልባጭ ለፃፍነው ደብዳቤ ምላሽ አልተሰጠንም፡፡

### 4.1.3 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ከ1999 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ 30/2002 የተጠናቀቀው የኢንስቲትዩቱ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የቀረበው የኦዲት አስተያየት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

- በሰኔ 30/2002 ዓ.ም በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 3,130,058.00 ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረድ በመቆየቱ ሊሰበሰብ ስለመቻሉ አጠራጣሪ በመሆኑ ተገቢው መጠባበቂያ (Provisions) ባለመያዙ የዓመቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ በብር 3,130,058 ከፍ ያለ እና የአራት ዓመቱ ወጪም በዚህ ያህል በማነስ የተመዘገበ በመሆኑ፣
- ለተሰብሳቢ ሂሳቡ ተገቢው ሌጀር ባለመያዙና ለኦዲት ባለመቅረቡ የተመለከተው ሚዛን (balances) ከማን እንደሚሰበሰብና ሊሰበሰብ ስለመቻሉ ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ፣
- በተለያዩ የኢንስቲትዩቱ የፈንድ ሂሳቦች ሲጠቃለሉ፣ (Inter fund balances) በመካከላቸው ያለው ሚዛን ዜሮ መሆን ሲገባው የተጣጣ (Net off) የተሰብሳቢ ሚዛን ብር 231,986 የሚያሳይና ይህም

እንዲታረቅ ባለመደረጉ የሂሳቡ አመዘጋገብ፣ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ በትክክል ስለመካተቱ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

- በሰኔ 30/2002 የሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ብር 6,685,570.00 ለረጅም ጊዜ የቆየ እና በቀጣይም እንዲከፈል ያልተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 35% ተከፋይ የገቢ ግብር ሆኖ በታክስ አዋጁ መሠረት ተጣርቶ መከፈል የነበረበት መሆኑ፣
- ሰኔ 30/2002 በተመለከተው የሂሳብ መግለጫ ሌጀርና በገንዘብ ዝውውር ምዝገባው መካከል የብር 500,921.00 በክሬዲት (Credit) ልዩነት የሌጃሩ በመብለጥ የሚታይ ሲሆን ምንም ዓይነት ማስተካከያ ያልተደረገለት በመሆኑ፣
- በተለያዩ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ፈንድ የባንክ ሂሳብ ማስታረቅና፣ የጥሬ ገንዝብ ቆጠራ መግለጫዎች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ብር 4,148,758.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ሚዛኑ ላይ የተደረሰው በብር 767,887.00 ክሬዲት ሚዛን ከተጣጣ (Net off) መሆኑ ለዚህም የተሰጠ ምክንያት /ማብራሪያ/ ባለመኖሩ፣
- ኦዲት በተደረገው ሂሳብ ሚዛንና በኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ምዝገባ መካከል ብር 608,919.00 የፈንድ ሂሳብ ልዩነት ያለው ሲሆን ለዚህ ምንም ማብራሪያ ያልተሰጠ በመሆኑ፣
- የሲዳ ፕሮጀክት ፈንድ (SIDA/SAREC) ሂሳብ ተዘግቷል ቢባልም ይህንን የሚያስረዳ ምንም ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን ካለፉት አመታት የዞረ የተጣራ ሂሳብ ብር 18,366.00 በሰኔ 30/2002 የኢንስቲትዩቱ ፈንድ ሂሳብ መታየቱ፣

ከላይ የተመለከቱት ሊያስከትሉ በሚችሉት የመረጃ ውስንነት በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁት የ4 ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች /የገቢ፣ ወጪና ሀብትና እዳ/ ትክክለኛነት ላይ አስተያየት መስጠት ኦዲተሮቹ አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

ይኸው ሪፖርት ለመ/ቤታችን እንደደረሰ በተገኙት ግኝቶች ላይ ፋኩልቲውና የአ.አ ዩኒቨርሲቲ የወሰዱትን የማስተካከያ እርምጃ

እንዲገለጽልን ለዩኒቨርሲቲው የቦርድ ሰብሳቢና ለዩኒቨርሲቲው በግልባጭ ለፃፍነው ደብዳቤ ምላሽ አልተሰጠንም፡፡

### 4.1.4 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአርክቴክቸር፣ ሕንፃ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት

ከ1999 እስከ ሰኔ 30/2002 ዓ.ም የተጠናቀቀው የኢንስቲትዩቱ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የሂሳብ መግለጫ ሌጀር (Financial ledger) ሁሉም ፈንድ ኦዲት ባለመቅረቡ፣ የቀረበው የዝርዝር ሂሳብ ምዝገባ ሌጀር ለተወሰኑት ሂሶቦች ትንተና (Analysis) ተብሎ ሌጀሩን የሚተካ ለምርመራ የተመረጠውን ሂሳብ ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች በየፈንድ ሂሳብ (Project fund, general fund & special find) ተለይተው ባለመቅረባቸው እና ለረዥም ጊዜ የቆዩ በመሆናቸው በኢንስቲትዩቱ የተያዘው መጠባበቂያ በቂ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከቱት ከኢንስቲትዩቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው መ/ቤቶች የሚፈለግ ብር 211,810.00 ለረዥም ጊዜ የቆየ ስለትክክለኛነቱ እንዲሁም ሊሰበሰብ ለመቻሉ በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ፣
- የኢንስቲትዩቱ የተለያዩ የፈንድ ሂሳቦች ሲጠቃለሉ በመካከላቸው ያለው ሚዛን ዜሮ መሆን ሲገባው የተጣራ ዴቢት ሚዛን ብር 192,549.00 በመታየቱ ሂሳቡ በወቅቱ ሙሉ በሙሉና በትክክል ስለመመዝገቡ ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ የአራት አመታት በጥቅሉ ብር 67,090.00 ምንም አይነት እንቅስቃሴ የሌለው በመሆኑ፣
- በባንክ ያለ ሂሳብ ብር 5,677,319.00 እና በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ብር /961,748.00/ የሂሳብ ሚዛኑ የተደረሰበት በቅደም ተከተሉ በክሬዲት ብር 1,182,911.00 እና ብር 999,590.00 በማጣጣት (Net off credit balance) ሲሆን የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ

ባልተዘጋጀበት እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ለኦዲት ባልቀረበበት ስለትክክለኛነቱ መረጋገጥ ባለመቻሉ በሰኔ 30/20025 የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሚዛን ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ብር 480,949.00 የተከፋይ ሂሳብ ለበርካታ ዓመታት ያልተከፈለ ሲሆን፣ ያልተከፈለበት ምክንያት እና ስለትክክለኛነቱ በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ፣
- ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች የተገኘ ብር 2,074,850.00 በገቢ (Income) መያዝ ሲገባው በተከፋይ /ዕዳነት/ በስህተት በመያዙ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ በዚህን ያህል ከፍ ተደርጐ እንዲያዝና ገቢውም በማነስ በመያዙ ምክንያት፣
- ኦዲት በተደረገው በጀት ዓመታት 1999 እስከ 2002 ዓ.ም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለኢንስቲትዩቱ የተለቀቀው በጀት ምን ያህል እንደሆነ ማረጋገጫ ባለመሰጠቱ በሂሳብ መግለጫው የታየው በጀት ትክክለኛነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

ከላይ የተዘረዘሩት የመረጃ ክፍተት ሊያስከትል በሚችል ውስንነት የኢንስቲትዩቱ የ4 ዓመታት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

ይህም ሪፖርት ለመ/ቤታችን እንደደረሰን ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ እና በአ.አ ዩኒቨርሲቲ በኦዲት ሪፖርቱ በተሰጡት የመሻሻያ እርምጃ ተወስዶ ውጤቱ እንዲገለጽልን ብንጠይቅም ይህ ሪፖርት እስተከተዘጋጀበት ድረስ የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

### 4.1.5 <u>አ.አ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ</u>

ከ1999 እስከ ሰኔ 30/2002 ዓ.ም የተጠናቀቀው የኢንስቲትዩቱ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በርካታ ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎች መጥፋት፣ የምዝገባ አለመደረግና በስህተት የተመዘገቡ በመኖራቸው፣

- በፋኩልቲው የተሰብሳቢና ተከፋይ ተቀጽላ ሌጀር (subsidiary ledger) ባለመያዙ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ማጣራት ባለመቻሉ፣
- ብር 777,593.00 ረዥም ዓመታት የቆየ በባንክ ያለ ሂሳብ ብር 1,068,158.00 ልዩነት በፕሮጀክት ፈንድ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያው የሚታዩና የልዩነቱ መንስዔ ባለመታወቁ በሂሳብ መግለጫው የተመለከተውን የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ትክክለኛነትና አሳማኝነት ማወቅ ባለመቻሉ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ጥቅል ተከፋይ ብር 459,619.00 ለረዥም ጊዜ የቆየ አሁንም ያልተከፈለ መሆኑና ስለትክክለኛ ተከፋይነቱ አሳማኝ ምክንያት አለመቅረቡ፣
- በየፈንድ ሂሳቦቹ መካከል ያለው የብር 535,517.00 ዝውውር በጥቅሉ ብር 711,969.00 ላለፉት አራት ዓመታት ምንም እንቅስቃሴ የሌለው በመሆኑ፣

ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማረጋገጫ ባለፉት አራት ዓመታት የተለቀቀ በጀት ማረጋገጫ (conformation) ባለመሰጠቱ፣

ከላይ የተመለከቱት ሊያስከትሉ በሚችሉት የመረጃ ውስንነት በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁት የ4 ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች /የገቢ፣ ወጪና ሀብትና እዳ/ ትክክለኛነት ላይ አስተያየት መስጠት ኦዲተሮቹ አስተያየት መስጠት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

ይኸው ሪፖርት ለመ/ቤታችን እንደደረሰ በተገኙት ግኝቶች ላይ ፋኩልቲውና የአ.አ ዩኒቨርሲቲ የወሰዱትን የማስተካከያ እርምጃ እንዲገለጽልን ለዩኒቨርሲቲው የቦርድ ሰብሳቢና ለዩኒቨርሲቲው በግልባጭ ለፃፍነው ደብዳቤ ምላሽ አልተሰጠንም፡፡

### 4.1.6 <u>የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መንገድ ፈንድ</u>

ሰኔ 30/2004 የተጠናቀቀው የከተማ አስተዳደሩ የመንገድ ፈንድ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የተሰጠው ኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው።

- በሰኔ 30/2004 በሂሳብ መግለጫው የፈንድ ምንጭና አጠቃቀም ከተመለከተው ብር 387,184.00 የፈንድ አጠቃቀም ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ፣
- በአስተዳደሩ የመንገድ ፈንድ ምዝገባ እና ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ከተገኘው ማረጋገጫ መካከል የብር 264,150.00 ልዩነት (በበጀት ተልኳል የተባለው በማነስ) በማሳየቱ፣

በከተማ አስተዳደሩ የተዘጋጁት የፈንድ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

### 4.1.7 <u>የደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን መንገድ ፈንድ</u>

ሰኔ 30/2004 የተጠናቀቀው የባለሥልጣኑ የመንገድ ፈንድ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው ኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- በበጀት ዓመት መጨረሻ በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ብር 1,754.00 የቆጠራ መግለጫ ሊቀርብ ባመቻሉ ገንዘቡ ስለመኖሩ ሌላ ማረጋገጫ መገኘት ባለመቻሉ፣
- የሚጣራ የቫውቸር ሂሳብ (Suspense on hand) ብር 1,653,192.00 ለረዥም ጊዜ የቆየና ስለትክክለኛነቱም በቂ ማረጋገጫ ባለመገኘቱ፣
- በበጀት ዓመቱ ለብር 2,199,531.00 ወጪ ማስረጃው ለኦዲት ባለመቅረቡ፣ ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የተላከው በጀት ማረግገጫ እና በባለሥልጣኑ ወጪ በተደረገው መካከል የብር 4,144,863.00 ልዩነት (በበጀት ተልኳል የሚለው በማነስ) የሚያሳይና ለዚህም በቂ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ፣
- በበጀት ዓመቱ የብር 25 ሚሊዮን ብድር ከመደበኛ በጀት የተወሰደ በዚያው ዓመት የተወራረደ ቢሆንም ከፕሮጀክት ስምምነቱ ውጭ በመሆኑ፣

የተዘጋጁት የፈንድ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

## 5. ስለልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ፣ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 5.1 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ የማይደረግ መሆኑ፣
- በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ የማይካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2 <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ ክምችት እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ የማያደርጉ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች /ልዩነት ሲያጋጥሚቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም በምርት ተግባር ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

### 5.3 ተሰብሳቢ ሂሳብ

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋግሩ ተሰብሳቢው እየበዛና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለእዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት /ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አልተሳካም፣
- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአወሳሰዱ፤ አፈቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን እዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለእዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛው

የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየተ ተሰጥቷል፡፡

## 5.4 <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፤ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፤ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

## 5.5 <u>ተከፋይ ሂሳቦች</u>

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ማዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ

ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በየወቅቱ እንዲከፍሉ ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

### 5.6 ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉ ቁጥጥር እናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፣ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፣ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፣ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

## 6. በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ አጥጋቢ ሲሆን በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠራት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈትና በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣

- በባንክ ማሳወቅያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣
- ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽ፣
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ
- የአንዱን በጀት ዓመት ፕሮጀክት ወጪ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑ፣
- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠንና በፈፃሚ መ/ቤት/ቅ/ጽ/ቤት ገቢ የሆነው/የተመዘገበው ሂሳብ መካከል ልዩነት መኖሩ፣
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ ሂሳብ አያያዝ የተመለከቱት ችግሮች እንዲስተካከሉ በየኦዲት ሪፖርቶቹ አስተያየት ተሰጥቷል።

## 7. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

### 7.1 የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

### 7.2 ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣
  - የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥና የሥራ ቅልጥፍናና የውስጥ ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣
  - ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተበቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከውስጥና ፣ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም በኦዲት ሪፖርቶች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## 8. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች

**መ/ቤታችን** ባለው መረጃ /እስከ ጥር 30/2006 ዓ.ም የተሰበሰበ /መሰረት ከ2 ዓመት በላይ የቆዩ ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች/ ዝርዝር በአባሪ-36/ እንዳሉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ መ/ቤቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡